



የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች ቅፅ 7

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች

## ቅፅ 7

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሚያዝያ 2001 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
# ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች

## ቅፅ 7

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

<u>አዲስ አበባ</u>



## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት

ከዚህ ዕትም በፊት በነበሩ ቅፆች በርካታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች ታትመው በመላው ሀገሪቱ ለሚገኙ ፍርድ ቤቶችና ለሌሎችም የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሠራጩ ተደርጓል፡፡ ይህም በዋናነት፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ ሥር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሠጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል ተብሎ በመደንገጉ ፍርድ ቤቶች የሰበር ችሎቱ የሰጠውን የሕግ ትርጉም ተከትለው እንዲሠሩ ለማስቻል ነው፡፡ በየፍርድ ቤቶች ለተመሣሣይ ጉዳዮች ይሰጥ የነበረውን የተለያዩ ወሳኔዎች በማስቀረት የፍርድ ቤቶች ውሣኔዎች ወጥነት እንዲኖራቸውን ተገማችም እንዲሆኑ ከማድረግ አኳያ ጠቀሜታው ከፍተኛ በመሆኑም ነው፡፡

በሌላ በኩል ውሣኔዎቹ በጥራዝ መልክ መዘጋጀታቸው ጥናትና ምርምር ለሚያካሂዱ የሕግ ተማሪዎችና ምሁራን፣ ለጠበቆችና ለህብረተሰቡ በአጠቃላይ ውሳኔዎቹን በቀላሉ ለማግኘት ያስችላል የሚል እምነት አለን፡፡

**ተገኔ ጌታነህ**

**የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት**

## ማውጫ

ገጽ


**የውል ህግ** ........ 1

የሰ/መ/ቁ 12719 ........ 2
ሉክሰር የቱሪስትና የጉዞ ወኪል ኃላ/የተ/የግ/ማህበር እና ብሩኔይስ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር

የሰ/መ/ቁ 20232 ........ 9
አቶ ትዕግሥቱ ብዛ እና አቶ ይሃ ይብሬ

የሰ/መ/ቁ 20979 ........ 14
የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና እነ የወ/ሮ ግምጃ በሐቲ ወራሽ

የሰ/መ/ቁ 21531 ........ 17
ኢትዮ ትሬዲንግ የንግድ ሥራ ማስፋፊያ እና የውሃ ሃብት ሚኒስቴር

የሰ/መ/ቁ 23609 ........ 21
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ አሰበወርቅ ዘገየ

የሰ/መ/ቁ 30298 ........ 26
አቶ የሺወንድም አቡሐይ እና አቶ አየነው ማለደ

**የመያዣ ውል** ........ 30

የሰ/መ/ቁ 16218 ........ 31
የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ ወ/ሮ አስካለ ሁንዴ

የሰ/መ/ቁ 25863 ........ 38
የኢት/ልማት ባንክ እና የኢት/ንግድ ባንክ

የሰ/መ/ቁ 29269 ........ 42
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ ዋለልኝ አያሌው

የሰ/መ/ቁ 29375 ........ 48
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ተስፋዬ ገብረጊዮርጊስ

የሰ/መ/ቁ 33295 ........ 51
ወ/ሪት ብርሃኔ አበበ እና እነ አቶ ማርቆስ ተርፋ

**የኪራይ ውል** ........ 58

የሰ/መ/ቁ 23024 ........ 59
ወ/ሮ ፋጤ በሽር እና መልዓከገነት ዮሐንስ አምባው እና የኪራይ ቤቶ ኤጀንሲ

የሰ/መ/ቁ 24221 ........ 63
ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ ወ/ሮ አረጋሽ አምደሚካኤል

የሰ/መ/ቁ 25938 ........ 67
የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና የአቶ ገ/ሕይወት ከበደም ወራሾች

የሰ/መ/ቁ 28025 ........ 71
የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ታደለ አበበ

የሰ/መ/ቁ 30894 ........ 74
ወ/ሮ መዓዛገነት ዳኜ እና የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ

የሰ/መ/ቁ 31601 ........ 80
ወ/ሮ መዓዛ ይሕደጎ እና እነ አየለ ወልዴ

የሰ/መ/ቁ 31634 ........ 83
ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ የአቶ ወርቁ ሚስት ወ/ሮ ጽጌ በየነ

የሰ/መ/ቁ 31917 ........ 90
የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና ወ/ሮ ለምለም ገ/ትንሳኤ

የሰ/መ/ቁ 32521 ........ 94
የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና ዳባ ኢጃቶ

የሰ/መ/ቁ 34456 ........ 99
የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ እና ወ/ት ደብሪቱ ወልደሃና

**የሽያጭ ውል** ........ 103

የሰ/መ/ቁ 16455 ........ 104
ወ/ት አዜብ ሽፈራው እና ወ/ሮ ታየች ንጉሴ

የሰ/መ/ቁ 18380 ........ 108
አቶ ማሞ ደምሴ እና እነ አቶ አያሌው ገ/እግዚአብሔር

የሰ/መ/ቁ 22448 ........ 112
ኦርቢስ የንግድና ቴክኒክ ክፍል አ/ማህበር እና አቶ ሙሉነህ ካሳ

የሰ/መ/ቁ 22860 ........ 116
ሰንላይት ኢንዱስትሪና ማከፋፈያ ኩባንያ እና አቶ ካሣዬ ዘውዴ

የሰ/መ/ቁ 23331 ........ 119
ጀማል ሐሚድ እና እነ ወ/ሮ ለተሃይማኖት ተክሌ

የሰ/መ/ቁ 23895 ........ 122
ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል እና መኮንን ሉሌ

የሰ/መ/ቁ 24554 ........ 125
አቶ አይሸሹም ጋተው እና እነ የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ

የሰ/መ/ቁ 24974 ........ 132
እነ አቶ ፈቃዱ ዴሬሎ እና እነ አቶ ንጉሴ ወርቁ

የሰ/መ/ቁ 25165 ........................................................................136
አቶ እርቄ ጎዳ እና አቶ አህመድ አብዱልሐሚድ
የሰ/መ/ቁ 26996 ........................................................................140
አቶ በቀለ ደቦጭ እና እነ ወ/ሮ አዛለች ደሣለኝ
የሰ/መ/ቁ 27349 ........................................................................146
ብሔራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና ዘላቂ ግብርና ተሐድሶ ኮሚሽን
የሰ/መ/ቁ 28663 ........................................................................150
አቶ ካሣሁን ገዛኸኝ እና ወ/ሮ አልማዝ ወልዴ
የሰ/መ/ቁ 29233 ........................................................................153
አቶ ሙሂዲን ፋሪስ እና አቶ ኢያሱ በዕደ ማርያም
የሰ/መ/ቁ 31223 ........................................................................159
ወ/ሮ ለምለም መኩሪያ እና ወ/ሮ ሙሉእመቤት ጌታሁን
የሰ/መ/ቁ 31482 ........................................................................163
ወ/ሮ ዓለምነሽ ወ/አገኘሁ እና አቶ አባተ ተፈሪ
የሰ/መ/ቁ 31640 ........................................................................166
አቶ ገረመው ግዛው እና አቶ ፈቃዱ ያደቴ
የሰ/መ/ቁ 32222 ........................................................................170
አቶ መሐመድ ኢብራሂም እና አቶ ታይደር ማች
የሰ/መ/ቁ 32899 ........................................................................174
ወ/ሮ አስካለ ማርያም ታደሰ እና አቶ ተሸመ ካሣዬ

**የጠበቆች ፈቃድ** ........................................................ 180

የሰ/መ/ቁ 25287 ........................................................................181
ሜድሮክ ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ በዛወርቅ ሺመላስ

**ውርስ** ....................................................................................191

የሰ/መ/ቁ 23322 ........................................................................192
ወ/ሮ አዳነች ወርዶፋ እና እነ ወ/ሮ አስናቀች ወርዶፋ
የሰ/መ/ቁ 25869 ........................................................................197
ወ/ሮ አየለች አልታዬ እና ወ/ሮ አስናቀች አየለ
የሰ/መ/ቁ 30158 ........................................................................201
ወ/ሮ ፀሐይነሽ አደም ሞግዚት ሐይሉ ሲሳይ እና የኮ/ል እሸቱ ተስፋዬ ወራሾች
የሰ/መ/ቁ 30991 ........................................................................207
እማሆይ ወይንሸት አድማሱ እና እነ ወ/ሮ ክብነሽ ስዩም የሰ/መ/ቁ
32414........................................................................................212
ወ/ሮ ባዩሽ ደጀኔ እና እነ ወ/ሮ ሃሳብ ከፋይ ጌራወርቅ
የሰ/መ/ቁ 34076 ........................................................................217
ወ/ሮ ዘነበወርቅ ወልዱ ፀጋ እና እነ እማሆይ ድብቅነሽ ግዛው

**መድን** .................................................................................220

የሰ/መ/ቁ 22530........................................................................221
የቀድሞው የኢትዮጵያ ጭነት ማመላለሻ ኮርፖሬሽን እና እነ አጂፕ ኢትዮጵያ አክሲዮን ማህበር
የሰ/መ/ቁ 24703 ........................................................................225
የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ት ቢሮ
የሰ/መ/ቁ 24704 ........................................................................229
የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ ጤና ቢሮ
የሰ/መ/ቁ 28254 ........................................................................234
የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና መኮንን መስፍን
የሰ/መ/ቁ 31334 ........................................................................239
የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ወ/ሮ ለተብርሃን በየነ

**ወንጀል** ............................................................................ 246

የሰ/መ/ቁ 21411 ........................................................................247
የቤንሻንጉል ጉመዝ ክልል ዐ/ሕግ እና ወ/ር ሰይድ እንድሪስ ዩሱፍ
የሰ/መ/ቁ 22069 ........................................................................251
የአማራ ብ/ክ/መንግሥት ፍትሕ ቢሮ እና አቶ አስማማው አራጌ
የሰ/መ/ቁ 22452 ........................................................................255
የኦሮሚያ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እና አሣምነው ገ/መስቀል
የሰ/መ/ቁ 22514 ........................................................................262
አቶ ኩራት ተገኝ እና ዓቃቤ ህግ
የሰ/መ/ቁ 23855 ........................................................................265
የጉምሩክ ዐቃቤ ሕግ እና አቶ ፀጋሁን መንግሥቱ
የሰ/መ/ቁ 24278 ........................................................................270
ሰለሞን ሄርጃቦ እና የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ የሥ/ፀ/ሙ/ኮ/ዐ/ሕግ

የሰ/መ/ቁ 28952 ....................................................................273
የጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ እና እነ ባንቲ ታኤራ
የሰ/መ/ቁ 29325 ....................................................................275
ኤርምያስ ካሣ ተፈራ እና ዓቃቤ ሕግ
የሰ/መ/ቁ 31731 ....................................................................278
የኦሮሚያ ጠቅላይ ዕቃቤ ሕግ እና ዘሪሁን ታደሰ
የሰ/መ/ቁ 31734 ....................................................................283
አቶ አስናቀ በቀለ እና ዓቃቤ ሕግ
የሰ/መ/ቁ 34077 ....................................................................287
አቶ ሰይድ ይመር እና የአማራ ክልል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን
የሰ/መ/ቁ 34280 ....................................................................292
አቶ ግርማይ ደስታ እና ዓቃቤ ሕግ
የሰ/መ/ቁ 34521 ....................................................................297
የአማራ ብ/ክ/መ/ፍትሕ ቢሮ እና ስንታየሁ ተፈራ
የሰ/መ/ቁ 35611 ....................................................................300
ሻለቃ ታደሰ ካሕሳይ እና የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ

**ግብር** ....................................................................303

የሰ/መ/ቁ 18809 ....................................................................304
አቶ ሚሊዮን ዑመር እና የፌደራል የአገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን

**የንግድ ተቋማት** ....................................................................307

የሰ/መ/ቁ 19258 ....................................................................308
አቶ ተክሌ ዋቅጅራ እና አቶ ሾንጣ ጉቡ
የሰ/መ/ቁ 23389 ....................................................................314
የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አ/ማኀበር እና እነ ባህሩ አብርሃም
የሰ/መ/ቁ 28923 ....................................................................318
የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ አክስዮን ማሕበር እና የባህር ዳር ልዩ አስተዳደር እና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ

**አፈጻጸም** ....................................................................323

የሰ/መ/ቁ 10489 ....................................................................324
የስራና ከተማ ልማት ሚ/ር ተተኪ መሠረተ ልማት ሚ/ር እና የቀድሞ ብሔራዊ መሐንዲሶችና ሥራ ተቋራጮች ኃ/የተ/የግ/ማ
የሰ/መ/ቁ 18576 ....................................................................330
ወ/ሮ ደስታ መኮንን እና ወ/ት መሰሉ ጌታሁን
የሰ/መ/ቁ 19283....................................................................335
ወ/ሮ መድኃኒት ኃይሉ እና የኮንስትራክሽን ቢዝነስ ባንክ
የሰ/መ/ቁ 22481 ....................................................................340
አቶ ክፍሌ ወልዴ እና ፔትራም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኀበር
የሰ/መ/ቁ 22930 ....................................................................350
ወ/ሮ ታድሬ አባተ እና ወ/ሮ ዓለም ገ/የሱስ
የሰ/መ/ቁ 23733 ....................................................................353
ሃፍቶም ገ/እብዝጊ እና እነ ሙሉ ካሳ
የሰ/መ/ቁ 23989 ....................................................................356
አቶ ደስታ ሠርዳ እና የመከተል ዞን ፍትህ መምሪያ
የሰ/መ/ቁ 25031 ....................................................................360
ወ/ሮ አልታየወርቅ ኃ/ማርያም እና አቶ ዓለማየሁ ገለቱ
የሰ/መ/ቁ 26553 ....................................................................363
የባህርዳር ልዩ ዞን ገንዘብ መምሪያ እና የኮንስትራክሽ ቢዝነስ ባንክ እና ሙክታር መሐመድ
የሰ/መ/ቁ 27574 ....................................................................370
ወ/ሮ አለሚቱ ተረፈ እና የትግል ፍሬ ልብስ ስፌት ማኀበር
የሰ/መ/ቁ 28019 ....................................................................373
አቶ ብርሃኑ ገ/እግዚአብሔር እና ወ/ሮ ገርጊስ ናይዝጊ
የሰ/መ/ቁ 28154 ....................................................................376
የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
የሰ/መ/ቁ 28362 ....................................................................379
አቶ መሐመድ ኑር ጀብራል እና እነ ወ/ሪት ውበት ላሊሶ
የሰ/መ/ቁ 29344 ....................................................................383
ወ/ሮ ዝማም ህሉፍ እና አቶ መረሣ ገ/ዩሐንስ
የሰ/መ/ቁ 29371 ....................................................................387
ሶፊያ መሐመድ እና እነ ኢብራሂም መሐመድ
የሰ/መ/ቁ 29653 ....................................................................391
አቶ ነጋ ደምሴ እና ሃምሳ አላቃ አዲሱ ደምስ
የሰ/መ/ቁ 33760 ....................................................................394
ሐጂ ታጁ ለገሠ እና የጎንደር ከተማ የመሀል አራዳ ቀበሌ አስተዳደር

# የውል ህግ

# ልዩ ልዩ

የሰ/መ/ቁ. 12719

ታህሣሥ 17 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

**አመልካች፡-** ሉክሰር የቱሪስትና የጉዞ ወኪል ኃ/የተ/የግ/ማኅበር - አልቀረበም፡፡

**ተጠሪ፡-** ብሩኔይስ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር - ጠበቃ ተስፋዬ ዘውዴ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፣

**ፍ ር ድ**

የአሁኑ አመልካች ኅዳር 28 ቀን 1993 ዓ.ም. ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ፣ የአሁኑ ተጠሪ ሚያዝያ 21 ቀን 1991 ዓ.ም. ካቻማሌ አስ.ፒ. ኤ. ለተባለ ድርጅት የአሜሪካን ዶላር 540,000 /አምስት መቶ አርባ ሺህ/ ለመክፈል ግዴታ ገብቷል፡፡ ከዚህ በኋላ ተጠሪ እና ካቻማሌ አስ ፒ ኤ ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. ባደረጉት ተጨማሪ ውል መሰረት ተጠሪ ላለበት ዕዳ ከፊል ክፍያ እንዲሆን ጠቅላላ ዋጋቸው የአሜሪካን ዶላር 452,338 /አራት መቶ ሃምሣ ሁለት ሺ ሦስት መቶ ሰላሣ ስምንት/ ወይም በኢትዮጵያ ብር 3,673,000 /ሦስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰባ ሦስት ሺህ/ የሆኑ አዲስ አበባ አምቼ ኩባንያ የቆሙ አምስት አውቶብሶችን ለአመልካች ለማስረከብ ግዴታ ገብቷል፡፡ ተጠሪ በገባው ግዴታ መሠረት አውቶብሶቹን ለአመልካች ስላላስረከበ በፍ/ቤቱ አስገዳጅነት እንዲያስረክበውና አውቶቡሶቹን ባለመረከቡ ምክንያት አመልካች ያጣውን ጥቅም ከህጋዊ ወለዱ ጋር እንዲከፈለው ጠይቋል፡፡ ተጠሪ ጥር 7 ቀን 1993 ዓ.ም. ከሰጠው መልስ መካከል፣ አመልካች ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. ተፈረመ በተባለው ስምምነት ላይም ሆነ



ሚያዝያ 21 ቀን 1991 ዓ.ም. በተደረገው ውል ላይ ተዋዋይ ወገን ባለመሆኑ ሠነዱን መሠረት አድርጎ የዳኝነት ጥያቄ ለማቅረብ የሚያስችለው መብት የለም፤ ከተገለፀው ሰነድ ላይ ስሙ የተመለከተ ቢሆንም እንደ ካቻማሊ ኤስ. ፒ. ኤ. ሆኖ አውቶቡሶቹን ሊረከብ እንጂ ርክክቡ ለከሳሹ የባለቤትነት መብት እንዲያጎናጽፍ ታስቦ የተፃፈ አይደለም፡፡ ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም የተፃፈው ሰነድ እንደዋናው ውል በሁለት ምስክሮች ያልተረጋገጠ ስለሆነ የሚያጎናጽፈው መብት የለም፤ ከዚህ በተጨማሪ ይህ ሰነድ ተጨማሪ ውል ሳይሆን ደብዳቤ ብቻ በመሆኑ ተጠሪ ስለዕዳው አከፋፈል አዲስ ሐሣብ አቀረበ እንጂ የገባው ግዴታ የለም የሚል ይገኝበታል፡፡ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ግንቦት 19 ቀን 1995 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. የተፃፈው ሰነድ አዲስ የውል ሐሣብ የያዘ ደብዳቤ እንጂ ተጨማሪ ውል ባለመሆኑ ፍ/ቤቱ ጥያቄውን አልተቀበለውም፡፡ ተከሣሽ ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን አውቶቡሶች ለከሳሽ ሊያስክብም ሆነ ዋጋቸውን ሊተካ እንዲሁም ርክክብ ቢፈፀም ኖሮ ተሽከርካሪዎቹ ሊያስገኙ ይችሉ የነበረውን ጥቅም ተከሣሽ ለከሳሽ ሊከፍል አይገደድም በማለት ወስኗል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰኔ 24 ቀን 1995 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይኸን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ ይህ ችሎት ታህሣሥ 30 ቀን 1996 ዓ.ም. መዝገቡ ለሰበር እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ የግራ ቀኙን መልስ እና የመልስ መልስ ከመዝገቡ ጋር አያይዟል፡፡ በዚህ ጉዳይ ውሣኔ ማግኘት የሚገባው ጭብጥ፣ ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. በአሁኑ ተጠሪና በካቻማሊ ኤስ. ፒ. ኤ. መካከል ተፈረመ የተባለው ሰነድ የዕዳ ክፍያ ተጨማሪ ስምምነት ሳይሆን አዲስ ሐሣብ የቀረበበት ደብዳቤ ስለሆነ መልስ ሰጭ በዚህ ደብዳቤ የሚገደድበት ምክንያት የለም መባሉ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ይሆናል፡፡

ይህ ችሎት አቤቱታውን በሥር ከተደረጉ ክርክሮች እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ የአሁኑ አመልካች በሥር ፍ/ቤት አቅርቦት የነበረው ክስ፣ የአሁኑ ተጠሪ ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. ከካቻማሊ ኤስ. ፒ. ኤ. ጋር ተጨማሪ ውል ሲያደርግ አምስት አውቶብሶችን ለኔ ለማስረከብ ግዴታ የገባ በመሆኑ በገባው ግዴታ መሠረት ርክክቡን እንዲፈጽምልኝ፤ ርክክቡም በመዘግየቱ የቀረብኝን ጥቅም ይተካልኝ በማለት ጠይቋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠውም መልስ ሆነ ለሰበር ቅሬታው ጥር 27 ቀን 1996 ዓ.ም. ለዚህ ችሎት ከሰጣቸው መልሶች መካከል፣ ማያዝያ 21 ቀን 1991 ዓ.ም. የተደረገው ስምምነት ተከሳሽን /የአሁን ተጠሪ/ እና ካቻማሊ ኤስ ፒ ኤን ብቻ የሚመለከት ነው፡፡ ሰኔ 30 ቀን 1991 ተፃፈ የተባለውም ሰነድ ቢሆን ተጠሪንና ካቻማሊ ኤስ ፒ ኤን ብቻ የሚመለከት ሆኖ በሰነዱ ላይ የከሳሽ /የአመልካች/ ስም መጠቀሱ በሰነዱ ላይ የተመለከቱትን አውቶቡሶች እንደካቻማሊ ኤስ ፒ ኤ ሆኖ እንዲረከብ እንጂ ከርክክቡ በኋላ የባለቤትነት መብት እንዲያገኝ ታስቦ የተዘጋጀ ባመሆኑ የሥር ከሳሽ የሆነው የአሁኑ አመልካች ተዋዋይ ወገን ያልሆነበትን ሰነድ መነሻ አድርጎ መብት ለመጠየቅ አይችልም፡፡ ሦስትኛ ወገኖች የውል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ውሉ በግልጽ ለይቶ የማመልከት ግዴታ ያለበት መሆኑን በመግለጽ ሰፊ መልስ ሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል የአመልካች ጠበቃ በበኩሉ፣ ተዋዋይ ወገኖች በውሉ ያልነበሩ ሦስተኛ ወገኖችን የውሉ ተጠቃሚ ስለሚያደርጉበት የሕግ አግባብ፤ ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. የአሁኑ ተጠሪ በራሱ አነሳሽነት ለአሁኑ በስር ባለገንዘቡ /በካቻማሌ አስ. ፒ. ኤ./ ተቀባይነት በማግኘቱ በገባው ግዴታ ለአሁኑ ተጠሪ አውቶቡሶቹን የማስረከብ ግዴታ ያለበት መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡

በበኩላችን ጉዳዩን በሚከተለው አኳኋን መርምረናል፡፡ በመሠረቱ ከውል የሚመነጭ መብትም ሆነ ግዴታ የሚመሰረተው ውሉን በፈቃዳቸውና በስምምነታቸው ባቋቋሙት ተዋዋይ ወገኖች ላይ መሆኑ አጠያያቂ



አይደለም፡፡ በውሉ መደረግ ጊዜ ተዋዋይ ወገን ያልነበሩ ሦስተኛ ወገኖች የመብቱ ተጠቃሚዎችም ሆነ የግዴታው ተጠያቂዎች ሊሆኑ እንደማይችሉ የፍትሐብሔር ሕግ ቁ. 1952/1/ ያስገነዝባል፡፡ ይህ አጠቃላይ መርህ Privity of contract or Relative Effect of contract በመባል የሚታወቀው የውል ሕግ አጠቃላይ መርህ ነው፡፡ ውሎች ባቋቋሟቸው ሰዎች ላይ ሕግ ናቸው የሚለው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1731 አነጋገርም ከዚህ መርህ ጋር የሚጣጣም ድንጋጌ ነው፡፡ ከዚህ አጠቃላይ መርህ በተለየ ሁኔታ በአንድ ውል ምስረታ ጊዜ የውሉ ተካፋይ ያልነበሩ ሦስተኛ ወገኖች ወደ ውሉ ውጤት ሊገቡ የሚችሉበት አግባብ በሕጉ የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ የተመለከተ ስለመሆኑ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1957 እና በሚቀሉት አንቀጾች መሠረት ለሦስተኛ ወገን ጥቅም ሲባል የሚደረጉ የውል ስምምነቶች /Contract for the Benefit of third parties/፣ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2212/1/ እና 2222 መሠረት ወካይ የተባለው ተወካዩ ከሌላው ጋር ላደረገው የውል አፈፃፀም ተጠያቂ የሚሆንበት አግባብ ወይም በንግድ ሕግ ቁጥር 701/1፣ 706 መሠረት ለአንድ የተለየ ተጠቃሚ ጥቅም ሲባል የሚደረጉ የኢንሹራንስ ውሎች የዚህ አጠቃላይ የውል ሕግ መርህ ልዩነቶች /Exceptions/ ስለመሆናቸው ለአብነት ለመጥቀስ የሚቻል ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ሚያዝያ 21 ቀን 1991 ዓ.ም. በተደረገ ውል የአሁኑ ተጠሪ 540,000 (አምስት መቶ አርባ ሺ) የአሜሪካን ዶላር ለካቻማሊ ኤስ. ፒ. ኤ. ለመክፈል ግዴታ የገባ መሆኑ ታውቋል፡፡ ከዚህ የግዴታ ስምምነት ጥቂት ወራት በኋላ የአሁኑ ተጠሪ እራሱ ባዘጋጀው ሰነድ ቀደም ሲል የነበረበትን የገንዘብ ዕዳ መቀነሻ ይሆን ዘንድ ዋጋቸው የአሜሪካን ዶላር 462,338 የሆኑ የሻንሲ ቁጥራቸው የተጠቀሱትን አምስት አውቶቡሶች በአይነት ለአሁኑ አመልካች ለማስረከብ፣ ቀሪውንም የገንዘብ ዕዳ ለባለገንዘቡ በየወሩ በሚደረግ የክፍያ ስርዓት ለማጠናቀቅ ከባለገንዘቡ ጋር ስምምነት

ተደርሶ በውሉ መደረግ ጊዜ የውሉ ተካፋይ ያልነበረውን የአሁኑን አመልካች የውሉ ተጠቃሚ /Beneficiary/ አድርገው ሰይመውት የነበረ መሆኑ ታውቋል፡፡ በአሁኑ ተጠሪ እና በካቻማሊ ኤስ. ፒ. ኤ. መካከል ዕዳን በአይነት ለመቀነስ መግባባት ላይ ተደርሶ ያልነበረ ቢሆን ኖሮ የአሁኑ ተጠሪ እራሱ ባዘጋጀው ሰነድ በባዶ ሜዳ ተነስቶ የአሁኑን አመልካች የውሉ ተጠቃሚ አድርጎ ይጠቅሰው ነበር ብሎ ለማለትም ጭራሹኑ የሚቻል አልነበረም፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ከሥር ባለገንዘቡ /ካቻማሊ ኤስ. ፒ. ኤ./ ጋር ያደረገው ዋናው ውል /ሚያዝያ 21 ቀን 1991 ዓ.ም. የተደረገው/ በልዩ ሥርዓት እንዲደረግ ሕግ የሚያስገድድ በመሆኑ ከቀድሞው ውል ጋር በተዛመደ አኳኋን የተደረገው የሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም ተጨማሪ ውል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1684 በተመለከተው አኳኋን በዝምታም ጭምር መቀበል የሚቻል የነበረ ቢሆንም ተዋዋይ ካቻማሊ ኤስ.ፒ. ኤ. በፊርማውም ጭምር አረጋግጦታል፡፡ በተጨማሪ የአሁኑ ተጠሪ ውሉ በተደረገ ማግሥት ማለትም ሐምሌ 1 ቀን 1991 ዓ.ም. ለእዳው መቀነሻ እንዲሆን ታስቦ ለአሁኑ አመልካች ለማስረከብ በተጨማሪ ውሉ ግዴታ የገባባቸው አውቶቡሶች ከማናቸውም ዕዳ ነፃ መሆናቸውን ማረጋገጫ መስጠቱን ይህ ችሎት ከሥር መዝገቡ ጭምር ተረድቷል፡፡ ተጠሪ በገባው ግዴታ መሠረት አውቶቡሶችን ለአሁኑ አመልካች ባለማስረከቡ ተዋዋይ /ካቻማሊ አስ. ፒ. ኤ./ በተከታታይ ጊዜያት ግዴታውን እንዲወጣ አሳስቦታል፡፡ ግዴታውንም የማይወጣም ከሆነ የሕግ እርምጃ ለመውሰድ የሚገደድ መሆኑን ጭምር ሲገልጽ ቆይቷል፡፡ ይህ አካሄድ ደግሞ የተጠሪ ጠበቃ እንደሚለው ሳይሆን የሕጉን አግባብ የተከተለ አካሄድ መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁ. 1958/2/ ያስገነዝበናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካችም ቢሆን በጠበቃው አማካኝነት ተጠሪ አውቶቡሶችን እንዲያስረክበው ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ መቆየቱን ከጉዳዩ መረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ሁሉ ሁኔታ በአንድነት ተደምሮ ሲታይ ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. የተፈረመው ሰነድ ተጠሪ እንደሚለው አዲስ የውል ሐሣብ የቀረበበት ደብዳቤ



ሳይሆን የሕጉን ሥርዓት የተከተለና የሁሉም ወገኖች ማለትም የተዋዋዩ /የካቻማሌ አስ.ፒ.ኤ./ የተስፋ ሰጭው /የአሁኑ ተጠሪ/ እና የተጠቃሚው /የአመልካች/ ይሁንታ የነበረበት ተጨማሪ ውል መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡

የሥር ፍ/ቤት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1734 መሠረት ከዋናው ውል መደረግና ከዚያ በኋላ የተዋዋይ ወገኖች የሐሣብ አንድነት ምን እንደነበረ ከፍ ብለን በገለጽነው አኳኋን መርምሮ ውሣኔ ላይ መድረስ ሲገባው ዋናው ውል ራሱ ልዩ የፎርም ስርዓት እንዲከተል ሕጉ በአስገዳጅነት የጠየቀው መስፈርት ሳይኖር ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. ዋናውን ውል ተከትሎ ተዘጋጀ የተባለው ሠነድ የአፃፃፍ ስልቱ ከውል ይልቅ የደብዳቤ ቅርጽ ያለው ነው፣ ፊርማውም ቢሆን በካቻማሊ ኤስ. ፒ. ኤ. ሊሰፍር የሚችልበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል በሚል በሕግ ያልተደገፈ ግምታዊ /Speculation/ እሳቤ ላይ ደርሶ ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. በግራ ቀኙ የተፈረመው ሰነድ ደብዳቤ እንጂ ተጨማሪ ውል አይደለም ብሎ ማለቱ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመጨረሻ የውሉ ተጠቃሚ የሆነው የአሁኑ አመልካች በካቻማሌ ኤስ. ፒ. ኤ. እና በአሁኑ ተጠሪ መካከል ተደርጎ የነበረውን የውል ስምምነት የተቀበለው በመሆኑ በተስፋ ሰጭው ማለትም በአሁኑ ተጠሪ ላይ ውሉ የሚያስገኛቸውን መብቶች በማይመለስ አኳኋን ይዞ እንደሚቆይ እና ተስፋ ሰጭው በተዋዋዩ ማለትም በካቻማሌ ኤስ. ፒ. ኤ. ላይ ሊኖረው የሚችለውን የግል የሆኑትን መከራከሪያዎች ሰበብ በማድረግ በተጠቃሚው ላይ መቃወሚያ ሊያደርግ የማይችል ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1961 ያስገነዝባል፡፡ አጠቃላይ የሕጉ አፈፃፀም ይህ ሆኖ ሳለ የአሁኑ ተጠሪ ከግዴታው ጋር ጭራሽ ባልተገናኘ ሁኔታ ካቻማሊ ኤስ. ፒ. ኤ. ውክልናዬን ስለሰረዘ ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. የተደረገውን ስምምነት ሰርዣለሁ ብሎ ማለቱ ከተጠያቂነት አያድነውም ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. በተጠሪውና በካቻማሌ ኤስ. ፒ. ኤ. መካከል የአሁኑን አመልካች ተጠቃሚ በማድረግ የተፈረመው ሰነድ የዕዳ መክፈያ ተጨማሪ ስምምነት ነው ብለናል፣
2. ተጠሪ ለአሁኑ አመልካች ለማስረከብ ግዴታ የገባውን የሻንሲ ቁጥራቸው የተመለከቱትን አምስት አውቶቡሶች ለአመልካች ያስረክብ፣
3. ተጠሪ አውቶቡሶቹን ማስረከብ ካልቻለ ጠቅላላ ዋጋቸው 452,338 /አራት መቶ ሃምሣ ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ሰላሣ ስምንት/ የአሜሪካን ዶላር ወይም በአፈፃፀም ወቅት በሚኖረው የምንዛሬ ተመን መሠረት ዋጋው በብር ተሰልቶ ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚኖረው ሕጋዊ ወለድ ጋር ለአመልካች ይክፈል፣
4. አመልካች ወጭና ኪሣራ የማቅረብ መብቱ ተጠብቋል፣

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መዝ/ቁጥር 20232

ሐምሌ 24 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
አሰግድ ጋሻው
መስፍን ዕቁበዮናስ
ተሻገር ገ/ሥላሴ
ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- አቶ ትዕግሥቱ ብዛ ቀርቧል

ተጠሪ፡- አቶ ይሃ ይብሬ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው አመልካች ነሐሴ 17 ቀን 1997 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት ሲሆን የጉዳዩ መነሻ አመልካች ጥቅምት 14 ቀን 1989 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር ያደረጉት ውልና ለውሉ ማረጋገጫና ማስፈፀሚያነት በዚሁ ቀን በቁጥር ኢ.ዲ 657900 የሆነ ቼክ ብር 90,000 (ዘጠና ሺህ) የካቲት 1 ቀን 1989 ዓ.ም የሚከፈል ለተጠሪ ከሰጡ በኋላ ገንዘቡ እንዳይከፈል አግደውብኛል በማለት ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ክስ አቅርቦ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች ያቀረቡትን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በቀረበው ክስ መሠረት በቼኩ የተመለከተውን ገንዘብ የሥር ተከሣሽ (አመልካች) እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ይህንኑ ውሣኔ አፀናው፡፡

ለሰበር የቀረበው አቤቱታ አመልካች ቼኩን የሰጠው ተገዶ ያለፍቃዱና ያለፍላጐት መሆኑን በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ የውል ህጐችን መሠረታዊ መርሆዎች በግልጽ ተንድለው እያሉ የሥር ፍ/ቤት የቀረበውን ሠነድ ሕጋዊ እንዳልሆነ እና ውሉ ጉድለት እንደሌለበት አድርጐ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለው በመሆኑ እንዲሻርለት ጠይቋል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም መዝገቡን ከመረመረ በኋላ ይህንኑ ቅሬታ ለማጣራት ተጠሪ እንዲቀርብ ያዘዘ ሲሆን ተጠሪው ሊቀርብ ባለመቻሉ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ሰኔ 7 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት አዟል፡፡

በዚሁ ሁኔታ መዝገቡ ተመርምሯል፡፡ ከቀረበው አቤቱታና ከሥር ፍ/ቤት ውሣኔ አንፃር አመልካች ቼኩን የፈረምኩት ተገድጄ ነው በማለት ያቀረበው የሕግ ክርክር ውሉን ፈራሽ ያደርገዋል ወይስ አያደርገውም የሚለውን እንደሚከተለው ከውል ሕጐች መሠረታዊ መርህ ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

በፍሬ ነገር ክርክር ደረጃ በሥር ፍ/ቤት ውሣኔ እንደተብራራው አመልካች ለተጠሪ የብር 90,000 (ዘጠና ሺህ) ተከፋይ ቼክ ጥቅምት 14 ቀን 1989 ዓ.ም መስጠቱን አልካደም፡፡ ሆኖም በቼኩ ክፍያ አለመፈፀም ያቀረበው መቃወሚያ ቼኩና ውሉ የተፃፈው ተጠሪ በወረዳ 5 ፖሊስ ጣቢያ አሳስሮት በእሥር ላይ ሆኖ ተገዶ የፈረመው ስለሆነ እና በዚሁ ወንጀል የፖሊስ ጣቢያው አዛዥና መርማሪ ፖሊስ በወንጀል ተከሰው በዐቃቤ ህግ ክስ የተመሠረተባቸው መሆኑን በመግለጽ ለዚህም የሰውና የሰነድ መከላከያ ማስረጃ በማቅረብ በቼኩ የተመለከተውን ገንዘብ ለመክፈል እንደማይገደድ ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍ/ቤትም ይህንኑ ጉዳይ ለማጣራት አመልካች ያቀረባቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ ቼኩን ለማስፈረም የኃይል ሥራ ተፈጽሟል ለማለት አይቻልም በማለት መቃወሚያውን ውድቅ አድርጓል፡፡

በሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ውስጥ እንደተመለከተው የማስገደድ ተግባር በአመልካች ላይ ስለመፈፀሙ የቀረበው የሰውና የሰነድ ማስረጃ እንዲሁም በወቅቱ የፖሊስ ጣቢያው አዛዥ በነበረው ሻ/ል ክብረት ከበደ ላይ የቀረበው የወንጀል ክስ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ. 07009 ጥቅምት 11 ቀን 1998 ዓ.ም በልዩ ወ/መ/ሕግ አዋጅ ቁጥር 214/74 አንቀጽ 23-1ሀ መሠረት የተሰጠው



የጥፋተኛነት ውሣኔ ሲታይ በወቅቱ አመልካች ውሉን የተዋዋለው በአስገዳጅ ሁኔታ ሥር ሆኖ እንደነበር የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡

ይህ ሁኔታ ከሕጉ አንፃር ምን ውጤት ሊኖረው ይችላል የሚለውን ለማጤን ከውል መሠረታዊ መርህ ጋር መጤን አለበት፡፡ ቼክ የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ መሆኑ በንግድ ሕግ ቁጥር 715 የተመለከተ ነው፡፡ በእነዚህ የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታዎች የሚፈጠሩባቸውና የሚረጋገጡባቸው ናቸው፡፡ የሰነዱ አውጪ ግዴታ የሚገባበት ሲሆን የሰነዱ አምጪ /ያዥ/ የመብት ወይም ጥቅም ማረጋገጫ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ይህንን ሁኔታ ለመፍጠር እንደማንኛውም ውሎች የውል ህግ መሠረታዊ ድንጋጌዎች መሟላት እንዳለባቸው የሚያከራክር አይደለም ፡፡ ምክንያቱም እነዚህ የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች መሠረት በባህሪያቸውና በዓላማቸው ልዩ ቢሆንም ተዋዋይ ወገኖች በዚህ ሰነድ መብትና ግዴታ ለመፍጠር የውል ሕግ አጠቃላይ መርሆዎችን አሟልተውና አክብረው መገኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከእነዚህ መሠረታዊ መርሆዎች ውስጥ አንደኛው ውሉን ለመፈፀም (ለመዋዋል) የተዋዋይ ወገኖች ፈቃደኛነትና ነፃነት መኖር አስፈላጊነት ነው፡፡ ውል በተዋዋይ ወገኖች ሙሉ ፈቃደኛነት ላይ ካልተመሠረተ በሕግ ፊት የፀና ሊሆን አይችልም በመሆኑም የውል መፈረስ ምክንያት ከሚሆኑት መሠረታዊ ነገሮች አንዱ በውል አመሠራረት ሂደት ውስጥ በአንደኛው ወገን የሚፈፀም የኃይል ወይም የማስገደድ ተግባር ነው፡፡ ይህ መሠረታዊ መርህ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1679 ስር በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ይህንን መሠረታዊ መርህ በዝርዝር የሚያመለክተው የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1706 እና ተከታዩ የማስገደድ ተግባሩ በማን ተፈፀመ? እንዴትስ ተፈፀመ? በማን ላይ ተፈፀመ የሚሉትን ሁኔታዎች በዝርዝር አመልክቷል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ላይ ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተው አመልካች ቼኩን የፈረመው በፖሊስ ጣቢያ ታስሮ በፖሊስ ጣቢያው አዛዥ አስገዳጅነት እንደሆነ በቀረቡት ማስረጃዎች በሥር ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡

በዚህ አይነት አስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ የተደረገው ውል ፈቃደኛነትና የመዋዋል ነፃነት ጉድለት ያለበት መሆኑን መገንዘብ የሚያዳግት አይደለም፡፡ ይህ ሁኔታ በተፈጠረ ጊዜ ደግሞ ውሉን ስለመፈፀም መቃወሚያ አድርጐ ማቅረብ ስለመቻሉ በንግድ ሕግ ቁጥር 841 ተመልክቷል፡፡

በዚህ የንግድ ሕግ ቁጥር 841 ድንጋጌ መሠረት የቼኩ አውጪ በአምጪው ላይ መቃወሚያ ሊያደርግ የሚችለው ቼኩን ያገኘው ቅን ልቦና በጐደለው ሁኔታ ወይም ቼኩን ሲያገኝ ከባድ ጥፋት ያደረገ መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት አሁን የቀረበውን የቼክ ክፍያ ጥያቄ በተመለከተ ተጠሪው ቼኩን ከአመልካች ያገኘው ቅን ልቦና በጐደለው ሁኔታ ከመሆንም አልፎ በማስገደድ ተግባር በመሆኑ ከባድ ጥፋት መፈፀሙ ተረጋግጧል፡፡

ስለዚህ አንድ የኃይል ሥራ ወይም የማስገደድ ተግባር አንድ ተዋዋይ ወገን ሳይወድና ሳይፈቅድ ከፍላጐቱ ውጪ የውል ግዴታ እንዲገባ ለማስገደድ በቃላት ወይም በድርጊት የሚፈፀም ሕገ ወጥ ማስፈራት ወይም ዛቻ ወይም በአካል ላይ የሚፈፀም አድራጐት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በአመልካች ላይ የተፈፀመው የማስገደድ ተግባር እሥር እና ዛቻ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጦ እያለ የሥር ፍ/ቤት በምን ተገደደ በዱላ ወይስ በሌላ በማለት ጭብጥ በመያዝ የመገደድ ተግባር አልተፈፀመበትም በማለት የወሰደው አቋምና የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ አተረጓጐም ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ መሠረታዊ የሆነውን የፈቃደኛነትና የመዋዋል ነፃነትን የሚጋፋ ተግባር ተፈጽሞ እያለ ጉድለት የለበትም ማለት ሕግ ለተዋዋይ ወገኖች የመዋዋል ነፃነት ያደረገውን ጥበቃ በእጅጉ የሚያላላ ውሣኔ ሆኖ በመገኘቱ የሥር ተከሣሽ የአሁን አመልካች ያለፈቃዱ እና ፍላጐቱ ተገዶ በፈረመው ቼክ ክፍያ ሊገደድ አይገባም ብለናል፡፡ ስለዚህ የአመልካች መቃወሚያ በንግድ ሕጉ ቁጥር 841 እና በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1679 መሠረት ተቀባይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡



**ው ሣ ኔ**

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05017 ግንቦት 24 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍቤት በመዝገብ ቁጥር 32762 መጋቢት 16 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ለአመልካች በክሱ ክርክር ምክንያት ለደረሰበት ወጪና ኪሣራ በቁርጥ ብር ሁለት ሺህ (2000) እንዲከፍለው ብለናል፡፡

መዝገቡ ዘግተን ወደመዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 20979

የካቲት 13 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

አብዱራሂም አህመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን-ነ/ፈጅ ጋሻው በርጋ ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** የወ/ሮ ግምጃ በሐቲ ወራሽ ወ/ሮ ሒሩት ቢያድግልኝ - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፣

## ፍ ር ድ

የአሁኑ አመልካች በሥር ፍ/ቤት አሻሽሎ ባቀረበው ክስ ለወ/ሮ ግምጃ በሐቲ ሰኔ 2 ቀን 1992 ዓ.ም በተፈረመ የቴሌፎን ደንበኛነት ውል ቁጥር 626382 የሆነ የስልክ መስመር ወራሻቸውና ወኪላቸው በሆነችው በአሁኗ ተጠሪ አማካኝነት አስገብቶ የነበረ መሆኑን ገልጾ፣ ከየካቲት ወር 1994 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ ወር 1994 ዓ.ም. ድረስ የሚፈለገውን የአገልግሎት ሂሣብ ብር 5023.36 ስላልከፈሉ የአሁኗ ተጠሪ ወራሽ በመሆኗ እንድትከፍል ጠይቋል፡፡ የአሁኗ ተጠሪ የፍ/ሕ/ቁ 2023/ሀ/ በመጥቀስ የተከራከረች ሲሆን አመልካችም ክሱ በይርጋ ቀሪ እንደማይሆን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ የተቀረለት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በግንቦት 16 ቀን 1996 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ፣ የአሁኑ አመልካች ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልጾ የተጠየቀው የስልክ አገልግሎት ሂሣብ የተጠሪ አውራሽ ከሞቱ በኋላ የቆጠረ ስለሆነ እንደ ውርስ ዕዳ የሚቆጠር አይደለም በማለት የቀረበውን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡



የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይኸው ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ ይህ ችሎት መጋቢት 21 ቀን 1998 ዓ.ም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ቅሬታ መርምሮ መዝገቡ ለሰበር እንዲቀርብ ከወሰነ በኋላ የግራ ቀኙን መልስ እና የመልስ መልስ አቀባብሏል፡፡

በበኩላችን ጉዳዩን መርምረናል፡፡ የአሁኗ ተጠሪ የሟች ወራሽ መሆኗን አልካደችም፡፡ በአመልካች አማካኝነት የስልክ መስመሩ በገባ ጊዜ ወኪል ሆና በውሉ ለመገደድ የተስማማች መሆኗም ታውቋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የአሁኗ ተጠሪ አውራሼ የምትላቸው ሰው በሞቱ ጊዜ የውሉን መቋረጥም ሆነ ውሉን ተከትሎ ከአውራሽዋ ሞት በኋላ በስልክ መስመሩ በሚጠየቅ ዕዳ ኃላፊ የማትሆን መሆኗን በመግለጽ ለአመልካች መ/ቤት አላሳወቀችም፡፡ የአሁኑ አመልካች ደግሞ በራሱ አነሳሽነት የተጠሪን አውራሽ ሞት የሚያውቅበት መንገድ የለም፡፡ በዚህ መሠረት አውራሽ የሆነ ሰው ከሞተም በኋላ ቢሆን የሚመጣን የስልክ ሂሣብ የመክፈሉ ግዴታ ውርሱን የተቀበለው ወራሽ ነኝ የሚለው ወገን መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ የስር ፍ/ቤት ዕዳው አውራሽ ከሞቱ በኋላ የቆጠረ የስልክ ሂሣብ ስለሆነ ተጠሪን አይመለከትም ብሎ ማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በሚያዚያ 16 ቀን 1996 ዓ.ም. በፍ/መ/ቁ. 11657 የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በሚያዝያ 26 ቀን 1997 ዓ.ም በመ/ቁ. 33089 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡

2. ተጠሪ ከየካቲት እስከ ሚያዝያ ወር 1994 ዓ.ም የሚፈለግባትን ሂሣብ ብር 5023.36 /አምስት ሺህ ሃያ ሦስት ከሰላሳ ስድስት/ ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ /9%/ ጋር ለአመልካች ትክፈል፡፡ የስልኩን ቀፎ ትመልስ ወይም ዋጋውን ብር

238.70/ሁለት መቶ ሠላሳ ስምንት ከሰባ/ ለአመልካች ትክፈል በማለት ተወስኗል፡፡

3. መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 21531

ጥር 30 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

መስፍን እቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

**አመልካች፡-** ኢትዮ.ትሬዲንግ የንግድ ስራ ማስፋፊያ-አቶ ብርሃኑ አስረስ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** የውሃ ሃብት ሚኒስቴር - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡ ይህ ፍርድ የካቲት 29 ቀን 1999 ዓ.ም. ከተደረገው የቃል ክርክር በኂላ የፍርዱ ግልባጭ በዛሬው ቀን ተፈርሞ ወጭ ተደርጓል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ክርክር የጀመረው የአሁን አመልካች በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአሁኑ ተጠሪ ላይ በጥቅምት 20 ቀን 1995 ዓ.ም የተፃፈ ክስ በመመስረታቸው ነው፡፡ የክሱም ይዘት በአጭሩ፣ ከሣሽ የተከሣሹ ደንበኛ ለሆነው በኢጣሊያ ለሚገኘው ጋዚና ትሬዲንግ ለሚባለው የእቃዎች አቅራቢ ድርጅት የአገር ውስጥ ወኪል ሲሆን፣ ተከሣሹ ከዚሁ አቅራቢ ድርጅት በግዢ ወደ አገር ውስጥ ላስገባቸው ዕቃዎች የክሊራንስ ሰነዶችን በወቅቱ ለከሣሹ ባለማቅረቡ እነዚሁ አቃዎች በጅቡቲ ወደብ አላግባብ ለ15 ቀናት በመቆየታቸው ከሣሹ ለወደብ ኪራይና ለደመራዥ ብር 14,558.17 (አሥራ አራት ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ ስምንት ከአስራ ሰባት) ክፍያ ፈጽሜ ለተከሣሽ ያስረከብኩ በመሆኑ ተከሣሹ ይህንን ገንዘብ ሊተካልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡ ተከሣሹ መ/ቤት ለክሱ በሰጠው መልስ፣ ከሻጩ ጋራ ባደረግነው ውል መሠረት የሚጠበቅብኝን ክፍያ ሙሉ በሙሉ ፈጽሜያለሁ፣ በውሉ አንቀጽ 6

መሠረት የኢንሹራንስ ምስክር ወረቀት ማቅረብ የከሣሹ ግዴታ እንጂ የተከሣሽ አይደለም፣ በሌላ በኩል ከሣሽ ለዚህ ክፍያ የተዳረገው ተከሣሹ ሠነዶቹን በጊዜ ባለማቅረቡ ለመሆኑም በተጨባጭ ማስረጃ አላረጋገጠም ሲል ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠው ውሣኔ፣ በውሉ አንቀጽ 6 መሠረት የኢንሹራንስ የምስክር ወረቀት ለገዢው ወይም ለባንክ የማቅረብ ኃላፊነት የአቅራቢው ማለትም የከሣሽ ነው፣ ከሣሽ ለሰጠው አገልግሎት በውሉ መሠረት ተከፍሎታል፣ በውሉ አንቀጽ 17 መሠረት የዋጋ ለውጥ ካልተደረገ በቀር ለከሣሽ የሚሠጠው ዋጋ በጨረታ ያስቀመጠውን ያህል ብቻ ነው፣ በመሆኑም ከሣሽ ተጨማሪ ገንዘብ እንዲከፈላቸው መጠየቃቸው ግራ ቀኙ በጥር 4 ቀን 1992 ዓ.ም. ካደረጉት ውል መንፈስ ውጪ ነው ሲል የከሣሽን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡

ከሣሽ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 26105 ኅዳር 6 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ይግባኛቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ከ/ፍ/ቤቱ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም ሲል ይግባኙን በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት በሰኔ 22 ቀን 1997 ዓ.ም. ሠርዞታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታም የቀረበው አመልካች መስከረም 11 ቀን 1998 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ የስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለታቸው ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው አንኳር ነጥቦች ሲጠቃለሉ አመልካቹ በውልም ሆነ በሕግ ባልተጣለብኝ ግዴታ ለወደብ ኪራይና ለዳመራዥ ክፍያ የተዳረኩት የኢንሹራንስ ሰነዶቹ በጊዜው ባለመቅረባቸው ብቻ ሣይሆን ተጠሪው እቃውን ከወደብ ለማንሣት አስፈላጊ የሆኑትን የማጓጓዣ ሰነዶችን አና ገንዘብ ሚኒስትር እቃዎቹ ከቀረጥ ነፃ ወደ አገር ውስጥ እንደገቡ ለተጠሪው መ/ቤት የሚሰጠውን ደብዳቤ ተጠሪው በቸልተኝነት በጊዜው ሊያስረክበኝ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ነው፤ ተጠሪው ማለትም የዕቃው ባለቤትና ገዢው በን/ሕ/ቁ 48 እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2221/1/ እና /2/ የተጣለበትን ግዴታ በአግባቡ አልተወጣም፤ በሌላ በኩል የተጠሪው



ኃላፊነት ሊታይ የሚገባው ከውሉ አንፃር ብቻ ሣይሆን ከውል ውጪ የሚመነጩ ኃላፊነቶችንም ከሚመለከቱ ሕጎች አንፃር ነው፤ በመሆኑም እቃዎቹ በወደብ የዘገዩት በተጠሪው ጥፋት በመሆኑ ገንዘቡን ተጠሪ ሊተካ ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ይህም የሰበር ሠሚ ችሎት የሰበር አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪን በማስቀረብ በግራ ቀኙ መካከል የካቲት 28 ቀን 1998 ዓ.ም. የቃል ክርክር አካሂዷል፡፡ በቃል ክርክሩ ወቅት ተጠሪ ቀርበው ያሠሚቸው መከራከሪያ ነጥቦች በአጭሩ ሲቀመጡ፡- በመጀመሪያ ደረጃ አመልካቹ የሻጩ የጋዚና ትሬዲንግ ወኪል እንጂ የተጠሪ ወኪል አይደለም፤ አመልካቹ በውሉ መሠረት የኢንሹራንስ ሠነዶችን በጊዜው ባለማቅረባቸው ለተዳረጉት የወደብ ኪራይና ደመራዥ ክፍያ ተጠሪ ተጠያቂ ሊሆን አይገባም፤ በተጨማሪም አመልካች እቃዎቹ በወደብ ለ15 ቀናት ዘገዩ ይበል እንጂ ከመቼ እስከመቼ እንደዘገዩ በመረጃ አላስደገፉም፤ በመሆኑም የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊሆን ይገባል የሚል ነው፡፡

ይህም የሰበር ሰሚ ችሎት የመዝገቡንና የግራ ቀኙን ክርክር በጥሞና መርምሯል፡፡ እንደተመረመረውም በዚህ ጉዳይ እልባት የሚሻው ጭብጥ “አመልካች በውሉ መሠረት የኢንሹራንስ ሠነድ አላቀረበም በሚል አመልካቹ ለወደብ ኪራይና ለደመራዥ የከፈለውን ክፍያ ተጠሪ ሊተካ አይገባም ተብሎ መወሰኑ አግባብ ነው ወይ?” የሚለው ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እንደሚታወቀው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ለውሣኔው መሠረት ያደረገው የውሉን አንቀጽ 6 ሲሆን ይህም አንቀጽ የኢንሹራንስ ሠነዶቹን ማቅረብ የአመልካቹ ግዴታ መሆኑን ይገልፃል፡፡ በመሠረቱ የኢንሹራንስ ዋነኛ ጠቀሜታ ኢንሹራንስ የተገባለት ዕቃ አደጋ ቢደርስበት በአደጋው ምክንያት የደረሰው ጉዳት ሣይካስ እንዳይቀር መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ከመዝገቡና ከግራ ቀኙ ክርክር መረዳት የሚቻለው ደግሞ እቃዎቹ ጅቡቲ ወደብ በሠላም መድረሳቸውን፣ አልፎ ተርፎም እቃዎቹ በወደብ ለ15 ቀናት ከዘገዩም በኋላ ቢሆን የኢንሹራንስ ሠነድ ባልቀረበበት ሁኔታ እቃዎቹ

ከተጠሪው እጅ በሠላም መድረሳቸውን ነው፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው እቃዎቹን ከወደብ ለማንሣት የኢንሹራንስ ሠነዱ መቅረብ አስፈላጊ እንዳልነበረ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪው እቃዎቹ በወደብ የዘገዩት አመልካቹ በውሉ መሠረት የኢንሹራንስ ሠነድ ባለማቅረቡ ነው ሲል ያቀረበው መከራከሪያ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ከዚህ ይልቅ አመልካቹ ለክፍያ የተዳረጉት እቃዎቹን ከወደብ ለማንሣት አስፈላጊ የሆኑትን የማንንኘ ሠነዶች በተለይም የገንዘብ ሚኒስቴር ከቀረጥ ነፃ ብሎ ለተጠሪው የሚሠጠው ደብዳቤ ተጠሪው መ/ቤት ለአመልካቹ በጊዜው ለማቅረብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው መሆኑ ታውቋል፡፡ በአጠቃላይ አመልካቹ ለተጠሪው ጥቅም በሌለበት ግዴታ የከፈለውን የወደብ ኪራይና የደመራኘ ክፍያ ተጠሪው ሊተካ አይገባም መባሉ አላግባብ መሆኑን ይህ ፍ/ቤት ተገንዝቧል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

- ተጠሪ ለአመልካች ብር 14,558.17 /አስራ አራት ሺህ አምስት መቶ ሃምሣ ስምንት ከአስራ ሰባት/ ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ይክፈል፣
- አመልካች ለዳኝነቱ የከፈለው ገንዘብ ተጠሪ ይተካለት፤
- የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፤
- መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፤

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰበር መ/ቁ. 23609

ታህሣሥ 15ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

መስፍን እቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ዘውዱ አሊ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ አሰበወርቅ ዘገየ - አልቀረበም

**<u>ፍ ር ድ</u>**

በሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡

ተጠሪ ለሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች መ/ቤት የሥራ ውላቸውን ያላግባብ ስላቋረጠባቸው ውዝፍ ደሞዝ የተጠራቀመ የዓመት እረፍት፣የቦነስ ክፍያ፣ አበል፣ የእቃ ማጓጓዣ ፣የኤርፖርት ታክስ፣የካሣ ክፍያ የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንዲከፍላቸው ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ከስራ የተሰናበቱት ያለአግባብ በመሆኑ ውዝፍ ደመወዝ፣ የእረፍት ጊዜ በገንዘብ ተለውጦ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና የአገልግሎት ካሣ የ6 ወር ደመወዛቸውን እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ውሣኔ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን ይህ ችሎትም የአመት እረፍትና የአገልግሎት ካሣ እንዲከፈላቸው የተሰጠውን ውሣኔ ሕጋዊነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡

ተጠሪም ቀርበው ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታው ውዝፍ ደሞዝ በተመለከተ ቀደም ሲል ከሰው ተወስኖላቸው የወሰዱ በመሆኑ በድጋሚ ሊከፈላቸው አይገባም፣

አመልካች የተመደቡበት የስራ ኃላፊነት ከፍተኛ እምነትን የሚጠይቅ ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸው በድርጅቱ ላይ ከፍ ያለ ጉዳት ሊያደርሱ ስለሚችሉ በፍ/ሕ/ቁ. 2577 መሠረት ያለማስጠንቀቂያ ሊሰናበቱ ችለዋል፡፡ ከስራ የተሰናበቱት በጥፋት ስለሆነ ካሣ ሊከፈላቸው አይገባም ብሏል፡፡ ተጠሪም የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ በአግባቡ ነው ሲሉ ዝርዝር መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህ ችሎትም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ተጠሪ ያለአግባብ ከሥራ ተሰናብቻለሁ በማለት ሊከፈላቸው የሚገባውን ክፍያ ዘርዝረው ክስ አቅርበዋል ከመዝገቡ እንደተረዳነውም አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል ያቋረጠው ጥፋት ፈጽመዋል በሚል ቢሆንም ጥፋት መፈፀማቸውን እንዳላስረዳ የሥር ፍ/ቤቶች አረጋግጠዋል ፡፡ ጥፋት መኖር አለመኖሩ ደግሞ የፍሬ ነገር ክርክር በመሆኑ በዚህ ሠበር ችሎት በድጋሚ የሚታይ አይሆንም፡፡ በመሆኑም የተጠሪ የሥራ ውል ያለበቂ ምክንያት ከተቋረጠ ተጠሪ ሊያገኙ የሚገባቸው ክፍያዎች ምንድናቸው የሚለውን መመለከት ተገቢ ነው፡፡ በተለይ አመልካች ቅሬታ ያቀረበባቸው ክፍያዎች የተጠራቀመ ደመወዝ፣ የዓመት እረፍት፤ የማስጠንቀቂያና የካሣ ክፍያዎችን የሚመለከቱ በመሆናቸው እነዚህ ክፍያዎች ለተጠሪ ሊከፈሉ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ተመልክተናል፡፡ ተጠሪ የሥራ መሪ በመሆናቸው የሣቸው ጉዳይ የሚታየው በፍትሐብሔር ሕጉ እንደመሆኑ የተያዘው ጉዳይ ስለሥራ ውል በፍ/ብ/ሕጉ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች አኳያ ተመርምሯል፡፡

የካሣን ጥያቄ በተመለከተ ከፍ ሲል እንደተገለፀው አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል ያቋረጠው ተጠሪ ጥፋት ፈጽመው ነው ቢልም ይህንን እንዳላስረዳ የሥር ፍ/ቤቶች አረጋግጠዋል በመሆኑም የተጠሪ የሥራ ውል የተቋጠረው ከሕግ ውጪ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ አሠሪው ውሉን ቀሪ ለማድረግ በቂ ምክንያቶች የሌለው እንደሆነ ለሠራተኛው ተገቢ የሆነ ኪሣራ ለመክፍል እንደሚገደድ በፍ/ሕ/ቁ. 2573 ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም



አመልካች ተጠሪ ከሥራ የተሰናበቱት በጥፋት ስለሆነ ካሣ ልክፍል አልገደድም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

የኪሣራውን ልክ በተመለከተ ግን ለሠራተኛው የሚከፈለው ባለፊው 3 ወር ከተቀበለው ደመወዝ ሊበልጥ እንደማይችል በፍ/ህ/ቁ. 2574(2) ሥር የተመለከተ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች የ6 ወር ደመወዝ በካሣ መልክ እንዲከፈል መወሰናቸው ተገቢ አይደለም፡፡

ሌላው የማስጠንቀቂያ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን አሠሪው ውሉን ቀሪ ለማድረግ አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ መስጠት እንደሚገባው በፍ/ሕ/ቁ. 2570/2/ ሥር ተቀምጧል፡፡ የሥራ ውሉ ከአንድ አመት በላይ ቆይቶ ከሆነ ማስጠንቀቂያው ቢያንስ ከ2 ወር አስቀድሞ ሊሰጠው ይገባል (የፍ/ህ/ቁ.257(2) ይመለከታል) ፡፡ አመልካች ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ አይገባም የሚለው ስራው ልዩ ችሎታንና ከፍተኛ እምነት የሚጠይቅ ነው በማለት የፍ/ሕ/ቁ. 2577 ን መሠረት አድርጎ ሲሆን የተጠሪ የሥራ አስኪያጅነት ሥራ ግን በዚህ አንቀጽ የሚሸፈን ባለመሆኑ የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

የተጠራቀመ ደሞዝን በተመለከተ አመልካች በሰበር አቤቱታው ለተጠሪ በባንክ ሂሣባቸው ደመወዛቸውን ገቢ ሲያደርግ ቆይቶ ደመወዝ ለተጠሪ ሊከፈል እንደማይገባ ሲረዳ ከሂሣባቸው ወጪ አድርጎ በመውሰዱ አመልካቹ የወሰደውን ገንዘብ እንዲመልስ ተጠሪ ክስ አቅርበው ስላስወሰኑበት በአፈፃፀም ገንዘቡን የተቀበሉ በመሆኑ በድጋሚ ደመወዝ ሊከፈላቸው እንደማይገባ ገልጿል፡፡ ይህ ችሎቱም መዝገቡን እንደመረመረው ተጠሪው አመልካች ወደ ሂሣባቸው ገቢ አድርጎ መልሶ የወሰደውን ገንዘብ እንዲመልስ በሌላ መዝገብ ክስ መስርተው አስወስነውበት ገንዘቡን የተቀበሉ መሆኑን፣ ይህም ገንዘብ የተጠሪ ደመወዝ መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በመሆኑም አመልካች የተጠሪን ደመወዝ እንዲመልስ በሌላ መዝገብ ተወስኖበት ከከፈለ

በኋላ ተጠሪ በድጋሚ ውዝፍ ደመወዝ ሊከፈላቸው የሚገባበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡

የመጨረሻው ነጥብ የዓመት እረፍትን የሚመለከት ነው ተጠሪ የሚከራከሩት የዓመት እረፍት ካልተወሰደ ተጠራቅሞ ሠራተኛው በሚመቸው ጊዜ እንደሚወስደው ካልወሰደ ግን በገንዘብ ተቀይሮ እንደሚከፈለው እና ከ90 ቀናት በላይ እረፍቱ አይተላለፍም የሚለው ክርክር የሕግ ድጋፍ እንደሌለው ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ በወቅቱ የነበረው የብሔራዊ ባንክ መመሪያ እረፍት ከ90 ቀናት በላይ ሊተላለፍ እንደማይችል ይገልፃል፣ ያም ቢሆን ተጠሪ እረፍታቸውን ተጠቅመውበታል፣ አላቸው ቢባል እንኳን በፍ/ሕ/ቁ. 2562 (3) መሠረት ከ20 ቀናት በላይ ያለው እረፍት ተቀባይነት የለውም በማለት ይከራከራል የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው የብሔራዊ ባንክ መመሪያ አልቀረበም፣ ቢቀርብም በፍ/ሕጉ ላይ ገደብ የማያስቀምጥ በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም በሚል ነው፡፡ ነገር ግን የፍ/ሕጉ የዓመት እረፍት ላልተወሰነ ጊዜ እንደሚተላለፍ ያስቀመጠው ነገር ስለሌለ መመሪያው በፍ/ሕጉ ላይ ገደብ አስቀምጧል ለማለት አይቻልም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ የብሔራዊ ባንክ መመሪያ እረፍት ከ90 ቀናት በላይ ሊተላለፍ አይችልም በማለት ያስቀመጠው ገደብ የለም በማለት በግልጽ ያቀረቡት የተቃውሞ ክርክር የለም፡፡ በፍ/ሕጉ ላይ ያልተመለከቱ ነገሮችን ደግሞ የመ/ቤቱ አስተዳደር መወሰኑ ሕገ - ወጥ ነው ለማለት አያስችልም፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች ተጠሪ እረፍታቸውን በሙሉ ተጠቅመዋል ይባል እንጂ የሥር ፍ/ቤት የተጠሪን ማህደር አስቀረቦ ተጠሪ ያልወሠዱት እረፍት መኖሩን ስላረጋገጠ በዚህ በኩል የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም በመሆኑም ተጠሪ የተጠራቀመ የ90 ቀን ብቻ ሊሰጣቸው ሲገባ የሥር ፍ/ቤት 522 ቀናት እረፍት እንዲያገኙ መወሰኑ ስህተት ነው፡፡



**ው ሣ ኔ**

1/ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 1759/87 ሐምሌ 30 ቀን 1993 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 4624 ታህሣሥ 7 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡

2/ ለተጠሪ የተጠራቀመ ደመወዝ እንዲከፈል የተሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

3/ አመልካች ለተጠሪ የ3 ወር ደመወዝ ካሣ ክፍያ እንዲከፍላቸው ተወስኗል፡

4/ አመልካች ለተጠሪ የ2 ወር ደመወዝ የማስጠንቀቂያ ክፍያ ይክፈላቸው፡፡

5/ አመልካች ለተጠሪ የ90 ቀን የዓመት እረፍት በገንዘብ ቀይሮ ይክፈላቸው፡፡

6/ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰበር መ/ቁ. 30298

ጥር 20 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ የሺወንድም አቡሐይ

ተጠሪ፡- አቶ አየነው ማለደ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው በተጠሪ ላይ ተሰጥቶ የነበረው የመጥፋት ውሣኔ ሲሰረዝ አመልካች ለ3ኛ ወገን በሽያጭ አስተላልፈውታል የተባለውን ቤት ለተጠሪ ሊመልሱ ይገባል የሚሉት በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጡት ውሣኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ሲሉ አመልካች የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ ተጠሪ ለሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ በአመልካች ጠያቂነት ቀደም ሲል በወረዳ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ የተሰጠው የመጥፋት ውሣኔ የተነሣ መሆኑን ገልፀው የግል ንብረቴ የሆነውና የዋጋ ግምቱም ብር 50.000 (ሃምሣ ሺህ) የሆነው ቤት አመልካች ለ3ኛ ወገን በሽያጭ ያስተላለፈው ስለሆነ እንዲመለስ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም ቀርበው በሰጡት መልስ ተጠሪ ከእናቴ ጋር ጋብቻ መሥርቶ እያለ እናቴን ጥሎ በመጥፋቱ በሽተኛ ስለነበረች እሷን ለማሣከም ገንዘብ በማስፈለጉ ቤቱ የተሸጠ ሲሆን የሽያጩ ዋጋም በከሣሽ



እንደተጠቀሰው ብር 50,000 /ሃምሣ ሺህ/ ሣይሆን ብር 25,000 /ሃያ አምስት ሺህ/ ነው በማለት ክሱ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን ከቀረበው ማስረጃ አኳያ መርምሮ ተከሣሽ ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት የከሣሽና የእናቴ የጋራ ሀብት ነው የሚል ክርክር ቢያቀርብም ከጎንደር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት የቀረበው የሰነድ ማስረጃና እንደዚሁም በከሣሽ በኩል የቀረቡት ምስክሮች በሰጡት ቃል ከሣሽ ከተከሣሽ እናት ጋር ጋብቻ ከመመሥረታቸው በፊት የሠሩት ቤት እንደሆነ ስለሚያረጋግጥ ተከሣሽ ቤቱ የጋራ ንብረት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም ካለ በኂላ ጠፍቷል የተባለ ሰው ከመጣ ጠፍቷል መባሉ ተሠርዞ ወደ ሌላ ሰው ተላልፎ የሚገኝ ንብረትም ሊመለስለት እንደሚገባ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 171(1) ላይ የተመለከተ በመሆኑ በዚሁ መሠረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ለከሣሽ ሊመለስ ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተከሣሽ በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታቸውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ አመልካች ተጠሪ ጠፍተዋል በማለት የመጥፋት ውሣኔ ካገኙ በኂላ ወራሽነታቸውን አረጋግጠው የተጠሪን ቤት ለ3ኛ ወገን መሸጣቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ ሲመለሱ ሊመለስላቸው የሚገባው የቤቱ ሽያጭ ዋጋ ወይንስ ቤቱ እራሱ የሚለው ነጥብ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 171 አኳያ አቤቱታው ለሰበር ቀረቦ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው ሆኖ በማግኘቱ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ነጥብ ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በተጠሪ ላይ የመጥፋት ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በሸያጭ ወደ 3ኛ ወገን የተላለፈ መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

የመጥፋት ውሣኔን ውጤት ቀሪ ከሚያደርጉ ምክንያቶች /effects of termination of absence/ አንዱ ጠፍቷል የተባለው ሰው መመለስ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 171 ላይ ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረትም ጠፋ የተባለው ሰው በተመለሰ ጊዜ ንብረቶቹን በሚገኙበት አኳኋን መልሶ የመረከብ እንደዚሁም የተሸጡትን ንብረቶች ዋጋ የማግኘት መብት እንዳለው በግልጽ ተመልክቷል፡፡

በተያዘውም ጉዳይ ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነው ቤት መሸጡ ከተረጋገጠ ከላይ ከተጠቀሰው ድንጋጌ አኳያ ተጠሪ ሊረከቡ የሚገባቸው የተሸጠውን ቤት ሣይሆን የሽያጩን ዋጋ ነው ማለት ነው፡፡ የሽያጩን ዋጋ በተመለከተም አመልካች በብር 25,000 /ሃያ አምስት ሺህ/ መሸጡን ሲገልፁ ተጠሪ ዋጋው ብር 50.000 (ሃምሣ ሺህ) እንደሆነ ከመግለጽ በስተቀር በዚህ ዋጋ የተሸጠ መሆኑን ማስረጃ አቅርበው አልተከራከሩም፡፡

ስለሆነም የበታች ፍ/ቤቶች በሽያጭ የተላለፈው ቤት ለተጠሪ ሊመለስላቸው ይገባል በማለት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 15240 በጥር 28 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ለአመልካች ይገባል ማለቱ እንደዚሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 11660 በመጋቢት 14 ቀን 1999 ዓ.ም ይግባኙን ባለመቀበል የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡



2. ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በብር 25.000 (ሃያ አምስት ሺህ) ስለመሸጡ የተረጋገጠ ስለሆነ ይህንኑ የሽያጭ ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚታሰብ 9% (ዘጠኝ በመቶ) ወለድ ጋር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

# የመያዣ

# ውል



የሠ/መ/ቁ. 16218

መጋቢት 16 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ አስያድ ጋዲሳ

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሮ አስካለ ሁንዴ - አልቀረቡም፡፡

2. አቶ አንቻሎ ቡሬ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ኀዳር 8 ቀን 1991 ዓ.ም. በተፈረመ የገንዘብ ብድር ውል ተጠሪዎች ከአመልካች ብር 140,000 (መቶ አርባ ሺ.ህ) ተበድረናል፡፡ ገንዘቡም ተከፍሎ የሚጠናቀቀው ጥር 22 ቀን 1992 ዓ.ም. የነበረ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ጥር 26 ቀን 1991 ዓ.ም. በተፈረመ የገንዘብ ብድር ውል ብር 90 ሺ.ህ ተበድረናል፡፡ ሁለተኛውም የብድር ገንዘብ ተከፍሎ የሚጠናቀቀው የካቲት 26 ቀን 1995 ዓ.ም. ነበር፡፡ ሆኖም የብድሩ የመጨረሻ መክፈያ ጊዜ ሳይደርስ በሕገወጥ መንገድ የመያዣ ንብረቶቹን የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ሳይሰጠን በዋስትና ያልተያዘውንም ንብረታችንን ጭምር በኃይል አስፈራርቶ ወስዶብናል፡፡ ስለዚህ ከሱቅ፣ ከእንጨትና ቁርስ ቤት የተቋረጠ ገቢ ብር 210,800.00 (ሁለት መቶ አሥር ሺ.ህ ስምንት መቶ ) ንብረቶቹ በሕገወጥ መንገድ በመወረሳቸው የደረሰብን ጉዳት ብር 146,890.00 (መቶ አርባ ስድስት ሺ.ህ ስምነት መቶ ዘጠና) የተወሰደብን ቤት ቢሸጥ ብር 310,000.00 (ሦስት መቶ አስር ሺ.ህ ) ሲሆን

የሚፈለግብን ዕዳ ከተቀነሰ በኋላ ብር 134,502.43 (መቶ ሠላሳ አራት ሺህ አምስት መቶ ሁለት ከአርባ ሦስት) ሊከፍለን ይገባል በማለት በአጠቃላይ ሌሎች ወጭዎችን ጨምረው ብር 492,192.43 (አራት መቶ ዘጠና ሁለት ሺህ አንድ መቶ ዘጠና ሁለት ከአርባ ሦስት) ተከሣሽ እንዲከፍል ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሣሾች ክስና ማስረጃ ለተከሳሽ ደርሶም በሰጠው መልስ ባንኩ ንብረቱን የተቆጣጠረው በአዋጁ ቁጥር 97/90 መሠረት ሕጋዊ ሥርዓትን ተከትሎ ስለሆነ ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 33/2/ አኳያ ከሳሾች ክስ ባቀረቡበት ነገር መብትና ጥቅም ስለሌላቸው መዝገቡ ሊዘጋ ይገባል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

በፍሬ ጉዳይ ክርክር ረገድ የሰጠው መልስ ተጠቃሎ ሲታይ የብድሩ መክፈያ ጊዜ ሳይጠናቀቅ ዕርምጃ ተወስዷል በማለት ከሣሾች ያቀረቡትን አቤቱታ በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2488/1/ መሠረት ውዝፍ ዕዳው ከጠቅላላ ዕዳው 1/10 ከሆነ የመጨረሻ መክፈያ ጊዜውን ሳንጠብቅ ዕርምጃ መውሰድ እንችላለን፡፡ ከዚህም ሌላ ባንኩ የንብረት ርክክብ ያደረገው በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት የሚመለከታቸው ተወካዮች በተገኙበት ነው በማለት ተከራክሮ ከሳሾች በጠየቁት የካሣ መጠንም ላይ ግምቱ የተጋነነ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በተከሣሽ በኩል የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በብይን ተቀባይነት የለውም ካለ በኋላ በጥር 26 ቀን 1991 ዓ.ም. በግራ ቀኙ መካከል በተፈረመው የብድር ውል ከሳሾች የብድሩን ገንዘብ አጠናቀው መክፈል የሚገባቸው በየካቲት 26 ቀን 1995 ዓ.ም. ሆኖ ሳለ እንደዚሁም ቀደም ብሎ በህዳር 8 ቀን 1991 ዓ.ም. ባደረጉት የብድር ውልም በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 መሠረት ተከሳሽ የ1 ወር ማስጠንቀቂያ ለከሳሾች መስጠት ሲገባው ይህን ሳያደርግ በመያዣ ያልያዘውንም የከሳሾችን ንብረት ጭምር ማሸጉ



አግባብነት የሌለው በመሆኑ ኃላፊነት አለበት ካለ በኋላ በመያዣ ከተያዘው ቤት ጋር የታሸጉት የከሳሾች ንብረት የዋጋ ግምታቸው እንዲገለጽለት ለሚመለከተው መ/ቤት ትዕዛዝ ሠጥቶ ብር 183,130.06 (አንድ መቶ ሰማኒያ ሦስት ሺህ አንድ መቶ ሠላሳ ከ ስድስት) እንደሆነ የተገለጸለት ቢሆንም በዚህ ረገድ ከሳሾች የጠየቁት ክፍያ ብር 146,890 (መቶ አርባ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና) ስለሆነ ይሄው የንብረት ዋጋ ግምት ሊከፈላቸው ይገባል ብሏል፡፡

በሌላ በኩልም የብድሩን ክፍያ በተመለከተ ከሳሾች የሚፈለገባቸው ቀሪ የብድር ገንዘብ ብር 175,497.57 (አንድ መቶ ሰባ አምስት ሺህ አራት መቶ ዘጠና ሰባት ከሃምሳ ሰባት) ሲሆን ተከሳሽ የተረከበው የከሳሾች ቤት ደግሞ ብር 310,000 (ሦስት መቶ አሥር ሺህ) እንደሆነ ስለተረጋገጠ ከከሳሾች የሚፈለገው ዕዳ ከቤቱ ግምት ሲቀነስ ብር 134,502.43 (አንድ መቶ ሠላሳ አራት ሺህ አምስት መቶ ሁለት ከአርባ ሦስት) ስለሚመጣ ይህንንም ተከሣሽ ለከሳሾች መክፈል አለበት ብሏል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ተከሣሽ የተረከባቸው የከሳሾች ሱቅ፣ ቁርስ ቤትና እንጨት ቤት ታሽገው በቆዩበት 138 ቀናት ከሣሾች ባቀረቡት የተጣራ ትርፍ ማስረጃ መሠረት በድምሩ ብር 210,800.00 (ሁለት መቶ አሥር ሺህ ስምንት መቶ ) ተከሣሽ ለከሳሾች መክፈል አለበት በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በአጠቃላይ ድምርም ብር 492,192.43 (አራት መቶ ዘጠና ሁለት ሺህ አንድ መቶ ዘጠና ሁለት ከአርባ ሦስት) የጠበቃ አበል በዚሁ ልክ 10 /አስር በመቶ/ ወጭና ኪሣራ በቁርጥ ብር 200 (ሁለት መቶ) ጨምሮ ተከሳሽ ሊከፍል ይገባል በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ተከሣሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርብም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ይህ ችሎትም የቀረበለትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ አመልካች በመያዣነት የያዛቸውን ንብረቶች በሕገወጥ መንገድ ይዟል በማለት ከላይ የተጠቀሰውን ገንዘብ ለተጠሪዎች ሊከፍል ይገባል በማለት በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ ተጠሪዎች ባሉበት ሊታይ የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

የዚህን ችሎት ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች የተጠቀሰውን ገንዘብ ለተጠሪዎች እንዲከፍል መወሰኑ አግባብነት አለውን? የሚለው በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት እንደዚሁም በአዋጅ ቁጥር 216/92 በተደረገው ማሻሻያ ባንኮች ለሰጡት ብድር አከፋፈል በመያዣነት በዋስትና የተቀበሉትን የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት የብድር ዕዳው እንዲከፈል በተወሰነው ጊዜ ሳይከፈል ከቀረ ከሠላሣ ቀናት ያላነሰ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የመያዣ ንብረቱን በሐራጅ ለመሸጥና ባለቤትነቱንም ለገዢው ለማዛወር ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡

ከአዋጁ ድንጋጌዎችም መረዳት የሚቻለው አበዳሪው ባንክ በዋስትና የያዛቸውን ንብረቶች የብድር ገንዘቡ ካልተመለሰለት ያለማንም ጣልቃገብነት አግባብነት ያላቸውን የሕጉን ድንጋጌዎች በመከተል በሐራጅ ሸጦ ለዕዳው ክፍያ ማዋል እንደሚችል እና በአሻሻጡ ሂደት ባንኩ ሕጉን ባለመከተል የፈጸመው ስህተት ቢኖርና በዚህም በባለዕዳው ላይ ጉዳት ቢደርስ ለዚህ ጉዳት ባንኩ ለባዕዳው ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ነው፡፡ በሕጉ ላይ የተቀመጡትም ዝርዝር ድንጋጌዎች ዓላማም በአዋጁ መግቢያ /Preamble/ ላይ በግልጽ እንደተመለከተው ባንኮች የሚሰጧቸውን ብድሮች በተቀላጠፈ አኳኋን ለመሰብሰብ እንዲችሉ ነው፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘም አዋጁን ለማስፈጸም እንዲረዳ አመልካች የፎርክሎዠር መመሪያ ለማውጣት እንዲችል ሥልጣን የተሰጠው ሲሆን



በዚሁ መሠረትም አመልካች ባወጣው የፎርክሎዠር መመሪያ ተበዳሪው በገባው የብድር ውል መሠረት ሁለት ተከታታይ ክፍያዎችን ወይም ከአጠቃላይ ብድሩ 1/10ኛ ካልከፈለ አበዳሪው ባንክ የፎርክሎዠር ውሣኔ እንደሚሰጥ ከዚህ በኋላም ተበዳሪው ከባንኩ የሚፈለግበትን ዕዳ በ30 ቀናት ውስጥ አጠቃሎ እንዲከፍል ማስጠንቀቂያ እንደሚሰጠው በዚህ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ከባለዕዳው የሚፈለገው ዕዳ ሳይከፈል ከቀረ ባንኩ የመያዣ ንብረቱን እንደሚይዝ መያዣ ሰጭው ንብረቱን ለማስረከብ ፈቃደኛ ካልሆነ ከሬጅስትራርና ከፖሊስ ጋር በመተባበር ንብረቱን በኃይል እንደሚይዝ ንብረቱ ከተያዘም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በባንኩ ባለሙያዎች አማካይነት እንደሚገመትና ከዚያም በ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶ ንብረቱ በሐራጅ እንደሚሸጥ ተመልክቷል፡፡

የተያዘውም ጉዳይ ከአዋጁ ከመመሪያውና እንደዚሁም ግራ ቀኙ ካደረጉት ውል አንፃር ሲታይ ተጠሪዎች ለሁለት ተከታታይ ጊዜ የብድር ክፍያ ማቋረጣቸው የተረጋገጠ ሲሆን አመልካች በአዋጁ በመመሪያውና በውሉ ባለበት ግዴታ መሠረትም የሠላሳ ቀን ማስጠንቀቂያ ለተጠሪዎች መስጠቱ በማስረጃ መረጋገጡን ይህ ችሎት ለመገንዘብ ችሏል፡፡

አመልካች ለተጠሪዎች የ30 ቀን ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኋላ ዕዳው ሳይከፈል በመቅረቱ በመያዣ የያዘውን ንብረት የተረከበ ሲሆን ይህም ከላይ እንደተመለከተው የፎርክሎዠር መመሪያው የሚፈቅድለት ከመሆኑም በላይ ተጠሪዎችም በገቡት የውል ግዴታ ዕዳው በከፊል ወይንም በሙሉ ሳይከፈል ቢቀር የሰላሣ ቀን ማስጠንቀቂያ ከተሰጠ በኋላ ንብረቱ ሊሸጥ እንደሚችል በውል ስምምነታቸውን የሰጡ በመሆኑ የአመልካች አድራጎት በአዋጁ በመመሪያውና በውሉ የተደገፈ ስለሆነ ሕገወጥ ነው የሚያሰኝ አይሆንም፡፡

አመልካች የመያዣ ንብረቱን ለመያዝ ሲዘጋጅ ተጠሪዎች ቀርበው ንብረቱን ለማስረከብ ፈቃደኛ እንዳልነበሩም በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ አመልካች የሚመለከታቸው አካላት እንዲገኙ

በማድረግ ንብረቱን በኃይል ለመያዝ እንደሚችል የፎርክሎዠር መመሪያው ሥልጣን የሚሰጠው ስለሆነ ተጠሪዎች በመያዣ የተያዘውን ንብረት ለአመልካች ለማስረከብና ክስ ያቀረቡባቸውንም የተለያዩ ንብረቶች ቀርበው ለመረከብ ፈቃደኛ ካልሆኑ እነዚህ ንብረቶች ተመዝግበው በንግድ መደብሮቹ ውስጥ እንዳሉ መታሸጋቸው ስለማይቀር ንብረቶቹን ከአመልካች ጠይቀው መውሰድ ከሚችሉ በስተቀር የዋጋ ግምታቸው እንዲከፈላቸው እንደዚሁም የንግድ መደብሩ በመታሸጉ ምክንያት ተቋርጦብናል የሚሉት ጥቅም እንዲከፈላቸው መጠየቃቸው ከእራሳቸው ተግባር የመነጨ በመሆኑና አመልካችም የአዋጁን ድንጋጌዎች በመተላለፍ የፈጸመው ተግባር ባለመሆኑ በዚህ ረገድ አመልካች ኃላፊ ነው ተብሎ በበታች ፍ/ቤቶች መወሰኑ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩልም አመልካች የተረከበው የተጠሪዎች ቤት የዋጋ ግምት ብር 310 000 /ሦስት መቶ አስር ሺህ/ እንደሆነ በተጠሪዎች በኩል የቀረበውን የዋጋ ግምት አስመልክቶ አመልካች ግምቱን በመቃወም ያልተከራከረ ስለሆነና ቤቱን ከተረከበ ጊዜ ጀምሮም ብድሩ እንደተከፈለ ሊቆጠር ስለሚችል የቤቱ ግምትና ከተጠሪዎች በቀሪነት የሚፈለገው የብድር ዕዳ ተቀናንሶ በልዩነት ከአመልካች የሚፈለገውን ብር 134,502.43 /አንድ መቶ ሠላሳ አራት ሺህ አምስት መቶ ሁለት ብር ከአርባ ሶስት/ ለተጠሪዎች እንዲከፍል በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የምሥራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ በመጋቢት 22 ቀን 1996 ዓ.ም በዋለው ችሎት የንብረቶቹን የዋጋ ግምትና የንግድ መደብሮቹ በመታሸጋቸው ምክንያት በተጠሪዎች ላይ ደርሷል የተባለን ኪሣራ በድምሩ ብር 357,690.00 /ሶስት መቶ ሀምሳ ሰባት



ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ብር/ አመልካች ለተጠሪዎች ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 11804 በሰኔ 21 ቀን 1996 ዓ.ም. በዚህ ረገድ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ አመልካች የአዋጁን ድንጋጌዎችንም ሆነ የአፈፃፀም መምሪያውን ባልተላለፈበት ሁኔታ ስለሆነ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስለተገኘ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች የተጠሪዎችን የንግድ መደብር ተረክቦ ያሸገው አዋጁና መመሪያው የሚፈቅድለት በመሆኑ ስለሆነ በንግድ መደብሩ ውስጥ ያሉትን ንብረቶች ለተጠሪዎች ከሚያስረክብ በስተቀር የንብረቶቹን የዋጋ ግምትም ሆነ የተቋረጠ ገቢ ሊከፍል ስለማይገባ አይከፍልም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. አመልካች በተረከበው ቤትና በብድሩ ገንዘብ መካከል ያለውን ብር 134,502.43 /አንድ መቶ ሠላሣ አራት ሺህ አምስት መቶ ሁለት ብር ከአርባ ሶስት ሳንቲም/ ለተጠሪዎች እንዲከፍል መወሰኑ በአግባቡ ስለሆነ ይህንኑ ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚታሰብ 9% /ዘጠኝ በመቶ/ ወለድ ጋር እንደዚሁም የጠበቃ አበል በዚሁ ልክ 10% /አሥር በመቶ/ ጨምሮ ለተጠሪዎች ይክፈል በማለት ተወስኗል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 25863

ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሠ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሠ ይርጋ

**አመልካች፡-** የኢት/ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ አዲስ ወልዴ

**ተጠሪ፡-** የኢት/ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ቀረቡ

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ በመያዣ በተሠጠ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለን የቀዳሚነት መብት የሚመለከት ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት የአፈፃፀም ባለዕዳ ከሆኑት ግለሠብ ጋር በነበረው የአፈፃፀም ክርክር አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418 መሠረት መቃወሚያ በማቅረቡ ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው አመልካች ለጎጂ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው አቤቱታ በአፈፃፀም በሃራጅ እንዲሸጥ የታዘዘው ንብረት አመልካች ለአፈፃፀም ባለዕዳው ብር 118,500(አንድ መቶ አስራ ስምንት ሺህ አምስት መቶ) ሲያበድር በመያዣ የያዘው በመሆኑ መያዣውም ቀድሞ የተመዘገበ ስለሆነ በንብረቱ ላይ የቅድሚያ መብት ያለው በመሆኑ ሐራጁ እንዲሰረዝለት ጠይቋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ክርክር የተነሣበትን ንብረት በመያዣ የያዘውና የቀዳሚነት መብት ያለው ተጠሪ ነው ሲል የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጓል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትም በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337 መሠረት ይግባኙን ሠርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ክርክር የተነሣበት ንብረት ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ማን



እንደሆነ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሁፍ ያቀረቡ ሲሆን ይህ ችሎትም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ ሂደት እንደተረዳነው አመልካች የሚከራከረው ክርክር የተነሣበትን የእህል መጋዘን ለሰጠው ብድር በመያዣ መያዙን እና መያዣውንም መጋቢት 6 ቀን 1988 ዓ.ም ያስመዘገበ መሆኑን ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ የአመልካች መያዣ አግባብ ባለው አካል ፊት ያልተመዘገበና በሠነዱ ላይ የሰፈረው ማህተምም በወቅቱ ሥራ ላይ ያልነበረና አጠራጣሪ መሆኑን፣ተጠሪ ግን ከአመልካች በፊት መያዣውን ሰኔ 23 ቀን 1990 ዓ.ም በማስመዝገቡ የቀዳሚነት መብት ያለው መሆኑን ተከራክሯል፡፡

ይህ ችሎትም ቀዳሚ መብት ያለው ማነው የሚለውን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡ አንድ የማይንቀሣቀስ ንብረት ለብዙ ዕዳዎች በመያዣ ሊሠጥ የሚችል መሆኑ በፍ/ህ/ቁ 3088 ሥር ተመልክቷል፡፡ ነገር ግን አንድ የማይንቀሣቀስ ንብረት በመያዣ ከተሰጠ በመብቱ ለመገልገል መያዣው አግባብ ባለው አካል መመዝገብ እንዳለበት የፍ/ህ/ቁ. 3052 ያስገነዝባል፡፡ ከሌሎች የመያዣ መብት ካላቸው ባለገንዘቦች በፊትም የቀዳሚነት መብት ለማግኘት መያዣውን ከሌሎቹ በፊት ቀድሞ ማስመዝገብ ይገባል (የፍ/ህ/ቁ 3081 ይመለከቷል)፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች መያዣውን ከተጠሪ በፊት ቀድሞ ማስመዝገቡን ገልጦ የቀዳሚነት መብት ያለው መሆኑን ተከራክሯል፡፡ ከመዝገቡም እንዳየነው አመልካች የመያዣ ውሉን በቦረና አስተዳደር አካባቢ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ የነገሌ ከተማ አስተዳደር ፅ/ቤት የመያዣ ውሉን ተቀብሎ ማህተሙን በማኖር መመዝገቡን አረጋግጧል፡፡ አመልካች መያዣው የተመዘገበው መጋቢት 6 ቀን 1988 ዓ.ም ነው በማለት ባቀረበው ክርክር ላይ የሥር ፍ/ቤት ያለው ነገር የለም ፍ/ቤቱ የአመልካችን

ጥያቄ ውድቅ ያደረገው መያዣው ተመዝግቧል በተባለበት ወቅት ሠነዱ ላይ ያረፈው ማህተም አጠራጣሪ ነው በሚል ብቻ ነው፡፡ እዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሠውም በወቅቱ ክልሉ የሚሠራው በኦሮሚኛ ሆኖ ይህ ማህተም እንዴት በአማሪኛ ሊሆን ቻለ ከሚል ጥርጣሬ ብቻ ነው፡፡ የማህተሙን ትክክለኛነት ወይም ሐሠተኛነት በተጨባጭ ያረጋገጠው ነገር የለም፡፡ ማህተሙ የአስተዳደር ፅ/ቤቱ አይደለም የሚባል ከሆነ ተቃራኒ ማስረጃ ሊቀርብ ይገባ ነበር፡፡ ተቃራኒ ማስረጃ ሣይቀርብና የማህተሙ ሀሰተኛ መሆን ሣይረጋገጥ በጥርጣሬ ብቻ የተደረሰበት መደምደሚያ ህጋዊ መሠረት የለውም፡፡

እንግዲህ የማይንቀሣቀስ ንብረት መያዣ ህጋዊ ውጤት እንዲኖረው መመዝገብ አስፈላጊ በመሆኑ (የፍ/ህ/ቁ 3052ን ይመለከቷል) አመልካችም ሆነ ተጠሪ መያዣቸውን በመዝጋቢው አካል አስመዝግበዋል፡፡ በአንድ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ብዙ ገንዘብ ጠያቂዎች የመያዣ መብት አስመዝግበው እንደሆነ ደግሞ የቀደምትነት መብታቸውን የሚሠሩበት ተራ የሚወሠነው መብታቸውን ያስመዘገቡበትን ቀን በመከተል እንደሆነ በፍ/ህ/ቁ. 3081/1/ ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች መያዣውን መጋቢት 6 ቀን 1988 ዓ.ምያስመዘገበ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ሰኔ 23 ቀን 1990 ዓ.ም ነው ያስመዘገበው:: ይህ ከሆነ ደግሞ የቀደምትነት መብት ያለው ቀድሞ መብቱን ያስመዘገበው አመልካች ነው፡፡

በሌላ በኩል ግን አመልካች እየጠየቀ ያለው የሐራጅ ሽያጩ እንዲሠረዝ ነው፡፡ በማይንቀሣቀስ ንብረት የመያዣ መብት የተሠጠው ገንዘብ ጠያቂ ንብረቱ በሌሎች ባለገንዘቦች የተያዘ እንደሆነ ከንብረቱ ዋጋ ላይ የሚፈልገው ገንዘብ ከሌሎቹ ገንዘብ ጠያቂዎች ለርሱ በቀዳሚነት እንዲከፈለው ከመጠየቅ ያለፈ መብት የለውም (የፍ/ህ/ቁ 3059(1) ይመለከቷል) የማይንቀሣቀሠው ንብረት ክፍያቸው በደረሠ ማንኛውም



ባለገንዘቦች ሊያዝና ሊሰጥ የሚችል ሲሆን የቀዳሚ መብት ያለው ባለገንዘብ ከሺያጩ ገንዘብ የርሱ እዳ በቅድሚያ እንዲከፈለው ከመጠየቅ በቀር ሺያጩ እንዳይከናወን ሊቃወም አይችልም፡፡

በመሆኑም አመልካች ምንም እንኳን መያዣውን ከተጠሪው በፊት በማስመዝገቡ ቀዳሚ መብት ቢኖረውም ይህ መብቱ ከሺያጩ ከተገኘው ገንዘብ የእርሱ እዳ ቀድሞ እንዲከፈለው ከማድረግ በቀር ሺያጩ እንዲሰረዝ ሊጠይቅ አይችልም፡፡

በአጠቃላይ የሥር ፍ/ቤት ማህተሙ አጠራጣሪ ነው በሚል ብቻ የአመልካችን ክርክር ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1) የጉጂ ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ 00246 ሰኔ 07 ቀን 1997 ዓ.ም የሠጠው ብይን እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 3286 ሚያዚያ 10ቀን 1998 ዓ.ም የሠጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡

2) ክርክር የተነሣበት የመያዣ ንብረት በሐራጅ ተሸጦ ከሚገኘው ገንዘብ አመልካች የሚፈልገው እዳ ተከፍሎት ተራፊ ገንዘብ ካለ ለተጠሪ እንዲከፈል ተወስኗል፡፡

3) መጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ.29269

ጥቅምት 15 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አቶ ሳሙኤል ገዛኸኝ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1ኛ. አቶ ዋለልኝ አያሌው ቀረቡ

2ኛ. ወ/ሮ ለመች ላቀው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ብሔራዊ ክልልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁጥር 07568 ታህሳስ 24 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት ዝርዝር ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት 2ኛ ተጠሪ ባለዕዳ ሆነው በምዕ/ጉጃ መስተዳደር ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት በአፈፃፀም መ/ቁ. 8291 በሆነው መዝገብ ላይ የአፈፃፀም ክሱ እየታየ ባለበት ጊዜ የአሁኑ አመልካች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.418 ን መሠረት በማድረግ ጣልቃ ገብቶ ተከራክሯል፡፡

ጣልቃ ለመግባት ያቀረበውም ምክንያት የፍርድ ባለመብት እንዲረከብ ትዕዛዝ የተሰጠበትን የባለዕዳዋን ንብረት አስቀድሜ ያስከበርኩት ስለሆነ ቤቱን ባለመብቱ አንዲረከብና ስመ ንብረትነቱም እንዲዛወርለት የተሰጠው ትዕዛዝ ቀሪ አንዲሆንልን ይታዘዝልን የሚል ነው፡፡ በማስረጃነትም በዚሁ ንብረት ላይ የማስከበሪያ ትዕዛዝ ጥቅምት 28 ቀን 1995 ዓ.ም ያሰጠበት መሆኑንና ባለዕዳ በተባለችው በአሁን 2ኛ ተጠሪ ላይ በዋስትና



ግዴታ ምክንያት ክሶ ፍርድ ያሰጠበት መሆኑን የሚገልፅ የሰነድ ማስረጃ አቅርቧል፡፡

በዚሁ አቤቱታ ላይ መልስ የተሰጠበት መሆኑን የሥር ፍ/ቤት ከገለፀ በኋላ የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቶ ምንም እንኳን የአሁን አመልካች በዚሁ ንብረት ላይ የማስክበሪያ ትዕዛዝ ያሰጠበት መሆኑ ቢረጋገጥም ማስከበር ብቻውን የቀዳሚነትን መብት የሚያስጥ ሆኖ አላገኘነውም ስለሆነም የቀረበው የአፈፃፀም ክስ ይቋረጥልኝ አቤቱታ ውድቅ ነው በማለት በይኗል፡፡

በዚህም ብይን የአሁን አመልካች ቅር ተሰኝቶ የይግባኝ አቤቱታ ለክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡

ፍ/ቤቱም በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ታህሳስ 24 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት በግራ ቀኙ መካከል የተነሳው አከራካሪ ነጥብ ክርክር ባስነሳው ቤት ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ወገን ማን ነው? የሚለው መሆኑን ለይቶ በጭብጥነት ከያዘ በኋላ ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በ2ኛ ተጠሪ ላይ አስቀድሞ ክስ ያቀረበ እና አስወስኖ የአፈፃፀም ክስ ያቀረበ መሆኑ ቢረጋገጥም 1ኛ ተጠሪ አቶ ዋለልኝ አያሌው ለ2ኛዋ ተጠሪ በወ/ሮ ለመች ላቀው ብር 80,000.00/ሰማንያ ሺህ/ ብድር ሲሰጡ ይህ የብድር ገንዘብ በተባለው ጊዜ ውስጥ ባይመለስ የክርክሩ መንስኤ የሆነውን ቤት ለማስረከብ የውል ግዴታ የገቡ መሆናቸውንና እንደ ግዴታቸው የገንዘብ መክፈያ ጊዜው የብድሩን ገንዘብ መመለስ አለመቻላቸው ተረጋግጦ በሥር ፍ/ቤት ጥቅምት 10 ቀን 1997 ዓ.ም በዋለው ችሎት ይኸው በ2ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ በፍኖተ ሰላም ከተማ ቀበሌ 02 በቁጥር መ/1/1984 ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት እንዲረከቡ ተወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የአፈፃፀም ክስ ያቀረበውም ከዚሁ ንብረቱን ይረከብ የሚለው ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በመሆኑ እና ንግድ ባንክ በቀጥታ ክሱ ጊዜ ይኸው ንብረት ታግዶ እንዲቆይ ማስደረጉም የፍርድ ባለመብት በቤቱ ላይ ያገኘውን መብት የሚያሳጣ ሆኖ ባለመገኘቱ የአመልካች ቅሬታ ተቀባይነት

ያለው አይደለም። እንዲሁም አንድ ንብረት በፍርድ ቤት ተከብሮ የመያዙ እውነታም ንብረቱ ከመያዙ በፊት ገንዘብ እንዲከፈላቸው በባለሀብቱ ላይ ያስፈረደ ወገን በቀረበ ጊዜ የተያዘውን ንብረት ለመውሰድ እንደማይከለክል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ፍ/ቁ.403 ይደነግጋል። አመልካች የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቤቱን በመያዣ የያዘው ባለመሆኑም ቀድሞ ክስ ማቅረቡ ብቻውን የ1ኛ ተጠሪን የአቶ ዋለልኝ አያሌውን መብት የሚያስቀር አይደለም የሚሉትን ምክንያቶች በመንተራስ የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ አፅንቷል። የአመልካችም የሰበር አቤቱታ ፍሬ ቃል፡-

የሥር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ለውሳኔው የሰጠው ምክንያት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.403 የተመለከተውን ድንጋጌ ትክክለኛ ትርጉም የተከተለ አይደለም።

ከ1ኛ ተጠሪ ይልቅ ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ ቀድመን መብታችንን ያስጠበቅን መሆኑ እየታወቀ እና በዚህም የተነሣ በሥነ ሥርአት ህጉ የተሰጠን ዋስትና እያለ ይህ ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን ያሳያል።

ይህም እንኳ ቢታለፍ የፍርድ ባለመብት እንደመሆናችን መጠን የባለዕዳዋ ንብረት ተሸጦ እንደየድርሻችን መከፋፈል ሲገባን ለ1ኛ ተጠሪ ብቻ እንዲሰጥ መደረጉ የህግ ድጋፍ ያለው ባለመሆኑ ይኸው ይታረምልን የሚል ነው።

ተጠሪዎችም የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዳኝነት ህግን መሠረት ያደረገ መሆኑን በመግለፅ ውሳኔው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

እኛም ጉዳዩን መርምረናል። እንደመረመርነውም የአሁን 1ኛ ተጠሪ የብድር ውልን መሠረት አድርጎ ክስ ከማቅረቡ እና ከማስወሰኑ በፊት የአሁን አመልካች በ2ኛዋ ተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ምክንያት ጥቅምት 28 ቀን 1995 ዓ.ም ይኸው ክርክር ያስነሳው ንብረት በማናቸውም መንገድ ቢሆን ወደ ሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ ያሳገደው ለመሆኑ በግራ ቀኙ መካከል



የተካደ ፍሬ ነገር አይደለም። ይህም መሆኑ ከተረጋገጠ በአመልካች በኩል የተፈፀመው ተግባር በ2ኛ ተጠሪ ላይ የገንዘብ ክስ አቅርቤአለሁ፤ እንደ ክሱ ባስፈርድ ፍርዱ ውጤት ያገኝ ዘንድ የተከሳሽ ንብረት ወደ ሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ በማለት ተከብሮ ይቆይልኝ የሚል በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3044 እንደተመለከተው ይህ የማሳገድ ተግባር ከፍርድ የመነጨ የመያዣ መብት መሆኑን ያመለክታል። ይኸውም ፍርድ ቤቱ የሰጠው ፍርድ ተፈፃሚነት እንዲያገኝ ለማረጋገጥ አንዱ ወገን ለሌላው ወገን በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ከሚያሰጠው የማስከበሪያ ትዕዛዝ አንዱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.154 መሠረት ግራ ቀኙ በክርክር ላይ እያሉ ከፍርድ በፊት በንብረት ላይ የሚሰጠው የማገጃ ትዕዛዝ ነው። ከላይ እንደተመለከተው አመልካች በዚሁ መሠረት የ2ኛዋ ተጠሪ ንብረት በማናቸውም መንገድ ቢሆን ወደ ሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ ተከብሮ እንዲቆይ ያስደረገ ለመሆኑ የተለየ ሆኖ ካልተገኘ አመልካች በዚሁ ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ የመያዣ መብት ያገኘ መሆኑን አረጋጋጭ ነው። እንደ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ትንተና የመያዣ መብት ሁልጊዜ ከውል ብቻ እንደሚመነጭ ተደርጎ የተሰጠው ትርጉም ስህተት ነው። በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3041 እንደተደነገገው መያዣ ከውል ብቻ ሳይሆን በቀጥታ ከሕግ ወይም በፍርድ ሊቋቋም ይችላል። በዚህ መሠረት አመልካች ከፍርድ ቤት ትዕዛዝ የመነጨ የመያዣ ውል ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ይህ በመያዣ የተያዘውን ንብረት ገንዘብ ጠያቂ ያስያዘው እንደሆነ ከንብረቱ ዋጋ ላይ የሚጠየቀው ገንዘብ ከሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች በፊት ለእርሱ በቀዳሚነት እንዲከፈለው የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.3059/1/ የተደነገገ በመሆኑ አመልካች የጠየቀው ዳኝነት ህጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ እያለ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ህግ ከሚደነግገው ውጭ በሥር ፍ/ቤት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት መፈፀሙን ያሳያል።

አንድ ንብረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተከብሮ የመያዙ እውነታ ንብረቱ ከመያዙ በፊት ገንዘብ እንዲከፈላቸው በንብረቱ ባለሀብት ላይ ያስፈረዱ

ወገኖች በቀረቡ ጊዜ የተያዘውን ሀብት ከመውሰድ እንደማያግዳቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 403 ተደንግጓል በሚል በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ትንታኔም ተመልክተናል፡፡ በመሠረቱ የዚህ ድንጋጌ አግባብነት ከድንጋጌው ርዕስ እንደምንመለከተው የአንድ የፍርድ ባለዕዳ ንብረት በእርሱ ላይ የቀረቡትን ገንዘብ ጠያቂዎች ፍላጐት የሚያሟላ ሆኖ ከተገኘ ይኸው ንብረቱ በእነዚህ ገንዘብ ጠያቂዎች መካከል እንዴት እንደሚከፋፈል የሚደነግግ እንጂ እንደ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አባባል አንደኛው ገንዘብ ጠያቂ ብቻውን ጠቅልሎ እንዲወስድ የሚያስችል አይደለም፡፡ የድንጋጌውም ተፈፃሚነት የፍርድ ባለዕዳውን ንብረት በተራ ባለገንዘቦች መካከል ማከፋፈል በሚቻልበት ሁኔታ ላይ የተወሰነ እንጂ የቀዳሚ መብትነት የሚመለከት አይደለም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶች ከፍርድ የመነጨ የመያዣ ውል የመኖሩን እውነታ ወደ ጐን በመተው ንብረቱን በሚመለከት በንብረቱ ላይ ያስወሰነው 1ኛ ተጠሪ ነው የሚለውን ብቻ መሠረት በማድረግ ለዚሁ 1ኛ ተጠሪ በንብረቱ ላይ የቀዳሚነት መብት እንዲኖረው በማድረግ የሰጡት ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የምዕ/ጐጃ መስ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአፈፃ/መ/ቁ.8291 በመስከረም 23 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና የአማራ ብሔ/ክል/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 07568 ታህሳስ 24 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው በመሆኑ ይኸው በፍኖተ ሰላም ከተማ ቀበሌ 02 በ2ኛዋ ተጠሪ በወ/ሮ ለመች ላቀው ስም ተመዝግቦ የሚገኘው የሆቴል ቤት ድርጅት ተሸጦ ከሽያጩ ገንዘብ የአሁን አመልካች የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለሚፈልገው ዕዳ በቅድሚያ



ሊውል ይገባል ብለናል፡፡ ስለሆነም አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት በዚሁ ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈፅም አዘናል፡፡ ግልባጩ ይድረሰው፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰበር መ/ቁ. 29375

ጥቅምት 19 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ሣሙኤል ገዛኸኝ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ተስፋዬ ገብረጊዮርጊስ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የማይንቀሣቀሱ ንብረት ከመያዣ ውል ጋር በተያያዘ ሁኔታ የተነሣውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በአማራ ብ/ክ/መ/ በምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪው በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው የመያዣ ውሉ በዋስትና ያላስያዝኩትን ቤት ጨምሮ ሽጦብኛል በማለት ነው፡፡ አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ በአዋጅ ቁ. 97/90 መሠረት በጨረታ የሸጥኩት በመያዣው ውል የተመለከተውን ቤት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ክርክሩን ከሰማ በኋላ፣ ተከሣሽ የመያዣ ውሉ ከተፈረመ በኋላ የተሠሩትን ሰርቪስ ቤቶች ጭምር የሸጠ በመሆኑ የሰርቪስ ቤቶቹ ግምት ለከሣሽ ይክፈል ሲል ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤትም ውሣኔውን አፅንቶአል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 23 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች በመያዣ ውሉ



መሠረት ከያዘው ቤት ጋር ተያይዘው ለተሠሩት ሰርቪስ ቤቶች ግምት እንዲከፈል የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አከራካሪው ነጥብ የሚወስነው ስለማይንቀሣቀሱ ንብረቶች መያዣ እና አፈፃፀሙን በሚመለከት በፍትሐብሔር ሕጉ በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ ከሥር ጀምሮ በተደረገው ክርክር በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው ለአሁኑ ክርክር መነሻ የሆኑት ሰርቪስ ቤቶች የተሠሩት አመልካች በዋስትና የያዘው ቤት ባለበት (በተሠራበት) ቦታ ላይ እንደሆነ ነው፡፡ ይህም ማለት ከዋናው ቤት በመቀጠል ወይም በማያያዝ የተሠሩ ናቸው ማለት ነው፡፡ የማይንቀሣቀሰው ንብረት በመያዣነት ከተሰጠ በኋላ አዲስ ሥራ ወይም ማሻሻል ቢደረግ የመያዣ ውሉን አፈፃፀም በተመለከተ የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 3066 ግልጽ የሆነ መልስ ሰጥቶአል፡፡ የማይንቀሣቀስ ንብረት መያዝ መብት የመያዣው መብት በሚመለከተው የማይንቀሣቀስ ንብረትና በዚሁ ንብረት ላይ የሚሠሩትን አዳዲስ ሥራዎች እንደሚጠቀልል ያመለክታል፡፡ ይህን ድንጋጌ ከያዝነው ክርክር ጋር አገናዝበን ስንመለከተው ተጠሪ ቤቱን በመያዣነት ለአመልካች ከሰጠ በኋላ ሠራሁአቸው የሚላቸው ሰርቪስ ክፍሎች ከመያዣው ውጪ ሊታዩ እንደማይችሉ ነው መገንዘብ የምንችለው፡፡ በመሆኑም ሰርቪስ ቤቶቹ የመያዣ ውሉ በተደረገ ጊዜ ያልነበሩና ያልተገመቱ ናቸው በሚል ምክንያት አመልካች የሰርቪሶቹን ግምት እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበባቸው በአማራ ብ/ክ/መ/ የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 3840 ሐምሌ 27 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው እና የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 07448 ጥር 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች የሰርቪስ ቤቱቹን ግምት የሚከፍልበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

ውሣኔው ለስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



የሰ/መ/ቁ. 33295

ግንቦት 21 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

መድህን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ፀጋዬ አስማማው

**አመልካች፡-** ወ/ሪት ብርሃኔ አበበ ጠበቃ ክፍሌ ታደሰ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ ማርቆስ ተርፋ ጠበቃ ቢኒያም ተርፋ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ፀሐይ መንበረ በሌሉበት ይታያል

3. አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማ ነገረፈጅ ሺጋው ሰውነት

4. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በሌሉበት ይታያል፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ 04227 ሐምሌ 30 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 23888 ሰኔ 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት በማመልከታቸው ነው፡፡ የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ፣ ተከራካሪዎች በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ካቀረቡት ክርክርና የከፍተኛ ፍርድ ቤት በትእዛዝ አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች በማስቀረብ መርምሮ በውሣኔው ካሰፈረው ለመረዳት እንደሚቻለው በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞው ወረዳ 3 ቀበሌ 52 የቤት ቁጥር 154 የሆነዉን ቤታቸውን ሁለተኛ ተጠሪ በ1986 ዓ.ም ለአቶ ሽሮ ገመቹ ይሸጣሉ፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን ለአቶ ሽሮ ገመቹ ከሸጡ በኂላ ቤቱን ለመሸጥ ለመለወጥ የሚያስችላቸውና ቤቱን

ለመሸጥ ለመለወጥ እንዲችል፣ ሌላ ሰው መወከል የሚያስችላቸውን የውክልና ስልጣን ይሰጣሉ፡፡ ከዚህ በኂላ አቶ ሽሮ ገመቹ በበኩላቸው የቤቱን ስመ ንብረት በስማቸው ሣያዛውሩ ቤቱ በሁለተኛ ተጠሪ ስም እያለ ለአንደኛ ተጠሪ አቶ ማርቆስ ተርፋ ከሸጠ በኂላ፣ ሁለተኛዋ ተጠሪ ቤቱን ስትሸጥለት ነሐሴ 18 ቀን 1987 ዓ.ም በቁጥር 21134/87 ዓ.ም በሰጠችው ውክልና ስልጣን መሰረት ሁለተኛው ተጠሪ ቤቱን እንዲሸጥና እንዲለውጥ የውክልና ስልጣን ይሰጣሉ፡፡

- አንደኛ ተጠሪ በበኩሉ የቤቱን ስመ ንብረት በስሙ ሣያዛውር ቤቱ በሁለተኛዋ ተጠሪ ስም እያለ አቶ ሽሮ ገመቹ የሰጠውን የውክልና ስልጣን በመጠቀም መስከረም 28 ቀን 1988 ዓ.ም ለአመልካች በብር 70,000 /ሰባ ሺ.ህ ብር/ ሽጦና ውሉም በአዲስ አበባ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ተረጋግጦ የቤቱን ዋጋ ብር 70,000/ሰባ ሺ. ብር/ ከአመልካች ተቀብሎ የቤቱን ካርታና ሣላን እንደዚሁም ሌሎች ማስረጃዎች ለአመልካች ያስረክባል፡፡
- ከዚህ በኂላ አንደኛው ተጠሪ መስከረም 28 ቀን 1988 ዓ.ም ለአመልካች የሸጠውን እና ስመ ንብረቱ በሁለተኛ ተጠሪ ስም ያለውን ቤት መያዣ በማድረግ፣ ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺ. ብር/ ጥቅምት 26 ቀን 1988 ዓ.ም ከሶስተኛው ተጠሪ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ ይወስዳል፡፡ ሶስተኛው ተጠሪም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በማቅረብ ጥቅምት 27 ቀን 1988 ዓ.ም ያስመዘግባል፡፡ አንደኛው ተጠሪ፣ የቤቱን ካርታና ሣላን ለአመልካች ያስረከበ በመሆኑ ቤቱን በመያዣነት ሲያስይዝ የቤቱ ካርታና ሣላን በእጁ አልነበረም፡፡ ስለሆነም ብድሩን ከወሰደ ከሃያ አምስት ቀን በኂላ የቤቱ ካርታ ሣላንና የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጠፍቶብኛል በማለት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አመልክቶ



ህዳር 21 ቀን 1988 ዓ.ም በቁጥር 33564 የሆነ የተመዘገበ ምትክ ካርታና ሣላን አውጥቷል፡፡

አመልካች የቤቱን ስመ ንብረት ለማዛወር ስትሞክር የገዛችው ቤት በመያዣነት ተይዞ በማግኘቷ ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክስ አቅርባለች፡፡ አንደኛው ተጠሪ ቤቱን የሸጠ መሆኑን ሣይክድ ገንዘብ አልተቀበልኩም ሰነዶቹንም በማጥፋት አመልካች እንዳትጠቀም አድርጌአለሁ የሚል ክርክር ያቀረበ ሲሆን፣ ሁለትኛዋ ተጠሪ ቤቱን የሸጥኩት ለአቶ ሽሮ ገመቹ በመሆኑም እኔ ልጠየቅ አይገባኝም ብላለች፡፡ ሶስተኛ ተጠሪ፣ የተመዘገበ የመያዣ ውል ያለኝ በመሆኑ በቤቱ ላይ ቀደምት መብት ያለኝ እኔ ስለሆንኩ የቤቱ ስመ ንብረት ይዛወርልኝ በማለት አመልካች ያቀረበችው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ አራተኛው ተጠሪ በበኩሉ እኔ የምከሰስበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የአመልካች ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት የወሰነ ሲሆን፣ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ አመልካች በቤቱ ላይ የምታነሣው የቀዳሚነትና የባለቤትነት መብት ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህ ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ የቤቱን ስመ ንብረት ለማዛወር ጠይቄ የነበረ ሲሆን በወቅቱ በመመሪያ በመታገዱ ብቻ ሣይዛወር ቀርቷል፡፡ ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም፣ አንደኛ ተጠሪ በማጭበርበር ሽጦ ገንዘብ የተቀበለበት ቤት ለሶስተኛ ተጠሪ መያዣ በማድረግ ገንዘብ መበደሩ፣ ለሶስተኛው ተጠሪ የቀዳሚነት መብት የሚያስገኝለት አይሆንም፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቶቹ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት ይባልልኝ በማለት ያመለከተች ሲሆን አንደኛ እና አራተኛ ተጠሪ በጋዜጣ ተጠርተው ባለመቅረባቸው ክርክሩ በሌሉበት ቀጥሏል፡፡ ሶስተኛው ተጠሪ በቤቱ ላይ ህጋዊ የቀዳሚነት መብት ያለኝ እኔ ነኝ በማለት የፍታብሔር ህግ የመያዣ ውል፣ ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ይዘት

በአጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ሶስተኛ ተጠሪ ከአንደኛው ተጠሪ ጋር ያደረጉት የመያዣ ውል በህግ በተደነገገው አግባብ የተመዘገበና የቀዳሚነት መብት የሚያስገኝ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች በማስቀረብ አረጋጋጦ በፍርድ ከመዘገበው ፍሬ ጉዳይ እንደተረዳነው ሶስተኛ ተጠሪ ከአንደኛው ተጠሪ ጋር የመያዣ ውል ተፈራርሞ 200,000 ብር (ሁለት መቶ ሺ) ያበደረው ጥቅምት 26 ቀን 1988 ዓ.ም ሲሆን የመያዣ ውሉ በአስተዳደሩ የተመዘገበው ጥቅምት 27 ቀን 1988 ዓ.ም ነው፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የቤቱን ስም ለማዛወር በአስተዳዳሩ ጥያቄ አቅርቤአለሁ የሚል ክርክር በማቅረቧ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሁለተኛ ተጠሪ ስም ያለው የቤቱ መዝገብና ማህደር እንዲቀርብ ትእዛዝ ሰጥቶ የልደታ ክፍለ ከተማ የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት በቁጥር ልደታ 114/10/4357/98 ታህሣስ 4 ቀን 1998 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ በጽ/ቤቱ በነበረው የመዋቅር ለውጥ ምክንያት ወ/ሮ ፀሐይ መንበረ ስም ተከፍቶ የነበረው ማህደር የጠፋ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መስሪያ ቤቱ ምትክ ማህደር በሶስተኛ ተጠሪ አመልካችነት መክፈቱን ገፆአል፡፡ ሶስተኛው ተጠሪ ተመዝግቧል የሚለው የመያዣ ውል ተመዝግቦና ተይዞ የተገኘው በአንደኛ ተጠሪ ስም ተከፍቶ በነበረውና እንደጠፋ በተረጋገጠው ማህደር ሣይሆን፣ በራሱ በሶስተኛ ተጠሪ አመልካችነት በተከፈተው ምትክ ማህደር ውስጥ ነው፡፡

እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ አንደኛ ተጠሪ የቤት ፕላንና ካርታ ሣይኖረው ከሶስተኛ ተጠሪ ጋር ያደረገውን የመያዣ ውል፣ የቤቱ ባለቤት በሆነችው ሁለተኛ ተጠሪ ስም የነበረው ማህደር በሌለበት ሁኔታ አራተኛው ተጠሪ በምን መንገድ ጥቅምት 27 ቀን 1988 ዓ.ም የአንደኛ ተጠሪና የሶስተኛውን ተጠሪ መያዣ ውል መዝገበው? አመልካች በወቅቱ የስም ይዛወርልኝ ጥያቄ ላለማቅረቧስ ማህደሩ በጠፋበት ሁኔታ እንዴት ለማረጋገጥ



ይቻላል የሚሉት ነጥቦች አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር መታየት አለባቸው፡፡

የማይንቀሣቀስ ንብረት መያዣ በማናቸውም አይነት ሰነድ ላይ የተመሰረተ ቢሆን ከተፃፈበት ቀን አንስቶ የማይንቀሳቀሰው ንብረት በሚገኝበት አገር ባለው በማይንቀሳቀስ ርስት መዝገብ ካልተፃፈ በቀር ማንኛውንም አይነት ውጤት እንደማያስገኝ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3052 የሚደነግግ ሲሆን የማይንቀሣቀስ ንብረትን መያዣ እንዲመዘግብ ጥያቄ የቀረበለት የማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ሰራተኛ የውሉን አመዘጋገብ ሥርአት የሚፈጽመው በዚህ ህግ ስለማይንቀሣቀሱ ንብረቶች አመዘጋገብ ሥርአት በሚመለከተው አንቀጽ በተደነገገው ደንብ መሰረት መሆን እንደ ሚገባው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3053 ንኡስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ ይኸም የሚያሳየው የመያዣ ውል በህጉ በተቀመጠው መሰረት በአግባቡ ካልተመዘገበ ህጋዊ ውጤት አይኖረውም፡፡ ከዚህ አንፃር የማይነቀሳቀስ ንብረት መያዣ መመዝገብ ያለበት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1605 እና 1607 የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው መሆን ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ሶስተኛ ተጠሪ ከአንደኛው ተጠሪ ጋር ያደረገው የመያዣ ውል እንዲመዘገብለት አስተዳደሩን ሲጠይቅ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1606 የተደነገገውን ሁኔታ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያልነበረ ሲሆን እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1607 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት መቅረብ የሚገባቸው አስረጅ ሰነዶች ባልቀረቡበት ሁኔታ ነው፡፡

ለዚህም ምክንያቱ አስተዳደሩ የመያዣ ውሉን አስመዘገብኩ በሚልበት ጥቅምት 27 ቀን 1988 ዓ.ም የቤቱ ካርታ እና ፕላን የለም፡፡ አንደኛው ተጠሪ በሐሰት ካርታና ፕላን ጠፍቷል ብሎ ምትክ ካርታ ፕላን ያወጣው ህዳር 21 ቀን 1988 ዓ.ም ነው፡፡ በሌላ በኩል በሁለተኛ ተጠሪ ስም የነበረው ማህደር በአስተዳደሩ መስሪያ ቤት ተፈልጐ ሊገኝ እንዳልቻለ ታውቋል፡፡ ይኸ ከሆነ አስተዳደር መስሪያ ቤቱ ሶስተኛ ተጠሪ በፍታብሔር

ህግ ቁጥር 1606 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1607 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ለመያዣ የተመዘገበው ቤት አስረጅ ሰነዶች ሳይቀርቡለት የአንደኛ ተጠሪ እና ሶስተኛ ተጠሪን ውል ብቻ በማየት ያደረገው ነው፡፡

ሶስተኛ ተጠሪ ህጋዊ የንብረት ማረጋገጫ ሰነድ በሌለበት ሁኔታ ከአንደኛው ተጠሪ ጋር ያደረገው የመያዣ ውል በመያዣ ተሰጠ የተባለው ቤት ማህደርና አስረጅ ሰነድ በሌለበት ሁኔታ በአስተዳደሩ መመዝገቡ በህጋዊ መንገድ ገብታ የንብረቱን ባለቤትነት የሚያረጋግጡ ሰነዶችን በእጇ አድርጋ ንብረቱን በይዞታዋ አድርጋ እየኖረችበት ካለችው ከአመልካች የተሻለ የቀዳሚነት መብት የሚያስገኝለት አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በሽያጭ ውሉ መሰረት ንብረቱ በስሟ ለማዞር ጥያቄ ያቀረበች መሆኑን ገልፃለች፡፡ ማህደሩ የጠፋ በመሆኑ አመልካች ጥያቄውን ማቅረብ አለማቅረቧን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ሶስተኛ ተጠሪም ቢሆን በራሱ አመልካችነት ምትክ ማህደር አስከፍቶ ስለተገኘ ብቻ መያዣ ውሉ በህጉ አግባብ ተመዝግቧል ማለት አይደለም፡፡ ስለሆነም ሶሰተኛ ተጠሪ፣ ተገቢውን ትጋት በማድረግ የንብረቱ ካርታና ፕላን እንደዚሁም ሌሎች አስረጅ ሰነዶች በአንደኛ ተጠሪ ሳይቀርብለት ተዋውሎና እና የመያዣ ውሉም አስፈላጊ ከሆኑ ሰነዶች ጋር ሣይቀርብ የመያዣ ውል አስመዝግቦ መገኘቱ የቤቱን ባለቤትነት የሚያረጋግጥ ማስረጃ በሌለበት የተፈፀመ በመሆኑ ከአመልካች የተሻለና የቀዳሚነት መብት የሚያስገኝለት አይደለም፡፡ ስለሆነም ህገ ወጥና የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት መሆኑን የሚያመላክቱ ማስረጃዎች እያሉና የመያዣ ውሉ የተደረገውም ሆነ የተመዘገበው የንብረቱ ካርታና ፕላን በሌለበትና ለሚመዘግበው አካል ባልቀረበበት ሁኔታ የሥር ፍርድ ቤት በቤቱ ላይ ሶስተኛው ተጠሪ የቀዳሚነት መብት አለው በማለት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት ብለን ወስነናል፡፡



**ው ሣ ኔ**

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትና የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ሶስተኛ ተጠሪ አመልካች መስከረም 27 ቀን 1988 ዓ.ም ገዝታ በይዞታዋ አድርጋ እየኖረችበት ባለው ቤት ላይ ከአንደኛ ተጠሪ ጋር ባደረጉት የመያዣ ውል መሰረት የቀዳሚነት መብት አለኝ በማለት የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡
3. በቤቱ ላይ የቀዳሚነት መብት ያላት አመልካች ስለሆነች የቤቱ ባለቤትነት ለአመልካች ሊተላለፍ ይገባል ብለናል፡፡
4. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግንቦት 21 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

# የኪራይ
# ውል



የሰ/መ/ቁ. 23024

ሐምሌ 24 ቀን 1999 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

ብርሃኑ አመነው

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ፋጤ በሽር - ጠበቃ አቶ ወልደሥላሴ ብርቱ ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** መልዓከገነት ዮሐንስ አምባው - ቀረበ፡፡

**ጣልቃ ገብ፡-** የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ነገረ ፈጅ አቶ ዓለሙ አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የካቲት 2 ቀን 1998 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ክርክሩ የጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ ያቀረበው ክስ በውክልና እንዲያስተዳድሩ የተሰጣቸውን ቤት እንዲያስረክቡ የሚል ነው፡፡ አመልካች በበኩላቸው ቤቱ ከከሣሽ /ተጠሪ/ ጋር አብረው ባቋቋሙት "መሠረት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር" ስም ተዛውሮ ኪራይም በንግድ ድርጅቱ ስም ሲከፈል የቆየ በመሆኑ ቤቱ እንደጋራ ንብረት ከሚቆጠር በስተቀር የግል ሊሆን ስለማይችል ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ኤጀንሲም በጣልቃ ገብነት በጉዳዩ ገብቶ አመልካችና ተጠሪ በጋራ ያቋቋሙት የንግድ ድርጅት የፈረሰና ሕልውና ያከተመ በመሆኑ የቤቱ ይዞታ ሊመለስለት እንደሚገባ አመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ክርክሩን መርምሮ የቤቱ ኪራይ ውል በንግድ ድርጅቱ ስም የተመዘገበ ስለሆነ አመልካችና ተጠሪ በቤቱ ላይ መብት ስለሌላቸው ሊከራከሩ አይችሉም፣ ጣልቃ ገብም በክርክሩ

ውስጥ የገባው ክርክሩን ለማስቆም ብቻ ስለሆነና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ ዓላማም ከዚህ ያለፈ ስላልሆነ የዳኘነቱን ጥያቄ በተገቢው መንገድ ከሚያቀርብ በስተቀር ይዞታው እንዲመለስልኝ በማለት ያቀረበውን አቤቱታ አልተቀበልነውም በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ ውሣኔውን በመቃወም ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱም "ቤቱን በኪራይ ለመያዝ ከግራ ቀኙ የተሻለ መብት ያለው ማነው" የሚል ጭብጥ መሥርቶ ተጠሪ ቀደም ሲል የንግድ ድርጅቱ ከመቋቋሙ በፊት በራሱ ስም ተከራይቶት የነበረው ቤት ከእጁ ሊወጣ የቻለው ለአመልካች በሰጠው ውክልና ምክንያት በመሆኑ፤ ከዚያ በኋላ በጋራ ያቋቋሙት ድርጅትም በመፍረሱና ውክልናውም በመሻሩ ግራ ቀኙ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1815 መሠረት ወደየነበሩበት ቦታ ሊመለሱ ይገባል፤ አመልካች ቤቱን ለተጠሪ ያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ጣልቃ ገብ ባለመጠራቱ በክርክሩ አልተካፈለም፡፡

አመልካች ለዚህ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት በንግድ ድርጅቱ ስም መከራየቱ እየታወቀና ድርጅቱም ከፈረሰ የድርጅቱ መልካም ስምና የተከራይ መብት የጋራ ከሚሆን ወይም የቤቱ ኪራይ ለጣልቃ ገብ ከሚመለስ በስተቀር በንግድ ሕግ በአንቀጽ 24 እና 26 መሠረት ቤቱ ለተጠሪ ሊመለስ አይገባውም የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ከተመረመረ በኋላ አመልካች ቤቱን ለተጠሪ ያስረክብ የተባለው በአግባቡ መሆኑን አለመሆኑን ለመርመር ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ከተደረገ በኋላ መዝገቡ ለውሣኔ ተቀጥሮ ሲመረመር በዚህ ጉዳይ በሥር ፍርድ ቤት በጣልቃ ገብነት ተከራካሪ የነበረው የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ በጠቅላይ ፍርድ ቤት በተደረገው የይግባኝ ክርክር ተካፋይ እንዲሆን አለመጠራቱ በከፍተኛ ፍ/ቤት ያገኘውን መብት የሚያሳጣና በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 40/5/ ላይ የተደነገገውን አሠራር ያልተከተለ ሆኖ በመገኘቱ በሰበር ክርክሩ በጣልቃ ገብነት ተካፋይ እንዲሆን ተበይኗል፡፡



ፍርድ ቤቱ በአጠቃላይ በአመልካች፣ በተጠሪና በጣልቃ ገብ መካከል የተደረገውን ክርክር ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በመሠረቱ ክርክሩን ያስነሳው ቤት ባሁኑ ጊዜ ፈርሶ ሕልውናው ባከተመው "መሠረት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር" ስም የኪራይ ውሉ ተመዝግቦ ኪራዩም በማኅበሩ ስም የሚከፈል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ለዚሁም የኪራይ ውሉ በማስረጃነት ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

ይሁን እንጂ የኪራይ ውሉ በድርጅቱ ስም ከመደረጉ በፊት ቤቱ በተጠሪ ስም እንደነበር አልተካደም፡፡ ቤቱ በድርጅቱ ስም የተዛወረውም አመልካች ከተጠሪ ባገኙት ውክልና መነሻነት ለመሆኑም ግራ ቀኙ ተማምነዋል፡፡ ተጠሪ ምንም እንኳን ውክልናው በኋላ ተሽሯል የሚል ክርክር ቢኖራቸውም ቤቱ በንግድ ድርጅቱ ስም ከመዛወሩ በፊት ውክልናውን ለመሻራቸው ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡

በመሆኑም ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት በማስረጃዎች ነጥረው ከወጡት ሁለት ፍሬ ነገሮች በመነሣት የቤቱ ባለይዞታ የንግድ ማኅበሩ እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል የንግድ ማኅበሩ ባሁኑ ወቅት ፈርሶ ሕልውናውን አጥቷል፡፡ የንግድ ማኅበሩ መፍረሱ ከተረጋገጠ ደግሞ የቤቱ እጣ ፈንታ የሚወሰነው በማኅበርተኞቹ ስምምነት ወይም በመካከላቸው ስምምነት ከሌለ ቤቱ የግል ወይም የጋራ ይሁን በማለት እርስ በርስ በሚያስነሱት ክርክር አይደለም፡፡ ምክንያቱም የቀድሞ የንግድ ድርጅት ማኅበርተኞች በቤቱ ላይ የባለቤትነት መብት የላቸውም፡፡ በሌላ አነጋገር ቤቱ የማኅበርተኞቹ የካፒታል አካል ሳይሆን የጣልቃ ገብ ንብረት ነው፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ በጋራ ያቋቋሙት የንግድ ማኅበር መፍረሱ እስከተረጋገጠ ድረስ በማኅበሩ ስም ከጣልቃ ገብ ላይ በተከራዩት ቤት አንዳቸውም የተሻለ የይዞታ መብት የላቸውም በማለት የወሰነው ባግባቡ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ተጠቃሚው ጣልቃ ገብ የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያስተናገደው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ግን ጣልቃ ገብን ባለመጥራት ከአመልካችና ከተጠሪ የተሻለ መብት ያለው ማነው? የሚል ጭብጥ መስርቶ ጣልቃ ገብን የሚጎዳ ውሣኔ መስጠቱ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 40/5/ ድንጋጌን ያልተከተለ አሠራር በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል፡፡

በተጨማሪም ተጠሪ በቤቱ ላይ ቀደም ሲል የንግድ ማኀበሩ ከመቋቋሙ በፊት የነበራቸው የተከራይነት መብት ከእጃቸው ሊወጣ የቻለው ለአመልካች በሰጡት ውክልና መነሻነት ነው በማለት ውክልናው የኪራይ ውሉ ወደ ድርጅቱ ስም በተዛወረበት ጊዜ የፀና እንደነበር እየተመለከተ ሕልውናው ባከተመና በሌላ ውል በተተካው በቀድሞ የኪራይ ውል ላይ ሕይወት በመዝራት ተጠሪ ቤቱን እንዲረከቡ የሰጠው ውሣኔ ምንም ዓይነት ሕጋዊ መሠረት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ በሕግ ተደግፎ ውሣኔ መስጠት ሲገባው ያለ ሕግ ወስኖ በመገኘቱ ሌላ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

- የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ. 20708 ጥር 12 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
- የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20/80 ግንቦት 17 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የመዝገብ ቁጥር 24221

ህዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-**መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍስሐ ወርቅነህ
ሐጎስ ወልዱ
ሂሩት መለሰ
ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ- ነ/ፈጅ አበበ ጥላዬ

**ተጠሪ፡-** እነ ወ/ሮ አረጋሽ አምደሚካኤል- ጠበቃ ዘውዱ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>**ፍ ር ድ**</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ቤት ይልቀቅልኝ በማለት በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ በሥር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ባለማግኘቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጸሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ 1ኛ ተጠሪ በሰኔ 1 ቀን 1974 ዓ.ም. በተደረገ ውል በወረዳ 21 ቀበሌ 04 ቁጥር 031/08 የሆነውን ቤት በወር ብር 212.50/ሁለት መቶ አስራ ሁለት ከሀምሳ/ ተከራይተው እያለ ውሉን በመጣስ ከአገር ሲወጡ ቤቱን ለ2ኛ ተከሳሽ አስተላልፈዋል፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሽም ቤቱን በሕገወጥ መንገድ ይገለገሉበታል፡፡ ስለዚህ የኪራይ ውሉ ተሰረዞ ቤቱን እንዲያስረክቡ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችም ባቀረቡት የመከላከያ መልስ 1ኛ ተጠሪ ለሕክምና ከኢትዮጵያ ውጭ ሲሄዱ እስኪመለሱ ድረስ 2ኛ ተጠሪ

በውክልና ንብረታቸውን እንዲጠብቁላቸው 2ኛ ተጠሪም ለተወሰነ ጊዜ ለሥራ ከአዲስ አበባ ውጭ ሲሄዱ 3ኛ ተጠሪ በቤቱ ውስጥ እንዳሉ ገልጸው ክሱ ከበቂ ኪሳራ ጋር ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መዝገቡን መርምሮ 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች የተከራዩትን ቤት ለሌላ ስለማስተላለፋቸው አመልካች በማስረጃ ያላረጋገጠ ሲሆን ተጠሪዎች ባቀረቧቸው ማስረጃዎች ግን 1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪን 2ኛ ተጠሪም 3ኛ ተጠሪን ንብረት ለማስተዳደር የሚያስችል ውክልና መስጠታቸውን ያረጋግጣል፡፡ ማንም ሰው ደግሞ ውክልና የመስጠት መብት ያለው ስለሆነ የኪራዩ ውል ሊሰረዝም አይችልም በማለት ክሱን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ይግባኙን ባለመቀበል የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው የቤት ኪራይ ውል ሊሰረዝ አይገባም ተብሎ በበታች ፍ/ቤቶች መወሰኑ ተጠሪዎች ባሉበት ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ሊፈታ የሚገባው የጉዳዩ ግብጥ በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው የቤት ኪራይ ውል ሊሰረዝ ይገባል? ወይንስ አይገባም? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ ይዘን አቤቱታውን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካችና 1ኛ ተጠሪ ባቋቋሙት የቤት ኪራይ ውል አንቀጽ 2.5 እና 2.6 ላይ ተከራይ የተከራየውን ቤት ያለአከራይ ፈቃድ ለሌላ ወገን ቢያስተላልፍ ውሉ እንደሚሰረዝ ተመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች አጥብቀው የሚከራከሩት 1ኛ ተጠሪ በሕክምና ምክንያት ወደ ውጭ አገር



ሲሄዱ ንብረታቸውን እንዲያስተዳድሩላቸው ለ2ኛ ተጠሪ ውክልና ሰጥተዋል፡፡ እንደዚሁም 2ኛ ተጠሪ ከአዲስ አበባ ውጭ ሲሄዱ በበኩላቸው ለ3ኛ ተጠሪ ውክልና የሰጡ በመሆኑ ድርጊቱ ውሉን የሚጻረር ባለመሆኑ ውሉ ሊሰረዝ አይገባም በማለት ነው፡፡

በእርግጥ ማንም ሰው ከባለቤትነት መብትም ይሁን ከይዞታ መብት በመነጨ በሚያዝበት ንብረት ላይ ውክልና የመስጠት ከሕግ የመነጨ መብት እንዳለው የሚያከራክር አይሆንም፡፡ በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ እንደተባለው ለሕክምና ከኢትዮጵያ ውጭ ሲሄዱ ለ2ኛ ተጠሪ ውክልና የሰጡ ቢሆንም 2ኛ ተጠሪ ረዘም ላለ ጊዜ በቤቱ ውስጥ መኖራቸው ሲታይ ከዚህም አልፎ እሳቸውም በበኩላቸው 3ኛ ተጠሪን መወከላቸው እንደዚሁም ለሕክምና ወደ ውጭ አገር ሄደዋል የተባሉት 1ኛ ተጠሪ ለረጅም ጊዜ ሳይመለሱ መቅረታቸው እነዚህ ሁኔታዎች በድምሩ ሲታዩ 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች በኪራይ የያዙትን ቤት ለ2ኛ ተጠሪ ማስተላለፋቸውን የሚያረጋግጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡ ይህ ፍሬ ነገር ከተረጋገጠ ደግሞ ግራ ቀኙ ባቋቋሙት የቤት ኪራይ ውል ላይ ከላይ እንደተመለከተው ተከራይ ያለአከራይ ፈቃድ በኪራይ የያዘውን ቤት ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ እንደማይችል የተሰማሙትን የሚጻረር እንደሆነ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ የውል ይሰረዝልኝ አቤቱታም ለፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ ዳኞች ውሉ እንዲሰረዝ ከመወሰናቸው በፊት የተዋዋዮችን ጥቅምና በቅን ልቦና የሚያስፈልገውን መሠረት ማጤን እንዳለባቸው እንደዚሁም ዓይነተኛ የውል መጣስ ተግባር /fundamental breach of contract/ ካልተፈጸመ ውሉ ይሰረዝ ሊሉ እንደማይችሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1785 ላይ የተመለከተ እንደመሆኑ መጠን ከዚህም አንጻር ሁኔታው ሲታይ 1ኛ ተጠሪ በኪራይ የያዙትን ቤት በውክልና ሽፋን ለሌላ ማስተላለፋቸውን መገንዘብ ስለተቻለና ይህም ቅን ልቦና የጎደለው መሆኑን የሚያሳይ፣ ከአመልካች ጥቅምም አኳያ ሲታይ በአዋጅ

የተቋቋመው የመኖሪያ ቤት ችግርን የተለያዩ ሁኔታዎችን ከግምት በማስገባት ቤት ለተቸገሩ ሰዎች የኪራይ መብት እንዲያገኙ ማድረግ በመሆኑ በዚህም ጉዳይ ውሉ እንዲሰረዝ የጠየቀው ይህንኑ ዓላማ ለማሳካት እንደሆነ የሚታመን ከመሆኑም በላይ የተከራዩ 1ኛ ተጠሪም ተግባር፣ ዓይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ተግባር መሆኑን መገንዘብ የተቻለ በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶቹ ውሉ ሊሰረዝ አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 20837 በግንቦት 22 ቀን 1995 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔና የፌዴ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 22487 በጥር 16 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው ሆነው ስለተገኙ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ መካከል በሰኔ 1 ቀን 1974 ዓ.ም የተደረገው የቤት ኪራይ ውል በ1ኛ ተጠሪ በኩል ዓይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ተግባር የተፈጸመበት ስለሆነ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 25938

መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ
መስፍን ዕቁበዮናስ
ታፈሰ ይርጋ
መድኅን ኪሮስ
ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት - ነ/ፈጅ አያሌው ሲበን

**ተጠሪ፡-** የአቶ ገ/ሕይወት ከበደም ወራሾች /2 ሰዎች/ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ውዝፍ የቤት ኪራይ ክፍያን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በወረዳ 15 ቀበሌ 30 የሚገኘውንና ቁጥሩ 602/10 የሆነውን ቤት በብር 1249 (አንድ ሺህ ሁለት መቶ አርባ ዘጠኝ) ሐምሌ 18 ቀን 1984 ዓ.ም. በተፃፈ ውል ተከራይተው ከመስከረም ወር 1985 ዓ.ም. እስከ መጋቢት ወር 1989 ዓ.ም. ያለውን የኪራይ ሂሣብ ስላልከፈሉ ይህንኑ የኪራይ ሂሣብ፣ መቀጫ 20% እና የውሃ አገልግሎት ሂሣብ በድምሩ ብር 176,564 (አንድ መቶ ሰባ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ስልሳ አራት) ከነወጪና ኪሣራው ይክፈሉ በማለት ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመሠረተው ክስ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪዎች በሰጡት መልስ በማስረጃነት የቀረበው የኪራይ ውል በአመልካች ያልተፈረመና በሁለት ምስክሮች ፊት ያልተረጋገጠ ስለሆነ ፈራሽ ነው፤ የአመልካች ድርጅት የወቅቱ የደንበኞች አገልግሎት ኃላፊ በብር 510 (አምስት መቶ አስር) ሂሣብ መከራየት እንደምንችል ገልፀውልን የሂሣብ ክፍሉ ሊቀበሉን ባለመፈለጋቸው የኪራዩን ሂሣብ ብር 15,000 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ) በአመልካች የሂሣብ ቁጥር ገቢ አድርገናል፤ ስለዚህ ልንከፍል

የሚገባን ተመሣሣይ ቤት ለኢትዮጵያውያን በሚከራይበት ዋጋ ተሰልቶ በባንክ የተከፈለው ገንዘብም ተቀንሶ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የቀረበው የውል ሰነድ በተከራይ የተፈረመ በአከራይ ግን ያልተፈረመ በመሆኑ የውሉ ረቂቅ እንጂ ውል አይደለም፤ ሆኖም ግን ተጠሪዎች ቤቱን ያለውል በመያዝ ሲጠቀሙበት በመቆየታቸው ያለአግባብ የበለፀጉበትን ከመስከረም 1985 ዓ.ም. እስከ መጋቢት 1989 ዓ.ም. ድረስ ያለውን ሂሣብ ተጠሪዎች ራሳቸው ባመኑት በብር 510 (አምስት መቶ አስር) ሒሣብ ተሰልቶ ከሚመጣው ብር 28,000 (ሃያ ስምንት ሺህ) ላይ ተከሣሽ የከፈሉት ብር 15,000 (አሥራ አምስት ሺህ) ተቀንሶ የሚቀረውን ብር 12,650 (አሥራ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ) ለአመልካች ይክፈሉ፤ ቅጣቱን በተመለከተም በግራ ቀኙ መካከል ውል በሌለበት ሁኔታ ተጠሪዎች ቅጣት እንዲከፍሉ አይገደዱም፤ የተጠየቀውን የውሃ ሂሣብ ግን ተጠሪዎች መክፈል እንደማይገባቸው ስላላስረዱ ብር 1,100 (አንድ ሺህ አንድ መቶ) ለአመልካች ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ቅሬታውን ባለመቀበል ውሣኔውን አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ ችሎቱም በአቤቱታው መነሻነት የስር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር የኪራይ ውል ነው ተብሎ በአመልካች በቀረበው ሰነድ ላይ አከራዩ አልፈረመበትም ተብሎ በግራ ቀኙ መካከል የኪራይ ውል የለም በማለት የተወሰነው በአግባቡ መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው ነጥብ ሆኖ ስላገኘው ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቷል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነው የስር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል ተደርጓል የተባለው ውል ረቂቅ እንጂ ውል አይደለም ለማለት የበቃው በማስረጃነት ባቀረበው ሰነድ ላይ አከራይና ምስክሮች አልፈረሙበትም ከሚል



መንደርደሪያ በመነሳት መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ በመሠረቱ በሁለት ተዋዋይ ወገኖች በማናቸውም ሁኔታ የተደረገ ስምምነት ውል ለማድረግ በቂ እንደሆነ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1719/1/ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ በግልጽ መገንዘብ እንደሚቻለው በሁለት ተዋዋይ ወገኖች መካከል የሚፀና ወይም ሕጋዊ ውጤት ያለው ውል ለመመስረት በሁለቱም መካከል ስምምነት መኖሩ ብቻ በቂ ነው፡፡ ስለዚህ ከኢትዮጵያ የውል ሕግ መሠረታዊ መርህ አንፃር በሕግ ወይም በተዋዋዮች በራሳቸው የተለየ ፎርም ካልተፈለገ በስተቀር ውልን ለመመስረት በተዋዋዮች መካከል ስምምነት መኖሩ ብቻ በቂ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ውል ሕጉ ያስቀመጠውን የፎርም መስፈርት አያሟላም ተብሎ ውድቅ ሊደረግ የሚችለው ይህንን ውል የሚመለከት በግልጽ የተቀመጠና የተለየ የአፃፃፍ ሥርዓት /ፎርም/ ኖሮ ተዋዋዮች ይህንን ፎረም ሳይከተሉ ከቀሩ ወይም በተዋዋዮች ምርጫና ፍላጎት ስምምነቱ በጽሁፍ ከመሆኑ በተጨማሪ ሌሎቹንም ፎርማሊቲዎች እንዲሟሉ መፈለጋቸው በጽሁፉ በራሱ ወይም በሌላ መልክ ተገልፆ ሲረጋጥና ውሉም ይህንን በመከተል የተደረገ ካልሆነ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም የውልን አፃፃፍ ፎርምን የሚመለከትው የፍ/ብ/ሕግ ክፍል /አንቀጽ 1719-1930/ የኪራይ ውል የተለየ ፎርም መከተል እንዳለበት የሚያስገድድ ድንጋጌ የለውም፡፡ በዚህም ምክንያት ሕጉ የኪራይ ውልን በጽሁፍ እንዲሆን የሚያዝ አስገዳጅ ድንጋጌ ባላስቀመጠበትና  ተዋዋዮች ውሉ በጽሁፍ እንዲሆን የተስማሙ መሆናቸው ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት ውሉ የሕጉን ፎርማሊቲ ያላሟላ ስለሆነ ፈራሽ ነው ሲል የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በተጨማሪም የፍ/ብ/ሕግ በተለይ የኪራይ ውልን በሚመለከተው ልዩ ድንጋጌው በአንቀጽ 2898/3/ ላይ የኪራዩ ውል መከናወን ጀምሮ እንደሆነ የውሉን መኖር በምስክሮች ወይም በግምት አስተያየት ማስረዳት እንደሚቻል ደንግጓል፡፡ በመሆኑም ክርክር የተነሳበት የኪራይ ውል መከናወን

የጀመረ መሆኑ ያላከራከረ ጉዳይ ከመሆኑ ባሻገር አመልካች የዚህን ውል መኖር በምስክር ወይም በግምት አስተያየት ከማስረዳት ይልቅ ተከራይ የፈረመበትን ማስረጃ በማቅረብ ያስረዳ ሲሆን ፍ/ቤቱ ይህ ማስረጃ ሕጉ በቂ ናቸው ከሚላቸው የማስረጃ አይነቶች የተሻለ መሆኑን ከግምት ውስጥ ባለማስገባት በግራ ቀኙ መካከል የኪራይ ውል የለም ሲል መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ነው ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 04072 ሚያዝያ 29 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 32027 ሚያዝያ 14 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽረዋል፡፡
2. በግራ ቀኙ መካከል የኪራይ ውል መኖሩን በመገንዘብ አመልካች በስር ባቀረባቸው ጥያቄዎች ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ እንዲወስን ጉዳዩ ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት 341/1/ መሠረት ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰበር መ/ቁ. 28025

ጥር 20 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረ ፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ አያሌው ሲበን

ተጠሪ፡- አቶ ታደለ አበበ - ቀረቡ

<u>ፍ ር ድ</u>

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉደይ የተጀመረው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ በመሠረተው ክስ ተጠሪ በወረዳ 21 ቀበሌ 01 ክልል ውስጥ ቁጥር 292/14 የሆነውን ቤት ተከራይተው ያልከፈሉት ውዝፍ ኪራይ እና የውሃ ክፍያ ያለባቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ቤት መስራታቸው ስለተረጋገጠ የኪራይ ውሉ ፈርሶ ቤቱን እንዲያስረክቡ እና ውዝፍ ኪራይ እና የውሀ ሂሣብ እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡

የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ባልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ሊፈርስ የሚችለው አከራዩ ለተከራዩ የ2 ወር ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሲሆን አመልካች ግን ይህን ስላላደረገ ውሉ ፈርሶ ቤቱን ለመረከብ ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፣ ተጠሪ ያለባቸው ቀሪ ዕዳ ብር 442.20 (አራት መቶ አርባ ሁለት ከሣያ) ስለሆነ ይህንን ገንዘብ ለአመልካች ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የመጀመሪያውን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የቀረበው ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊሻር ይገባዋል በሚል ነው፡፡

ከመዝገቡ እንደተረዳነው አመልካች የኪራይ ውሉ እንዲፈርስለት የጠየቀው ተጠሪ ግዴታቸውን አክብረው የኪራይ ገንዘቡን ባለመክፈላቸውና ቤት የሠሩ በመሆኑ ሲሆን ቤት ባይኖራቸውም እንኳን በፍ/ህ/ቁ. 2966 መሠረት የኪራይ ውል በአንድ ወገን ብቻ ሊፈርስ እንደሚችልም ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ተጠራቅሟል የተባለውን የቤት ኪራይ አጠናቀው በመክፈላቸው እና ማስጠንቀቂያ ያልተሰጣቸው በመሆኑ እንዲሁም ግዴታቸውን መፈፀም ባይችሉ ወደ ሌላ ቤት እንዲዛወሩ ከሚደረግ በቀር ቤቱን እንዲለቁ ሊጠየቁ እንደማይገባ ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ አግባብነት ካላቸው የቤትን ኪራይ ከሚመለከቱ ድንጋጌዎች አኳያ መርምሯል፡፡

በአመልካችና በተጠሪ መሃከል የተደረገው የኪራይ ውል ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ደግሞ ለተከራዩ በሚሰጥ ማስታወቂያ በማንኛውም ጊዜ ሊቋረጥ የሚችል መሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 2966(1) ሥር ተመልክቷል፡፡ አከራዩ በፈለገ ጊዜ ለተከራዩ ማስታወቂያ በመስጠት የኪራይ ውሉን ሊያፈርስ መብት አለው፡፡ ከፍ ሲል እንደተባለው አከራዩ ውሉን ለማፍረስ ማስታወቂያ ለተከራዩ መስጠት እንደሚያስፈልግው የተመለከተ ቢሆንም ማስታወቂያ መስጠት ግን ውሉን ለማፍረስ አስገዳጅ የሆነ ቅድመ ሁኔታ አይደለም፡፡ ተከራዩ ማስጠንቀቂያ ባለማግኘቱ የደረሰበት ጉዳት ወይ ኪሣራ ካለ ይህንኑ ከመጠየቅ በቀር ውሉ ሊፈርስ አይችልም በማለት ለመከራከር መብት አይሰጠውም፡፡

በተያዘው ጉዳይም በአመልካችና በተጠሪ መሃከል የተደረገው ውል ላልተወሰነ ጊዜ የሚቆይ በመሆኑ አመልካች በማንኛውም ጊዜ ማስታወቂያ ሰጥቶ ሊያቋርጠው ይችላል፡፡ ማስታወቂያ አለመስጠቱም ከፍ ሲል እንደተገለፀው በተጠሪ ላይ ኪሣራ ያደረሰ ከሆነ ተጠሪ ይህንኑ ሊጠይቁ ከሚያስችላቸው በቀር የውሉን መፍረስ አያስቀረውም፡፡ ተጠሪውም በክሱ ቤቱን እንዲለቁ ከተጠየቁበት ጊዜ ጀምሮ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ እስኪሰጥበት ጊዜ ድረስ እንኳን ወደ አንድ ዓመት የሚጠጋ ጊዜ አልፏል፡፡ በመሆኑም ቤቱን ለመልቀቅ እንድችል ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስላልተሰጠኝ ልለቅ አይገባም በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ የኪራይ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ በመሆኑ በማንኛውም ጊዜ አከራዩ ውሉን ማቋረጥ የሚችል ስለሆነ (የፍ/ሕ/ቁ. 2966 (1) ይመለከቷል) ተጠሪ የቤቱን ኪራይ ከፍዬ አጠናቅቄአለሁ፣ ሌላ ቤት መስራቴ ቤቱን እንድለቅ አያደርገኝም የሚለው ክርክራቸው ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የሥር ፍ/ቤት ማስጠንቀቂያ ባለመስጠቱ የኪራይ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ የፍ/ሕ/ቁ. 2966(1) አኳያ ሲመረመር ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1ኛ/ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20941 ግንቦት 19 ቀን 1995 ዓ.ም የኪራይ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት የሰጠው የውሣኔ ክፍልና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22378 በጥቅምት 22 ቀን 1999 ዓ.ም ይህንኑ የውሣኔ ክፍል በማጽናት የሰጠው ውሣኔ ተሽረዋል፡፡

2ኛ/ በአመልካችና በተጠሪ መሃከል በወረዳ 21 ቀበሌ 01 ቁጥር 292/14 በሆነው ቤት ላይ የተደረገው የኪራይ ውል ፈርሷል፡፡ ይህንኑ ቤት ተጠሪ ለአመልካች ያስረክቡ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰበር መ/ቁ. 30894

ሚያዝያ 30 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

አሰግድ ጋሻው

ደስታ ገብሩ

መስፍን ዕቁበዮናስ

መድሕን ኪሮስ

**አመልካች ፡-** ወ/ሮ መዓዛነነት ዳኜ

**ተጠሪ ፡-** ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ክርክሩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ የስር ከሣሽ ነሐሴ 26 ቀን 1997 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ የአሁኑ አመልካች የስር ተከሳሽ በአራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 05 የሚገኘው ቁጥሩ 608 የሆነውን ቤት በማካካሻነት ነው የያዙኩት፤ ኪራይ አልከፍልም ስላሉ ያልከፈሉትን ኪራይ እንዲከፍሉ ቤቱንም እንዲያስረክቡን ይወሰንል ሲል ክስ አቅርቧል፡፡

የአሁኑ አመልካች የሥር ተከሳሽ ደግሞ ጥቅምት 29 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ ቤቱ በማካካሻነት መንግስት የሰጠኝ በመሆኑ መንግስት የወሰደውንና በቀበሌ እጅ የሚገኘውን ቤቴን ሳይመልስልኝ በማካካሻነት የያዝኩትን ቤት እንድመልስ የቀረበው ክስ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግልኝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ ተከሳሽ ያለአግባብ የተያዘባቸው ቤት ካላቸው ከሰው ከሚጠይቁ በስተቀር የያዙትን የመንግስት ቤት ያለኪራይ ሊኖሩበት አይገባም፣ ብር 13,500 (አስራ ሦስት ሺህ አምስት መቶ) ክስ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀበት ጊዜ ድረስ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለከሳሽ ይክፈሉ፣ ቤቱንም ለከሳሽ ያስረክቡ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡



አመልካች ግንቦት 22 ቀን 1999 ዓ.ም ያቀረቡት አቤቱታም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ነው፡፡ የአቤቱታው ቅሬታም የከተማ ቦታንና ትርፍ ቤቶችን የመንግስት ያደረገው አዋጅ በወጣ ጊዜ በመንግስት ቤት እንዳለኝ በቅጽ 004 ተረጋግጦ አሁን የምኖርበትን የመንግስት ቤት ያለክፍያ እንድኖርበት ነሐሴ 3 ቀን 1968 ዓ.ም ተወስኗል፡፡ የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴርም በማካካሻነት ቤት የተወሰደባቸው ቤቶች ብዙ ናቸው ስለተባለ እስከሚጣራ የኪራይ መካካሱ ይቁም አሉ እንጂ በማካካሻነት ስም የያዘችውን ቤት ታስረክብ አላለም፡፡ በእኔና በመንግስት መካከል ያለው የቤት መቻቻል ውል አንደኛው ወገን ብቻ ሊያፈርሰው የሚችል አይደለም፡፡ ቀበሌና ኪራይ ቤቶች ለአሰራር እንዲያመች መንግስት ያቋቋማቸው የመንግስት መ/ቤቶች በመሆናቸው ከሳሽ ቤት ካለሽ ቀበሌን ክሰሽ፣ ጠይቂ ሊል የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ መንግስት በማካካሻነት የሰጠሁሽን ቤት መልሺ ሊለኝ የሚችለው የሰጠሁት ቤቴን ሲመልስልኝ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ውዝፍ ኪራይ ክፈይ ቤቱንም ለኪራይ ቤቶች አስረክቢ በማለት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ውሣኔው እንዲሻርልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪ ደግሞ መስከረም 23 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የአመልካች ቤት ኪራይ እንዲካካስ ነሐሴ 3 ቀን 1968 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር በጥቅምት 19 ቀን 1978 ዓ.ም ዓ.ም በፃፈው ማሳሰቢያ ሁኔታዎች እስኪጣሩ ድረስ ማካካሱ ለጊዜው እንዲቆም አዟል፡፡ በዚሁ መሰረት የፊተኛው ደብዳቤ የተሻረ በመሆኑ አመልካች የቤት ኪራይ መክፈል ነበረባቸው፡፡ ኪራይ

ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ውዝፍ ኪራይ ከፍለው ቤቱን እንዲለቁልን ክስ መመስረታችን በአግባቡ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔም የሚነቀፍበት የፈፀመው የሕግ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም ውሣኔው እንዲፀድቅልን በማለት ተከራክሯል፡፡

በበኩላችን ደግሞ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት አመልካች ያገኙት ለራሳቸው ቤት በማካካሻነት ነው እየተባለ ባለበት ጊዜ የራሳቸው ቤት ሳይመለሰላቸው የያዙትን ቤት ለመንግስት መልሱ መባሉ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም አመልካች ለቀረበባቸው ክስ በሰጡት መልስ የተከራከሩት መንግስት የእኔን ቤት ሲወስድ ክርክር ያስነሳውን ቤት ያለ ኪራይ እንድኖርበት በማካካሻነት ሰጥቶኛል፡፡ ይህን ቤቴን ሳይመልስልኝ የያዝሽውን ቤት ልቀቂ ሊለኝ አይችልም በማለት ነው፡፡ ክርክር ያስነሳውን ቤት አመልካች የያዙት በማካካሻነት ስለመሆኑ የሚጠቁሙ ሰነዶች ከመኖራቸውም በተጨማሪ ተጠሪ ቤቱን መጀመርያ አመልካች ያገኙት በማካካሻነት አይደለም በማለት ክዶ አልተከራከረም፡፡ የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴርም ጥቅምት 19 ቀን 1978 ዓ.ምበፃፈው ደብዳቤ ግለሰቧ ቤቱን በማካካሻነት የያዙት በብዙ ቤቶች መሆኑ ስለተደረሰበት ሁኔታውን ማጣራት አስፈልጓል፡፡ ኪራይ ቤቶች የመንግስት ቤት በማካካሻነት የተሰጠበት የግለሰቧ የሆነውን ቤት ቁጥር አጣርቶ ለከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር እንዲገለጽና የማካካሻ ኪራይም ለጊዜው እንዲቆም በማለት ነው ያሳሰበው፡፡ ይህ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተፃፈው ደብዳቤ ግለሰቧ ማለት አመልካችዋ ክርክር ያስነሳውን ቤት በኪራይ ማካካሻነት የያዙት በርግጥ በሰነዶቹ ላይ እንደተገለፀው ለመንግስት ያስረከቡት ቤት ኖሮአቸው ነው? ወይስ አይደለም? በማካካሻነት የያዙት መንግስት ለወሰደባቸው ቤት ከሆነስ ለአንድ ቤት ነው ወይስ ለበርካታ ቤቶች? የሚሉትን ጥያቄዎች ማጣራት አስፈላጊ



መሆኑንና ሁኔታው ከተጣራ በኋላ ደግሞ አስፈላጊውን ውሣኔ መስጠት እንደሚገባው ነው የሚገልፀው፡፡

ሆኖም ተጠሪው መ/ቤት በሚኒስቴሩ ደብዳቤ መሠረት አመልካች በማካካሻነት የመንግስትን ቤት የያዙበት መንግስት የወሰደባቸው ቤት ስለመኖርና ያለመኖሩ ማጣራት ሲገባው ይህን ሳያደርግና በርግጥም አመልካች የመንግስትን ቤት በማካካሻነት ስም የያዙት ያለአግባብ መሆኑን ሳያረጋግጥ ለመንግስት የሰጠሽው ቤት ካለ ከሰሽ ጠይቂ፤ የያዝሽውን ቤቱን ግን ልቀቂ በማለት ክስ መመስረቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የተመሰረተውን ክስና የተደረገውን ክርክር ስንመለከተው ደግሞ አመልካች ቤቱን የያዝኩት በማካካሻነት ነው በማለት እየተከራከሩ ባሉበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ቤቱን የያዙት በማካካሻነት ነው ወይስ አይደለም? በማካካሻነት የያዙት ከሆነስ መንግስት በዚሁ ክርክር ባስነሳው ቤት ማካካሻነት የወሰደውን ቤት ሊመልስላቸው ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ አጣርቶ መወሰን ሲገባው የማጣራት ቅድመ ሁኔታ የሚያስቀምጠውን ሚኒስቴሩ መ/ቤት ጥቅምት 19 ቀን 1998 ዓ.ም የፃፈውን ደብዳቤ ቀደም ብሎ የተሰጠውን የማካካሻነት ውሣኔ የሚሽር ነው በማለት በተሳሳተ ሁኔታ በመተርጐም ማካካሻነቱ ቀሪ ሆኖአል የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን ተገንዝበናል፡፡ የሥር ፍ/ቤቱ በማካካሻነት በያዝሽው ቤት ምትክ መንግስት የወሰደብሽ ቤት ያለው በቀበሌ እጅ ከሆነ ቀበሌውን ከሰሽ ከምትጠይቂ በስተቀር ቤቱን መንግስት ሳይሰጠኝ በማካካሻነት የያዝኩትን ቤት ልለቅ አይገባም በማለት ልትከራከሪ አትችይም በማለት የሰጠው ውሣኔም ቀበሌና ኪራይ ቤቶች ሁለት የመንግስት አካላት ቢሆኑም በማካካሻነት ተያዘ የተባለው ቤት ሁለቱንም የሚያቀራኛቸው በመሆኑ በአንድ ዘንግ ቆመው በጉዳዩ መከራከር የሚገባቸው መሆኑን የሥር ፍ/ቤት እንዳልተገነዘበው ለመረዳት ችለናል፡፡

ተደረገ የተባለው መቻቻል ወይም መካካስ አመልካች ሲያከራዩት የነበረው ቤት ውስጥ የነበሩት ተከራይ ግለሰቦችን ሳለማፈናቀል ሲባል ይህ ቤት በመንግስት እጅ ሆኖ እንዲቆይ መደረጉ አመልካች ኪራይ እየከፈሉ ሲኖሩበት የነበረውን የመንግስት ቤት አመልካችዋ ኪራይ ሳይከፍሉ እንዲኖሩበት በአመልካችዋና በመንግስት ፈቃድና ስምምነት የተደረገ ነው የሚመስለው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1840 መሠረት ተዋዋዮቹ አስቀድመው የመቻቻሉ ጉዳይ በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚፈፀም በመግለጽ የወሰኑበት ሆኖ ከተገኘ ደግሞ የውሉ መሰረዝ ወይም መፍረስ ጥያቄ ሲነሳ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1815 መሠረት ተዋዋዮቹ ወደነበሩበት የሚመለሱበት ሁኔታ ስለሚኖር የሥር ፍ/ቤት እነዚህን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ቤቱ የተያዘው በማካካሻነት መሆን ያለመሆኑን እንደዚሁም ቤቱ በማካካሻነት የተያዘው በአንድ ቤት ወይም በብዙ ቤቶች መሆን ያለመሆኑን ለማረጋገጥ እንዲቻል ቀበሌውን በጣልቃገብነት ክርክሩ ውስጥ አስገብቶና ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢውን መወሰን ሲገባው ይህን መንገድ ሳይከተል ማካካሻው ለጊዜው እንዲቆም የሚለውን የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ደብዳቤ ማካካሻነቱ ተሰርዟል እንደሚል አድርጐ በመተርጐም አመልካች ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት የሰው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና መሻር የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 57332 መጋቢት 13 ቀን 1998 ዓ.ም ወ/ሮ መዓዛ ገነት ዳኘ ክርክር ያስነሳውን ቤት ለኪራይ ቤቶች እንዲያስረክቡ እንደዚሁም ኪራይ ብር 13,500 (አስራ ሦስት ሺህ አምስት መቶ) እንዲከፍሉ በማለት የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 46871 ሚያዝያ 12 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡



2. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሥር ተከሳሽ የአሁኑ አመልካች የሆነውን ቤት በማካካሻነት በመያዝ ቤቱን እያከራየ ይገኛል የተባለው ቀበሌ በጣልቃ ገብነት ክርክሩ ውስጥ እንዲገባ በማድረግ፣ ማካካሻ የተደረገላቸው የአመልካችና የመንግስት ቤቶች የትኞቹ መሆናቸውን ለመለየት እንዲቻል ግራ ቀኙን አከራክሮ የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩ እንዲመለስለት ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 31601

የካቲት 11 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መሰሠ

ታፈሰ ይርጋ

መድህን ኪሮስ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ መዓዛ ይሕደጎ - ጠበቃ ግራዝማች አወቀ አእምሮ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች፡-** 1. አየለ ወልዴ ቀረበ፡፡

2. ጌታቸው ሃይለማርያም ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የኪራይ ውልን መነሻ በማድረግ የቀረበ የገንዘብ ክፍያ እና ቤት ልረከብ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በማኀበራዊ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበረችውም አመልካች ናት፡፡ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሠረተችው በውክልና የማስተዳድረውን ቤት በኪራይ ውል ይዘው እየተገለገሉበት ቢሆንም፤ ኪራዩን ግን ሊከፍሉ አልቻሉም፡፡ ስለዚህ የተጠራቀመውን ኪራይ ከፍለው ቤቱን ሊያስረክቡኝ ይገባል በማለት ነው፡፡ የማኀበራዊ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኝ ወገኖችን ካከራከረ በኋላ፣ ተከሣሾች የኪራዩን ገንዘብ ይክፈሉ፤ በኪራዩ መቀጠል ሁለቱ ወገኖች የማይስማሙ ከሆነም የሚፈለግባቸውን ኪራይ ከፍለው ቤቱን ለከሣሽ ያስረክቡ በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ክርክሩን የሰማ ሲሆን በመጨረሻም የማኀበራዊ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም በማለት ውሣኔውን ሽሯል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ይህንኑ አጽንቷል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡



በበኩላችንም አመልካች ሰኔ 27 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ክሱ በቀረበ ጊዜ የኪራይ ገንዘብ የተጠየቀበትን ቤት ግምት ጭምር መቅረብ ነበረበት፡፡ ግምቱ ቢቀርብም ኖሮ ጉዳዩ ክሱን ካየው የማኀበራዊ ፍ/ቤት ሥልጣን በላይ ይሆን ነበር በሚል የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ በቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሠረተችው በመሃከላቸው በተደረገው የኪራይ ውል መሠረት የሚፈለግባቸውን የኪራይ ገንዘብ እንዲከፍሏት እና በኪራይ ይዘውት የሚገኙትን ቤትም እንዲለቁላት ነው፡፡ በመዝገቡ እንደተገለጸውም በክሱ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ብር 4800 /አራት ሺህ ስምንት መቶ/ ነው፡፡ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 50 (1) እንደተመለከተው የቀበሌ ማኀበራዊ ፍ/ቤቶች ግምታቸው ከብር 5000 /አምስት ሺህ/ ያልበለጠ የንብረትና የገንዘብ ክርክሮችን የማየት /የመዳኘት/ ሥልጣን አላቸው፡፡ አመልካች ክሱን ለማህበራዊ ፍ/ቤት ያቀረበችው በዚህ መሠረት ሲሆን፣ ማኀበራዊ ፍ/ቤቱም ሥልጣን እንዳለው በመገንዘብ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የማኀበራዊ ፍ/ቤቱ ከስልጣኑ ውጪ ጉዳዩን አይቷል ለማለት አይቻልም፡፡ ተደጋግሞ እንደተገለጸው ለክሱ መነሻ የሆነው ምክንያት የኪራይ ገንዘቡ አለመከፈሉ ነው፡፡ አመልካች የከሰሰችው የኪራይ ውሉን መሠረት በማድረግ እስከሆነ ድረስ በቤቱ ላይ የንብረት ጥያቄ /የባለ ሃብትነት/ ያነሳች ይመስል በቤቱ ግምት መጠን ዳኝነት ከፍለሽ አልጠየቅሽም ወይም መጠየቅ ነበረብሽ የምትባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የተጠየቀው የኪራይ ገንዘብም በውሉ መሠረት ተሠልቶ ቀርቦ ሳለ ይግባኙን የሰማው ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ

ቁ. 227 (2)ን በመጥቀስ የዓመቱን ክፍያ በ20 ተባዝቶ መቅረብ ነበረበት የሚል ትችት መስጠቱ አግባብ አይደለም፡፡ እንደምንመለከተው የኪራይ ገንዘቡ የሚከፈለው በየወሩ ሲሆን በዚህ መሠረት ባለመከፈሉ ሂሣቡ ተሰልቶ ክሱ ቀርቧል፡፡ አመልካች ከዚህ ውጪ እንድታደርግ አትጠበቅም /በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 226 የተመለከተው ድንጋጌ ተሟልቷል/፡፡ ሲጠቃለል የቀበሌ ማኅበራዊ ፍ/ቤት ክሱን ያስተናገደው በሕጉ የተሰጠውን ሥልጣን መሠረት አድርጎ ነው፡፡ በመሆኑም ክሱን ለማየት ሥልጣን አልነበረውም ተብሎ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. አቤቱታ የቀረበበት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 01137 ሚያዝያ 25 ቀን 1998 ዓ.ም. የተሰጠው እና በከተማው አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03572 ሚያዝያ 3 ቀን 1999 ዓ.ም. በተሰጠው ትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በቂርቆስ ክ/ከተማ የቀበሌ 06 ማኅበራዊ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 2096 ሐምሌ 22 ቀን 1996 ዓ.ም. የተሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 31634

መጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

መድህን ኪሮስ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ

**ተጠሪዎች፡-** 1. የአቶ ወርቁ ደመሣ ሚስት ወ/ሮ ጽጌ በየነ በራሳቸው እና ሞግዚት በሆኑላቸው

ሀ. ትዝታ ወርቁ

ለ. ሚካኤል ወርቁ

ሐ. ቤተልሔም ወርቁ

2. ወ/ሪት ትዕግሥት ወርቁ
3. አቶ መላኩ ወርቁ
4. አቶ ዮሴፍ ወርቁ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ ጉዳይ መነሻ የሆነው የአሁኑ አመልካች በጥር 13 ቀን 1996 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ በወረዳ 7 ቀበሌ 29 የሚገኘው ቁጥር 550 /አምስት መቶ ሃምሳ ብር/ የሆነው ቤት አቶ ወርቁ ደመሳ ከኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ በወር በብር 500/አምስት መቶ/ ተከራይተዋል፡፡ ተከራይ ከሞቱ በኋላም ተከሣሾች የተከራዩን መብትና ግዴታ በመያዝና በመሸከም ተስማምተው በቤቱ መኖር ቀጥለዋል፡፡ ሆኖም ከሚያዝያ 1 ቀን 1987 ዓ.ም. እስከ ጥቅምት 30 ቀን 1996 ዓ.ም. የተወዘፈውን ኪራይ እንዲከፍሉ ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም ሊከፍሉ ባለመቻላቸው የቤቱን ውዝፍ ኪራይ ብር

51,500፣ /ሃምሳ አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/ ወለድ ብር 32,257.45 /ሠላሳ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ሰባት ብር ከ አርባ አምስት/ እና ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 770 /ሰባት መቶ ሰባ/ በድምሩ ብር 84,527.45 /ሰማኒያ አራት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ሰባት ከአርባ አምስት/ በመክፈል ቤቱን ሊያስረክቡኝ ይገባል በማለት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የመሰረተው ክስ ነው፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን በማከራከር ከሚያዝያ 1 ቀን 1987 ዓ.ም. እስከ መስከረም 1 ቀን 1994 ዓ.ም. ድረስ መከፈል የነበረበት የቤት ኪራይ ለማስከፈል ክሱ የቀረበው 2 ዓመት ካለፈ በኋላ በመሆኑ ኪራዩ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/መ/ መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል፡፡ ከመስከረም 1 ቀን 1994 ዓ.ም. በኋላ መከፈል የነበረበት ኪራይ ደግሞ ያለመከፈሉን ተከሳሾች ስላመኑ መክፈል አለባቸው፡፡ ወለዱን በተመለከተ ደግሞ ኪራዩ ሊከፈል ያልቻለው ተከሣሾች እንክፈል ሲሉ ከሣሽ ውዝፉን ካልከፈላችሁ ሌላውን አልቀበልም በማለቱ ምክንያት መሆኑን ስለተረጋገጠ ተከሣሾች ወለዱን መክፈል አይገባቸውም፡፡ በመሆኑም ተከሣሾች ከመስከረም 1994 ዓ.ም. ጀምሮ ውሣኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ የቤት ኪራይ ብር 22899/ሀያ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና ዘጠኝ/ ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 770/ሰባት መቶ ሰባ/ በድምሩ ብር 23,669.00/ሀያ ሦስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ዘጠኝ/ ለከሣሽ እንዲከፍሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተከሣሾች ያልፈፀሙት ግዴታ አለመኖሩ ባለመረጋገጡ ቤቱን ለከሣሽ ሊያስረክቡ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡

ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ፍርዱ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን በመሠረዝ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

አመልካች በሁለቱም ፍ/ቤቶች ውሣኔ ቅር በመሰኘቱ ምክንያት ለዚህ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው አቤቱታ የጠቀሳቸው ቅሬታዎችም አቶ ወርቁ ዳመሣ ከመስከረም 1985 ዓ.ም. እስከ መጋቢት 30 ቀን 1987 ዓ.ም. ያለውን የቤት ኪራይ እንዲከፍሉ ተከሰው ተወስኖባቸው አፈፃፀሙን እየተከታተልን እያለን በሞት ከዚህ ዓለም ተለይተዋል፡፡ የቤቱን ኪራይ



አስመልክቶ መብትና ግዴታ ያለው ሰው ካለ ማንነቱን እያጠያየቅን ቆይተናል፡፡ ኪራዩን በወቅቱ ለመሰበስብ የልቻልነውም በዚሁ ከዓቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ኪራዩ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/መ/ መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል ያሉት አግባብነት የለውም፡፡ መልስ ሰጭዎች ውዝፉን ሳይከፍሉ ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ ኪዩን እንክፈሉ ሲሉ መጀመሪያ ውዝፉን ካልከፈላችሁ የአሁኑን ብቻ አንቀበልም ማለታችንም በአግባቡ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች መልስ ሰጭዎች ውዝፉን መክፈል የለባቸውም፡፡ ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ ያለውን ኪራይም ያለወለድ መክፈል የለባቸውም፡፡ ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ ያለውን ኪራይም ያወለድ መክፈል አለባቸው፡፡ ያልተወጡት ግዴታም ስለሌለ ቤቱን ሊያስረክቡ አይገባም በማለት የሰጡት ውሣኔ ተቀባይነት የለውም፡፡ ይህ ውሣኔያቸው ልክ እንደክሳችን እንዲወስንልን የሚሉ ናቸው፡፡

መልስ ሰጭዎችም ሕዳር 30 ቀን 2000 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት መልስ ከሚያዝያ 1 ቀን 1987 ዓ.ም. እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1993 ዓ.ም. ድረስ ያለው የቤት ኪራይ በወቅቱ በአቶ ወርቁ ደመሣ ተከፍሏል፡፡ አልተከፈለም ቢባልም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/መ/ መሠረት እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው፡፡ አመልካች ኪራዩን በወቅቱ እንዳንሰባሰብ የሚቹን መብትና ግዴታ ማን እንደተሸከመ ባለማወቃችን ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት ነው ያለው በስር ፍ/ቤት የተነሣ ክርክር አይደለም፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ፍርድ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም፡፡ የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ውሣኔውን ማጽናቱ በአግባቡ ነው፡፡ አመልካች የኪራይ ውሉ እንዲቋረጥ የጠየቀው የውል ግዴታቸውን በውሉ አንቀጽ 4 መሠረት አልተወጡም ያለውም ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም ላወጣው ማስጠንቀቂያ ኪራይ ለመክፈል ፈቃደኞች መሆናችንን ገልፀናልና፡፡ በመሆኑም የውሉ አንቀጽ 4/2/ለ/ በኛው ላይ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔም የሕግ ስህተት የሌለው

በመሆኑ ውሣኔያቸው ፀድቆ እንድንሰናበት ይወሰንልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም ታህሣሥ 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው የመልስ መልስ ክርክሩን ለማጠናከር ሞክሯል፡፡

በበኩላችን ደግሞ ተጠሪዎች ከሚያዝያ 1 ቀን 1987 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1993 ዓ.ም. ድረስ ያለውን ውዝፍ የቤት ኪራይ መክፈል አለባቸው ወይስ የለባቸውም? ከመስከረም 1994 ዓ.ም. ጀምሮ ላልከፈሉት የቤት ኪራይስ ወለድ መክፈል አለባቸው ወይስ የለባቸውም? ቤቱንስ ለአመልካች መመለስ ይገባቸዋል ወይስ አይገባቸውም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ መዝገቡን መርምረነዋል፡፡

መዝገቡን እንደረመመርነውም አመልካች ተከራዩ በሞት ከዚህ ዓለም ከተለዩ በኋላ ኪራዩን መሰብሰብ ወይም ደግሞ ቤቱን መረከብ ሲኖርበት የሟች ወራሾች ቤቱን እየተጠቀሙበት መሆኑን እያወቀ ኪራዩን ሳይሰበስብ ከሚያዝያ 1987 ዓ.ም. እስከ ነሐሴ 1993 ዓ.ም. መቆየቱ በማናቸውም መስፈርት ከአቅም በላይ ነው ሊባል የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ነጥብ ላይ የሥር ፍ/ቤቶች ኪራዩ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/መ/ መሠረት እንደተከፈለ ተደርጎ መቆጠር አለበት በማለት መወሰናቸው በግባቡ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ከ1994 ዓ.ም. በኋላ ያለውን የኪራይ ክፍያን ስንመለከትም ተጠሪዎች ኪራዩን እንክፈል በማለት እየደጋገሙ ሲጠይቁት ከሚያዝያ 1 ቀን 1987 ዓ.ም. ጀምሮ ያለውን ውዝፍ ኪራይ ካልከፈላችሁ በስተቀር ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ ያለውን የቤት ኪራይ አልቀበልም እያለ ሳይቀበል ቀርቶ ሲያበቃ አመልካች በዚሁ ራሱ ሳይቀበል ባቆየው ክፍያ ወለድ መጠየቁ አግባብነት ስለሌለው አመልካቹ ወለድን አስመልክቶ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡



የመጨረሻውን ጭብጥ በተመለከተ ደግሞ ተጠሪዎቹ አቶ ወርቁ ዳመሣ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩበት ጊዜ ጀምሮ በየወሩ የቤቱን ኪራይ የመክፈል ግዴታ እያለባቸው ይህን ግዴታቸውን ያለመፈፀማቸውን ይልቁንም ኪራዩን እንዲከፈል መጠየቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ አመልካች ሳይጠይቅ ጠይቆ ፈቃደኝነት ካላገኘም ክስ ሳይመሰርት ሁለት ዓመት ያለፈ በመሆኑ ከ1987 ዓ.ም. እስከ 1993 ዓ.ም. የነበረው የቤት ኪራይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/መ/ መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል ማለታቸው በወቅቱ ማለት ሁለተ ዓመት ሳያልፍ እኛን በመክሰስ ገንዘብህን መሰብሰብ ነበረብህ፡፡ ይህን ባለማድረግህ መንግሥት የጣለብህን ግዴታ አልተወጣህም የሚል ትርጉም የሚሰጠው እንጂ ተጠሪዎች ኪራይ የመክፈል ግዴታቸውን ተወጥተዋል ማለት አይደለም፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024 /መ/ ዕዳው እንዲከፈል መጠየቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ሳይከፈል የቀረ ገንዘብ እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት የተደነገገው ደግሞ ባለገንዘቡ ሁለት ዓመት ሳይሞላው ክስም መስርቶ ቢሆን ገንዘቡን በወቅቱ ተግቶ እንዲሰበስብ ለማድረግ እና ሁለት ዓመት ካለፈው በኋላ ከሶም ቢሆን ገንዘቡን ለመሰብሰብ እንደማይችል ለማስገንዘብ እንጂ ባለዕዳው ሁለት ዓመት እስከሚያልፍ ዕዳውን ሳይከፈል ቢቆይ የመክፈል ግዴታውን እንደተወጣ ለመቁጠር ወይም ለማረጋገጥ አይደለም፡፡ በተጨማሪ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ኪራይ ያልከፈሉትን ተከራዮች ኪራዩን በክስ እንዲከፍሉ ከመገደድ የሚያድናቸው እንጂ ኪራዩን የመክፈል ግዴታቸውን እንደተወጡ የማያረጋግጥላቸው እንዳልሆነ ለመረዳት ችለናል፡፡

ይህን መሠረት በማድረግ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ ስንመለከተው ከ1987 ዓ.ም. እስከ 1993 ዓ.ም. የነበረው የቤት ኪራይ መጠየቅ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ሲታይ ሁለት ዓመት ያለፈበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/መ/ መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል፡፡ ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ መከፈል የነበረበት የቤት ኪራይም በወቅቱ ሳይከፈል የቀረው

አመልካች ክፍያውን አልቀበልም በማለቱ ምክንያት በመሆኑ ወለድ ሊጠየቅበት አይገባም በማለት መወሰናቸው በአግባቡ ነው፡፡ ተጠሪዎች ያልተወጡት ግዴታ የለም በማለት ቤቱን ለአመልካች ማስረከብ የለባቸውም በማለት የሰጡት ውሣኔ ደግሞ ተጠሪዎቹ በወቅቱ ያልተወጡትን በየወሩ ኪራይ የመክፈል ግዴታ እንደተወጡ የሚያረጋግጥ እና በውላቸው አንቀጽ 4 ላይ የተደነገገውን ግዴታ ያላገናዘበ፣ እንደዚሁም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024 መንፈስንም የሳተ በመሆኑ ውሣኔያቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 36746 ሐምሌ 24 ቀን 1998 ዓም የሰጠው ፍርድና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 49555 ሚያዝያ 15 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ የሚፀናና የሚሻር ነጥብ ያለበት በመሆኑ

ሀ/ ፍርድ ቤቶቹ የቤቱን ኪራይ የተመለከተውን ክፍያ መልስ ሰጭዎች ለአመልካች ብር 23,669.00 (ሃያ ሦስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ዘጠኝ) እንዲከፍሉ በማለት የወሰኑትን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንተናል፡፡

ለ/ በሌላ በኩል ደግሞ ፍ/ቤቶቹ መልስ ሰጪዎች ቤቱን ለአመልካች ማስረከብ የለባቸውም በማለት የሰጡትን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2. መልስ ሰጭዎች በፌ/መ/ደ/ፍቤት በዚህ ጉዳይ ውሣኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር የቤቱን ኪራይና ተጨማሪ እሴት ታክሱን በድምሩ ብር 23,669.00 (ሃያ ሦስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ዘጠኝ ) ለአመልካች ይክፈሉ ይፃፍ፡፡



3. መልስ ሰጪዎች በክሱ የተጠቀሰውን ቤት ለአመልካች እንዲያስረክቡ ቤቱን እስካስረከቡበት ቀን ድረስም ኪራዩን ይክፈሉ ይፃፍ፡፡

ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 31917

ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ነገረፈጅ ድጋፌ ለገሰ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ለምለም ገ/ትንሳኤ በሌሉበት ይታያል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 48841 ታህሣስ 4 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 52647 ሰኔ 12 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡ የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ ተጠሪ የንግድ ድርጅት ከሌላ ሰው ስትገዛ፣ ንግድ ይካሄድበት የነበረውን ቤት የመከራየት መብቷ ተጠብቆላታል፤ ቤቱ የአመልካች በመሆኑ በፊት የነበረው የኪራይ ተመን ተስተካክሎ ብር 2009 /ሁለት ሺ ዘጠኝ/ የተተመነ ቢሆንም ኪራዩ በዛብኝ ብላ በማመልከቷ ብር 1448 /አንድ ሺ አራት መቶ አርባ ስምንት/ እንደተደረገባት አመልካች በማመልከቻው ገልጿል፡፡ ሆኖም ተከሳሽ ወይም ተጠሪ በቀድሞው ኪራይ ብር 125/አንድ መቶ ሃያ አምስት/ ብቻ የከፈለች በመሆኗ ከታህሣስ ወር 1993 ዓ.ም እስከ ግንቦት 2 ቀን 1996 ዓ.ም ያለው የቤት ኪራይ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ 57,614.20 (ሃምሣ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ አስራ አራት ከሐያ) ከወጭና ኪሣራ ጋር



እንድትከፍል ይወሰንልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ አመልካች ይህንን ክሱን የሚያስረዱ የጽሑፍ ማስረጃዎችንም አቅርቧል፡፡

ተጠሪ የአመልካች ክስና ማስረጃ ከፍርድ ቤቱ መጥሪያ ጋር ደርሷት መልሷን ይዛ እንድትቀርብ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ቀርባ ባለመከራከሯ ጉዳዩን ተጠሪ በሌለችበት ታይቷል፡፡ ጉዳዩን ተጠሪ በሌለችበት ያየው የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ከሳሽ (አመልካች) በቀድሞ የኪራይ ተመን ከተከሳሽ (ተጠሪ) ኪራይ ሲቀበል ከቆየ በኋላ እንደገና አዲስ ተመን አውጥቻለሁ ይከፈለኝ በማለት መጠየቅ ስለማይችል ተከሳሽ የሁለት ወር ከሁለት ቀን ሂሳብ ብቻ በአዲሱ የኪራይ ተመን መሠረት ትከፍላለች በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሕግ እና የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ አመልካች ይኸ ውሣኔ መሠረታዊ ስህተት አለበት፤ ተጠሪ በአዲሱ የኪራይ ዋጋ ካልተስማማች ቤቱን ለአከራዩ ማስረከብ ነበረባት፤ ይህን አላደረገችም፤ እንደዚሁም በተመሣሣይ ጉዳይ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 23067 የሕግ ትርጉም የሰጠ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤቶች ይህንን በመተላለፍ የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ባለመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በአድራሻዋ ባለመገኘቷ በጋዜጣ ጥሪ የተደረገላት ሲሆን ያልቀረበች በመሆኑ የሰበሩ ክርክር በሌለችበት እንዲታይ ብይን ተሰጥቷል፡፡

በሥር እና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ የድርጅት ቤት ኪራይ ሲተመን ሙሉ እውቀት የነበራት መሆኑንና የኪራዩ መጠን በዝቶብኛል ብላ በማመልከቷ ኪራዩ ከሁለት ሺ ዘጠኝ ብር ወደ አንድ ሺ አራት መቶ አርባ ስምንት ብር ዝቅ እንዲል ተወስኖላታል፡፡ ተጠሪ ይህንን ለማስረዳት በአመልካች በኩል የቀረበውን ማስረጃ ቀርባ አላስተባበለችም፡፡

ተጠሪ ባቀረበችው አቤቱታ መነሻ ተሻሽሎ በተወሰነው የቤቱ ኪራይ የማትስማማ ከሆነ፣ ቤቱን ለአከራዩ በማስረከብ ከአመልካች ጋር የነበረው የአከራይ ተከራይ ውል ማቋረጥ ነበረባት፡፡

ተጠሪ የንግድ ድርጅቱን ስትገዛ የንግድ ድርጅቱ ያለበትን ቤት የመከራየት መብት የሚተላለፍላት እንደሆነ በንግድ ሕጉ ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የመከራየት መብት ስለተላለፈላት ከአመልካች ጋር የኪራይ ውል አላት፡፡ ይኸም በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው የኪራይ ውል ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ነው፡፡ ይህ ከሆነ አከራዩ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2966 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የኪራዩን ዋጋ እንደጨመረ አስታውቋል፡፡ ተጠሪ የታደሰው የኪራይ ውል በዝቷል በማለት አመልክታ ተሻሽሎላታል፡፡ ተጠሪ በተሻሻለው የኪራይ ውል ዋጋ ከደረሳት በኂላ በቤቱ መኖር ከቀጠለች በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2968 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ውሉ እንደታደሰ የሚቆጠር ይሆናል፡፡

ይህ ከሆነ ተጠሪ በተሻሻለው የኪራይ ውል መሠረት የመክፈል ግዴታ አለባት፡፡ ይህ ሆኖ እያለ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ በተሻሻለው የኪራይ ዋጋ መሠረት የመክፈል ግዴታ የለባትም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ስለሆነ ተጠሪ በተሻሻለው የቤት ኪራይ ዋጋ መሠረት 15% ተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር የመክፈል ግዴታ አለባት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 48841 ታህሣሥ 4 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 52647 ሰኔ 12 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው በመሆኑ ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ አመልካች ክስ ያቀረበበትን የኪራይ ሂሳብ ብር 57,614.20 /ሐምሣ ሰባት ሺ ስድስት መቶ አስራ አራት ከሃያ / 18% ተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር መክፈል ይገባታል ብለን ወስነናል፡፡
3. ወጭና ኪሣራ አመልካች ራሱን ይቻል

ይህ ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 32521

ሚያዝያ 7 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

ታፈስ ይርጋ

መድኅን ኪሮስ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ አብርሃም አጥላባቸው

ተጠሪ፡- እነ ዳባ ኢጃቶ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ባቀረበው ክስ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 24 ቀበሌ 15 ክልል የሚገኘውንና ቁጥር 802/1-2-803/ 1-2 የሆነውን ቤት ለቢሮ አገልግሎት በወር ብር 1,800 (አንድ ሺ ስምንት መቶ) ለኦሮሞ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት አከራይቶ የነበረ ሲሆን ተከራዩ ቢሮውን ወደ ሌላ ቦታ በመቀየሩ ከታህሳስ 1988 ዓ.ም. ጀምሮ በድርጅቱ ውስጥ የነበሩ አባሎች ወደ ኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን ስለተዛወሩ በቤቱ ውስጥ የነበሩት እዚያው እንዲቆዩ ስለፈለገ የኪራይ ውሉ ወደ ኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን ተዛውሮ በቢሮነት እንድንጠቀምበት ይፈቀድልን በማለት የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን በደብዳቤ ጠይቆ ሲከታተል ከቆየ በኋላ ውል ሳይፈጽም አባሎቹ በቤቱ እንዲጠቀሙ አድርጓል፡፡ በዚህ መሠረት የአሁን ተከሣሾች የኪራይ ውል ሳይኖራቸው ኪራይም ሳይከፍሉ ያለከሳሽ ፈቃድ ከጥር 1 ቀን 1998 ዓ.ም. ጀምሮ በሕገወጥ መንገድ እየተጠቀሙበት ስለሚገኝ በአጠቃላይ ያለውን ውዝፍ ኪራይ ብር 183,600.00 (አንድ መቶ ሰማኒያ ሦስት ሺህ ስድስት መቶ) ወለድ ብር 113,511.35 (አንድ መቶ አሥራ ሦስት ሺህ አምስት



መቶ አሥራ አንድ ከሰላሳ) በድምሩ ብር 297,111.35 (ሁለት መቶ ዘጠና ሰባት ሺህ አንድ መቶ አሥራ አንድ ከሰላሳ አምስት) ከፍለው ቤቱን ለከሣሽ እንዲያስረክቡ ይወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡

የከሣሽ ክስና ማስረጃ ለተከሳሾች ደርሶ መልስ እንዲሰጡ በታዘዘው መሠረት የተወሰኑት ተከሣሾች ቀርበው መልስ ሲሰጡ የተወሰኑት ደግሞ በአግባቡ ተጠርተው ባለመቅረባቸው በሌሉበት ጉዳዩ እንዲታይ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሠጥቷል፡፡ የቀረቡት ተከሣሾች በሰጡት መልስ ክስ የቀረበበት ቤት የከሣሽ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ ካለመኖሩም በላይ ከሣሽም አስተዳድሮት አያውቅም፡፡ ከሣሽ ከእኛ ጋር ውል ስላልፈጸመ በማናውቀው ውል መነሻነት የኪራይ ገንዘብ ልንጠየቅ አይገባም በማለት ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ለክሱ መሠረት የሆነውን ውል ከሳሽ ያደረገው ከኦሮሞ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት ጋር ሲሆን በዚህ ውል መሠረትም ተከሣሾች በቤቱ ውስጥ ሊገቡ መቻላቸውን ከሣሽ በክሱ ከመግለጹም በላይ በውሉ መሠረት ኪራይ ሊከፍል የተስማሙና ሲከፍል የቆየው ይሄው የኦሮሞ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት እንጂ ተከሣሾች አይደሉም ካለ በኋላ ውሉ ሳይታደስ ቀርቶ ቤቱ ያለ አግባብ ተይዞብኛልና ይለቀቅልኝ ወይም ውዝፍ ኪራይ ይከፈለኝ በማለት ሊጠይቅ የሚችለው በውል የተከራየውን ወገን እንጂ ተከሣሾችን አይደለም፡፡ እንደዚሁም ውሉ ስላለቀ ሊያስረክበን ይገባል ከሆነም ውሉን ለማፍረስ ውል የገባውን ወገን መክሰስ እንጂ ውሉ ባልፈረሰበት ሁኔታ ቤቱ እንዲለቀቅለት ያቀረበው ጥያቄ በአግባቡ አይደለም በማለት ክሱን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ከሣሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት

ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም በበኩሉ አቤቱታው ለሰበር ይቀርባል ብሎ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ ተጠሪዎች ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት ለአመልካች ሊያስረክቡ ይገባል ወይንስ አይገባም? ኪራይስ ሊከፍሉ ይገባልን? የሚለው በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ የሰበር አቤቱታው ተመርምሯል፡፡

ተጠሪዎች በሥር ፍ/ቤትም ሆነ በዚህ ችሎት ክርክር ሲደረግ አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት ባለንብረት ስላልሆነ ቤቱ ይለቀቅልኝም ሆነ ኪራይ ይከፈለኝ ማለት አይችልም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ሆኖም ግን አመልካች ክስ ያቀረበው ባለቤትነትን በመፋለም ረገድ /Petitory action/ ስላልሆነ የቤቱ ባለቤት ስለመሆኑ ማስረዳት የሚጠበቅበት አይሆንም፡፡ አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት ለኦሮሞ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት አከራይቶት እንደነበር በአስረጂነት ባቀረበው የኪራይ ውል የተረጋገጠ ሲሆን ተጠሪዎችም ከአመልካች ጋር የኪራይ ውል ሳይኖራቸው በቤቱ ውስጥ እንደሚኖሩ በአመልካች ማስረጃ ከመረጋገጡም በላይ በተጠሪዎችም አልተካደም፡፡

ከሣሽ የሆነ ወገን የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለማስለቀቅና ለመረከብ ክስ ባቀረበ ጊዜ በማናቸውም ምክንያትና ሁኔታ በዚሁ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ሠፍረው የሚገኙትን ሁሉ አጣምሮ መክሰስ እንደሚችል ተከሣሾችን አጣምሮ ስለመክሰስ /Joinder of defendants/ በሚደነግገው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 36/4/ ላይ ተመልክቷል፡፡

ለመብትም ሆነ ለግዴታ ምንጭ ውል ወይንም ሕግ ሲሆን ተጠሪዎች ግን ከውልም ሆነ ከሕግ የመነጨ መብት ሳይኖራቸው ለክርክሩ



ምክንያት በሆነው ቤት ላይ ያለአግባብ በመበልጸግ ላይ እንደሚገኙ መገንዘብ አያዳግትም፡፡

በሌላ በኩልም ጉዳዩን በመጀመሪያ የዳኝነት ሥልጣኑ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ለክሱ መሠረት በሆነው ቤት ላይ የውል ግንኙነት የተመሠረተው በአመልካችና በኦሮሞ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት መካከል እንጂ ከተጠሪዎች ጋር ስላልሆነ ቤት ይለቀቅልኝም ሆነ ኪራይ ይከፈለኝ ተብሎ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡ ይሁንና በአመልካችና በተጠቀሰው የኦሮሞ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት መካከል በዚሁ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ የኪራይ ውል እንደነበር የተረጋገጠ ቢሆንም ተከራዩ ቤቱን ለቆ ሄዷል ከተባለ የኪራይ ውሉ መቋረጡን የሚያስገነዝብ ከመሆኑም በላይ አመልካችም በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሠረተው ውሉን መሠረት በማድረግ ሳይሆን አላግባብ በልጽገዋል በማለት ስለሆነ ይህንኑ የተቋረጠ ውል መሠረት አድርጎ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ ውሣኔ በማጽናት የሰጠው ትዕዛዝ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 32793 ሚያዝያ 5 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 25411 ግንቦት 14 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ለክሱ ምክንያት በሆነው ቤት ከውልም ይሁን ከሕግ የመነጨ መብት ሳይኖራቸው እየኖሩበት ያለአግባብ የበለጸጉ ስለሆነና የበለጸጉበትም መጠን ቤቱ አስቀድሞ ሲከራይበት በነበረው ልክ ስለሆነ በዚሁ መሠረት አመልካች አስልቶ የጠየቀውን ብር

183,600.00 /አንድ መቶ ሰማንያ ሶስት ሺህ ስድስት መቶ/ ተጠሪዎች ለአመልካች በመክፈል ቤቱን ሊያስረክቡ ይገባል ተብሎ ተወስኗል፡፡

የወለድ ክፍያ ጥያቄውን በተመለከተ በመካከላቸው የኪራይ ውል ስለሌለ ተጠሪዎች ሊከፍሉ አይገባም ብለናል፡፡

3. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰበር መ/ቁ 34456

ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ብርሃኑ አመነው

መድሕን ኪሮስ

ፀጋዬ አስማማው

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ - ነገረ ፈጅ ቀርቧል፡፡

**መ/ሰጪ፡-** ወ/ት ደብሪቱ ወልደሃና - ጠበቃዋ ቀርቧል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገን የቤት ኪራይ ውል የሚመለከት ነው፡፡

ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው የአሁን አመልካች በስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረበው አቤቱታ በቀድሞ ወረዳ 21 ቀበሌ 01 ክልል ውስጥ የሚገኘውንና የቤት ቁጥር 288/1-5 የሆነውን ቤት ለመኖሪያ አገልግሎት በወር ብር 22 (ሃያ ሁለት ብር) የኪራይ ዋጋ ለአንድ ዓመት ጊዜ በ1977 ዓ.ም ለመልስ ሰጪ አከራይቶ የነበረ መሆኑን በመግለጽ መልስ ሰጪ በቤቱ ከአንድ ዓመት በላይ የተገለገለች በመሆኑ የኪራይ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚቆጠር በመሆኑ ውሉ አመልካች ለመልስ ሰጪ በሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ፈርሷል፡፡ ስለሆነም መልስ ሰጪ ቤቱን እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ ሲል በመጠየቁ ነው፡፡

ጉዳዮን በቅድሚያ ያስተናገደው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መልስ ሰጪ በኪራይ ምክንያት የያዘውን መኖሪያ ቤት ለአመልካች ሊያስረክብ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚል ጭብጥ መሥርቶ የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኂላ ምንም እንኳን የተደረገው የኪራይ ውል ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ

የሚቆጠር ቢሆንም እና የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2966 ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ማስጠንቀቂያ በመስጠት እንዲያበቃ ለማድረግ እንደሚቻል ቢደነግግም ግራ ቀኙ ከዚህ በፊት ለተወሰነ ጊዜ (ለአንድ አመት) ባደረጉት የኪራይ ውል ላይ ውሉ የሚፈርስበትን (የሚበቃበትን) ሁኔታዎች የዘረዘሩ በመሆኑና ከእነዚህ ዝርዝር ሁኔታዎች ውስጥ መ/ሰጪ አንዱንም ያላፈረሰች በመሆኑ ወይም ደግሞ በውሉ እንደተገለፀው ቤቱ ለመንግሥት አገልግሎት ስለመፈለጉ እና ምትክ ቤት ለመስጠት የተዘጋጀ ስለመሆኑ አመልካች ያላስረዳ በመሆኑ አመልካች ለመልስ ሰጪ ማስጠንቀቂያ ሰጥቼ ውሉን ያቋረጥኩ ስለሆነ ቤቱን ልረከብ ይገባል በማለት ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኘው የአሁኑ አመልካች የይግባኝ አቤቱታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ጉዳዮን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የሌለበት ነው በማለት የአመልካችን የይግባኝ አቤቱታ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍ/ቤቶች በውሳኔያቸው ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የፈፀሙ በመሆናቸው እንዲታረም በሚል ነው፡፡ ይህ የሰበር ችሎትም የስር ፍ/ቤት አመልካች ከመልስ ሰጪ ጋር ያደረገውን የኪራይ ውል አመልካች ለመልስ ሰጪ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ብቻ ማቋረጥ አይችልም፤ ውሉ ሊቋረጥ የሚችለው ቤቱ ለመንግሥት ሥራ ሲፈለግ ብቻ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ሲባል አቤቱታውን ለሰበር ችሎት በማስቀረብ የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር መርምሯል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የአሁኑ መልስ ሰጪ ለክርክሩ መንስኤ የሆነውን የመኖሪያ ቤት ለአመልካች ሊያስረክቡ አይገባም የሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ የቻለው በዋናነት በግራ ቀኙ መካከል ከዚህ ቀደም የተደረገ የቤት ኪራይ ውል የነበረ በመሆኑና በዚህ ውል ላይ ተከራካሪዎችቹ በመካከላቸው ያደረጉት የኪራይ ውል ቀሪ ሊሆን የሚችልባቸውን ምክንያቶች



የዘረዘሩ መሆኑንና ከእነዚህ የውል ማፍረሻ ምክንያቶች ውስጥ መልስ ሰጪ አንዱንም ያላፈረሱ መሆኑን ከግምት በማስገባት ነው፡፡ ከዚህም አልፎ ግራ ቀኙ ባደረጉት ውል መሠረት ቤቱ ለመንግሥት አገልግሎት የተፈለገ ከሆነ እንኳን አመልካች ምትክ ቤት በመስጠት ብቻ መልስ ሰጪን ከቤቱ ሊያስለቅቅ እንደሚችል የተስማሙ በመሆኑ የአመልካች ቤቱን ልረከብ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በሚል ነው፡፡

ይሁን እንጂ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2966 ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገን የኪራይ ውል ለማብቃት አከራዩ ተከራዩን ለማስታወቅ ወይም ተከራዩ አከራዩን ለማስታወቅ ይችላል በማለት በግልጽ ደንግጓል፡፡ በዚህ የሕግ ድንጋጌ መሠረትም በተዋዋዮች መካከል የተደረገው የኪራይ ውል የጊዜ ገደብ ያልተበጀለት በሆነ ጊዜ ከተዋዋዮቹ አንደኛው ወገን ውሉ እንዲያበቃ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉ ፍፃሜ እንዲያገኝ ለማድረግ እንደሚችሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይሁንና የስር ፍ/ቤት ግራ ቀኙ ቀደም ሲል ለተወሰነ ጊዜ ያደረጉትን የኪራይ ውል መሠረት በማድረግ በውሉ የተጠቀሰው የኪራይ ጊዜ ካለቀ በኋላና የውሉ አይነት ወደ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ከተቀየረ በኋላ መልስ ሰጪ ቀደም ሲል ለተወሰነ ጊዜ በተደረገው ውል መሠረት ግዴታቸውን የፈፀሙ (ያላፈረሱ) በመሆኑ አመልካች የኪራይ ውሉን ማስጠንቀቂያ በመስጠት በቻ ለማፍረስ (ለማብቃት) አይችልም፡፡ ውሉ ሊቋረጥ የሚችልበት ብቸኛ ምክንያት ቤቱ ለመንግሥስት ሥራ ሲፈለግ ነው፡፡ ይህም ቢሆን አመልካች ለመልስ ሰጪ ምትክ ቤት ሰጥቶ ነው ውሉን ለማቋረጥ የሚችለው በመሆኑም አመልካች ማስታወቂያ ሰጥቼ ውሉን ያቋረጥኩ ስለሆነ ቤቱን ልረከብ ይገባል በሚል ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የሕጉን መንፈስና ዓላማ ሙሉ በሙሉ ያላገናዘበ በመሆኑ መታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ጉዳዮን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ቢሆን የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ በሚገባ ሳይመረምር እንዳለ ተቀብሎ ማጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**ት እ ዛ ዝ**

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 11851 ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 55271 በጥቅምት 7 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. በአመልካችና በመ/ሰጪ መካከል የተደረገው የኪራይ ውል የፈረሰ በመሆኑ መ/ሰጪ በኪራይ ውሉ ምክንያት የያዙትን መኖሪያ ቤት ለአመልካች እንዲያስረክቡ ተወስኗል፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



# የሽያጭ ውል

የሰ/መ/ቁ. 16455

ኀዳር 26 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች ፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ጌታቸው ምህረቱ

አሠግድ ጋሻው

ሒሩት መለሠ

አብዱራሂም አህመድ

**አመልካች፡-** ወ/ት አዜብ ሽፈራው - አልቀረቡም፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ታየች ንጉሴ - ቀረቡ፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ከሣሽ ሲሆኑ አመልካች ደግሞ 1ኛ ተከሣሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት ክስም በወረዳ 21 ቀበሌ 24 ውስጥ የሚገኘውን ቁጥር 646 የሆነውን ቤት ለአሁኗ አመልካች የሰጧት ሲሆን ቁጥር 643 እና 644 የሆኑትን ቤቶች ግን አመልካች አጠቃልዬ እገዛቸዋለሁ በማለት ተረክበው ለሥር 2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች በማከራየት እየተጠቀሙ በመሆኑ ቤቶቹን ለቀው እንዲያስረክቡኝ የቤቶቹን ኪራይም እንዲከፍሉ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኗ አመልካችም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና ለፍሬ ጉዳዩም መልስ የሰጡ ሲሆን በመልሣቸው ላይ መጋቢት 2 ቀን 1985 የተደረገው የሽያጭ ውል እነዚህን ቤቶችንም የሚጠቀልል ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ካደረገ በኂላ በመ/ቁ. 2793/88 ተጠሪ የሽያጩ ውል እንዲፈርስ ባቀረቡት ክስ ፍ/ቤቱ የቤ/ቁ 643 እና 644 በተመለከተ የቀረበው ክስ ዳኝነት ያልተከፈለባቸው እና በሽያጭ ውሉ ያልተካተቱ በመሆኑ በሌላ መዝገብ በመክሰስ የመጠየቅ መብታቸው የተጠበቀ ነው በማለትና የሽያጭ ውሉ ግን ሊፈርስ እንደማይገባ በሰጠው ውሣኔ ላይ ቤቶቹ



በሽያጩ ውል ላይ እንዳልተካተቱ ከተረጋገጠ አመልካች ቤቶቹን አስረክበው ኪራዩንም እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ይህንኑ ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ቀደም ሲል በቀረበው ክስ አሁን ክርክር የተነሣባቸውን ቤቶች በተመለከተ ተጠሪ የዳኝነት ከፍለው እንዲጠይቁ በተሠጠው ውሣኔ ትችት ላይ ቤቶቹ በሽያጭ ውሉ አለመካተታቸው መገለፁን ምክንያት በማድረግ ብቻ አመልካች ቤቱን እንዲለቁ የወሰነው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረጉ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ መዝገቡንም እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው የአሁን ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ክስ የመሠረቱት አመልካች ቁጥር 646 የሆነውን ቤት ሲገዙ ክርክር የተነሣባቸውን ቤቶችም አጠቃለው እገዛለሁ ብለው የተረከቡ በመሆኑ እነዚህን ቤቶች እንዲመልሱላቸው ነው፡፡ አመልካች ደግሞ መጋቢት 2 ቀን 1985 ዓ.ም. የተደረገው የሽያጭ ውል እነዚህን ቤቶች የሚያጠቃልል መሆኑን በመግለጽ ሊለቁ እንደማይገባ ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ የቤ/ቁ 646ን የሸጡ መሆኑን አልካዱም፡፡ እንደውም ይህ የሽያጭ ውል እንዲፈርስላቸው በመ/ቁ. 2793/88 ክስ አቅርበው ውሉ ሊፈርስ እንደማይገባ ውሣኔ ያገኘ መሆኑን በክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ አሁን በዚህ መዝገብ የተነሣው ክርክር ይህ የሽያጭ ውል ክርክር የተነሣባቸውን የቤት ቁጥር 643 እና 644ን ያጠቃልላል አያጠቃልልም? የሚለው ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የወሰነው የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ክስ በቀረበበት ጉዳይ ላይ እነዚህ ሁለት ቤቶች በሽያጩ አለመካተታቸው ተረጋግጦ ተወስኗል በማለት ነው፡፡

ውሣኔ ማለት ተከራካሪዎቹ ወገኖች ያቀረቡትን ክስና መልስ እንዲሁም ማስረጃዎቹን መርምሮ ስለተከራካሪዎቹ ወገኖች መብትና ስለክሱ አወሳሰን ፍ/ቤቱ የሚሰጠው ውሣኔ ለመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ ለውሣኔ ከሰጠው ትርጉም መረዳት ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ፍ/ቤቱ በቀድሞ ክስ ተጠሪ ተገቢውን ዳኝነት ከፍለው ይጠይቁ ከማለት በቀር አሁን ክርክር የተነሳባቸውን ቤቶች በተመለከተ ክሱንና መልሱን እንዲሁም ማስረጃዎቹን መርምሮ ስለተጠሪም ሆነ ስለ አመልካች መብት የሰጠው ውሣኔ የለም፡፡ ግራ ቀኙ ተከራክረው ውሣኔ ባልተሰጠበት ጉዳይ ደግሞ ቤቶቹ በሽያጩ ውል ላይ አልተካተቱም በሚል በውሣኔ ትችቱ ላይ መግለፁ ብቻ በጉዳዩ ላይ ውሣኔ መሰጠቱን አያመለክትም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት ክርክር ተደርጎ ውሣኔ ያልተሠጠበትን ጉዳይ እንደተሰጠበት በመቁጠር ለውሣኔው መሠረት ማድረጉ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ፍ/ቤቱም ቀድሞ ውሣኔ ተሰጥቶበታል ወደሚለው መደምደሚያ በመድረሱም ግራ ቀኙ በቤቶቹ ላይ ያላቸውን ክርክርና ማስረጃ በአግባቡ ሣይመረምር ውሣኔ መስጠቱን ተገንዝበናል፡፡ እኛ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ መጋቢት 2 ቀን 1985 በተደረገ የሽያጭ ውል በወረዳ 21 ቀበሌ 24 የሚገኘውንና የቤት ቁጥር 646 የሆነውን ቤት መሸጣቸውን ተረድተናል፡፡ የሽያጭ ውሉን እንደተመለከትነውም በከተማ ቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ቁጥር 21/08700 በስማቸው የተመዘገበውንና በፕላን ቁጥር 96/57 በቦታ ይዞታ 308 ካ.ሜ. ላይ በ56 ካ.ሜ. ቦታ ላይ የሰፈረውን ቤት አዋሳኞቹን በመጥቀስ በብር 62,000(ስልሳ ሁለት ሺ) ለአመልካች ሸጠዋል፡፡ ይህ በሽያጭ ውሉ ላይ በተገለፀው የከተማ ቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ላይ ደግሞ የተጠቀሱት ቁጥር 643፣ 644 እና 646 የሆኑ ቤቶች ናቸው፡፡ የሽያጭ ውሉ እና የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተሩ አንድ ላይ ተገናዝበው ሲታዩም ተጠሪ ለአመልካች የሸጡት ሦስቱን ቤቶች በሙሉ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በተለይ በሽያጭ ውሉ ላይ ተጠሪ የቤ/ቁ 646ን ብቻ ለይተው እንደሸጡ የገለፁት ነገር



አለመኖሩ ሲታይም የሽያጭ ውል በባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተሩ ላይ የተጠቀሱትን ቤቶች በሙሉ የሚያጠቃልል መሆኑን ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ አሁን ክርክር የተነሳባቸውን ቤቶች ለአመልካች ያስረከብኩት ወደፊት ቤቶቹን አጠቃልዬ እገዛለሁ ስላሉኝ ነው ያሉ ቢሆንም ይህ ፍሬ ነገር እውነት ለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ነገር አላገኘንም፡፡ በአጠቃላይ ከላይ እንደተመለከተው አመልካች ቤቱን የያዙት መጋቢት 2 ቀን 1985 ዓ.ም. በተደረገው የሽያጭ ውል መሠረት ገዝተው በመሆኑ ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የተሠጠው ውሣኔ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37/94 በሐምሌ 26 ቀን 1994 ዓ.ም እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 15800 በግንቦት 23 ቀን 1996 ዓ.ም የተሰጡት ውሣኔ ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ቤቶቹን የያዙት ገዝተው በመሆኑ ቤቶቹን ሊለቁም ሆነ ኪራዩን ሊከፍሉ አይገባም፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ.18380

ጥቅምት 5 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ፍስሐ ወርቅነህ

ዳኜ መላኩ

ደስታ ገብሩ

አማረ አሞኜ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ ማሞ ደምሴ አልቀረቡም

ተጠሪ፡- 1ኛ. አቶ አያሌው ገ/እግዚአብሔር } አልቀረቡም

2ኛ. ወ/ሮ ታየች ብርሃኑ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የሐረር አውራጃ ፍ/ቤት በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል የ1ኛ ተጠሪ ባለቤት የሆኑት የ2ኛ ተጠሪ ስምምነት ሳይኖርበት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 658ን በሚጻረር ሁኔታ ስለሆነ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት ውሳኔ በመስጠቱና ይሄው ውሳኔ በክልሉ ከፍተኛና ጠቅላይ ፍ/ቤቶች በመጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ሲታይ አሁን አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ተደርጓል የሚሉት የቤት ሽያጭ ውል ይጽደቅልኝ በማለት ለሐረር አውራጃ ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱም ሰኔ 27 ቀን 1984 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሉ ፀድቋል በማለት ውሳኔ ሠጥቶ ተጠሪዎች ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/358 በሚፈቅደው መሠረት ይ/ባዮች ወደ ክርክሩ ገብተው ጉዳዩ በድጋሚ እንዲታይ በማለት ጉዳዩን ወደ አውራጃው ፍ/ቤት መመለሱን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡

ከዚህ በኋላም በአውራጃው ፍ/ቤት 2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት አቤቱታ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ሕጋዊ ባልና ሚስት መሆናቸውን ገልጸው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውና በሐረር ከተማ ከፍተኛ 2 ቀበሌ 14 ክልል የሚገኘው ቁጥር 707 የሆነው ቤት ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ ዘመን በጋራ መሥራታቸው፣ ሆኖም ይህንኑ ቤት 1ኛ ተጠሪ ያለ ባለቤታቸው ስምምነት ለአመልካች መሸጣቸውና ይህም የፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 658ን የሚጻረር ስለሆነ የሽያጩ ውል እንዲጸድቅ አስቀድሞ በፍ/ቤቱ የተሰጠው ውሳኔ መብቴን የነካ ስለሆነ ይሄው ውሳኔ ይሰረዝልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡፡

1ኛ ተጠሪም በይዘቱ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የሕግና የፍሬ ነገር ክርክር በማቅረብ አስቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ ሊሰረዝ ይገባል ብለዋል፡፡

አመልካችም በበኩላቸው አቤቱታው መሠረት የሌለው መሆኑን በመዘርዘር ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የተከራከሩ ሲሆን በሌላ በኩልም ወ/ሮ ከበቡሽ በጅጋ የተባሉት በክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ተፈቅዶላቸው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ሰኔ 17 ቀን 1984 ዓ.ም በተጻፈ ውል ከባልና ሚስቱ (ከተጠሪዎች) በመግዛት የቤቱ ካርታና ቁልፍ በእጃቸው እንደሚገኝ ገልፀው አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በዚሁ ቤት ላይ ያደረጉት ውል ሕገ ወጥ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ውድቅ ሊያደርግው ይገባል በማለት የበኩላቸውን ክርክር አቅርበዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለትም የአውራጃው ፍ/ቤት የተጋቢዎች የጋራ የሆነን የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ የተጋቢዎች ስምምነት አስፈላጊ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.658/ሀ/ ላይ የተመለከተ ስለሆነና በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች የሸጡት ያለ ባለቤታቸው (2ኛ ተጠሪ) ስምምነት ስለሆነ ይሄው ውል ፈራሽ ነው በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከቱትም የክልሉ ከፍተኛና ጠቅላይ ፍ/ቤቶች ይህንኑ ውሳኔ አጽንተዋል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ግራ ቀኙ ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ይፈርሳል ተብሎ ውሳኔ መሰጠቱ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊመረመር እንደሚገባው በማመን ተጠሪዎች ቀርበው መልስ እንዲሰጡ ትዕዛዝ ሠጥቷል፡፡

ይሁንና 1ኛ ተጠሪና የ2ኛ ተጠሪ ወራሾች በጋዜጣ እንዲጠሩ ትዕዛዝ ተሰጥቶ በዚሁ መሠረት በጋዜጣ ቢጠሩም አልቀረቡም፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታውም እንደሚከተለው ተመርም [ ል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው የአሁን አመልካች በሐረር አውራጃ ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡት ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ተደርጓል የሚሉት ውል ይጽደቅልኝ በማለት ነው፡፡

ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ማናቸውም አቤቱታ ተመርምሮ ውሳኔ (remedy) ሊሰጠው የሚችለው የቀረበው አቤቱታ ለፍ/ቤት ሊቀርብ የሚችል (justicable) ሆኖ በሚገኝበት ጊዜና እንደዚሁም አቤቱታው የክስ ምክንያት ያለው ሆኖ በሚኝበት ጊዜ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ የቤት ሺያጭ ውል ይጽደቅልኝ የሚል እንደመሆኑ መጠን ማናቸውም ውል በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1678 ላይ የተመለከቱትን የውል አመሠራረት መርሆዎች /Elements of contracts/ መሠረት አድርጎ እስከተቋቋመ ድረስ በሕግ አግባብነት ተቋቁሟል ለማለት የሚቻል ሲሆን ከዚህ አልፎ ውሉ በፍ/ቤት እንዲጸድቅ የሚያስገድድ የሕግ ማዕቀፍ የለም፡፡ በመሠረታዊ ሕጉ /substantive law/ ላይ የዚህ ዓይነቱ ግዴታ ከሌለ ደግሞ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ በመሠረታዊ ሕግ የተሰጠን መብትና ግዴታን ማስፈጸሚያ እንጂ በእራሱ የመብትና ግዴታ ምንጭ ሊሆን አይችልም፡፡

ስለሆነም የቤት ሽያጭ ውል ይፅደቅልኝ በማለት አቤቱታ ማቅረብ ለፍ/ቤት በማይቀርብና የክስ ምክንያትም በሌለው ነገር አቤቱታ እንደማቅረብ የሚቆጠር በመሆኑ የአውራጃው ፍ/ቤት ይህንኑ አቤቱታ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.231 (1) (ሀ) መሠረት ተቀባይነት የለውም ማለት ሲገባው ውሳኔ መሰጠቱ እንደዚሁም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚሁ መሠረት ማረም ሲገባው ተጠሪዎች በተቃዋሚነት ገብተው ጉዳዩ በድጋሚ እንዲታይ መወሰኑና ከዚህም በኋላ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቤቱታው የክስ ምክንያት የለውም ማለት ሲገባው በዚህ ሁኔታ የተሰጠውን ውሳኔ ማጽናቱ ያለአግባብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የሐረር አውራጃ ፍ/ቤት ታህሳስ 30 ቀን 1985 ዓ.ም በመ.ቁ 73/84 የሰጠው ውሳኔ የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግንቦት 18 ቀን 1987 ዓ.ም በመ.ቁ.31/86 የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ኅዳር 27 ቀን 1997 ዓ.ም በመ.ቁ 00001 የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽ [ ል፡፡ ይጻፍ፡፡

2. አመልካች ለሐረር አውራጃ ፍ/ቤት የቤት ሽያጭ ውል ይፅደቅልኝ በማለት ያቀረቡት ለፍ/ቤት የማይቀርብና የክስ ምክንያት የሌለው ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡

3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ

ቤ/ኃ

የሰበር ፍይል ቁጥር 22448

ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- ኦርቢስ የንግድና ቴክኒክ ክፍል አ/ማህበር - ግርማ ሥላሴ ጠበቃ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሙሉነህ ካሣ ጠበቃ ቀረቡ

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካች ታህሣሥ 8 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መነሻ ነው፡፡

የጉዳዩ የስር አመጣጥ ተጠሪ ጥር 8 ቀን 1993 ዓ.ም ከአመልካች ጋር ባደረገው ውል 10 የመርቸዲስ ቤንዚን አክተርስ ከባድ የጭነት ተሽከርካሪዎች በወቅቱ ዋጋቸው ለመግዛት ተስማምቶ ውሉ ሲደርግ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ.ህ) ሊከፍል፣መኪኖቹ ጂቡቲ ወደብ ሲደርሱ 2ኛውን ክፍያ ብር 767,236 (ሰባት መቶ ስልሳ ሰባት ሺ.ህ ሁለት መቶ ሠላሰ ስድስት) ለመክፈልና መኪኖቹን ከተረከበ በኋላ በየደረጃው ሌሎች ክፍያዎችን ለመፈፀም ተስማምቶ በዚሁ መሠረት ብር 500,000 (አምስት ሺ.ህ) የመጀመሪያ ደረጃ ክፍያ ፈፅሞ እያለ መኪኖቹን አመልካች በወቅቱ ሊያስረክበው ባለመቻሉ የከፈለውን ገንዘብ አጠፌታ እንዲከፍለው ክስ አቅርቧል አመልካችም በበኩሉ መኪኖቹን ለማስረከብ ያልተቻለው ተጠሪ ሁለተኛውን ክፍያ ባለመክፈሉ እንደሆነ በመግለፅ ለክሱ መልስ ሰጥቷል፡፡ ክሱ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በርግጥም ተጠሪ በውሉ መሠረት የሚፈለግበትን ክፍያ አለመፈፀሙን በመግለፅ 2ኛውን ክፈያ ለተከሣሽ ከፍሎ መኪኖቹን እንዲረከብ በማለት ወስኗል፡፡



ተጠሪም በዚሁ ውሳኔ ላይ በመመርኮዝ የአፈፃፀም ፋይል የከፈተ ሲሆን በአፈፃፀም የጠየቀውም ሁለተኛውን ክፍያ ብር 767,236 (ሰባት ሺ. ስልሳ ሰባት ሁለት መቶ ሠላሳ ስድስት) ከፍሎ መኪኖቹን እንድረከብ የሚል ነው አመልካችም በበኩሉ ተጠሪ ተረቺ እንጅ ረቺ ስላልሆነ የአፈፃፀም መዝገብ ሊከፍት አይችልም፣የፍርድ ቤቱም ውሣኔ ይህን ለማድረግ የሚያስችለው አይደለም በማለት ተከራክሯል ፍርድ ቤቱም በጥቅምት 18 ቀን 1997 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተጠሪ በውሉ መሠረት የመኪናዎቹን ቀሪ ዋጋ ከፍሎ መኪናዎቹን ይረከብ በማለት በሠጠው ትዕዛዝ መሠረት አመልካች ለተጠሪ በውሉ መሠረት የመኪናዎቹን ዋጋ ብር 12,152,980.70 (አሥራ ሁለት ሚሊየን አንድ መቶ ሃምሳ ሁለት ሺ.ህ ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ከሰባ) ከፍሎ መኪኖቹን እንዲረከብ መግለጫ ቢሰጥም ተጠሪ ግን 2ኛውን ክፍያ ብር 767,236 (ሰባት መቶ ስልሳ ሰባት ሺ.ህ ሁለት መቶ ሠላሳ ስድስት) ብቻ ከፍዬ መኪናዎቹን እንድረከብ ብጠይቅም አመልካች ፈቃደኛ አልሆነም በማለት ለፍ/ቤት በማመልከቱ ፍርድ ቤቱም በጥቅምት 2 ቀን 1997 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠውን ትዕዛዝ በመሻር አመልካች ብር 767,236 (ሰባት መቶ ስልሳ ሰባት ሺ.ህ ሁለት መቶ ሰላሳ ስድስት ብር) ተቀብሎ መኪኖቹን እንዲያስረክብ በግንቦት 19 ቀን 1997 ዓ.ም የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ትዕዛዝ ሰጥቷል ለፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ ውሣኔውን አፅንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ መነሻነት ሲሆን ይህ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን በማስቀረብ አከራክሯል ክርክሩንም ከሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በዚህ ጉዳይ ለቀረበው ክርክር መሠረት የሆነው የፌ/ከ/ፍ/ቤት በዋናው ጉዳይ ጥር 7 ቀን 1996 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ላይ "ከሳሽ በውሉ መሠረት 2ኛ ክፍያውን ለተከሣሽ ከፍሎ መኪናዎቹን ከሚረከብ በቀር ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም ብሎ ወስኗል" በማለት ያሠፈረው የድምዳሜ

ዐረፍተ ነገር ነው፡፡ ተጠሪም ዐረፍተ ነገሩ የፍርድ ባለመብት አድርጐኛል በማለት አፈፃፀም የከፈተ ሲሆን አመልካችም በበኩሉ ባንድ በኩል ተጠሪ የፍርድ ባለመብት አለመሆኑን በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ መኪኖቹን ለመረከብ የሚችለው በውሉ ላይ በተመለከተው ዋጋ መሠረት ሣይሆን አሁን ባለው የገበያ ዋጋ መሠረት ነው የሚል ነው ፍርድ ቤቱ ከላይ የተመለከተውን የመደምደሚያ ዐረፍተ ነገር ያስቀመጠው አመልካች ቀደም ሲል ለክሱ ሰጥቶት በነበረው መልስ ላይ ተጠሪ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1757 መሠረት በቅድሚያ የበኩሉን ግዴታ ሣይወጣ አመልካች መኪናዎቹን ከጂቡቲ አስመጥቶ እንዲያስረክብ ለመጠየቅ በማለት ያቀረበውን በመቀበል የሰፈረ እንጂ ተጠሪን የፍርድ ባለመብት ለማድረግ አይደለም በሌላ አነጋገር ተጠሪ በቀብድ የከፈልኩትን ገንዘብ በአጠፌታ መመለስ ይገባዋል በማለት ባቀረበው የውል ይሰረዝልኝ ክስ ፍርድ ቤቱ ውሉ ሊሰረዝ አይገባውም ምክንያቱም ተጠሪ የበኩሉን ግዴታ አልተወጣም፣ተጠሪ መብቱን መጠየቅ የሚችለው ግዴታውን ከተወጣ በኋላ ነው በማለት ክሱን ውድቅ ከማድረግ በስተቀር ተጠሪን የፍርድ ባለመብት ማድረጉን አያመለክትም፤ይልቁንም ፍርድ ቤቱ በሥረ ነገር ክርክሩ በዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ ለመስጠት ለውሉ መፍረስ የሚያበቃ ምክንያት አለ ወይ? በማለት ጭብጥ መያዙ ከላይ የተገለፀውን አባባል ያጠናክራል፡፡ ይህን መነሻ በማድረግ ተጠሪ በቀብድ መልክ የከፈልኩት ገንዘብ ይመለስልኝ በማለት ውሉ እንዲፈርስለት ክስ አቅርቦ የሥር ፍርድ ቤትም ውሉ አይፈርስም፣ምክንያቱም ውሉ ሊፈፀም ያልቻለው በአመልካች ጥፋት አይደለም በማለት አመልካች ያቀረበውን ክርክር በተቀበለበት ሁኔታ የአሁኑ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት ሆኗል ለማለት አልተቻለም፡፡ በተጨማሪም ተጠሪ ከሥር ጀምሮ ዳኝነት ባልተጠየቀበት ጉዳይ የፍርድ ባለመብት ሆኗል መባሉ ተገቢ ካለመሆኑም በላይ አመልካች ለክሱ ሰጥቶት በነበረው መልስ ላይ ተጠሪ 2ኛውን ክፍያ በመፈፀም መኪኖቹ ከጂቡቲ ወደብ ተነስተው ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ባለማድረጉ ለከፍተኛ



የወደብ ኪራይ ተዳርገናል በማለት ካቀረበው ክርክር አንፃር ተጠሪ የበኩሉን ግዴታ እንዳልተወጣ የሥር ፍርድ ቤት አረጋግጦ የቀረበውን ክስ ውድቅ ማድረጉን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ውል ይፍረስ ተብሎ በቀረበ ክስ ላይ ውሉ መፍረስ የለበትም ተብሎ በአሁኑ አመልካች የቀረበው የክስ መከላከያ ተቀባይነት አግኝቶ ክሱ ውድቅ በሆነበት ሁኔታ ክሱ ውድቅ የተደረገበት ተጠሪ የፍርድ ባለመብት ሆኗል መባሉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል ምክንያቱም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378/1/ በተመለከተው መሠረት የፍርድ እንዲፈፀም ለመጠየቅ ችሎታ ያለው ፍርድ የተፈረደለት ሰው (ወገን) ብቻ በመሆኑና በተያዘው ጉዳይ ግን ተጠሪ ክሱ ውድቅ የተደረገበት በመሆኑ ነው፡፡

## ው ሣ ኔ

- የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአፈፃፀም መ/ቁ.31336 እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 20370 ህዳር 29 ቀን 1998 ዓ.ም አመልካች ያልተከፈለውን ቀሪ ገንዘብ ተቀብሎ መኪናዎቹን ያስረክብ በማለት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል ይፃፍ፡፡
- የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በሥራ-ነገር ክርክሩ (በዋናው ጉዳይ) በተሰጠው ውሳኔ መሠረት አፈፃፀም ሊጠይቁ የሚችሉበት የህግ አግባብ የለም ብለናል፡፡
- ግራ ቀኙ ወጪያቸውን ይቻቻሉ
- መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 22860

የካቲት 18 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡-መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** ሰንላይት ኢንዱስትሪና ማከፋፈያ ኩባንያ - ነ/ፈጅ ብርሃኑ ወንደሰን

**ተጠሪ፡-** አቶ ካሣዬ ዘውዴ - አልቀረበም፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው ጉዳይ የጀመረው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረ ሲሆን ለተጠሪ በሁለት የዱቤ ሰነዶች የውሃ ማሞቂያ መሸጡንና ተጠሪ ግን ለገዙት ዕቃ ዋጋቸውን ስላልከፈሉ የዕቃዎቹን ዋጋ ብር 44,930 /አርባ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሠላሣ/ ብር እንዲከፍሉ ጠይቋል፡፡ ተጠሪም ክሱን ክደው ተከራክረዋል:: ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በከሣሽና በተከሣሽ መሀከል የተደረገ የሽያጭ ውል አልቀረበም፡፡ የዱቤ ሰነዱ በፍ/ሕ/ቁ. 1685 መሠረት ተጠሪን አያስገድዳቸውም፡፡ የሽያጭ ውል ተያይዞ ባለመቅረቡም ውሉ በከሣሽና በተከሣሽ መሀከል አለ ለማለት አይቻልም ሲል የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል ሠርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አቤቱታው በአጭሩ ሲጠቃለል ሽያጩ የተደረገው በዱቤ ሰነድ /Credit invoice/ ሆኖ ሣለ የዱቤ ሰነዱ ጋር የሽያጭ ውል አልተያያዘም በማለት ፍ/ቤቱ ክሱን ውድቅ ማድረጉ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡



ይህ ችሎትም ከዱቤ ሰነዱ በተጨማሪ ሌላ የሽያጭ ውል አልቀረበም በማለት ክሱ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ ተጠሪም ቀርበው ለቀረበው ክስ ምንም ዓይነት ማስረጃ ስላልቀረበ ውሣኔው ስህተት የለውም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

አመልካች በሥር ፍ/ቤት ክስ የመሠረተው ተጠሪ በዱቤ ሽያጭ የገዙትን ውሃ ማሞቂያ ዋጋ እንዲከፍሉ ነው፡፡ አንድ ግዴታ እንዲፈፀምለት የሚጠይቅ ሰው ለግዴታው መኖር ማስረጃ ማቅረብ እንዳለበት በፍ/ሕ/ቁ. 2001/1/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪው ውሃ ማሞቅያውን መግዛታቸውንና ገንዘብ የመክፈል ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ አንድ ግዴታ መኖሩን ለማስረዳት ሕጉ የተለየ ማስረጃ እንዲቀርብ ያዘዘ ካልሆነ በቀር ግዴታው መኖሩን በጽሑፍ በምስክር፣ በሕሊና ግምት፣ በተከራካሪው ወገን እምነት ወይም በመሐላ ማስረዳት እንደሚቻል በፍ/ሕ/ቁ. 2002 ሥር ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች እንዲያስረዳ የሚጠበቅበት ተጠሪ በዱቤ የውሃ ማሞቂያ ገዝተው የተረከቡ መሆኑን ነው፡፡ የውሃ ማሞቂያ ሽያጭ ውል ደግሞ በተለየ ሁኔታ እንዲደረግ ወይም ውሉ ስለመደረጉ የተለየ ማስረጃ እንዲቀርብ ሕጉ የማያስገድድ በመሆኑ አመልካች ሽያጩ ለመከናወኑ ማንኛውንም ማስረጃ ማቅረብ ይችላል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች ሽያጭ ለመደረጉ የዱቤ ሰነድ /Credit invoice/ አቅርቧል፡፡ ይህ የዱቤ ሰነድ ግራ ቀኙ ተስማምተው እስከፈረሙት ድረስ የዱቤ ሽያጭ መከናወኑን ለማስረዳት በቂ ነው፡፡ ሕጉ ይህ አይነቱ ሽያጭ በጽሁፍ እንዲሆን ስለማያዝዝ ከዱቤ ሰነዱ በተጨማሪ ሌላ የጽሁፍ ውል እንዲቀርብ የሚጠየቅበት ምክያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት ከዱቤ ሽያጩ ጋር የጽሁፍ ውል ባለመያያዙ ሽያጭ

ተከናውኗል ማለት አይቻልም ሲል የደረሰበት መደምደሚያ ስህተት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በሌላ በኩል ግን አመልካች ሽያጭ መከናወኑን ለማስረዳት ባቀረበው የዱቤ ሰነድ ላይ የፈረሙት አመልካችና ሌላ አብይ የተባሉ ግለሰብ እንጂ ተጠሪ አይደሉም፡፡ በእርግጥ ተጠሪ ፈርመውበት ቢሆን ኖሮ የጽሁፍ ሠነድ በላዩ ላይ ስለሚገኘው የስምምነት ቃልና በላዩ ላይ ስለተፃፈው ቀን በተፈራራሚዎቹ መካከል ሙሉ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ ይሆን ነበር /የፍ/ሕ/ቁ. 2005/1/ ይመለከቷል/:: በተያዘው ጉዳይ ግን ተጠሪ በሰነዱ ላይ ያልፈረሙ በመሆኑ በሰነዱ ላይ ሰለሠፈረው ጉዳይ ተስማምተዋል ወይም ግዴታ ገብተዋል ለማለት አይቻልም፡፡ በዚህ ችሎት በተደረገው የቃል ክርክር አመልካች ሰነዱ ላይ የፈረሙት ግለሰብ የተጠሪ ወኪል ናቸው ይበል እንጂ ይህ ክርክር ከስር ያልተነሣ አዲስ ነገር በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 329/1/ መሠረት ተቀባይነት የለውም፡፡

በመሆኑም አመልካች ያቀረበው ሰነድ በአመልካችና በተጠሪ መሀከል የዱቤ ሽያጭ ውል መደረጉን እና በዚህም ምክንያት ተጠሪ የእቃውን ዋጋ የመክፈል ግዴታ ያለባቸው መሆኑን አያስረዳም፡፡ በዚህም ምክንያት ምንም እንኳን የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን ክስ ውድቅ ለማድረግ የሰጠው ምክንያት ስህተት ቢሆንም ክሱን ውድቅ ማድረጉ ግን በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መጋቢት 5 ቀን 1997 ዓ.ም በመ/ቁ. 11568 የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 38828 ኀዳር 23 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንተዋል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ 23331

ታህሳስ 1 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍስሐ ወርቅነህ
ሐጎስ ወልዱ
ሂሩት መለሰ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ጀማል ሐሚድ - ቀረበ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ለተሃይማኖት ተክሌ
2. ወ/ሮ ኪሮስ ወልዱ
3. ወ/ሮ ምዕራፍ ወልዱ
4. ተመስገን ወልዱ
5. መብራቱ ወልዱ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ከሕግ ውጭ ተይዞ የሚገኘውን ቤት ይለቀቅልን በማለት ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻነት የተጀመረውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ለቀረበበት ክስ መልስ የሰጠ ሲሆን፣ በዚህም አከራካሪው ቤት ከ2-5 ያሉት ተጠሪዎች እህት ከሆነችው ገዝቶ የያዘው እና ከገዛው በኋላም ለውጦ (አሻሽሎ) በመስራት እየተጠቀመበት መሆኑን በመግለጽ ተከራክሮአል፡፡ ክስ የቀረበበት የወረዳ ፍ/ቤትም የሁለቱንም ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች እንዲለቅ ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ በየደረጃው ይግባኝ የቀረበላቸው የበላይ ፍ/ቤቶችም ውሣኔውን አፅንተዋል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች የካቲት 16 ቀን 98 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ስምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በአመልካች እና ቤቱን በሸጠችለት የተጠሪዎች እህት መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል ሳይፈርስ አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች እንዲያስረክብ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህንን ነጥብ በግራ ቀኝ ወገኖች ከቀረበው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው አከራካሪው ቤት በቀበሌው ገበሬ ማህበር ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ ተጠሪዎች ቤቱ እንዲለቀቅላቸው ክስ የመሠረቱት ሠርተነዋል በማለት ሳይሆን አባታችን መሬቱን በ1962 ዓ.ም ከሌላ ሰው ገዝቶ የቆርቆሮ ቤት ሠርቶበታል በማለት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ቤቱን መስከረም 13 ቀን 1984 ዓ.ም ከወ/ሮ ንግሥት ወልዱ ጋር ባደረገው የሽያጭ ውል ገዝቶና አሻሽሎ በመስራት የሚኖርበት መሆኑን በመግለጽ ተከራክሮአል፡፡ የሁለቱ ወገኖች ክርክር ይህን ሲመስልም በአመልካች እና በወ/ሮ ንግስት ወልዱ መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል ደግሞ ፈርሶአል አልተባለም፡፡ ውሉ የሕግን መስፈርት አያሟላም የሚል ክርክርም አልቀረበበትም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔም የተመሠረተው ውሉ ሕገወጥ ነው ወይም በማናቸው ሁኔታ ፈራሽ ሆኖአል በሚለው ላይ ሳይሆን አመልካች ቤቱን የገዛው መብት ከሌለው ሰው ነው በሚለው ላይ ነው፡፡ በበኩላችን እንደምናየው ወ/ሮ ንግስት ወልዱ (ቤቱን የሸጠችው ሰው) የተጠሪዎች እህት እንደሆነች በተጠሪዎችም ጭምር የታመነ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ወ/ሮ ንግስት የሟች ወራሽ ነች ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ቤቱን ለመሸጥ መብት አልነበራትም ወደሚለው መደምደሚያ መድረስ የሚቻል አይደለም፡፡ በሌላም በኩል ተጠሪዎች ቤቱ የተሸጠው ያለአግባብ ነው የሚል እምነት ቢኖራቸው ውሉ ፈራሽ ነው



ይባልላቸው ዘንድ አግባብ ያለውን አካሄድ በመከተል መጠየቅ ነበረባቸው፡፡ በዚህ መልክ የተደረገ ክርክር የለም፡፡ ማስረጃም አልቀረበም፡፡ እውነታው ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች በቤቱ ላይ መብት የለውም ለማለት የሚቻልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ቤቱን ይልቀቅ በማለት በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ፣

1. አቤቱታ የቀረበበት በኦ/ብ/ክ/መ በምስራቅ ሸዋ ዞን በሻሸመኔ ወረዳ ፍ/ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ 240/93 የካቲት 14 ቀን 93 ዓ.ም ተሰጥቶ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 482/93 ግንቦት 7 ቀን 95 ዓ.ም በተሰጠው እና በኦ/ብ/ክ/መ/ጠ/ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 01642 ታህሳስ 4 ቀን 98 ዓ.ም በተሰጠው ውሣኔ እንዲሁም በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 35730 የካቲት 8 ቀን 98 ዓ.ም በተሰጠው ትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ//ብ/ሥ/ሥ/ሕግ.ቁ 348(1)መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. አመልካች አከራካሪውን ቤት ለተጠሪዎች እንዲያስረክብ የሚገደድበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራቀኝ ወገኖች የራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 23895

ታህሳስ 15 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

አመልካች፡- ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል

ተጠሪ፡- መኮንን ሉሌ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሽያጭ ውልን መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ በተጠሪው ላይ ክስ የመሠረተው ተጠሪ በሁለቱ መካከል በተደረገው የሽያጭ ውል መሠረት በግዢ ለተረከበው ወፍጮ መክፈል የሚገባውን ዋጋ ከነመቀጫው በጠቅላላው ብር 63,010 እንዲከፍለው ነው፡፡ ተጠሪ ለቀረበበት ክስ መልስ በመስጠት ተከራክሮአል፡፡ ፍ/ቤቱም ክርክሩን ከሰማ በኋላ፣ በሁለቱ መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል ተከሣሹ በውሉ መሠረት አፍርሶታል /ቀሪ አድርጎታል/፡፡ ከዚህ በኋላም ቀደም ሲል ተደርጎ በነበረው ውል አይነት የሽያጭ ውሉ አልታደሰም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት በመልካች የቀረበውን ክስ ውድቅ አድርጎአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤትም የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አመልካች መጋቢት 18 ቀን 98 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ የሽያጭ ውል ከሚገዛበት ሕግ አንፃር በማየት አግባብነቱን ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የተከራካሪዎቹ ወገኖች ግንኙነት የተመሠረተው በዕቃ ሽያጭ ውል ላይ ነው፡፡ በዚሀ ውል መሠረት አመልካች ወፍጮዎችን ለተጠሪ ሸጦአል፣ ተጠሪም በውሉ መሠረት ወፍጮዎቹን ተረክቦ የነበረ ሲሆን፣ ዋጋቸውን ግን አልከፈለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ወፍጮዎቹ በውሉ መሠረት ትክክለኛ ሆነው አልተኙም ወይም ጉድለት ያለባቸው ናቸው በሚል ለአመልካች ያስታወቀበት ሁኔታ የለም፡፡ ገንዘቡን እንዲከፍል በተጠየቀ ጊዜ /ሲከሰስ/ ያቀረበው መከራከሪያም የወፍጮዎቹን ትክክል አለመሆን የሚመለከት አይደለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረጉት ውሉ እንደፈረሰ በመቁጠር እንጂ የሽያጭ ውል አፈፃፀምን በተመለከተ የተደነገገውን ሕግ መሠረት በማድረግ አይደለም፡፡

እንደምንመለከተው ጉዳዩ የዕቃ ሽያጭ ውልን የሚመለከት እንደመሆኑ የተከራካሪዎቹ ወገኖች መብትና ግዴታ መታየት ያለበት "ስለ ልዩ ውሎች" በሚል በተደነገገው በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ አስራ አምስት ሥር ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የሻጩን ግዴታ እና ገዢውም ዕቃውን እንደተረከበ ሊወስዳቸው የሚገቡ እርምጃዎች ምን እንደሆኑ ያመለክታሉ፡፡ ሻጩ በውሉ በተመለከተው መሠረት ትክክለኛውን ዕቃ ለገዢው የማስረከብ ኃላፊነት እንዳለበት በፍ/ብ/ሕግ ቁ 2287 እና 2288 እንደተደነገገው ሁሉ ገዢም ዕቃው በውሉ መሠረት የተሟላ አይደለም ወይም ጉድለት ያለበት ነው የሚል እምነት ካለው በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማስታወቅ ግዴታ አለበት /የፍ/ብ/ሕግ ቁ 2291፣ 2292/፡፡ ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በሽያጭ ውሉ መሠረት የተረከባቸው ወፍጮዎች ጉድለት ያለባቸው ናቸው በሚል አመልካችን ያስታወቀበት ጊዜ

/ሁኔታ/ የለም፡፡ ጉድለትን መሠረት በማድረግም በአመልካች ላይ ክስ አልመሠረተም ወይም የሽያጭ ውሉን ቀሪ እንዲሆን አላደረገም፡፡ በመሆኑም የሽያጭ ውሉ ፈርሶአል በማለት የስር ፍ/ቤቶች የደረሱበት መደምደሚያ ትክክል አይደለም፡፡ ይህን መደምደሚያ መሠረት በማድረግ የተሰጠው ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. አቤቱታ የቀረበባቸው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10908 ጥቅምት 1 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 34216 የካቲት 10 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ . 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ብር 63,010.00 /ስድሳ ሦስት ሺህ አስር/ ከነዳኝነቱ እንዲሁም ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ዘጠኝ በመቶ /9%/ ወለድ ጋር ለአመልካች ይክፈል ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ አመልካች ዝርዝሩን አቅርቦ ያስወስን ብለናል፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 24554

ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አቶ አይሸሹም ጋተው - ጠበቃ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች፡-** እነ የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ጠበቃ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ክርክሩ የተጀመረው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን አመጣጡን በተመለከተም የአሁኑ አመልካች ሐምሌ 25 ቀን 1994 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ የተከሳሾች አውራሽ የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ነሐሴ 24 ቀን 1985 ዓ.ም. በተፃፈ የቤት ሽያጭ ውል ስምምነት አድርገን በወረዳ 12 ቀበሌ 11 የሚገኘው ቁጥሩ 1408 የሆነውና በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኘውን የግል ቤታቸው በብር 15,000 /አስራ አምስት ሺህ ብር/ ሸጠውልኝ ከዚሁ ሽያጭ ገንዘብ ብር 10,000 ተቀብለው ቀሪውን ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ ስም ሲዞርልኝ ሊቀበሉ ተስማምተው በእማኞች ፊት ፈርመዋል፡፡ በዚሁ መሠረትም ውሉ እንዲፀድቅልን ለዞን 4 ወረዳ 12 ፍ/ቤት መዝገብ ከፍቼ የተከሳሾች አውራሽ ከመሞታቸው በፊት መጥሪያ ደርሶአቸው ቤቱን የሸጡ በመሆኑ ስሙ በከሣሽ ስም ቢዞር ተቃውሞ እንደሌላቸው የወረዳው ፍ/ቤት ቀርበው አመልክተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ተቃዋሚ ቢኖር እንዲቀርብ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ማስታወቂያ እንዲወጣ አዝዞ ተቃዋሚ ባለመቅረቡ መጋቢት 15 ቀን 1987 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ ውሉን አጽድቆ የቤቱን ባለቤትነት ስም በከሣሽ ስም እንዲዞዋወር ትዕዛዝ ሰጥቶአል፡፡

በዚህ መሠረትም የሥራና ከተማ ልማት በስሜ ካርታ ሠርቶ ሰጥቶኛል። ነገር ግን ሟች የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ቤቱን ሲሸጡልኝ ስለቤቱ ርክክብ ሣይፈፀም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። በመሆኑም ፍ/ቤቱ ባለቤት የሆንኩለትን ቤት ተከሣሳሾች ያለአግባብ እየተጠቀሙበት በመሆኑ መብቴን ጠብቁ ቤቱን እንዲያስረክበኝ ክስ ካቀረብኩበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ተከሣሾች የተጠቀሙበት የቤት ኪራይ ሂሣብ ተምኜ የመካስ መብቴ ይጠበቅልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል።

ተከሣሾች ከሆኑት የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ወራሾች መካከል 2ኛ ተከሣሽ ወ/ሪት ክብርወርቅ ሞገስ እና 5ኛ ተከሣሽ ወ/ሪት የምስራች ሞገስ ታህሣሥ 12 ቀን 88 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ በማቅረብ ክርክር የቀረበበት ቤት የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ እና ወ/ሮ ፋናዬ አየለ በጋብቻ ያፈሩት ስለሆነ እናታችን ወ/ሮ ፋናዬ አየለ ሳታውቅ የተደረገው የሽያጭ ውል በሕግ ፊት ተቀባይነት የለውም በማለት የተከራከሩ ሲሆን 1ኛ፣ 3ኛ እና 4ኛ ተከሣሾች በተገቢው ሁኔታ ተጠርተው ያልቀረቡ ስለሆነ ክሱ በሌሉበት እንዲታይ ፍ/ቤቱ ታህሣሥ 23 ቀን 1993 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ብይን ሰጥቷል። ጣልቃ ገብ አመልካች ወ/ሮ ፋናዬ አየለ የተከሳሽ እናት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41/1/ መሠረት በክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ጠይቀው ፍ/ቤቱ ፈቅዶላቸው መጋቢት 3 ቀን 1993 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት መልስ ክስ የቀረበበት ቤት የጣልቃ ገብና የሟች የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ የጋራ ሀብት ስለሆነ ከሣሽና ሟች የተዋዋሉት የቤት ሽያጭ ውል ሕጋዊ ሊሆን አይችልም በማለት ተከራክረዋል።

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ካዳመጠ በኋላ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2266 ጀምሮ በተደነገጉት መሠረት የሽጭ ውል ተፈፀመ የሚባለው ገዢው ገንዘብ በውሉ መሠረት ሲከፍልና የገዛውን ነገር ሲረከብ ሻጭም የሸጠውን ነገር ከዶጋፊ ማስረጃዎች ጋር ለገዢው ሲያስረክብ ነው። በዚህ ጉዳይ ከሣሽ የሆኑት አቶ አይሸሹም ጋተው ግን ከተከሣሾች አውራሽ



ገዛሁ ያሉትን ቤት እንደውሉ አፃፃፍ አልተረከቡም። ባለመረከባቸውም ስም እንዲዛወር ክስ አቅርበው ውሉን በፍ/ቤት አስመዝግበው ቤቱን እንዲረከቡ አሁን የተያዘው ክርክር ያስነሳውን መዝገብ ከፍተዋል። ከመረከብ ጥያቄያቸው በመረዳትም ነሐሴ 24 ቀን 1985 ዓ.ም የተደረገው ውልና በፍ/ቤት ተመዝግቦ ስም እንዲዛወር ተወስኖ በስማቸው የባለቤትነት ማረጋገጫ ያገኙበት ምክንያት የሽያጩ ውል የተደረገው የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ሚስት የሆኑት ወ/ሮ ፋናዬ አየለ ሳያውቁና ስምምነታቸውን ሳይገልፁ በመሆኑና የማይንቀሳቀስ ሃብቱንም በእጃቸው ከማድረጋቸውና ባለ ይዞታ ከመሆናቸው በፊት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1196 ድንጋጌ መሠረት ውጤት የሚኖረው አይደለም። በመሆኑም ተከሣሾች ቤቱን ለከሣሽ የማስረከብ ግዴታ የለባቸውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል።

የፌ/ከ/ፍ/ቤትም የቀረበለትን ይግባኝ ተመልክቶ ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሰርዞታል።

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ ለማስለወጥ ሲሆን ቅሬታውም የቤቱን ሽያጭ የሚቃወም ካለ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዲቀርብ ማስታወቂያ ወጥቶ ወ/ሮ ፋናዬ አየለ ቀርበው አልተቃወሙም። የሽያጩን ገንዘብ ባለቤቴ ናቸው ከሚሉዋቸው የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ከሚካፈሉ በስተቀር በአግባቡ የተደረገውን የሽያጭ ውል ሊያፈርሱ የሚችሉበት የሕግ ምክንያት የለም። ሚስት ነኝ የሚሉት ተቃዋሚ ቤቱ በተሸጠበት ጊዜ ከባላቸው ተለይተው ወደናዝሬት በመሄድ ሌላ ባል አግብተው ይኖሩ ስለነበር በቤቱ ላይ ምንም መብት የላቸውም። ሽያጩ ከተደረገ 13 ዓመት ሆኖታል። ከአስራ ሶስት ዓመት በኋላ መጥተው የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ በማለት ያቀረቡት ጥያቄም ተቀባይነት የለውም። የሽያጭ ውሉ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት የፀደቀና ማረጋገጫ የተሰጠበት ነው። ሚስት መብት ነበራቸው የሚባሉም ከሆኑ የሽያጭ ውሉን የሚቃወም ካለ እንዲቀርብ ተብሎ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎ ሳይቀርቡ ፍ/ቤቱ የሽያጭ ውሉን

ካጸደቀና ማረጋገጫ ከተሰጠበት በኋላ ባቀረቡት ጥያቄ የሽያጭ ውሉን ሊያፈርስ የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች የሽያጭ ውሉ ተፈፃሚነት የለውም ተከሳሾች ቤቱን ለገዢው እንዲያስረክቡ አይገደዱም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ይሻርልኝ ቤቱንም እንዲሰጡኝ እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎች ደግሞ በሰጡት መልስ የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ የሸጡት ቤት የግላቸው አይደለም፡፡ የሽያጭ ውሉን በፍ/ቤት ያፀደቁትም በሐሰተኛ መንገድ ነው፡፡ የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ሚስት የሆንኩት መልስ ሰጭ መፃፍ ማንበብ ስለማልችል በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ወጣ የተባለውን ማስታወቂያ አላየሁትም፡፡ ቀሪዎቻችንም ቤቱን ከአባታችን በውርስ ያገኘነው ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶቹ የሽያጭ ውሉ ተቀባይነት የለውምነኽ ተከሣሾች ቤቱን ለከሣሽ ማስረከብ የለባቸውም በማለት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት ስለሌለበት ሊፀድቅልን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በበኩላችን ደግሞ የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ወራሾች ክርክር ያስነሳውን ቤት ለአመልካች የማያስረክቡበት ምክንያት አለ ወይስ የለም? ወ/ሮ ፋናዬ አየለ የሽያጩን ውል በመቃወም ጣልቃ መግባት የነበረባቸው በመ/ቁ. 2643 ነው ወይስ በመ/ቁ. 561/86? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነው የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ወራሾች የሆኑት ተጠሪዎች የሚያቀርቡት መከራከሪያ ነጥብ ክርክር ያስነሳው ቤት የአባታችን የ50 አለቃ ሞገስ ማሞና የእናታችን ወ/ሮ ፋናዬ አየለ በመሆኑና የተሸጠውም እናታችን ሳታውቅና ስምምነቷን ሳትሰጥ ነው፣ ቤቱ የተሸጠው በአግባቡ አይደለም፡፡ እኛ ደግሞ የአባታችን ወራሾች በመሆናችን የቤቱ ግማሽ ይገባናል፡፡ በመሆኑም ቤቱን ለሥር ከሣሽ ለአሁኑ ተጠሪ ልናስረክብ አይገባም የሚል ነው፡፡ ይህን የወራሾች ክርክር ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ስንመለከተው የውርስ ንብረት ነው የሚሉት ቤት አባታቸው የ50 አለቃ



ሞገስ ጽጌ በሕይወት እያሉ በ1985 ዓ.ም. ለአመልካች የሸጡትና የሽያጭ ውሉም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2877 መሠረት በጽሑፍ የተደረገና በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 መሠረት ደግሞ የሽያጭ ውሉ በመጋቢት 15 ቀን 1987 ዓ.ም. በፍ/ቤት የተረጋገጠና የቤት ባለቤትነቱንም ለአመልካች እንዲዛወርላቸው የተወሰነ በመሆኑ ይህ ቤት የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ሃብት መሆኑ በዚያን ጊዜ ያበቃለት ሆኗል፡፡ ቤቱ የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ማለት የወራሾቹ አባት የሆኑት ሰው ንብረት ካልሆነ ደግሞ ወራሾቹ  ንብረትነት ጥያቄ የሚያነሱበት ምክንያት አይኖርም፡፡ እንደዚሁም ወራሾቹ ቤቱን ለአመልካች አናስረክብም ለማለት የሚያስችላቸው መብት የሌላቸው በመሆኑ ክርክራቸው ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ቤቱ የተሸጠው የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ሚስት የሆነች እናታችን ሳታውቅና ስምምነቷን ሳትሰጥበት በመሆኑ የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት የሚያቀርቡትን ክርክር በተመለከተም ይህን ክርክር መነሻ በማድረግ የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ሚስት የሆኑት ወ/ሮ ፋናዬ አየለ ራሳቸው በመቃወም አመልካችነት ጣልቃ ገብተው እየተከራከሩ የሚገኙ በመሆኑ ክርክሩ በወራሾቹ  የሚነሳበትና የሚቀጥልበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ወራሾች ቤቱን ለአመልካች የማስረከብ ግዴታ የለባቸውም በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ያለመሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ደግሞ የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ቤቱን ነሐሴ 24 ቀን 1985 ዓ.ም. ለአመልካች መሸጣቸውንና የሽያጭ ውሉም በጽሑፍ መደረጉን፣ ይህን የሽያጭ ውል በመያዝ ገዢና ሻጭ ሽያጩን ለማስመዝገብና የባቤትነቱን ስም ለማዛወር ፍ/ቤት ዘንድ መቅረባቸውን፣ ፍ/ቤቱም ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዲጣራ ካደረገ በኋላ የመጣ ተቃዋሚ ያለመኖሩን በማረጋገጥና የግራ ቀኙን ስምምነትንም በመረዳት ውሉ እንዲፀድቅ፣ የባለቤትነት ስምም ከሻጭ ወደ ገዢ እንዲዛወር በማለት መወሰኑን በመ/ቁ. 561/86 መጋቢት 15 ቀን 1987 ዓ.ም.

ከተሰጠው ውሣኔ ለመረዳት ችለናል፡፡ ወ/ሮ ፋናዬ አየለ በወቅቱ በጋዜጣው ጥሪ መሠረት ወይም በሌላ መንገድ ሰምተው፣ በሰሙበትና ባወቁበት ጊዜ መቃወሚያ በማቅረብና ጣልቃ በመግባት መከራከር የነበረባቸው የሽያጭ ውሉ በፀደቀበትና የቤቱ ባለቤትነት ስም ለገዢው እንዲዛወር ተብሎ በተወሰነበት የመዝገብ ቁ 561/86 በተደረገው ክርክርና በተሰጠው ውሣኔ ላይ እንጂ ቤቱን ያስረክቡን ተብሎ በቀረበው ክስ ጣልቃ ገብተው ሊከራከሩ የሚችሉበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ምክንያቱም አመልካች ቤቱን አስረክቡኝ እያሉ ያሉት በፀደቀው የሽያጭ ውልና ስም እንዲዛወር ተብሎ በፍ/ቤት በሌላ መዝገብ ተወስኖ ባደረ ጉዳይ በመሆኑ ቤቱን የተመለከተ መብት የሽያጭ ውሉ በፍርድ ቤት በፀደቀበትና የባለቤትነት መብት ለገዢው እንዲዛወር ተብሎ በተወሰነበት ጊዜ የታየና ያለቀለት ጉዳይ በመሆኑ ተጠሪዋ ይህ ውሣኔ በተሰጠበት የመ/ቁ. 561/86 ጣልቃ ገብተው መከራከር ነበረባቸው፡፡ ክሱ በፀደቀልኝ የሽያጭ ውልና ስም እንዲዛወርልኝ በተወሰነልኝ መሠረት ቤቱን ያስረክቡኝ የሚል እንጂ የሽያጭ ውሉ ይጽደቅልኝ የሚል ባለመሆኑ በፀደቀው የሽያጭ ውልና ስም እንዲዛወር ተብሎ አስቀድሞ በሌላ መዝገብ በፍ/ቤት ተወስኖ ባደረው ጉዳይ ጣልቃ ገብተው የሽያጭ ውሉን በዛን ጊዜ ያልተቃወሙት አመልካች በዚሁ ቤቱን ያስረክቡኝ በሚለው ክስ ላይ ጣልቃ መግባት አይችሉም፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም ቤቱን ያስረክቡኝ በማለት በአመልካች ኋላ የቀረበውን ክስ መነሻ በማድረግ ግራ ቀኙን ባከራከረበት ጊዜ ጣልቃ ልግባ በማለት የአሁን ተጠሪ ሲያመለክቱ ጣልቃ መግባት ያለባቸው ቀደም ብሎ የሽያጭ ውሉ ይጽደቅልኝ የባለቤትነት ስምም እንዲዛወርልኝ በማለት አመልካች ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት ግራ ቀኙን አከራክሮ ሌላው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔ በሰጠበት የመ/ቁ. 561/86 እንጂ ኋላ በቀረበው በዚሁ የቤት ያስረክቡኝ ክስ አይደለም በማለት ጥያቄውን ውድቅ ሊያደርገው ሲገባ ጣልቃ እንዲገቡ በመፍቀድ አከራክሮ በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የነበረው ፍ/ቤት



የሰጠውን ውሣኔ በሚሽር መልኩ የሽያጭ ውሉ በአግባቡ የተደረገ ባለመሆኑ ሊፈርስ ይገባል፤ ተከሣሾች ቤቱን የማስረከብ ግዴታ የለባቸውም በማለት የሰጠውን ውሣኔ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 እና 41 ጋር በማገናዘብ ስንመለከተው ውሣኔዉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትና የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና መታረም የሚገባው ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 2643 ሰኔ 3 ቀን 1995 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሣኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23795 የካቲት 1 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የቤት ሽያጭ ውሉ በፍ/ቤት የፀደቀና የቤቱ ባለቤትነት መብትም ወደ አመልካች እንዲዞር ተብሎ የተወሰነ በመሆኑ ቤቱ የውርስ ንብረት አይደለም፡፡ የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ወራሾችም ቤቱን የመውረስ መብት የላቸውም፡፡ የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ሚስትም ጣልቃ በመግባት መከራከር የነበረባቸው የሽያጭ ውሉ በፀደቀበትና የባለቤትነት ስም ለገዢው /ለአመልካች/ እንዲዛወር ተብሎ ውሣኔ በተሰጠበት ክርክር እንጂ ቤቱን ለመረከብ በቀረበው ክስ መሆን የለበትም፡፡ ተጠሪዎች በወረዳ 12 ቀበሌ 11 የሚገኘውንና ቁጥሩ 1408 የሆነውን ቤት ለአመልካች በውሉ መሠረት እንዲያስረክቡ በማለት ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 24974

ታህሳስ 8 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍስሐ ወርቅነህ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- 1. አቶ ፈቃዱ ዴሬሎ
2. ወ/ሮ ዓይናለም በሻህ — ጠበቃ ሙላት ፈለቀ
ተጠሪ፡- 1. አቶ ንጉሴ ወርቁ - ቀረቡ
2. ወ/ሮ ሐረገወይን ጀማነህ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው በአመልካቾችና በተጠሪዎች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ተሰርዞ ውሉ ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ በሥር ፍ/ቤቶች በመወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካቾች ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ ተጠሪዎች በአመልካቾች ላይ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በወረዳ 16 ቀበሌ 04 ክልል የቤት ቁጥር 898 የሆነውን ቤት በታህሳስ 1 ቀን 1977 ዓ.ም. በተፃፈ የሽያጭ ውል በብር 58,000 /ሃምሣ ስምንት ሺህ/ ከሣሾች ለተከሣሾች ሸጠን ውሉ በተደረገ ዕለት ብር 50,000 /ሃምሣ ሺህ/ የተቀበልን ሲሆን ቀሪውን 8,000 /ስምንት ሺህ/ ደግሞ በ30 ቀን ውስጥ ቤቱን አስረክበን እንደሚከፈለን በተስማማነው መሠረት ቤቱን ያስረከብን ቢሆንም ቀሪው ገንዘብ ያልተከፈለ ስለሆነ ውሉ እንዲፈርስና ወደነበርንበት እንድንመለስ ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡



ክሱና ማስረጃው ለተጠሪዎች ደርሶም በሰጡት መልስ የውሉን መደረግ አምነው ውሉ በተፈረመ በ30 ቀን ውስጥ ከሳሾች የሸጡትን ቤት ከእዳና ዕገዳ ነፃ አድርገው ውል ክፍል ቀርበው መሸጣቸውን በማረጋገጥ ሲፈርሙ ቀሪው ብር 8,000 (ስምንት ሺ) እንደሚከፈላቸው በውሉ ላይ የተስማማን ቢሆንም ይህንን ግዴታ ካለመወጣታቸው በላይ በክስ ከተጠየቀው ገንዘብ ላይም ክስ ከመቅረቡ በፊት ብር 5,000 (አምስ ሺ) ለከሳሾች የከፈለን ስለሆነ ውሉ ይፍረስል በማለት ያቀረቡት ክስ ከበቂ ኪሣራ ጋር ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተከሳሾች በቀሪነት የሚፈለግባቸውን ገንዘብ እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 1977 ዓ.ም. ድረስ አጠቃለው ለመክፈል በውል ግዴታ ገብተው ክፍያውን አለመፈጸማቸው የተረጋገጠ ስለሆነ ግራ ቀኙ ያደረጉት ውል ፈርሶ ወደነበሩበት ሊመለሱ ይገባል በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ተከሣሾች በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ሊሰረዝ ይገባል? ወይንስ አይገባም? የሚለው በመሆኑ ከሕጉ ጋር ተገናዝቦ ተመርምሯል፡፡

ታህሣሥ 1 ቀን 1977 ዓ.ም. በተፃፈ ውል ግራ ቀኙ የቤት ሽያጭ ውል ማድረጋቸውንና ውሉ በተደረገ ዕለት ሻጮች የአሁን ተጠሪዎች ብር 50,000 /ሃምሳ ሺህ/ የተቀበሉ መሆኑን ግራ ቀኙ ተማምነውበታል፡፡ ተጠሪዎች ውሉ ይሰረዝልን በማለት በክስ የጠየቁት ቀሪው ብር 8,000

(ስምንት ሺ.ህ)  አልተከፈለንም በሚል ምክንያት ነው፡፡ በውል አፈፃፀም ሂደት ከተዋዋዮች አንዱ የውሉን ግዴታ ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ ሌላው ወገን እንደሁኔታው ውሉ እንዲፈጸምለት መጠየቅ እንደሚችል ይህም ካልሆነ ውሉ እንዲሰረዝ ጥያቄውን ማቅረብ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1771 ላይ ተመልክቷል፡፡ የውል ይሰረዝልኝ ጥያቄ ለፍ/ቤት በቀረበ ጊዜ ዳኞች ውሉ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ውሣኔ ከመስጠታቸው በፊት የተዋዋዮችን ጥቅምና ለቅን ልቦና የሚያስፈልገውን ነገር መሠረት ማድረግ እንዳለባቸው፣ በውሉ ላይ ዓይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ተግባር /fundamental breach of contract/ ካልተፈጸመ በስተቀር ዳኞች ውል ይሰረዝ ማለት እንደሌለባቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1784 እና 1785 ላይ ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በቤት ሽያጭ ውሉ መሠረት ለተጠሪዎች መከፈል ከሚገባው ገንዘብ አብዛኛውን አመልካቾች እንደከፈሉ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህም ውሉ በአመዛኙ እንደተፈጸመ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ውሉ ባመዛኙ መፈጸሙ ከተረጋገጠ ደግሞ ዓይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ተግባር ተፈጽሟል ለማለት የማይቻል ከመሆኑም በላይ ከቅን ልቦና መለኪያ አኳያም ሲታይ ተጠሪዎች በቀሪነት የሚፈለገውን አነስተኛ ገንዘብ እንዲከፈላቸው በመጠየቅ ውሉ ውጤት እንዲኖረው ማድረግ እየቻሉ እንዲሰረዝ መጠየቃቸው ተቀባይነት ያለው ምክንያት አይደለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ቀሪው ገንዘብ ባለመከፈሉ ምክንያት የቀረበውን የውል ይሰረዝልኝ ክስ ተቀብለው ውሉ እንዲሰረዝ መወሰናቸው የሕግ ስህተት  ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10356 ነሐሴ 16 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 43067 ግንቦት 9 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካቾች መሠረታዊ የሆነ የውል መጣስ ተግባር ያልፈጸሙ ስለሆነ ከተጠሪዎች ጋር ያደረጉት ውል ሊሰረዝ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 25165

ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

መድህን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አቶ እርቁ ጎዳ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ አህመድ አብዱልሐሚድ - ባለቤታቸው ቀርበዋል

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የሠፈረውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በፌ/ከ/ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሣሽ የነበሩ ሲሆን በአሁን አመልካችና አሁን በክርክሩ ውስጥ በሌሉት ሌሎች ሁለት ሰዎች ላይ በጥቅምት 30 ቀን 1996 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ ከ2ኛዋ ተከሣሽ ከወ/ሮ ወይንሸት ካሣሁን ጋር ሚያዝያ 7 ቀን 1988 ዓ.ም በተፃፈ ሰነድ የባህል ጋብቻ መሥርተን በሰኔ 3 ቀን 1992 ዓ.ም ጋብቻውን በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ያስመዘገብን ሲሆን 1ኛው ተከሣሽ አቶ ውሂብ ማዘንጊያ ከ2ኛዋ ተከሣሽ በተሰጠው የውክልና ስልጣን ስሙ በ2ኛዋ ተከሣሽ የሆነውን የጋራ ቤታችንን ያለ ከሣሽ እውቅና ለ3ኛ ተከሣሽ (ለአሁን አመልካች) በመጋቢት 5 ቀን 1994 ዓ.ም በተፈረመ ውል በብር 160,000 (አንድ መቶ ስልሳ ሺህ) ሸጠው የገንዘቡን መጠን ዝቅ በማድረግ ቤቱ የተሸጠው በብር 23,000 (ሃያ ሦስት ሺህ) መሆኑን የሚገልጽ ውል በመጋቢት 12 ቀን 1994 ዓ.ም በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው ተፈራርመዋል፡፡ ቢሆንም የቤት ሽያጭ ውሉ የተደረገው ከቅን ልቦና ውጪ በመሆኑ ውሉ ፈርሶ የባለቤትነት ስሙ በ2ኛዋ ተከሣሽ እንዲመዘገብ ይደረግልኝ ሲሉ ፍ/ቤቱን ጠይቀዋል፡፡ 1ኛው ተከሣሽ ከ2ኛ ተከሣሽ በተሰጠኝ ውክልና መሠረት በፈፀምኩት ውል ልከሰስ አይገባም



የሚል መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩም ረገድ ከ3ኛው ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) ጋር በጋራ በሰጡት መልስ የቤት ሽያጭ ውሉ የተደረገው በብር 23,000 (ሃያ ሦስት ሺህ) እንጂ በብር 160,000 (አንድ መቶ ስልሳ ሺህ) የተደረገ ውል የለም፡፡ ጋብቻ መኖሩንም አናውቅም፣ ቤቱ የተመዘገበው በ2ኛዋ ተከሣሽ ስም ከመሆኑ ባሻገር 2ኛ ተከሣሽ ትዳር እንደሌላቸው ከሚኖሩበት ቀበሌ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ከሣሽ(የአሁን ተጠሪ) ጉዳት ደርሶብኛል ካሉ 2ኛዋን ተከሣሽ ከሚጠይቁ በቀር በቅን ልቦና የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ሊፈርስ አይገባም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የ1ኛውን ተከሣሽ ተቃውሞ በመቀበል ከክርክሩ ያሰናበታቸው ሲሆን የአሁን አመልካች ውሉን በፈፀመበት ወቅት 2ኛዋ ተከሣሽ ትዳር እንዳላት እንደማያውቁ ክደው የተከራከሩት በተጠሪ ያልተስተባበለ በመሆኑ አመልካች በቅን ልቦና በተዋዋሉት የቤት ሽያጭ ውል መሠረት በህጉ አግባብ የባለቤትነት መብት ያገኙበትን ንብረት ሊያጡ አይገባም ሲል የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ የአሁን ተጠሪ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24830 በህዳር 6 ቀን 1998 ዓ.ም ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ቅሬታቸውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት በይግኝ አቅርበዋል፡፡

ይግባኙ የቀረበለት የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1266 እና አ/ቁ. 213/92 አንቀጽ 68/ሀ/'ን ጠቅሶ በማይንቀሣቀስ የጋራ ንብረት ላይ ለመዋዋል የሁለቱ ተጋቢዎች ስምምነት ያስፈልጋል፣ ማስረጃውን የሰጠው ቀበሌም 2ኛዋ መ/ሰጭን በነዋሪነት ያስመዘገበ ከመሆኑም በላይ ስለጋብቻው መኖር አለመኖር የማስረዳት ብቃት የለውም ከዚህ እና ሁለት የተለያየ የሽያጭ ዋጋ ያላቸው ውሎች በተዋዋዮች ስምምነት ከመደረጋቸው አንፃር የውሉ አደራረግ ከመነሻው በተንኮል መሆኑን፣ በአጠቃላይ የውሉ አደራረግ ለህሊና ብቻ ሣይሆን ለህግም ተቃራኒ ነው ማለት ይቻላል በሚል ምክንያት ውሉ በአ/ቁ. 213/92 አንቀጽ 69/1/ መሠረት ሊፈርስ ይገባል ሲል የከ/ፍ/ቤት ውሣኔን ሽሮታል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታም የቀረበው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት

በመ/ቁ. 22126 በግንቦት 21 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡

ይህም ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ተመልክቶ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ የተወሰነው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር በሚል ተጠሪን አስቀርቦ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በመሠረቱ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ውሉን ለማፍረስ ምክንያት ያደረገው የቀበሌ ጽ/ቤት የጋብቻ መኖር አለመኖርን የማስረዳት ብቃት የለውም፣ ጋብቻን የመመዝገብ ስልጣን በተሰጠው እና የጋብቻ የምስክር ወረቀት ከሚሰጠው አካል ማስረጃ አልተጠየቀም፣ ሁለት የተለያየ የሽያጭ ዋጋ ያላቸው ውሎች መደረጋቸው የውሉ አደራረግ ከመሠረቱ የተንኮል መነሻ የነበረው ነው የሚል ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ጉዳይ አመልካቹ ቤቱን ሲገዙ ከቀበሌ ማስረጃ መጠየቃቸው የቀበሌ ጽ/ቤት የነዋሪዎችን አሠፋፈርና የአኗኗር ሁኔታ በተመለከተ ከማንኛውም ተቋም በተሻለ መረጃዎችን ሰብስቦ የሚመዘግብ ከመሆኑ አንፃር መረጃው አግባብነት ያለው ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ቀርበው በውልና ማስረጃ ካስፀደቁት ውል በተጨማሪ በብር 160.000 (አንድ መቶ ስልሳ ሺህ) የተደረገ ሌላ ውል አለ ያሉ ሲሆን፣ ነገር ግን ህጉም ሆነ ይህ ፍ/ቤት ከግንዛቤ የሚያስገባው ያልፀደቀውን እና አመልካች የካዱትን የመንደር ውል ሣይሆን በአዋዋይ የፀደቀውንና በብር 23,000 (ሃያ ሦስት ሺህ) የተደረገውን የሽያጭ ውል ብቻ ነው፡፡ ከነዚህ ነጥቦች በመነሣት አመልካች የቤቱ ባለቤትነት በወ/ሮ ወይንሸት ካሣሁን ስም መሆኑን፣ ወ/ሮ ወይንሸትም ትዳር የሌላቸው መሆኑን በበቂ ሁኔታ አረጋግጠው የፈፀሙት የሽያጭ ውል ለሕግና ለሞራል ለቅን ልቦናም ተቃራኒ ነው ሊባል የሚችል ሆኖ አለተገኘም፡፡ በመሆኑም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የአመልካችን የቅን ልቦና መከራከሪያ ወደጎን በመተው የሽያጭ ውሉ ይፈርሣል ሲል የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡



**ው ሣ ኔ**

1/ በወረዳ 16 ቀበሌ 11 የቤ.ቁ. 098 የሆነውን ቤት አስመልክቶ መጋበት 12 ቀን 1994 ዓ.ም የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል አይፈርስም ብለን ወስነናል፡፡

2/ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22126 በግንቦት 21 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

3/ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24830 ህዳር 6 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

4/ ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 26996

በየካቲት 18 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ታፈሠ ይርጋ

ሱልጣን አባተማም

አሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ በቀለ ደቦጭ - ጠበቃ መ/አለቃ ሽፈራው አመኑ

**ተጠሪዎች፡-** 1/ ወ/ሮ አዛለች ደሣለኝ

2/ ወ/ሮ አምሣለ ኃይሉ

3/ ወ/ሮ አስቴር ኃይሉ

4/ አቶ ጌድዮን ኃይሉ

5/ አቶ ፍቅሩ ኃይሉ

6/ አቶ በትሩ ኃይሉ

7/ ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ

ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ክርክር የተጀመረው በኦ/ብ/ክ/መ/የጅማ ዞን ከ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች ከሣሾች አመልካቹ ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ፡፡ የአሁን ተጠሪዎች በጥቅምት 12 ቀን 1996 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ አመልካቹ የ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና የተቀሩት ተጠሪዎች አባት ከሆኑት ከሟች ግራዝማች ኃይሉ ወ/ፃድቅ በጥቅምት 22 ቀን 1986 ዓ.ም ባደጉት ውል ግምቱ 1,300,000.00 (አንድ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሺ.ህ) ብር የሆነው የእንጨት መሠንጠቂያ ፋብሪካ ግማሽ በብር 650,000.00 (ስድስት መቶ ሃምሳ ሺ.ህ) ገዝተው ከውሉ ገንዘብ ውስጥ ብር 160,000.00 (አንድ መቶ ስልሳ ሺ.ህ) የከፈሉ ሲሆን የቀረው ብር 490,000.00 (አራት መቶ ዘጠና ሺ.ህ) እስከ



አሁን ድረስ ያልተከፈለ በመሆኑና አመልካቹም የሽያጭ ስምምነቱ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ የፋብሪካው ሰራ አስኪያጅ ሆኖ እየሠራ ያለ በመሆኑ ከፋብሪካው ላይ የሚፈለግ ልዩ ልዩ እዳ ክፍሎ ከሆነ ተሣስበን ቀሪውን ገንዘብ ከወለዱ ጋር እንዲከፈለን እንዲሁም ፋብሪካውን ለወደፊት በጋራ እንድንጠቀምበት እንዲወሰንልን በማለት ፍ/ቤቱን ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካች ለተጠሪዎች ክስ በሰጠው መልስ ግማሽ ፋብሪካውን በብር 650,000 (ስድስት መቶ ሃምሳ ሺ.ህ) መግዛቱ እና ቀብድ ብር 160,000 (አንድ መቶ ስልሳ ሺ.ህ) መክፈሉን ሣየስተባብል ነገር ግን በውሉ መሠረት ቀሪውን ገንዘብ ብር 490,000 (አራት መቶ ዘጠና ሺ.ህ) ለመክፈል የሚገደደው የመንግሥስትና የግለሰብ የተለያዩ እዳዎች ተከፍለው ስመንብረቱ በስሙ ከተዛወረ በኂላ መሆኑን ሆኖም ፋብሪካው ቀድሞ በ1971 ዓ.ም የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በዕዳ መያዣነት እንደያዘው በአሁኑ ሰዓትም ባንኩ በፋብሪካው ላይ የቀዳሚነት መብት አለኝ በሚል የወሰደው እና በእጄ የማይገኝ በመሆኑ ክሱ የሕግ ድጋፍ የለውም ሲል መልስ ሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአሁን አመልካች የተከሣሽ ከሣሽ በመሆን በዚያው መዝገብ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ያቀረበ ሲሆን፣ በየካቲት 5 ቀን 1996 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ክስ 1ኛ ተጠሪ እና ባለቤታቸው በዋስትና የተያዘውን ፋብሪካ ከዕዳና እገዳ ነፃ የሆነ በማስመሰል የሸጡልኝ በመሆኑ ውሉ ፈርሶ የከፈልኩትን ቀብድ ብር 160,000 (አንድ መቶ ስልሳ ሺ.ህ) በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1885/2/ መሠረት እጥፍ አድርገው ብር 320, 000 (ሦስት መቶ ሃያ ሺ.ህ) ከወጪና ኪሣራ ጋር እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ ሲል ፍ/ቤቱን ጠይቋል፡፡

የሥር ከሣሾች ለተከሣሽ ከሣሽነት ክሱ በሰጡት መልስ በተከሣሽ ከሣሽነት የቀረበው ክርክር ከዚህ ቀደም በተመሣሣይ ጉዳይ በመ/ቁ. 19/94 ውሣኔ ያገኘ በመሆኑ ድጋሚ ሊቀርብ አይችልም፣ ውሉ ተሠርዞ በቀብድ የተሰጠው ገንዘብ ይመለስ ቢባል እንኳ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1810/1/ እና በቁጥር

1845 መሠረት ክሱ በይርጋ የሚታገድ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የጅማ ዞን ከ/ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ የከሣሾችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የአሁን ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክስ በተመለከተ፣ ፋብሪካው በመያዣ የተያዘ በመሆኑ የአሁን አመልካች (የሥር ተከሣሽ) እንደፍላጎቱ ስሙን ማዛወር አይችልም፣ ከሣሾቹ ከስምምነቱ በፊት በፋብሪካው ላይ ያለውን ዕዳ በመክፈል ከእዳ ነፃ አድርገው ስሙ ከተዛወረለት በኋላ ቀሪው ብር 490,000(አራት መቶ ዘጠና ሺህ) እንደሚከፈል ውሉ በግልጽ አስቀምጦ ሣለ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ውሉ ሊፈፀም ይገባል ማለት አስቸጋሪ ስለሚሆን የከሣሾቹ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፤ ያለ ሲሆን የተከሣሽ ከሣሹን ክስ በተመለከተ ደግሞ ተጠሪዎች በባንክ አዳ የተያዘን ንብረት አመልካቹን (የሥር ተከሣሽን) በማሳሳት ሸጠውለት ብር 160,000(አንድ መቶ ስልሳ ሺህ) ወስደው ቀሪውን ብር 490,000(አራት መቶ ዘጠና ሺህ) ስመንብረት በተከሣሽ ስም ካዛወሩ በኋላ ለመውሰድ ያደረጉት ስምምነት ሊፈፀም የማይቻል ስምምነት ሆኖ የተገኘ ስለሆነ ተጠሪዎች (የሥር ከሣሾች) ቅን ልቦና የሌላቸው መሆኑን በመገንዘብ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1885(2) መሠረት የወሰዱትን ብር 160,000(አንድ መቶ ስልሳ ሺህ) እጥፍ በማድረግ ብር 320,000(ሦስት መቶ ሃያ ሺህ) ከፍለው ውሉ እንዲፈርስ ሲል ወስኗል፡፡

የጅማ ዞን ከ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለኦ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት የቀረበ ሲሆን የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ በሚያዝያ 26 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ የተጠሪዎችን መቃወሚያ ከግምት ውስጥ በማስገባት የአሁን አመልካች (በስር መ/ሠጭ) ቁጥሩ 19/94 በሆነ ሌላ መዝገብ በተጠሪዎቹ (በስር ይ/ባዮች) ላይ የዚህ ክርክር መነሻ በሆነው ውል መሠረት ስመንብረቱን በስሜ እንዲያዛውሩልኝ፤ በዚህ ፋብሪካ ምክንያት ያወጣሁትን ወጭ እና በድርጅቱ ላይ ያለውን ዕዳ እንዲከፍሉኝ



ሲሉ ክስ አቅርበው ተጠሪዎቹ በውሉ መሠረት የድርጅቱን ግማሽ ስመንብረት እንዲያዛውሩ እና ለድርጅቱ የወጣውን እዳ ከተለያዩ ወጪዎች ጭምር ብር 215,460.13(ሁለት መቶ አስራ አምስት ሺህ አራት መቶ ስልሳ ከአስራ ሦስት) እንዲከፍሉት ተወስኖ እያለ አመልካች ውል ይፍረስልኝ ብሎ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ በማቅረቡ ብቻ ውሉ እንዲፈርስ ተብሎ መወሰኑ ትክክል ሆኖ አልተገኘም፣ ተጠሪዎቹም ግዴታቸውን እንደስምምነቱ ሣይፈጽሙ ቀሪው ገንዘብ ሊከፈለን ይገባል በማለት ያቀረቡት ቅሬታም ተቀባይነት የለውም ያለ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የአሁን አመልካች የፋብሪካው ስራ አስኪያጅ ሆኖ በሠራበት ጊዜ ከፋብሪካው የሚገኘው ገቢ በማስረጃ ተጣርቶ ተጠሪዎቹ የድርጅቱ ገቢ ይከፈለን በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ውሣኔ እንዲያኝ በማለት መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343 መሠረት ወደ ጅማ ዞን ከ/ፍ/ቤት መልሶታል፡፡

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ መዝገቡ በሰጠው ውሣኔ ቅር የተሠኙት የአሁን አመልካች ለክልሉ ሰበር ችሎት አቤቱታቸውን ቢያቀርቡም የኦ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤታቸውን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

አመልካች በመስከረም 12 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በስር ፍ/ቤት ውሉ ፈርሶ ተጠሪዎች አመልካች የከፈሉትን ቀብድ እጥፍ አድርገው ይመልሱ ሲል የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ከድርጅቱ የተገኘውን ገቢ በተመለከተ አጣርቶ የመሠለውን ይወስን ሲል መወሰኑ እና የክልሉም ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ይህንን ውሣኔ ማጽናቱ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አቤቱታቸው ለዚህ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይህም ችሎት የአመልካችን አቤቱታ ተመልክቶ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውና አመልካች የገዙት ፋብሪካ በእዳ በባንክ የተሸጠ በመሆኑ ስም ሊዛወር ስለማይችል ውሉ ሊፈርስ ይገባል ተብሎ በስር ፍ/ቤት

የተሰጠው ውሣኔ እንዲሻር መወሰኑ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቦ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር አድርገዋል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው የአ/ጠ/ፍ/ቤት የጅማ ዞን ከ/ፍ/ቤት ውሉ ፈርሶ ተጠሪዎቹ የተቀበሉትን ቀብድ እጥፍ አድርገው ይክፈሉ ሲል የሰጠውን ውሣኔ ለመሻር መሠረት ያደረገው አመልካቹ ከዚህ ቀደም በመ/ቁ. 19/94 ተጠሪዎቹ የፋብሪካውን ስመንብረት ያዛውሩልኝ ለፋብሪካው እዳ የተከፈለ ገንዘብ ይመለስልኝ ሲሉ ባቀረቡት ክስ በተጠሪዎች ላይ ያስወሰኑ በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 መሠረት ዳግመኛ ክስ ሊመሠርቱ አይችሉም በሚል ነው፡፡ በመሠረቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 ተፈፃሚነቱ ቀድሞ በተወሰነው ክርክር የስረ ነገር እና የተያዘው ጭብጥ አንድ አይነት በሆነ ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ግን ምንም እንኳ ቀድሞ በመ/ቁ. 19/94 የቀረበው ክርክር በፋብሪካ ሽያጭ ውሉ ዙሪያ የሚያጠነጥን ቢሆንም በክሱ የተጠየቀውም ዳኝነት ይሁን አከራካሪ የነበረው ጭብጥ ከውሉ መፍረስና አለመፍረስ ጋር የተገናኘ ባለመሆኑ አመልካች ውል ይፍረስልኝ ሲሉ ያቀረቡት ክስ በድጋሚ የቀረበ ክርክር ነው ሊባል የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

አመልካቹ በተያዘው ጉዳይ ያቀረቡት ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ. 5 ሥር የሚካተት አይደለም ከተባለ ደግሞ የውሉን መፍረስ አግባብነት መመርመሩ ተገቢ ይሆናል፡፡ የክርክሩ መነሻ በሆነው ውል የተሸጠው ፋብሪካ በአሁኑ ሰዓት ባንክ ለእዳው ማስፈፀሚያ ያዋለው መሆኑን ከስር ፍ/ቤት ጀምሮ ከተደረጉት ክርክሮች እና ከተሰጡት ውሣኔዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የውሉ ጉዳይ የሆነው ፋብሪካ በአመልካቹ ስም ሊዛወርም ሆነ አመልካች በውሉ ላይ ተመርኩዞ ሊተላለፍለት የሚችል መብት አይኖርም፡፡ በሌላ አነጋገር የዚህ ውል ጉዳይ የሆነው እንደ ፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1715 ድንጋጌ አነጋገር ሊፈፀም የማይችል ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የውሉ ጉዳይ ሊፈፀም የማይችል በሆነ ጊዜ ውሉ እንደሚፈረስ ይኸው ድንጋጌ ይገልፃል፡፡ አንድ ውል ሲፈርስ ደግሞ ውጤቱ የሚሆነው ተዋዋዮቹን ወደ ነበሩበት ቦታ



መመለስ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1815 ይደነግጋል፡፡ ይህም ችሎት የጅማ ዞን ከ/ፍ/ቤት ውሉ ይፈርሣል ሲል የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ መሆኑን የተገነዘበ ሲሆን ከፍተኛ ፍ/ቤቱ አመልካች የፈፀሙት ክፍያ ቀብድ በመሆኑ ተጠሪዎች እጥፉን ይመለሱ ሲል የሰጠውን ውሣኔ ግን በውሉ ክፍያው ቀብድ መሆኑ ካለመገለፁ አንፃር አልተቀበለነውም፡፡ በመሆኑም ይህ ችሎት የፋብሪካ ሽያጭ ውሉ ይፈርሣል፣ ተጠሪዎቹም አመልካች የከፈሉትን ብር 160,000 (አንድ መቶ ስልሳ ሺህ) ሊመልሱ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ የአ/ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ.22676 በሚያዝያ 26 ቀን 1998 ዓ.ም አመልካች በውሣኔ ያለቀውን ክርክር በድጋሚ ማቅረብ አይችልም ሲል ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 ላይ ተመርኩዞ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

2. የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎቹ የወሰዱትን ቀብድ እጥፍ አድርገው ብር 320,000 (ሦስት መቶ ሃያ ሺህ) ይክፈሉ ሲል የሰጠውን ውሣኔ አሻሽለን፣ክፍያው ቀብድ ለመሆኑ ውሉ ስለማይገለጽ ተጠሪዎች ሊመልሱ የሚገባው የወሰዱትን ብር 160,000 (አንድ መቶ ስልሳ ሺህ) ነው በማለት ውሉ ይፈርሣል ሲል በመ/ቁ.02939 በሰኔ 23 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ አጽንተነዋል፡፡

ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 27349

ታህሳስ 8 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** ብሔራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኩባንያ ኮ/ል ደነቀው

**ተጠሪ፡-** ዘላቂ ግብርና ተሐድሶ ኮሚሽን አልቀረበም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በይግባኝ ተመልክቶ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካችና በሥር 1ኛ ተከሣሽ ላይ በምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ 1ኛ ተከሣሽ ልዩ ልዩ የቢሮ ዕቃዎችን ለመግዛት በወጣው ጨረታ ተካፋይ በመሆን ብር 468,540.00 (አራት መቶ ሺህ አምስት መቶ አርባ) የሚያወጡ ልዩ ልዩ ዕቃዎችን በ120 ቀን ውስጥ ሊያቀርብ ስምምነት ተፈራርሞና 2ኛ ተከሣሽ በቀረበው የሥራ አፈፃፀም ዋስትና አሸናፊ ሆኖ ሙሉ ክፍያ የተፈፀመለት ቢሆንም በውሉ መሠረት ጊዜውን ጠብቆ አብዛኛውን ዕቃ በጥራት አሟልቶና አስተካክሎ ያላቀረበ ስለሆነ በክስ የተጠየቀውን ተከሳሾች ባልተነጣጠለ ኃላፊነት እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቆ ተከሳሻች ቀርበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና ሙሉ መልስም በመስጠት ተከራክረዋል፡፡



በተከሳሾች በኩል በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የተነሳው ክርክርም በውሉ አንቀጽ 8 መሠረት ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚችለው ሐምሌ 12 ቀን 1991 ዓ.ም. በተፈረመው ውል አንቀጽ መሠረት በሁለት ተዋዋይ ወገኖች መካከል አለመግባባት ቢከሰት ጉዳዩ ወደ አስታራቂ ኮሚቴ ሊመራ እንደሚገባውና አስታራቂ ኮሚቴውም ውሣኔ ከሰጠ በኂላ ቅሬታ ቢኖር ሲሆን በቀጥታ ወደ ፍ/ቤት መሄድ ግን ውሉን የሚቃረን ስለሆነ ፍ/ቤት ሊቀበለው አይገባም የሚል ነው፡፡

የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም በዚህ ረገድ የቀረበውን መቃወሚያ መርምሮ ግራ ቀኙ ባቋቋሙት ውል አንቀጽ 8 ላይ ተከሳሾች በጠቀሱት መልኩ ስምምነት የተደረገ ስለሆነና በሕግ አግባብነት የተቋቋሙ ውሎች በተዋዋዮች ላይ አሳሪ ስለሚሆኑ በዚህ ሁኔታ የቀረበው ክስ ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 244/2/ረ/መሠረት ተቀባይነት የለውም በማለት ክሱን በብይን ውድቅ አድርጓል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ መ/ሰጪዎች በይ/ባይ አማካይነት በውሉ መሠረት በስምምነት ለመጨረስ በደረሰባቸው ማሳሰቢያና ማስጠንቀቂያ መሠረት መቅረብ ሲገባቸው ያልቀረቡ በመሆኑና ይህ ከሆነ ደግሞ በውላቸው ላይ አለመግባባት ከተከሰተ ጉዳዩ ወደ ፍ/ቤት ከመቅረቡ በፊት በመከራከር ወይም በሚመርጧቸው አስታራቂ ኮሚቴዎች ለመፍታት መስማማታቸው ብቻውን ይግባኝ ባዮችን ወደ ፍ/ቤት ጉዳዩን ከማቅረባቸው በፊት በስምምነታቸው መሠረት መጨረስ ነበረባቸው ተብሎ ጉዳያቸውን ወደ ፍ/ቤት የማቅረብ መብታቸው የሚነፈግበት ምክንያት የለም የሚል ትችት በውሣኔው ላይ አስፍሮ የሥር ፍ/ቤት ብይን በመሻር የፍሬ ጉዳይ ክርክሩ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይታይ በማለት ጉዳዩን መልሷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎቱም የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ ጉዳዩ በፍ/ቤት መታየት አለበት ተብሎ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው

ውሣኔ ሊጣራ የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ ክርክሩ በፍ/ቤት ሊታይ ይችላል? ወይንስ አይችልም? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ ይዘን አቤቱታውን መርምረናል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው ውል ማንኛውም አለመግባባት ቢፈጠር ጉዳዩን በስምምነት ለመፍታት ይህም ካልተቻለ በአስታራቂ አማካኝነት ለመጨረስና ወደ ፍ/ቤት ለመሄድ የተስማሙት በእነዚህ አማራጮች አማካይነት ጥረት አድርገው ያልተቻለ ከሆነ ነው፡፡ በዚህ መልኩ ስምምነት የተደረገ መሆኑም ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ ተጠሪ በዚህ የውል ቃል መሠረት ላለመግባባቱ ዕልባት ለመስጠት በማሰብ ለአመልካቾች ማሳሰቢያ ቢላክላቸውም ያልቀረቡ ስለሆነ ክሱ በቀጥታ ለፍ/ቤት ሊቀርብ እንደቻለ በመጥቀስ ተከራክሯል፡፡

ይሁንና የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በውሣኔው ላይ እንዳሰፈረው በሕግ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች በተዋዋዮች ላይ ሕግ እንደመሆናቸው መጠን ግራ ቀኙ በዚህ መልኩ ለመፈፀም ፈቃዳቸውን እስከሰጡ ድረስ በዚህ የውል ቃል የማይገደዱበት ምክንያት ሊኖር አይችልም፡፡ ተጠሪ ጉዳዩን በውሉ መሠረት ለመጨረስ በማሰብ ለአመልካች ማሳሰቢያ ስለመላኩ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው ቢባል እንኳን ማድረግ የሚጠበቅበት በውሉ መሠረት አስታራቂ ሽማግሌዎች ተሰይመው ጉዳዩ ዕልባት እንዲያገኝ ዳኝነት መጠየቅ እንጂ በቀጥታ ክስ ማቅረቡ ውሉን የሚፃረር በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በውሉ ላይ ተመስርቶ ክሱን በብይን ሳይቀበል መቅረቱ የሚነቀፍ አልነበረም፡፡ ሆኖም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የዚህ ዓይነት ስምምነት ቢኖርም ወደ ፍ/ቤት ከመቅረብ አያግዳቸውም በማለት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን መሻሩ በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው ውል አለመግባባትን በአስታራቂ ወይም በዘመድ ዳኛ አማካይነት ለመጨረስ



ያደረጉት ስምምነት በፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 1765 የተፈቀደ ከመሆኑም በላይ ማንኛውም ውል በሕግ አግባብ እስከተቋቋመ ድረስ በተዋዋዮች ላይ ሕግ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1731/1/ ላይ የተመለከተ በመሆኑ በዚህ ሁኔታ ጉዳዩ በቀጥታ በፍ/ቤት መታየት ይችላል በማለት የሥር ፍ/ቤትን ብይን በመሻር የፍሬ ጉዳይ ክርክሩ እንዲታይ ጉዳዩን ወደ ሥር ፍ/ቤት መመለሱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ለፍ/ቤት በመ/ቁ. 02001 ጥቅምት 6 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት በመሻር የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 333/93 የካቲት 27 ቀን 1995 ዓ.ም. የሰጠው ብይን ጸንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሠበር መ/ቁ. 28663

ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ተገኔ ጌታነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- አቶ ካሣሁን ገዛኸኝ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አልማዝ ወልዴ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የዚህ ጉዳይ መነሻ ተጠሪ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል ቤንች ማጂ ዞን ሸካ ወረዳ ፍ/ቤት 1ኛ/ አቶ ታደሰ ገ/የሱስ 2ኛ አቶ ካሣሁን ገዛኸኝ (የአሁኑ አመልካች) ላይ የውል ይፍረስልኝ ክስ በማቅረባቸው ነው፡፡ የክሱም ይዘት በአጭሩ 1ኛው ተከሣሽ የትዳር አጋሬ ሲሆን እኔ በሌለሁበት የጋራ ሀብታችን የሆነውን መኖሪያ ቤት ለ2ኛ ተከሣሽ ሚያዚያ 12 ቀን 1994 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል የሸጠለት ሲሆን እኔ ከአንድ ዓመት በኂላ ስመለስ 1ኛው ተከሣሽ በጩቤ አስፈራርቶኝ ተገድጄ በውሉ ላይ ፈርሜአለሁ፡፡ ስለዚህ ይህ በግዳጅ የተፈፀመ ውል ይፍረስልኝ ብለዋል፡፡ 1ኛው ተከሣሽ ክሱን አምኖ የተቀበለ ሲሆን፣2ኛው ተከሣሽ ግን በመልሱ ውሉን ፈቅዳ ፈርማለች ክሷን ከ2 ዓመት በላይ ቆይታ መመሥረቷ ከቅን ልቦና ውጪ መሆኑን ያሣያል ሲል ተከራክሯል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት ምስክሮችን ያዳመጠ ሲሆን ምስክሮቹም ውሉ በተፈረመበት ዕለት ባልና ሚስቱ መጨቃጨቃቸውን የቃላት ዛቻ እንደነበረ መስክረዋል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት በውሣኔው ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1706 አንፃር ውሉን ተገዳ መፈረሟ በመረጋገጡ እና የፍ/ህ/ቁ. 658(ሀ) በሚያዘው መሠረት በተጋቢዎቹ መሀል ስምምነት ሣይኖር በማይንቀሣቀስ ንብረት መዋዋል ስለማይቻል ውሉ ይፈርሣል፣ 2ኛ ተከሣሽ ቤቱን ያስረክብ ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች በውሣኔው ቅር በመሠኘት ለቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኛቸውን ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ ይግባኛቸውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች አቤቱታውን በመቀጠል ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም አቤቱታቸውን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታም የቀረበው የወረዳው ፍ/ቤት ውሉ ይፈርሣል ሲል የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚል ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታም ለሰበር እንዲቀርብ ታዞ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተካሂዷል፡፡ ይህ ችሎት በፍሬ ጉዳዩ ላይ የተነሱትን ክርክሮችና የስር ፍ/ቤት ውሣኔዎችን ምርምሯል፡፡ እንደተመረመረውም በዚህ ጉዳይ መፍትሔ የሚሻው ነጥብ የቤት ሽያጭ ውሉ የተጠሪ ሙሉ ፈቃድ ያልታከለበት ነው በሚል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 658 አንፃር ውሉ ይፈርሣል መባሉ አግባብ ነው ወይ? የሚለው ነው፡፡

የወረዳው ፍ/ቤት ተጠሪዋ ውሉ ላይ የፈረመችው ተገድዳ በመሆኑ በውሉ ልትገደድ እንደማይገባ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1706ን መሠረት አድርጎ ወስኗል፡፡ ከዚህም ባሻገር አመልካች ከተጠሪዋ ባለቤት ከአቶ ታደሰ ገ/የሱስ ጋር የፈፀመው የቤት ሽያጭ ውልም ቢሆን ከተጠሪዋ ፈቃድ ወጪ የተፈፀመ ነው በሚል የፍ/ብ/ህ/ቁ. 658ን መሠረት አድርጎ ውሉ ይፈርሣል ሲል ወስኗል፡፡ በእርግጥ በዚህ ድንጋጌ ስር የተጠቀሱትን ተግባራት ለመፈፀም የሁለቱ ተጋቢዎች ስምምነት እንደሚያስፈልግ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን የዚህ ድንጋጌ ተፈፃሚነት በሁለቱ ተጋቢዎች መካከል እንጂ የሦስተኛ ወገን ተዋዋዮችን መብት የሚነካ አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ የድንጋጌው ውጤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 686 ላይ በግልጽ ተጠቅሷል፡፡ ይኸውም አንደኛው ተጋቢ ወገን በቁጥር 658 ላይ የተጣለበትን የስልጣን ገደብ ተላልፎ የጋራ ሀብትን የሚጎዳ ተግባር ፈጽሞ ቢገኝ የጋብቻው ግንኙነት በሚቋረጥበት

ወቅት በካሣ ተጠያቂ መሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም በቁጥር 658ን የተፃፈው ድንጋጌ በምንም ዓይነት አንዱ ተጋቢ ወገን ከሦስተኛ ወገን ጋር ያደረገውን ውል ለማፍረስ ምክንያት አይሆንም፡፡ በአጠቃላይ ይህ ችሎት የስር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ህ/ቁ. 658 መሠረት አድርገው ውሉ ይፈርሣል ሲሉ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ በአመልካች እና በአቶ ታደሰ ገ/የሱስ መካከል ሚያዝያ 12 ቀን 1994 ዓ.ም የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ፀንቷል፡፡

2/ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/የቤንች ማጂ ዞን ሻላ ወረዳ ፍ/ቤት ግንቦት 3 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

3. በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/የቤንች አካባቢ ከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02954 ግንቦት 14 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡

4. በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ሠሚ ችሎት በመ/ቁ. 15221 ታህሳስ 17 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



የሰ/መ/ቁ. 29233

ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አብዱልቃድር መሐመድ

ብርሃኑ አመነው

መድኀን ኪሮስ

ፀጋዬ አስማማው

አሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሙሂዲን ፋሪስ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ኢያሱ በዕደ ማርያም ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 22359 ታህሣሥ 13 ቀን 99 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ ላይ የቀረበ ሲሆን ጉዳዩ ከቤት ሽያጭ ውል ጋር የተያያዘን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበሩት የአሁን አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ የመሠረቱት ክስም በውል የገዛሁትን ቤት እንዲያስረክቡኝ እንዲሁም ዋጋውን በማካካስ በሸጥኩላቸው ጊዜ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺ.ህ) ቅድሚያ ክፍያ ተቀብለው ሲያበቁ ቤቱን ባለመረከባቸው ለዘበኛ ብር 750.00 (ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ.ህ) ከፍያለሁ፡፡ የሸጡልኝ ቤት ባለማስረከባቸው በወር ብር 10,000 (አስር ሺ.ህ) በማከራየት አገኝ የነበረውን የሶስት ወር ኪራይ ብር 30,000 (ሰላሳ ሺ.) አሳጥተውኛል፡፡ በመሆኑም የሸጥኩላቸውን ቤት እንዲረከቡና የሸጡልኝን ቤት እንዲያስረክቡኝ፡፡ ለዘበኛ ያወጣሁትን ወጪ ብር 750.00(ሰባት መቶ ሃምሳ) እንዲከፍሉኝ፣ እንደዚሁም ቤቱን አከራይቼ አገኝ የነበረውን ብር 30,000(ሰላሳ ሺ.ህ) እና እስኪያስረክቡ ድረስ በየወሩ ብር 10,000 (አስር ሺ.) እንዲታሰብ እንዲከፍሉኝ እንዲወስንልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪ ደግሞ በሰጡት መልስ ቤቶቹን ለመሻሻጥ ውል ያደረግን መሆኑ አይካድም፡፡ ሆኖም በተፈራረምነው የውል ጽሑፍ ላይ የተቀመጡትን የቤቶቹን ሰነዶች የመለዋወጥና በአዲስ አበባ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በመቅረብ ሽያጩን የማስመዝገብና የሽያጩን የማስፈፀም ሥራዎች አልተከናወኑም፡፡ ከሣሽ የሸጡልኝ ቤት የሚመለከት ካርታም ይሁን የቤት ባለቤትነት ደብተር የላቸውም፡፡ አስፈላጊዎቹን የሸጡልኝ ቤት ሰነዶች እንዲሰጡኝ፤ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ሄደን ሽያጩን እንድናስመዘግብና ውሉ እንዲፈፀም ጠይቂያቸው ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ በመቀጠልም የተጀመረውን የቤት ሽያጭ ውል ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል ማስጠንቀቂያ ጽፌላቸዋለሁ በመሆኑም ውሉ ረቂቅ እንጂ የተሟላና ተግባራዊ ሊሆን የሚገባው ባለመሆኑ ክሱ ውድቅ ሆኖ ልሰናበት ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ በሰጠው ውሣኔ ውሉ የሚፈፀምበት ምክንያት የለም፡፡ ተከሳሽ የከሻሽን ቤት ከሣሽ ደግሞ የተከሣሽን ቤትና የቤቶቹን ሰነዶች ይረካከቡ ብሏል፡፡

ይግባኙ የቀረበለት የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ በአሁኑ አመልካችና ተጠሪ መካከል የተደረገ በሕግ የሚታወቅ የቤት ሽያጭ ውል የለም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ደግሞ ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ያደረግነው የቤት ሽያጭ ውል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1720/2/ መሠረት የሚፀና ውል ነው፡፡ ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 መሠረት ፈራሽ ነው ወይም ደግሞ ውሉ ሥልጣን ባለው አካል ያልተመዘገበ በመሆኑ በረቂቅነት ደረጃ የሚታይ ነው በማለት በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በጽሑፍ ከተደረገ የፀና ይሆናል ተብሎ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2877 የተደነገገውን የሚቃረን በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና ሊታረም የሚገባው ነው፡፡



በመሆኑም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሮ ፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ይፅናልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ ደግሞ በሰጡት መልስ በመካከላችን የተደረገው ውል ረቂቅ ነው፡፡ ውሉ የተሟላ ሊሆን ይችል የነበረው በተስማማነው መሠረት አመልካች የሸጡልኝን ቤት ሰነዶች ሲያቀርቡና የሁለቱንም ቤቶች ሰነዶች ይዘን ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በመቅረብ የሽያጩ ውል የተመዘገበ እንደሆነ ነው፡፡ አመልካች በተስማማነው መሠረት ግዴታቸውን አልተወጡም፡፡ አመልካች ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ) አልከፈሉኝም፡፡ የሰጡኝ ቅድሚያ ክፍያ ብር 50,000 መሆኑን በክርክራቸው ላይ ጠቅሰዋል፡፡ ከእኔም የሽያጭ ገንዘብ አልተቀበሉኝም፡፡ በበኩሌ የአመልካች ሁኔታ የተጀመረውን የቤት ሽያጭ ስምምነት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሆኖ ስላላገኘሁት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2348 እና 2349 መሠረት የተጀመረውን የሽያጭ ውል ስምምነት ለማቋረጥ ማስጠንቀቂያ ሰጥቻቸዋለሁ፡፡ ውሉም በተስማማነው መሠረት በፍ/ቤትም መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተመዘገበ በመሆኑ በረቂቅነት የሚታይ እንጂ የተሟላና ሊፈፀም የሚገባው ውል አይደለም፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 ስር የተደነገገውን መሠረት በማድረግ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገ በሕግ የሚታወቅ የቤት ሽያጭ ውል የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ እንዳችም የሕግ ስህተት የለበትም፡፡ በመሆኑም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ሊፀናልኝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በበኩላችን ደግሞ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገ በሕግ የሚታወቅ የቤት ሽያጭ ውል አለ ወይስ የለም? በሕግ የሚታወቅ የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል ከሌለስ ተዋዋዮቹ ወደነበሩበት ሊመለሱ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም አመልካችና ተጠሪ የቤቱን ሽያጭ አስመልክቶ የተዋዋሉት የቤት ሽያጭ ውል የሽያጩ ስምምነት በጽሑፍ

ሰፍሮ ከተፈራረሙ በኋላ የሁለቱን ቤቶች ካርታ ይዘው በውል ክፍል ቀርበው ከተፈራረሙ በኋላ ሽያጩን አስመዝግበው ለመጨረስ እንደነበር ግራ ቀኙ ካቀረቡት ክርክርና የሥር ፍ/ቤት ከሰጠው ውሣኔ ለመረዳት ችለናል፡፡ በውል ጽሑፋቸው ባሰፈሩት ስምምነት መሠረት በውል ክፍል ቀርበው ሽያጩን እንዳያስመዘግቡ በአመልካች በኩል በስምምነት ጽሁፍ ላይ የሰፈረውን ግዴታ ያለመፈፀም ሁኔታ እንቅፋት መሆኑንም ግራ ቀኙ ካደረጉት ክርክር ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ተሟልተው ግራ ቀኙ ማስረጃዎቻቸውን ይዘው በመቅረብ የሽያጭ ውሉን በፍ/ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ካላስመዘገቡት ደግሞ ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1720/1/ መሠረት በተቀዳሚ ውልነት ወይም በረቂቅነት ደረጃ ላይ የቀረበ እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 መሠረት የተደረገ የተሟላ ውል ነው ለማለት የሚቻል አይሆንም፡፡ በመሆኑም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል በሕግ የሚታወቅ የቤት ሽያጭ ውል የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ የተደረገው ውል ተቀዳሚ ውል ወይም ረቂቅ ውል እንጂ ሊፈፀም የሚገባው የተሟላ ውል አይደለም ማለት በመሆኑ ፍ/ቤቱ የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በሌላ በኩል ግን ውሉ በተቀዳሚ ውልነት ወይም በረቂቅ ውልነት ደረጃ ላይ ባለበት ጊዜ በውል ስምምነት አድራጊዎቹ የተደረገ የገንዘብ ወይም የሌላ ነገር ልውውጥ ቢኖር ውሉ ሊፈፀም የሚያስችለው ደረጃ ላይ ባልደረሰበት ጊዜ የውል አድራጊዎቹ ወደነበሩበት መመለስ ተገቢ በመሆኑና በዚህ ጉዳይም አመልካች ለተጠሪ ከፈልኩ የሚሉት ብር 50,000.00(ሃምሳ ሺ.ህ) ስላለና ተጠሪም በስር ፍ/ቤትም ይሁን በዚሁ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንን ክደው የተከራከሩ ባለመሆኑ የግራ ቀኙ ወደነበሩበት መመለስ አስፈላጊነት በግልጽ ስለሚታይ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በግራ ቀኙ የተደረገ የሚፈፀም የቤት ሽያጭ ውል የለም በማለት ሲወስን ግራ ቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ በማለት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1815 መሠረት መወሰን ሲገባው ይህን በማለፉ



ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና ሊሻሻል የሚባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22359 ታህሣሥ 13 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. በመልካችና በተጠሪ መካከል ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል ያልተሟላና በረቂቅነት ደረጃ ላይ ያለ በመሆኑ ውሉ እንዲፈፀምልኝ በማለት በመልካች የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ ይህን አስመልክቶ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ ግራ ቀኙ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱና ተጠሪ በቅድሚያ ክፍያነት የተቀበሉትን ብር 50,000 /ሃምሣ ሺ.ህ / ለአመልካች እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡ ይፃፍ፡፡ ውሣኔውን ፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያስፈጽም፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል:: ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ::

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

**<u>የሀሣብ ልዩነት</u>**

እኔ በአምስተኛ ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ ከአብላጫው ድምጽ በአመልካችና በተጠሪው መካከል ያለው ውል ፈርሶ፣ ሁለቱም ወደነበሩበት፣ እንዲመለሱ በሰጠው ማጠቃለያ ተስማምቼ አብላጫው ድምጽ ከዚህ ውሣኔ ለመድረስ ከሰጠው ምክንያት የተለየ ምክንያት ያለኝ በመሆኑ፣ ይህንን የልዩነት ሃሣብ ጽፌአለሁ፡፡ አንድ ተዋዋይ ወገን፣ ሌላው ወገን ውል ይፈጽምልኝ የሚል ክስ ለማቅረብ የሚችለው፣ በራስ በኩል ያለውን ግዴታ ሲፈጽም እንደሆነ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1771 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ለተጠሪው የሸጠውን ቤት፣ ካርታና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች እንዲያስረክቡ በተጠሪው ተጠይቀው የቤቱን ካርታና ኘላን እንደዚሁም ሌሎች ሰነዶችን ለማስረከብ ባለመቻላቸው ምክንያት ውሉ ያልተፈፀመ በመሆኑ አመልካች በራሳቸው በኩል፣ የገቡትን የውል ግዴታ ስላልተወጡ ተጠሪው ውል ይፈጽምልኝ በማለት ለመጠየቅ አይችሉም፡፡ እንደውም በራሳቸው በኩል የነበረውን ግዴታ የተወጡት ተጠሪ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1771 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አመልካች ውሉን እንዲፈጽም ወይም ውሉ ፈራሽ እንዲሆን መጠየቅ የሚችሉ በመሆኑ ተጠሪ አመልካች በእሳቸው በኩል ያለውን ግዴታ አልፈፀሙም በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ ውሉን ፈራሽ ለማድረግ በቂ ምክንያት ነው፡፡ ከዚህ ውጭ በግራ ቀኙ መካከል የተደገው ውል ረቂቅ እንጂ በሕግ ውጤት ሊያስከትል የሚችል ውል አይደለም በማለት አብላጫው ድምጽ የሰጠው የሕግ ምክንያት እኔን የሚያሣምን ባለመሆኑና በአመልካችና በተጠሪው መካከል ያለው ውል፣ አመልካች የበኩሉን ግዴታ ባለመፈፀሙ ምክንያት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1771 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ፈራሽ መሆን ያለበት በመሆኑ፣ አብላጫው ድምጽ በሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ በመስማማት፣ ውሉ ፈራሽ በሚሆንበት ምክንያት ላይ ያለኝን የልዩነት ሀሣብ አስፍሬያለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 31223
ሚያዝያ 7 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ
ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሰምሰም መኩሪያ ቀርባለች፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ሙሉእመቤት ጌታሁን ጠበቃው ቀርቧል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ከመዝገቡ እንዳየነው ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የቤት ሽያጭ ውል አፈፃፀምን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ አመልካች ናት፡፡ በተጠሪዋ ላይ ክስ የመሠረተችውም ቀደም ሲል በተደረገው የሽያጭ ውል መሠረት በቀሪ የሚፈለግባትን የቤቱ ዋጋ እንድትከፍላት፣ የውሉን አፈጻጸም በማዘግየትዋም በውሉ የተመለከተውን መቀጫ እንድትከፍል፤ እንደውሉ የማትፈጽም ከሆነ ደግሞ ውሉ ፈርሶ ወደየነበሩበት እንዲመለሱ እንዲወሰን በመጠየቅ ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ተከሣሽን አስቀርቦ ክርክሩን የሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ገንዘቡ የሚከፈለው ሻጭ የሆነችው ከሣሽ የቤቱን ስም በተከሣሽ ስም ስታዛውር ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ክሱን ሰርዞአል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ውሣኔውን አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሰኔ 11 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የስር ፍ/ቤቶች የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረጉበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ

መሠረትም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተካሄደው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው የግራ ቀኙ ወገኖች ግንኙነት የተመሠረተው በውል ላይ ነው፡፡ ይህም ሚያዝያ 28 ቀን 1996 ዓ.ም. የተደረገው /የተፈረመው/ የቤት ሽያጭ ውል ሲሆን፣ የሁለቱን ወገኖች መብትና ግዴታ በዝርዝር ይዞአል፡፡ አመልካች ቤትዋን በብር 185,000 /አንድ መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ/ ለተጠሪ ለመሸጥ መስማማትዋን፣ ውሉ በተፈረመበት ዕለትም ከዋጋው ላይ ብር 60,000 /ስድሳ ሺህ/ መቀበልዋን፣ ቀሪውን ብር 125,000 /አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺህ/ ደግሞ ቀደም ሲል በቤቱ ላይ በፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔና ለፍርድ አፈፃፀም የተላለፈውን ትዕዛዝ አስነስታ ማስረጃውን ቤቱ ለሚገኝበት የሕብረት ሥራ ማኅበር አቅርባ በሷና በሟች ባለቤቷ ስም የተመዘገበውን ቤት በተጠሪ ስም እንዲመዘገብ ስታደርግ ወዲያውኑ እንዲከፈላት መስማማቷን ውሉ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ በውሉ በተመለከተው መሠረት ቤቱን ለመግዛት መስማማቷ እና ውሉ በተፈረመበት እለት ከከፈለችው ብር 60,000 /ስልሳ ሺህ/ ሌላ በቀሪ የሚፈለግባትን ብር 125,000 /አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺህ/ አመልካች ግዴታዋን እንደተወጣች ወዲያውኑ ለመክፈል እንደተስማማች በውሉ በግለጽ ተመልክቷል፡፡

አመልካች ወደ ክስ ያመራችው ተጠሪ እንደውሉ ለመፈጸም ፈቃደኛ አልሆነችም በማለት እና የበኩልዋን ግዴታ ግን እንደተወጣች በመግለጽ ነው፡፡ ከእርሷ የሚፈለገው ግዴታ ከላይ በዝርዝር የተመለከተው ሲሆን፣ በእርግጥም ይህ በሚገባ ስለመፈጸሙ በጽሑፍ እና በቃል በተደረገው ክርክር ተረጋግጧል፡፡ ቀደም ሲል በቤቱ ላይ ተሰጥቶ የነበረውን የፍርድ ቤት ውሣኔ እና ለፍርድ አፈፃፀም መመምሪያ ተላልፎ የነበረውን ትዕዛዝ አስነስታ፣ ማስረጃውንም ለሕብረት ስራ ማኅበሩ አቅርባ ተጠሪን አንድትተካ ስለማድረግዋ በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ጭምር ግራ ቀኝ ወገኖች



አረጋግጠዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ እንደሚያመለክተው ፍ/ቤቱ በውሉ ላይ ያልተመለከተው እና ግራ ቀኝ ወገኖች በግልጽ የስምምነታቸው አካል ያላደረጉትን "የስም ማዛወር" የሚል አስተሳሰብን መሠረት በማድረግ ነው ውሣኔ የሰጠው፡፡

በበኩላችን እንደምናየው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተፈረመው ውል ግልጽ ነው፡፡ ጠቅላላ አነጋገር የሚመስል አገላለጽ በፍጹም አይታይበትም፡፡ ውሎች ግልጽ ሆነው በሚገኙበት ጊዜ ዳኞች ግልጽ ሆኖ ከሚሰማው መራቅ ውሉን መተርጎም እንደማይችሉ /እንደማይገባቸው/ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1733 ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ቀሪውን ገንዘብ ለመክፈል በግልጽ የተስማማችው በቤቱ ላይ የነበረው መሰናክል ተወግዶ በማኅበሩ ዘንድ አመልካችንና ሟች ባለቤትዋን ተክታ ስትመዘገብ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በሚገባ ተፈጽሞአል፡፡ ለነገሩ መግባት አያስፈልግም እንጂ ይነሳ ከተባለም በማህበራት ይዞታ ስር ያሉትን ቤቶች በተመለከተ የሻጭን ስም በገዢው ስም ከመተካት ያለፈ ነገር ሊከናወን ስለማይችል ተጠሪ በውሉ መሠረት አልተፈጸመላትም ለማለት የሚያስችል የሕግ ምክንያት አይኖርም፡፡ ሲጠቃለልም አመልካች ግዴታዋን አልተወጣችም የሚባልበት የሕግ ምክንያት ስለሌለ የስር ፍ/ቤት በውሉ የሌለ እና አስፈላጊ ያልሆነ ተጨማሪ ግዴታ እንዳለባት በመቁጠር የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌ/መ/ደፍ/ቤት በመ/ቁ. 43844 ሰኔ 26 ቀን 1997 ዓ.ም. ተሰጥቶ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 41177 መጋቢት 25 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡

2. ተጠሪ በቀሪ የሚፈለግባትን የቤቱን ዋጋ ብር 125,000 /አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺህ/ ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ አለቀ ድረስ 9% /ዘጠኝ በመቶ/ ወለድ በመጨመር ለአመልካች ትክፈል ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 31482

ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ዓለምነሽ ወ/አገኘሁ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ አባተ ተፈሪ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአማራ ብሄራዊ ክ/መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረብርሃን ወረዳ ከተማ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት የአፈጻጸም ክስ በደብረብረሃን ከተማ ቀበሌ 03 ክልል የሚገኘውና የቤ.ቁ. 167 የሆነውን ቤት የአፈጻጸም ተከሳሽ በብር 18,500 (አስራ ስምንት ሺህ አምስት መቶ) ሸጠልኝ ቤቱንም አስረክቦኝ ነገር ግን ባለሐብትነቱን በስሜ ባለማዛወሩ ምክንያት በዚሁ ፍ/ቤት ክስ አቅርቤበት ስም እንዲያዛውር የተወሰነ ስለሆነ በዚሁ ውሳኔ መሰረት ይፈጸምልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የአፈጻጸም አቤቱታውም ለአፈጻጸም ተከሳሽ የአሁን ተጠሪ ደርሶ በሰጡት መልስ ለአፈጻጸም ክርክሩ ምክንያት የሆነውና በሽያጭ የተላለፈው ቤት የእራሳቸው እንዳልሆነ በመግለጽ ስም ማዛወር አልችልም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአፈጻጸም ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለትም የወረዳው ፍ/ቤት በሽያጭ ለአፈጻጸም ከሳሹ ተላልፏል የተባለው ቤት ባለሐብትነት በማን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ የሚመለከተውን አካል ጠይቆ በአፈጻጸም ተከሳሽ ስም ሳይሆን በሌላ ግለሰብ ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ በመረጋገጡ የአፈጻጸም

ከሳሹ ስም ይዛወርልኝ በማለት ያቀረቡት የአፈጻጸም ማመልከቻ በአግባቡ ስላለሆነ ሊፈጸም አይችልም ብሎ በሽያጩ ጊዜ የአፈጻጸም ተከሳሹ የተቀበሉትን ብር 15,000(አስራ አምስት ሺህ) ለአፈጻጸም ከሳሹ ሊመልሱ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአፈጻጸም ከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረስ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ በፍርድ አፈጻጸም ወቅት አስቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ መሻሩ ለሰበር ቀርቦ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ ተመርምሯል፡፡

አመልካች በደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ዳኝነት የጠየቁት ቤት ሸጠልኝ ርክክቡ የተከናወነ ቢሆንም ስም ያላዛወረልኝ ስለሆነ እንዲያዛውር ይወሰንልኝ በማለት ሲሆን የወረዳው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ ሻጩ ስም ሊያዛውሩ ይገባል በማለት ውሳኔ መስጠቱን ከመዝገቡ ለመረዳት ችለናል፡፡

በዚህ ውሳኔ መሰረት ይፈጸምልኝ በማለት የአፈጻጸም ከሳሽ/የአሁን አመልካች/ የአፈጻጸም ማመልከቻ ሲያቀርቡ አስቀድሞ ተከሳሹ ስም ሊያዛውሩ ይገባል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በይግባኝ አስካልተሻረ ድረስ ትክክል እንደሆነ የሚገመት በመሆኑ ይህንኑ ውሳኔ ከማስፈጸም በስተቀር ውሳኔውን በአፈጻጸም በመሻር ሻጩ የሽያጩን ገንዘብ ለገዢው ሊመልስ ይገባል ተብሎ ውሳኔ መስጠቱ ሙግቱ የሚመራበትን የሥነ-ሥርዓት ሕጉን የሚጻረር ሆኖ ተገኝቷል፡፡



በሌላ በኩልም ለአፈጻጸም ክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ባለቤትነቱ በአፈጻጸም ተከሳሹ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ሳይሆን በሌላ 3ኛ ወገን ስም ተመዝግቦ ይግኛል ቢባል እንኳን ዋናው ክርክር ሲደረግ ይህ 3ኛ ወገን የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.41 በሚፈቅደው መሰረት በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ መብቱን ማስጠበቅ የሚችል ከመሆኑም በላይ ዋናው ክርክር ሲደረግ ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚችልበት ሁኔታ ካልተፈጠረም በሌለበት የተሰጠው ውሳኔ መብቱን የነካ ከሆነ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 በሚፈቅደው መሰረት በሌለበት የተሰጠው ፍርድ እንዲሰረዝለት ከሚጠይቅ በስተቀር ፍ/ቤቱ በእራሱ አስተያየት ሊመለከተው አይችልም፡፡

ስለሆነም ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ጉዳዩ ይመለከተኛል የሚል 3ኛ ወገን ባልቀረበበት ሁኔታ ፍ/ቤቱ በእራሱ አስተያየት በሽያጭ ለአፈጻጸም ከሳሹ ተላልፏል የተባለው ቤት በ3ኛ ወገን ስም የተመዘገበ ስለሆነ አፈጻጸሙ ሊቀጥል አይችልም በማለት የሽያጩ ገንዘብ ሊመለስላቸው ይገባል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05529/99 መጋቢት 12 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የሰሜን ሸዋ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13181 ግንቦት 24 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 378/99 ግንቦት 30 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በውሳኔው መሰረት እንዲያስፈጽም ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰበር መ.ቁ. 31640

የካቲት 11 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ ገረመው ግዛው ከጠበቃ ተሾመ ደምሴ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ፈቃዱ ያደቴ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው ተጠሪ በክስ የጠየቀውን ገንዘብ አመልካች የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት በበታች ፍ/ቤቶች በመወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ሲታይ ተጠሪ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ ተከሣሽ የሠ.ቁ.1-07889 የሆነውን መኪና በነሐሴ 4 ቀን 1991 ዓ.ም በተፃፈ ውል በብር 34,000 (ሠላሣ አራት ሺህ) ሸጦልኝ መኪናውንም ያስረከበኝ ቢሆንም ስም ሣያዛውር በመቅረቱ ምክንያት ክስ አቅርቤበት በግንቦት 9 ቀን 1996 ዓ.ም ስም እንዲያዛውር ተወስኖበት ጉዳዩ በአፈፃፀም ላይ ይገኛል፡፡ የስም ዝውውሩን በተመለከተ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በይግባኝ ክርክር ላይ እያለን መኪናውን ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ትእዛዝ ከፍ/ቤቱ በመተላለፉ እስከ የካቲት 30 ቀን 1993 ዓ.ም መኪናውን ለማንቀሳቀስ ችዬ ነበር፡፡ ነገር ግን ከመጋቢት 1 ቀን 1993 ዓ.ም ይህ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ መኪናውን ማንቀሣቀስ ያልተቻለ ስለሆነና የመኪናውም የቀን ገቢ ብር 50 በ1710 ቀናት ሲባዛ በድምሩ ብር 85.500 (ሰማንያ አምስት ሺህ አምስት መቶ) ከወለድ ወጭና ኪሣራ ጋር ተከሳሽ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

የከሣሽ ክስና ማስረጃም ለተከሣሽ ደርሶ በሰጠው መልስ በመካከላቸው የመኪና ሽያጭ ውል የተደረገ መሆኑን አምነው በፍ/ቤት ትእዛዝ እስከ የካቲት 30 ቀን 1993 ዓ.ም መኪናው ከተንቀሳቀሰ ከዚያ ወዲህም ቢሆንም ለፍ/ቤት አመልክቶ ማንቀሣቀስ እየቻለ በገዛ ፈቃዱ አቁሞት ከሆነ ተከሣሽ ኃላፊ ሊሆን አይችልም፡፡ እንደዚሁም ከሣሽ መኪናውን ከተረከበ 7 ዓመት ያለፈው ስለሆነ ውሉ ጉዳት አድርሷል በውሉ አፈፃፀም ጉዳት ደርሷል ሳይባል በውሉ መሠረት ስም እንዳዛውር በተወሰነው መሠረት ስም ከማዛወር በስተቀር ሌላ ዕዳ ለመክፈል የገባሁት ግዴታ ስለሌለ ክሱ ከኪሣራ ጋር ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መዝገቡን መርምሮ ለክሱ ምክንያት የሆነው (ታክሲ) መኪና ባለቤትነቱን ተከሣሽ በሕግ ተገደው በከሣሽ ስም እንዲያዛውሩ እስከተደረገበት ግንቦት 9 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ የመኪናው ባለቤትነት በተከሣሽ ስም ተመዝግቦ እንደነበር የሚታመን ሲሆን በመኪናው ላይ ቦሎ ለማስለጠፍ ደግሞ የመኪናው ባለንብረት መቅረብ እንዳለባቸውና ተሽከርካሪውን ለምርመራ ክፍሉ በማሣየት ማስመርመር እንደሚገባቸው የተረጋገጠ ሲሆን ተከሣሽ ግን ይህን ባለማድረጋቸው ተሽከርካሪው ሊንቀሣቀስ ያልቻለ በመሆኑ በከሣሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ናቸው ካለ በኂላ መኪናው ያለ ሥራ የቆመበትን የ3 ዓመት ከ2 ወር ከ9 ቀን በድምሩ ብር 57.450 (አምሣሰባት ሺህ አራት መቶ ሃምሣ) ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ አመልካች ለተጠሪ የጉዳት ኪሣራ ሊከፍል ይገባል በማለት በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች ለተጠሪ የጉዳት ኪሣራ ሊከፍል ይገባልን? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ ይዘን ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የጉዳት ኪሣራ ጥያቄ ከውልም ሆነ ከውል ውጭ ባለ ግንኙነት ላይ ተመሥርቶ ሊቀርብ የሚችል ሲሆን ከውል ጋር በተያያዘ የሚቀርብ የጉዳት ኪሣራ ጥያቄ የሚመዘነው ውሉ በአግባቡ ተፈጽሞ ቢሆን ኖሮ ጥያቄ አቅራቢው ሊኖረው ከሚችለው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ጋር ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ በግራ ቀኙ መካከል በመኪና ሽያጭ ውል ላይ ተመሥርቶ የነበረ ግንኙነት ተቋቁሞ እንደነበር የተረጋገጠ ሲሆን በዚሁ ውል መሠረትም የመኪናው ገዢ የሆኑት የአሁን ተጠሪ ሻጩ (አመልካች) ባለቤትነቱን በስሜ ያላዛወረ ስለሆነ እንዲያዛውር ይወሰንልኝ የሚል አቤቱታ ለፍ/ቤት አቅርበው ይሄው አቤቱታም በፍ/ቤት ተቀባይነት አግኝቶ ሻጭ የመኪናውን ባለሀብትነት በገዢው ስም ሊያዛውሩ ይገባል በማለት ፍ/ቤቱ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩልም አመልካች ስም ማዛወር እንደሚገባቸው በፍርድ የተወሰነ ቢሆንም በውል ግዴታ ውስጥ ባለዕዳ የሆነው ወገን የጉዳት ኪሣራ ከፋይ የሚሆነው ውሉን አሟልቶ ሣይፈጽም ሲቀር ወይም ውሉን ከስምምነቱ ውጭ አዘግይቶ በመፈፀሙ የተነሣ በሌላው ተዋዋይ ወገን ላይ በገንዘብ የሚተመን ኪሣራ የደረሰ መሆኑ ሲረጋገጥ እንደመሆኑ መጠን አመልካች ስም የማዛወር ኃላፊነት አለበት ተብሎ ውሣኔ የተሰጠ ቢሆንም የሽያጭ ውሉ በተደረገ ጊዜ የመኪናው ባለቤትነት የተመዘገበው በሻጭ በአሁን አመልካች ስም ሣይሆን በሌላ ግለሰብ ስም መመዝገቡን ተጠሪ ያውቅ



እንደነበር ሻጭም መኪናውን ለመሸጥ የሚያስችል የውክልና ሥልጣን የነበረው ስለመሆኑ ገዢው (ተጠሪ) አረጋግጦ ግዢውን እንዳልፈፀመ መገንዘብ የተቻለ ከመሆኑም በላይ አመልካች የመኪናውን ባለሀብትነት በተጠሪ ስም ለማዛወር የበኩሉን ጥረት አድርጎ ነገር ግን በተጠሪ አለመቅረብና አለመከታተል ምክንያት የስም ዝውውሩ ተግባራዊ ሊሆን እንዳልቻለም ተረጋግጧል፡፡

የስም ዝውውሩ ውጤታማ ሊሆን የሚችለው በሻጩ ቀጥተኛ የውል ፈፃሚነት (specific performance) ብቻ የሚከናወን ሣይሆን የገዥውም ድጋፍ ታክሎበት ለውጤት የሚበቃ በመሆኑ በዚሁ መሠረት የበኩሉን አስፈላጊ ድጋፍ ተጠሪ ለአመልካች በመስጠት ስም እንዲዛወር ማድረግ ሲገባው ይህንን ባልፈፀመበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ለተጠሪ የጉዳት ኪሣራ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብሔር ሕጉ ውልን አለመፈፀምንና የጉዳት ኪሣራ አከፋፈልን አስመልክቶ በቁጥር 1771 እና ተከታዮቹ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ጋር የተገናዘበ ባለመሆኑ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 11081 በጥቅምት 2 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 50188 በሰኔ 13 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበባቸው ስለሆነ በፍ.ብ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ. 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የጉዳት ኪሣራ ሊከፍል አይገባም በማለት ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 32222

የካቲት 4 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መሰሠ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** አቶ መሐመድ ኢብራሂም ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ታይደር ማች - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በአስረጂነት ያቀረቡት ውል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 መሠረት በውል አዋዋይ ፊት ያልተደረገ ስለሆነ ክስ የቀረበበትን ቤት ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ በመስጠታቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ የአሁኑ ተጠሪ በመልካች ላይ በጋምቤላ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ በጋምቤላ ከተማ ወረዳ 1 ቀበሌ 03 ክልል በስሜ ተመዝግቦ ከሚገኘው ሁለት ክፍል ቆርቆሮ ቤት አንዱን ተከሣሽ /የአሁን አመልካች/ ይዞ ሰለሚገኝ እንዲለቅ ይወሰንልኝ በማለት የጠየቀ ሲሆን ተከሳሽም በሰጠው መልስ ክስ የቀረበበትን ቤት ከከሣሽ ጋር በነበረን ውል መሠረት በእሱ እጅ በነበረው ይዞታ ላይ ሁለት ክፍል ቤት ሰርቼ አንዱን ክፍል ለእሱ ሌላውን ክፍል ደግሞ ለእኔ እንዲሆን የተስማማን ስለሆነ ክሱ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ተከሣሽ ክስ የቀረበበት ቤት ባለመብት ስለመሆኑ ያረጋግጥልኛል በማለት ያቀረበው ውል ሥልጣን በተሰጠው መንግሥታዊ



አካል ያልፀደቀ ከመሆኑም በላይ ከሣሽ ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች ቤቱና ይዞታው የእራሱ መሆናቸውን የሚያረጋግጡ ስለሆነ ክስ የቀረበበትን ቤት ተከሣሽ ለከሣሽ ሊያስረክብ ይገባል በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

በተከሣሽ ይግባኝ ባይነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የጋምቤላ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ በግራ ቀኙ መካከል መስከረም 1 ቀን 1988 ዓ.ም. ተደርጓል የተባለው ውል ሥልጣን ባለው አካል የፀደቀ ስላልሆነ ግዴታን ሊፈጥር አይችልም ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች ውሉ ተቀባይነት ሳያገኝ የመቅረቱ አግባብነት ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ በግራ ቀኙ መካከል ተደርጓል የተባለው ውል በሕግ አግባብ የተደረገ ስላልሆነ ተቀባይነት የለውም ተብሎ በበታች ፍ/ቤቶች መወሰኑ አግባብነት አለውን? የሚለው በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው የአሁን ተጠሪ በጋምቤላ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ዳኝነት የጠየቁት ተከሣሽ ቤቱን ያለአግባብ ይዞ ስለሚገኝ እንዲመልስ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ ተከሣሽ የአሁን አመልካችም ቤቱን ያለአግባብ አለመያዛቸውን ገልጸው መስከረም 1 ቀን 1988 ዓ.ም. ከከሣሽ ጋር ባደረጉት ውል መነሻነት በከሳሽ ይዞታ ላይ ተከሣሽ ሁለት ክፍል ቤት እንዲሰሩና አንዱ ለከሳሽ ሌላው ቤት ደግሞ ለተከሣሽ እንዲሆን በተስማሙት መሠረት ሁለት ክፍል ቤቱን ሠርተው አንዱን ከሳሽ እንደተረከቡና ሁለተኛውንና ክስ የቀረበበትን ቤት ደግሞ ተከሣሽ የተረከቡት መሆኑን ገልጸው ክሱ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሉ የጸና አይደለም ያለው ውል ለማዋዋል በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት የተደረገ ስላልሆነ ነው በማለት ነው፡፡ በእርግጥ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ የሚደረጉ ውሎች ውል ለማዋዋል በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ካልተደረጉ ዋጋ ሊኖራቸው እንደማይችል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 እና 1720 ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ግራ ቀኙ መስከረም 1 ቀን 1988 ዓ.ም. ያደረጉት ውል ይዘት ሲታይ ውሉ በተደረገ ጊዜ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ያልነበረ በመሆኑ በዚህ ውል መነሻነት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት ከአንዱ ወደ ሌላው ተላልፏል የሚያስብል አይደለም፡፡ ከስምምነታቸውም በግልጽ መገንዘብ የሚቻለው ይዞታው የከሳሽ በሆነ ቦታ ላይ ተከሣሽ ሁለት ክፍል ቤቶችን በመስራት አንዱን ለከሳሽ በመስጠት ሌላውን ቤት ደግሞ ለእራሳቸው ለመውሰድ መስማማታቸውን ስለሆነ ይህ ስምምነት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 ድንጋጌ የሚገዛ አይሆንም፡፡ ይልቁንም የማይንቀሳቀስ ንብረት መሥራትና መሸጥን አስመልክቶ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2876 ላይ እንደተመለከተው አንዱ ወገን ተዋዋይ ለሌላው ወገን ተዋዋይ አንድ ቤት አንድ የቤት ክፍል ወይም ገና የሚሰራ ሕንፃ ለመስጠት ግዴታ የሚገባበት ውል የአንድ ሕንፃ የሥራ ውል ከሚባል በስተቀር የሽያጭ ውል ሊባል እንደማይችል ስለተመለከተ የበታች ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 አኳያ መመልከታቸው በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩልም በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ውል የሕንፃ ሥራ ውል ነው ከተባለ የውሉን አመሰራረት የሚገዛው የማይንቀሳቀስ ንብረት የሥራ ውልን አስመልክቶ በቁጥር 3019 እና 3020 ላይ በተመለከተው መሠረት ሲሆን ከዚህ አኳያም ውሉ የተለየ የአፃፃፍ ሥርዓትን ተከትሎ መደረግ የሚገባው ሳይሆን የሥራው መጀመሪያም ሆነ የዋጋ ክፍያ ውሉ በአግባቡ እንደተመሠረተ የሚያረጋግጥ እንደሆነ በቁጥር 3020/2/ ላይ የተደነገገ በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች በግራ ቀኙ መካከል በሕግ አግባብ



የተቋቋመ ውል የለም በማለት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የጋምቤላ ክልል ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00321 በጥር 15 ቀን 1999 ዓ.ም. እንደዚሁም የጋምቤላ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00605 በሰኔ 22 ቀን 1997 ዓ.ም. በግራ ቀኙ መካከል የተደረገ ውል የሰጧቸው ውሳኔዎች ውል የለም በማለት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል በሕግ አግባብ የተቋቋመ ውል ያለ ስለሆነ ውሉን አስመልክቶ ባነሱት ክርክር ላይ የጋምቤላ ክልል ዞን ከፍ/ፍ/ቤት የበኩሉን ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 341 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 32899

ግንቦት 21 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች** ፡- ወ/ሮ አስካለ ማርያም ታደሰ ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- አቶ ተሾመ ካሣዬ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች በመጋቢት 5 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ተከሳሽ በሱልልታ ሙሎ ወረዳ የማህበር አባል ነኝ በማለት ድርሻዬ ነው ያሉትን ቦታ በብር 18,400 (አስራ ስምንት ሺ.ህ አራት መቶ) ሸጠውልኝ የቦታውን ካርታ አስረክበውኛል፡፡ ቦታውን አጥሬ ለመስራት ስሞክር ግን ቦታው የተገኘው በሕገወጥ መንገድ ነው በማለት የመሬት አስተዳደር ቦታውን ወርሶብኛል፡፡ በመሆኑም ተከሳሽ ገንዘቤን እንዲመልስልኝ ይወስንልኝ የሚል ክስ አቅርበዋል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ ሌላ ቤት የገዛባቸው አቶ ኤልያስ ደምሴ የተባሉት ተከሳሽ ደግሞ በሰጡት መልስ ይህ ክስ መቅረብ የሚገባው በቤት ሥራ ማህበሩ እንጂ በእኔ ላይ አይደለም፡፡ ከሣሽ ካርታውን የተቀበሉት ከማህበሩ እጅ በመሆኑ ስለቦታው ሕጋዊነት መጠየቅ ያለባቸው ማህበሩ ነው፡፡ በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ከከሳሽ አልተቀበልኩም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ካዳመጠና ማስረጃም ከሰማ በኂላ ተከሳሽ ገንዘቡን መቀበላቸውንና በውላቸው ደግሞ ቦታውን ለከሣሽ ካላስረከብኩኝ ገንዘቡን እመልሳለሁ_በማለት ግዴታ መግባታቸውን በማስረጃ ስለተረጋገጠ በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ለከሳሽ ይክፈሉ ሲል ወስኗል፡፡

በመቀጠልም ፍ/ቤቱ የአሁኑ ተጠሪ በተከሳሽ ስም የተመዘገበው ቤት የገዛሁት በመሆኑ እግዱ ይነሳልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ደግሞ በተከሳሽ ላይ ቀደም ብሎ የወሰዱት ገንዘቤን እንዲመልሱልኝ ያስወሰንኩኝ በመሆኑና ቤቱም ተሸጦ ገንዘቤን የማስመልስበት የተከሳሹ ሃብት በመሆኑ እግዱ መነሳት የለበትም በማለት ተቃውመዋል፡፡

ፍ/ቤቱም አቶ ተሾመ ካሣዬ ገዛሁት የሚሉትን ቤት የሽያጭ ውል ስልጣን ባለው አካል ያልተመዘገበ በመሆኑ የሽያጭ ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2878 መሠረት ውጤት የለውም፡፡ እግዱ በቀረበው አቤቱታ መልኩ ሊነሳ የሚችልበት ምክንያት የለም በማለት ጥያቄውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

በዚህ የእግዱ ይነሳልኝ ጥያቄ መሠረት የአሁን ተጠሪ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱም ይግባኝ ባይ ቤቱን ከአቶ ኤልያስ ደምሴ መስከረም 19 ቀን 98 ዓ.ም በተፈፀመ የሽያጭ ውል ገዝተው ስም ለማዛወር በሒደት ላይ መሆኑን ገልጾ ነው ውልና ማስረጃ የእግድ ትዕዛዙን የመዘገበው፤ ሽያጩ በክብር መዝገብ የተመዘገበው የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለመመዝገብ ስልጣን ባለው አካል በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት እግዱ አይነሳም ማለቱ በአግባቡ አይደለም በማለት እግዱ እንዲነሳ ሲል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ይግባኝ ቀርቦለት ይግባኙን መሠረት በማድረግ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ የፌ/ከ/ፍ/ቤቱን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ለዚህ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረቡትም የፌ/ከ/ፍ/ቤትና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰጡትን ውሣኔ በመቃወም ነው፡፡ ቅሬታውም አቶ ኤልያስ ደምሴ ገንዘቡን ከንብረታቸው እንዲከፍሉኝ ተወስኖልኛል፡፡ አቶ ተሾመ ካሣዬ ቤቱን ገዝቸዋለሁ ቢሉም የሽያጭ ውሉ ስልጣን ባለው አካል አልተመዘገበም፡፡ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሽያጭ ውሉን ለማስመዝገብ ጥያቄ መቼ

እንዳቀረበ ሳያጣራ ተመዝግቧል በማለት እግዱን ያነሳው በአግባቡ አይደለም፡፡ ጠ/ፍ/ቤቱም የከ/ፍ/ቤቱን ውሣኔ ማጽናቱ ተገቢ አልነበረም፡፡ ሁለቱም ፍርድ ቤቶች በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2878 የተደነገገውን ሳያገናዝቡ የሰጡዋቸው ውሣኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው ስለሆኑ ተሽረው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ሊፀናልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

ተጠሪው ደግሞ በሰጡት መልስ የሽያጭ ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2878 መሠረት እስከተመዘገበ ድረስ ስም ያለመዛወር የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡ የሽያጭ ውሉ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ ቀደም ብሎ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ/ 16109 ሚያዝያ 12 ቀን 99 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ የሽያጭ ውሉ ከመዝገቡ ጋር መያያዝ በቂ ነው ተብሏል፡፡ በመ/ቁ/ 21448 የተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1123 ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የለውም፡፡ የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠው የሽያጭ ውሉ ከተያያዘ በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊፀናልኝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በበኩላችን ደግሞ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በቤቱ ላይ የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ በተጠሪው አመልካችነት ሊነሳ ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 የሚገኘው የቤት ቁጥር አዲስ የካርታ ቁጥሩ ኮ/ቁ/ 09/3/መ/00/180/ 6904/00 በሆነው ቤት ላይ የእግድ ትዕዛዝ የሰጠው መጋቢት 29 ቀን 98 ዓ.ም ነው፡፡ ይህ የእግድ ትዕዛዝ ደግሞ በኮልፌ ቀራንዮ መሬት አስተዳደር ባለሥልጣን ተመዝግቧል፡፡ እግዱ በተመዘገበበት ጊዜም ቤቱ በአቶ ኤልያስ ደምሴ ስም የተመዘገበ መሆኑን እና የሽያጭ ውሉ ከማህደሩ ጋር የተያያዘ ቢሆንም የስም ማዞሩ ጉዳይ በሂደት ላይ ያለ መሆኑን የመሬት አስተዳደር ባለስልጣኑ ገልጾአል፡፡ ነገር ግን የመሬት አስተዳደር ባለስልጣኑ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል



ያለው የሽያጭ ውል መቼ ከመዝገቡ ጋር እንደተያያዘ አልገለፀም፡፡ በማስረጃነት ቀርቦ ከፍ/ቤቱ መዝገብ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን የሽያጭ ውል ጽሑፍም ስንመለከተው እላዩ ላይ ክብ የውሎችና የክብር መዝገብ ማስረጃ ማህተም ከማረፉ በስተቀር ይህ ማህተም መቼ የውል ጽሑፉ ላይ እንደተደረገ አይታወቅም፡፡ በሽያጭ ውሉ ጽሑፍ ላይም ይሁን ጀርባ ያረፈ አራት ማዕዘን ማህተም የለም፡፡ የሽያጭ ውሉ በክብር መዝገብ ውስጥ የተያያዘው መቼ እንደሆነ ካልታወቀ ደግሞ የተያያዘው የእግድ ትዕዛዙ ከመሰጠቱ በፊት ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የሽያጭ ውሉ የተያያዘው የእግድ ትዕዛዙ ከመሰጠቱ በፊት ነው ከተባለም በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2878 የአንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ንብረቱ ባለበት አገር በሚገኘው በማይንቀሳቀስ ሃብት መዝገብ ካልተፃፈ በቀር በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ውጤትን ሊያስገኝ አይችልም ተብሎ ከተደነገገው ጋር በማዛመድ ስንመለከተው የሽያጭ ውሉ በማይንቀሳቀስ ሃብት መዝገብ ከመፃፉ በፊት የሽያጭ ውሉ መኖር ያለመኖሩ አስቀድሞ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ይህ በተጠሪውና በአቶ ኤልያስ ደምሴ መካከል ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል ግን በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1723 በፍ/ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት የተሰራ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ በመሆኑም ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል ጽሑፍ በማይንቀሳቀስ ሃብት መዝገብ የተፃፈው ሳይረጋገጥ በመሆኑ ውሉ በመልካች ላይ የሚያመጣው ለውጥ ወይም የሚያስገኘው ውጤት የለም፡፡

በተጠሪው በመከራከርያነት የተጠቀሰው ቀደም ብሎ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ/ 16109 የሰጠውን ውሣኔ ስንመለከተውም ፍ/ቤቱ የውሉ ከማይንቀሳቀስ ሃብት መዝገብ ጋር መያያዝ በቂ ነው ያለው የሽያጭ ውሉ ግንቦት 9 ቀን 1987 ዓ.ም በውልና ማስረጃ ምዝገባ መምርያ አዋዋይነት የተደረገ መሆኑን

በመመልከቱ ምክንያት በመሆኑ ጉዳዩ በዚህ መዝገብ ከሚታየው ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ ባለመሆኑ የተጠሪው ክርክር አግባብነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን የሽያጭ ውሉን ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ተረጋግጦ የቀረበለትን የሽያጭ ውል ተቀብሎ ከማይንቀሳቀስ ሃብት መዝገብ ላይ ከማያያዝና ከመፃፍ በስተቀር የማዋዋልና የማረጋገጥ ስልጣን ስለሌለው የፌዴራል ከፍ/ፍ/ቤትና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የመሬት አስተዳደሩ ባለስልጣን የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሽያጭ ውል የመመዝገብ ስልጣን አለው፤ የሽያጭ ውሉ በዚሁ ሁኔታ የተመዘገበ በመሆኑ እግዱ መነሳት አለበት በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና መታረም የሚገባው ነው፡፡

በመሆኑም አመልካች ቀደም ብለው ክርክር ባስነሰው ቤት ላይ የእግድ ትዕዛዝ ያሰጡት ከአቶ ኤልያስ ደምሴ የሚፈልጉትን ገንዘብ ለማስመለስ በመሆኑና በዚሁ መሠረትም ያስወሰኑ ስለሆነ ቤቱን በሐራጅ በማሸጥ ገንዘባቸውን የማስመለስ መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡ ይህ መብታቸው ቀሪ ሊሆን ይችል የነበረው የቤቱ ባለቤትነት ከአቶ ኤልያስ ደምሴ ወደ ተጠሪ ዞሮ ቢገኝ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ቤቱ በአቶ ኤልያስ ደምሴ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ በመሆኑና በማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ የተያያዘው የሽያጭ ውልም ስልጣን ባለው አካል ያልተረጋገጠ በመሆኑ ቀደም ብሎ የተሰጠው እግድ ተነስቶ የባለቤትነቱ ስም ወደ ተጠሪው እንዲዛወር ማድረግ ተጠሪው ያለአግባብ እንዲጠቀሙ አመልካች ደግሞ በፍርድ ያገኙትን መብት እንዲያጡ የሚያደርግ በመሆኑ እግዱ በተጠሪው አመልካችነት የሚነሳበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ በዚሁ ምክንያትም የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና ሊሻር የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡



<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 29717 ሐምሌ 17 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 50420 መጋቢት 13 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው በመሆናቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 የሚገኘው በካርታ ቁጥር ኮ/ቁ/09/3/ መ/00/180/6904/00 የተመዘገበው ቤት ላይ በመ/ቁ/ 32777 ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው እግድ በተጠሪው አመልካችነት ሊነሳ የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ እግዱ ሊነሳ የሚችለው አመልካች ከአቶ ኤልያስ ደምሴ እንዲከፈላቸው የተወሰነላቸው ብር 18,400 ሲከፈላቸው ወይም ደግሞ ቤቱን በሐራጅ ለመሸጥ እንዲቻል አመልካች እግዱ እንዲነሳ ሲጠይቁ ነው በማለት ተወስኗል፡፡ በዚሁ መሠረትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 32777 ጥቅምት 22 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን እንዲችሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ

# የ ጠ በ ቆ ች
# ፈ ቃ ድ

የሰበር መ/ቁ 25287

ሐምሌ 29 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጐስ ወልዱ

ወ/ት ሂሩት መለሰ

አቶ መድህን ኪሮስ

አቶ በላቸው አንሺሶ

አመልካች፡- ሜድሮክ ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር አልቀረበም

ተጠሪ፡- አቶ በዛወርቅ ሺመላሽ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የክርክሩን አመጣጥ በተመለከተ የአሁን ተጠሪ የሥር ከሣሽ መጋቢት 18 ቀን 1993 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ በተከሣሽ ድርጅት ውስጥ ከግንቦት 24 ቀን 1989 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥቅምት 20 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ በሕግ አገልግሎት ሃላፊነት ተቀጥሬ ያገለገልኩ ሲሆን በፌደራል ፍ/ቤቶች ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥን ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/92 መሠረት ለተከሳሹ አገልግሎት ለመስጠት በመቸገሬ ምክንያት ተከሣሹ ሁኔታውን እንዲያሻሽል ብጠይቅ ተከሣሹ የሥራ ውሌን አቋርጧል፡፡ የተከሳሹ ሥራ አስኪያጅ በብር 5,000 /አምስት ሺህ ብር/ ደመወዝና የመኪና አበል (በተጨማሪነት) የቀጠሩኝ ቢሆንም ይህ ክፍያ ሣይከፈለኝ የቆየ በመሆኑ የ43 ወራት የአገልግሎት ቀሪ ክፍያ ብር 76,411፣ የመኪና ማካካሻ ክፍያ ብር 43,000፣ የትራንስፖርት አበል ብር 21,500፣ እ.ኤ.አ. ህዳር 23 ቀን 1999 በተፃፈ ደብዳቤ የታመነ ብር 1,349.74፣ ዳላስ ሄጄ የተመለስኩበት የውሎ አበል ብር 5,049፣ የአውሮፕላን ትኬት ክፍያ ብር 2,607፣ የ3 ወር ያልተከፈለ አበል ብር 19,500፣ የ3 ዓመት ወለድ ብር 30,495፣ በድምሩ ብር 199,911.74

(አንድ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ አንድ ብር ከሰባ አራት ሳንቲም) እንዲከፈለኝ ወደ ሥራም እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

ተከሳሽም ጥቅምት 14 ቀን 1994 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ የከሣሽ የክፍያ ጥያቄዎች በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 162 መሠረት በይርጋ የታገዱ ናቸው፤ ሊከፈላቸው የሚገባ ደመወዝ ላይ የተደረገ ስምምነት የለም፣ ደመወዛቸው ሲከፈላቸው እንደቆየው ነው፣ ፊርመው ሲቀበሉት በነበረው ገንዘብ ላይ ክርክር መፍጠራቸው አግባብ አይደለም፤ ዳላስ ሄደው የተመለሱበት የውሎ አበል ተከፍሏቸዋል፤ ብር 1,349.74 ሊከፈላቸው አይገባም፤ የአውሮፕላን ትኬቱን በተመለከተ ብር 2,607 ለመክፈል ፈቃደኛ ሆነን እያለ ከሣሽ ጥያቄ ባለማቅረባቸው ዕድሉ አልፏቸዋል፤ ከሣሽ የሶስት ወር ደመወዝና አበል ያሉት የመቼ እንደሆነ ያልተገለፀ ከመሆኑም ሌላ ከሣሽ እስከተሰናበቱበት ጊዜ ድረስ ያለ የሚገባቸው ደመወዝና አበል ተከፍሎአቸዋል፤ ከሣሽ የተሰናበቱት በአግባቡ ነው፤ የሚከፈላቸው ወለድም የለም በማለት ከተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ካደመጠ በኋላ ከሣሽ ያቀረቡት የአውሮፕላን ትኬት፣ የውሎ አበልና የብር 1,349.74 ክፍያ መከፈል ከነበረበት ጊዜ አንስቶ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ሲሰላ አንድ አመት ያለፈበት እንደመሆኑ ክፍያው በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 162 መሠረት በይርጋ የታገደ ነው፤ የደመወዝ ጥያቄውም እንደዚሁ ክስ ከቀረበበት ጊዜ አንድ አመት ወደኋላ በመቁጠር ሲታይ ጊዜ ያለፈበት በመሆኑ በአዋጅ አንቀጽ 162(1) መሠረት በይርጋ ቀሪ መሆን የሚገባው ነው፤ በሌላ በኩል ተከሣሽ ከሣሽን ከሥራ ያሰናበተበት ምክንያት አቶ ዳንኤል ተገኑ ከፃፉት ሪፖርት በመነሳት እንጂ ሌላ ተከሣሽ አልሰራም ያሉ ስለመሆናቸው የሚያሳይ ማስረጃ ባለመገኘቱ ሥንብቱ ሕጋዊ አይደለም፡፡ በመሆኑም የተከሣሽ ወደ ሥራ መመለስ ለሥራ ግንኙነቱ የማይመች ሊሆን ስለሚችል ከሣሽ ለከሣሽ የሥራ ስንብት፣ የሁለት ወር የማስጠንቀቂያና የስድስት ወር የካሣ ክፍያ በመክፈል ከሣሽን እንዲያሰናብት፤ ከይርጋ የተረፈውን ክፍያ በተመለከተ የከሣሽ የደመወዝ ብር 5,000 ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ ባለመኖሩና ከሣሽ የጠየቁት የሶስት ወር ክፍያም የመቼ እንደሆነ ተብራርቶ ስላልቀረበ የሶስት ወር ደመወዝ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም፤ ኃላፊዎቹ በመጻጻፍ ሒደት ላይ ስለነበሩ የከሣሽ ደመወዝ ብር 5,000 እንዲሆንላቸው ተወስኖ ሊሆን እንደሚቻል ተገንዝበናል፡፡ ልዩነቱን የይርጋ ጊዜ ከሚጀምርበት መጋቢት 21 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ እስከተሰናበቱበት ጥቅምት 20 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ ያለውን የስምንት ወር ልዩነት ተከሳሽ ለከሳሽ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች የፌ/መ/ደፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በድርድር ላይ ያለ ደመወዝ እንደተወሰነ ደመወዝ ተደርጐ ሊወሰድ አይችልም፣ የሠራተኛው ደመወዝ ብር 4,524 ነው፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት የሠራተኛው ደመወዝ ብር 5,000 ነው ያለው በአግባቡ አይደለም፡፡ ሰራተኛው እስከተሰናበቱበት ጊዜ ድረስ ደመወዛቸውን ሲያገኙ የቆዩ በመሆናቸው የስምንት ወር የደመወዝ ልዩነት ይከፈላቸው ተብሎ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔም ተቀባይነት የለውም፡፡ የስንብትና የማስጠንቀቂያ ክፍያ ለሰራተኛው እንዲከፈላቸው የተባለውም በአግባቡ አይደለም፡፡ ስንብቱ ሕገወጥ በመሆኑ ድርጅቱ የስንብት ክፍያና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ለሰራተኛው ሊከፍላቸው እንደሚገባ ግልጽ ቢሆንም ድርጅቱ ይህን ክፍያ መፈፀሙን በስንብት ደብዳቤው ስለገለፀና ሠራተኛውም ይህ ክፍያ አልተከፈለኝም ብለው ስላልተከራከሩ ድጋሚ ሊከፈላቸው አይገባም በማለት ድርጅቱ በብር 4,524 የደመወዝ ሒሳብ አስልቶ ካሣ ለሰራተኛው ይክፈል በማለት በፌ/መ/ደ/ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በመቀጠልም አመልካች የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለዚህ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታውን አቅርቧል፡፡ ቅሬታውም ተጠሪ ከሥራ የተሰናበቱት የተቀጠሩበትን ሥራ አልሰራም በማለታቸው ነው፡፡ ተጠሪው ሥራውን አልሰራም ያሉትም ኩባንያው የጥብቅና ፈቃድ ካላወጣልኝ ወይም ደግሞ የኩባንያው ሽሪክ (ባለአክሲዮን) አድርጐ ካላስመዘገበኝ ሥራ መስራት አልችልም፡፡ ከሠራሁ በወንጀል የሚያስጠይቀኝ በመሆኑ ሁኔታው ሊመቻችልኝ ይገባል በማለት ነው፡፡ እንዲህ የሚል ሐሳብ ስለማቅረባቸው ራሳቸው የፃፉት ደብዳቤ ያስረዳል፡፡ አቶ ዳንኤል ተገኑ የፃፉት ደብዳቤም ተጠሪው አልሰራም ማለታቸውን ያረጋግጣል፡፡ እንደዚሁም አቶ ዳንኤል ተገኑ በመከላከያ ምስክርነት ቆጥረናቸዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የወሰኑትም የቀረቡትን ማስረጃዎችና የተደረገውን ክርክር ባለመገንዘብና በመከላከያ ምስክርነት የቆጠርናቸውን አቶ ዳንኤል ተገኑን ምስክርነት ባለመሰማት ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪው የተቀጠሩበትን ሥራ አልሰራም በማለታቸው በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 26(1) እና 28 መሠረት የተሰናበቱ ናቸው፡፡ ስንብቱ ሕጋዊ ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤቶች ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ የአዋጁን ድንጋጌ የሚፃረር በመሆኑ ውሳኔቸው መሠረታዊ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበትና ሊታረም የሚገባው ነው የሚል ነው፡፡

ተጠሪው ደግሞ በሰጡት መልስ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ የመ/ደ/ፍ/ቤት ከሰጠው ውሳኔ የተለየ በመሆኑ አመልካች ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ ነበረበት፡፡ ይህን አልፎ ለሰበር ችሎት አቤቱታ ማቅረቡ ተቀባይነት የለውም፡፡ ድርጅቱ የጥብቅና ፈቃድ ካላስወጣልኝ ሥራ አልሰራም አላልኩም ባለአክሲዮን አድርጐ ካላስመዘገበኝ የምክር አገልግሎት አልሰጥምም አላልኩም፡፡ አመልካች አልተሰማልኝም ያሉት ምስክር የሚያውቀውን በጽሑፍ ስለገለፀ ለምን ቀርቦ አልመሰከረም አይባልም፡፡ ተፈጠረ ሳልኩት ችግር መፍትሄ ሳይሰጥበት ድርጅቱ እኔን ማሰናበቱ ተገቢ አይደለም፡፡ የፌ/ከ/ፍ/ቤት ድርጅቱ ለችግሩ መፍትሄ ሳይፈለግ የተወሰደው የሥራ ስንብት እርምጃ ሕገወጥ ነው በማለት የወሰነው በአግባቡ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበትና በአግባቡ የተሰጠ በመሆኑ ሊፀናልኝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ግራ ቀኙ ያደረጉት የቃል ክርክርም በመቅረፀ ድምፅ ከተሞላው ካሴት ወደ ጽሑፍ ተመልሶ ጽሑፉ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ አመልካች ያቀረበው የመልስ መልስም እንደዚሁ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

በበኩላችን ደግሞ አመልካች ኩባንያ ተጠሪውን ያሰናበታቸው በሕገወጥ መንገድ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም ተጠሪው ሐምሌ 7 ቀን 1992 ዓ.ም ለአቶ ንጉሴ አበራ በፃፉት ደብዳቤ አዋጅ ቁጥር 199/92 በአንቀጽ 31 የጥብቅና አገልግሎት መስጠት የሚፈልግ ሰው ከፍትህ ሚኒስቴር የጥብቅና ፈቃድ ማግኘት እንዳለበት ደንግጓል፣ እንደዚሁም የግል ድርጅት ወይም ኩባንያ ኃላፊ ወይም ባለአክሲዮን ወይም ሽሪክ የሆኑ ሰዎች የጥብቅና ፈቃድ ሳይኖራቸው የጥብቅና አገልግሎት መስጠት እንደሚችሉ በአዋጁ አንቀጽ 31(1) ሥር ተደንግጓል፣ እኔ እነዚህን መስፈርቶች ስለማላሟላ የጥብቅና አገልግሎት ብሰጥ በሕጉ እቀጣለሁ፣ የድርጅቱን ወይም የኩባንያውን ጥቅም ለማስጠበቅ በፍርድ ቤት መከራከር ሕጋዊ የውክልና ሥልጣን የተሰጠው ሰው፣ የኩባንያ ኃላፊ፣ ባለአክሲዮን ወይም ሽሪክ መሆንን ይጠይቃል፡፡ ፍ/ሚኒስቴር የጥብቅና ፈቃድ የሚሰጠው የሙሉ ሰዓት ተቀጣሪ ላልሆነ ሰው እንጂ ለሙሉ ሰዓት ተቀጣሪ አይደለም፡፡ በመሆኑም መመርያችሁን እጠብቃለሁ ማለታቸውን ተመልክተናል፡፡ የዚህ ደብዳቤ ይዘት ደግሞ የሙሉ ሰዓት ተቀጣሪ ሆኜ መስራት ብቀጥል የጥብቅና ፈቃድ ስለማይሰጠኝ የጥብቅና ፈቃድ ማግኘት አልችልም፡፡ ያለ የጥብቅና ፈቃድ ለመስራት የሚቻልበት ሌላው አማራጭ ደግሞ የኩባንያው ሐላፊ ባለአክሲዮን ወይም

ሽሪክ በመሆን ቢሆንም እኔ ባለአክሲዮን ወይም ሽሪክ ወይም ደግሞ የኩባንያው ኃላፊ ባለመሆኔ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት አልችልም፡፡ ፈቃድ ሳይወጣልኝ ወይም ባለአክሲዮን ሆኜ ሳልመዘገብ የሕግ አገልግሎት ለኩባንያው ብሰጥ በወንጀል የምቀጣ በመሆኑ መፍትሄ እስከሚፈለግልኝ ጊዜ ድረስ የተቀጠርኩበትን ሥራ አላከናውንም የሚል ነው፡፡

ተጠሪው መጋቢት 18 ቀን 1993 ዓ.ም ባዘጋጁት የክስ ማመልከቻና ታህሳስ 17 ቀን 94 ዓ.ም ባቀረቡት የመልስ መልስ የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት በቅድሚያ የጥብቅና ፈቃድ እንደሚያሻ፣ ፈቃድ ሳይኖር አገልግሎት መስጠት በወንጀል እንደሚያስጠይቅ፣ ለግል ኩባንያም ቢሆን ያለ ጥብቅና ፈቃድ አገልግሎት መስጠት የሚችሉት የድርጅት ሃላፊ ወይም ሽሪክ መሆን እንደሚያስፈልግ የጠበቆች አዋጅ ይደነግጋል፤ ላይሰንስ (የጥብቅና ፈቃድ) የማገኝበት መንገድ ሳይቀየስና ፈቃድ ሳይኖረኝ ብሰራ በወንጀል እንደምቀጣ እየታወቀ አቶ ዳንኤል ተገኑ ሆራ ሆቴል በሚመለከት የሕግ አገልግሎት እንድሰጥ ማዘዛቸው እኔን ለማስወንጀል ወይም ደግሞ የተመደበበትን ሥራ አልሰራም ብሏል በማለት እርምጃ ለማስወሰድ የታሰበ ነበር በማለት ያቀረቡት ክርክርም ኩባንያው የጥብቅና ፈቃድ ካላስወጣልኝ ወይም ደግሞ የባለአክሱዮንነት ምዝገባ ካላደረገልኝ ሥራውን አልሰራም ማለታቸውንና ሆራ ሆቴልን የተመለከተውን ሥራም ሳያከናውኑ መቅረታቸውን በማመን የተከራከሩ መሆናቸውን የሚያስረዳ ነው፡፡

አቶ ዳንኤል ተገኑ ሰኔ 7 ቀን 1993 ዓ.ም በፃፉት ደብዳቤ አቶ በዛወርቅ ሽመላሽ የሆራ ሆቴል ኮንትራትን በተመለከተ የሕግ አስተያየት እንዲሰጡ እንደነግራቸው በተሰጠኝ መመሪያ መሠረት ብነግራቸውም አዲሱ ሕግ አይፈቅድልኝም በማለት የሕግ አስተያየታቸውን ለመሰጠት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል በማለት የሰጡትን መግለጫ ተጠሪው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስና የመልስ መልስ ከጠቀሷቸው የመከራከሪያ ነጥቦች ጋር በማገናዘብ ስንመለከተው ተጠሪው በኩባንያው የጥብቅና ፈቃድ የማገኝበት



ሁኔታ ካልተመቻቸልኝ እና ፈቃዱን ካልያዝኩኝ በስተቀር ለድርጅቱ የሕግ አገልግሎት አልሰጥም በሚል አቋማቸው መሠረት ሆራ ሆቴልን የሚመለከት የሕግ አስተያየት ሳይሰጡ የቀሩ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

እንደዚሁም ተጠሪው ነሐሴ 9 ቀን 1992 ዓ.ም ለአቶ ንጉሴ በፃፉት ደብዳቤ ሆራ ሆቴልን የሚመለከት የሕግ አስተያየት እንድሰጥ በአቶ አልፍሬድ መመሪያ መሰጠቱን አቶ ዳንኤል ነግሮኛል እንዲህ ዓይነት የሕግ አስተያየት (ምክር) መስጠት በአዲሱ አዋጅ ሊያስጠይቅ ይችላል እያልኩኝ እየወተወትኩኝ እንደዚህ ዓይነት መመሪያ ለምን እንደተሰጠ አልገባኝም፣ አሁንም ቢሆን በቅድሚያ የጥብቅና ፈቃድ የማገኝበት መንገድ እንዲቀየስ አሳስባለሁ ማለታቸው ኩባንያው የጥብቅና ፈቃድ ስላላስወጣልኝ ሥራውን አላከናውንም በማለት የሕግ አገልግሎት ሳይሰጡ መቅረታቸውንና ለወደፊቱም ድርጅቱ ፈቃዱን ካላስወጣላቸው በስተቀር የተመደቡበትን የሕግ አገልግሎት የመስጠት ሥራ እንደማያከናውኑ የሚያስረዳ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪው በስር ፍ/ቤቶች ባደረኩት ክርክር አመልካች /የሥር ተከሳሽ/ ኩባንያው ለቀጠራቸው የሕግ ባለሞያዎች የጥብቅና ፈቃድ የማስወጣት ግዴታ ያለበት መሆኑንና ይህን ግዴታውን መወጣት ሲገባው ሳይወጣ የቀረ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ ኩባንያው ይህ ዓይነቱ ግዴታ ያለበት መሆኑን የሚደነግግ ሕግ አለ ብለው አልጠቀሱም አልተከራከሩምም፡፡ ኩባንያው ሰዎችን በባለአክሲዮንነት የሚመዘግብ ከሆነም የኩባንያውን መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በማድረግ ከሚጠይቁ በስተቀር ተጠሪው የሕግ አገልግሎት እንዲሰጡ ተብሎ በባለአክሱዮንነት ወይም በሽሪክነት ሊመዘግባቸው የሚገደድበት ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪም በፃፉት ደብዳቤ በምሳሌነት ጠቀሱት እንጂ ኩባንያው በባለአክሲዮንነት ወይም በሽሪክነት እንዲመዘግባቸው በግልጽ የጠየቁ ባለመሆኑ ይህን ነጥብ አመልካች በክርክሩ ውስጥ ማካተቱ ተገቢ አይደለም፡፡

ከዚህ በላይ በተዘረዘረው ሁኔታ ተጠሪው የጥብቅና ፈቃድ በኩባንያው አማካኝነት ካልወጣልኝ በስተቀር የተመደብኩበትን የሕግ አገልግሎት የመስጠት ሥራ አላከናውንም በማለት ሥራ ማቆማቸው ራሳቸው ባደረጉት ክርክር ያመኑበትና ከግራ ቀኙ በቀረቡት የጽሑፍ ማስረጃዎች የተረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪው የተቀጠርኩበትን ሥራ አልሰራም አላልኩም በማለት ለሰበር አቤቱታው በሰጡት መልስና በቃልም ባደረጉት ክርክር መግለፃቸው ተቀባይነት የለውም፡፡

ሌላው ቁምነገር ደግሞ ተጠሪው ኩባንያው የጥብቅና ፈቃድ ካላወጣልኝ የሕግ አገልግሎት ሥራ አልሰራም፣ ከሠራሁኝ በወንጀል እቀጣለሁ የሚሉት ቀደም ብለው የወሰዱትን የጥብቅና ፈቃድ ሳይመልሱና የሕግ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶችም በውክልና የሕግ ባለሞያዎችን እንዳያሰሩ በአዋጅ ባልተከለከለበት ጊዜ ነው፡፡ የጥብቅና ፈቃድ እያላቸው በውክልናም መሥራት እየቻሉ ለኩባንያው የሕግ አገልግሎት ብሰጥ በወንጀል እቀጣለሁ ማለታቸውም ግልጽ አይደለም፡፡

አመልካች ለቀጠራቸው የሕግ ባለሞያዎች ከፍትህ ሚኒስቴር የጥብቅና ፈቃድ የማስወጣት ግዴታ ሳይኖርበትና ተጠሪው ለአመልካች የጥብቅና ማለትም የሕግ አገልግሎት ቢሰጡ በወንጀል የሚቀጡበት የሕግ ምክንያት በሌለበት ጊዜ ተጠሪው ድርጅቱ የጥብቅና ፈቃድ ካላስወጣልኝ በስተቀር የተቀጠርኩበትን የሕግ ምክር አገልግሎት የመስጠት ሥራ አላከናውንም የሚሉበትና አመልካች ደግሞ ተጠሪው ምንም ሥራ ሳይሰሩ ሰራተኛዬ ናቸው በማለት ደሞዝ እየከፈለ የሚቆይበት ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪው በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 13(2) ሥር የተደነገገው የአሠሪውን ትእዛዝ የመቀበል ግዴታቸውን ያልተወጡ በመሆኑ አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 26(1) መሠረት ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሥራ ቅጥር ውሉን ለማቋረጥ ይችላል፡፡ አመልካች የሥራ ውሉን በአዋጁ አንቀጽ 26 እና 28 መሠረት ማቋረጡና ተጠሪውን ማሰናበቱም በአግባቡ ነው፡፡



በመሆኑም አመልካች ተጠሪውን ከሥራ ያሰናበታቸውን የተቀጠሩበትን የሕግ ምክር አገልግሎት የመስጠት ሥራ ለመስራት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ተጨባጭ የሥራ ትእዛዝን አልቀበልም በማለታቸው ምክንያት መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠና ተጠሪም ያመኑበት ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤቶች ስንብቱ ሕገወጥ ነው፣ አመልካች ለተጠሪው ካሣ ይከፈል በማለት ውሳኔ መስጠታቸው አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ፍርድ ቤቶቹ የግራ ቀኙን ክርክርና የቀረበላቸውን ማስረጃ በሚመለከት ውሳኔ መስጠት ሲገባቸው የቀረበላቸው ማስረጃ የሚያስረዳውን ቁምነገር በመተውና ተጠሪው በክርክራቸው ያመኑትን ከግምት ውስጥ ባለማስገባት የተጠሪውን የግል ማህደር በማስቀረብ ተጠሪው የተቀጠሩበትን ሥራ ለማከናወን ፈቃደኛ አለመሆናቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ከማሕደራቸው ስላላገኘን ለመስራት ፈቃደኛ ስላለመሆናቸው የሚያስረዳ ማስረጃ የለም፣ ስንብቱ ሕገወጥ ነው፣ አመልካች ለተጠሪው ካሣ ይከፈል በማለት የሰጡት ውሳኔም የአዋጅ ቁጥር 42/85 ዓላማን የሳተና ለተጠሪው የማይገባቸውን መብት ያጐናፀፈ በመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና መታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/08459 ህዳር 21 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 43679 ሚያዝያ 17 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪው ከሥራ የተሰናበቱት ድርጅቱ /ኩባንያው/ የጥብቅና ፈቃድ ካላወጣልኝ በስተቀር የተቀጠርኩበትን የሕግ ምክር አገልግሎት የመስጠት ሥራ አላከናውንም በማለታቸውና በተጨባጭም ሆራ

ሆቴልን የተመለከተ የሕግ አስተያየት አልሰጥም በማለታቸው ምክንያት መሆኑ በማስረጃ ስለተረጋገጠ ስንብቱ ሕጋዊ ነው፡፡ የሥራ ስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም በማለት ወስነናል፡፡ ፍፃፍ፡፡

3. ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ወጪና ኪሣራ ይቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ



# ው ር ስ

የሰ/መ/ቁ. 23322

ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ታፈሰ ይርጋ

አቶ መድሕን ኪሮስ

አቶ ዓሊ መሐመድ

አቶ ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አዳነች ወርዶፋ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** እነ ወ/ሮ አስናቀች ወርዶፋ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን አመጣጡም የአሁንዋ አመልካች ህዳር 10 ቀን 97 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ የውርስ አጣሪው በ16/2/97 ዓ.ም ያቀረቡት ሪፖርት በአግባቡ የቀረበ አይደለም፡፡ አጣሪው ሊጸድቅ የማይገባውን የስጦታ ውል መነሻ በማድረግ ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ በውርስ እዳነት መመዝገብ የማይገባውን እዳ መዝግበዋል፡፡ ያቀረብኳቸውን ማስረጃዎች በአግባቡ አልመረመረም፡፡ ወራሾች ሳንስማማበት የውርስ ንብረት ለወራሾች እንዲከፋፈል ወስነዋል፡፡ በመሆኑም የውርስ አጣሪው ሪፖርት መጽደቅ የለበትም በማለት አመልክተዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የውርስ አጣሪው የሟች የኑዛዜና ያለኑዛዜ ወራሾች እነማን እንደሆኑ፣ የሟች የውርስ ሃብት ምን እንደሆነ ከውርሱ ሐብት ላይ ሊከፈል የሚገባውን እዳ ምንነት እና በኑዛዜ የተሰጠ ስጦታ ለተቀባዩ መክፈልን በተመለከተ የግራ ቀኙን አቤቱታና ማስረጃ መርምረው ያቀረቡት ሪፖርት የሚነቀፍበት ምክንያት የለም፡፡ አመልካች አለኝ የሚሉት መብት ካላቸው ዳኝነት ከፍለው በክስ ከሚጠይቁ በስተቀር የውርስ አጣሪውን ሪፖርት ባለማጽደቅ በዚህ መዝገብ ሊጠይቁ የሚችሉበት ሁኔታ የለም በማለት አቤቱታውን ባለመቀበል ሪፖርቱን አጽድቆታል፡፡

የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ከአመልካች የቀረበለትን ይግባኝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡትም የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ትእዛዝ በመቃወም ነው፡፡ በአቤቱታው ውስጥ የተጠቀሱት ቅሬታዎችም የውርስ አጣሪው የሟችን ሃብት በአግባቡ አላጣሩም፡፡ በሕግ መፍረስ የሚገባውን የስጦታ ውል አጽድቀዋል፡፡ የቆጠርኳቸውን ማስረጃዎች ባለመስማት መብቴን አጣብበውብኛል፡፡ ያለአግባብ የውርስ ንብረቶችን ወራሾች እንድንከፋፈል ወስነዋል፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም የውርስ አጣሪው ያቀረቡትን ሪፖርት እንዳያጸድቅ፣ የውርስ ማጣራቱ ሥራ እንደገና እንዲካሄድ እንዲያደርግልኝ ያቀረብኩትን ጥያቄ ባለመቀበል ሪፖርቱን ማጽደቁ በአግባቡ አይደለም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ትእዛዝ መሰረትዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ትእዛዙ ሊሻርልኝ ይገባል የሚሉ ናቸው፡፡

1ኛ ተጠሪ ሐምሌ 30 ቀን 99 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ የውርስ አጣሪው በኑዛዜ ስጦታው ላይ ያሉትን ምስክሮች አስቀርበው በመስማት የኑዛዜ ስጦታው የህግ ስህተት የሌለበት መሆኑን አጣርተው የአሁንዋ አመልካችንና ሌሎቹን ወራሾች በዝርዝር መዝግበው ባደረጉት ማጣራት መሰረት ሪፖርታቸውን ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ማቅረባቸው በአግባቡ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶቹ ሪፖርቱን ለማጽደቅ የሰጡት ትእዛዝም መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም፡፡ በመሆኑም ትእዛዙ ሊጸድቅልን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ ደግሞ ሐምሌ 30 ቀን 99 ዓ.ም ጽፈው በሰጡት መልስ ውርስ አጣሪው የውርስ ንብረቱን በአግባቡ አላጣሩም የ1ኛ ተጠሪን ቤት በውርስ ንብረት ውስጥ ማካተት ሲኖርባቸው በስጦታ ያገኙት ነው በማለት መወሰናቸው ተቀባይነት የለውም፡፡ አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመውጣቱ በፊት

ሟች ለእኔ የሰጡኝን ቁጥሩ 432 የሆነውን ቤት በውርስ ንብረት ውስጥ ያለማካተታቸው ግን በአግባቡ ነው፡፡ በመሆኑም የውርስ አጣሪው ሪፖርት ባለበት ሁኔታ እንዲፀድቅ መደረጉ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

በበኩላችን ደግሞ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የውርስ ንብረት አጣሪውን ሪፖርት ምንም ጉድለት አላገኘሁበትም በማለት ያፀደቀው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም የውርስ አጣሪው ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ሪፖርት ቁጥሩ 432 የሆነው ቤት አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመውጣቱ በፊት ሟች ወ/ሮ ደጊቱ ደንጓሬ ለወ/ሮ አሰለፈች ወርዶፋ በስጦታ የሰጡዋቸው በመሆኑ የውርስ ሐብት አይደለም በማለት ወስኛለሁ፣ ቁጥሩ 431 የሆነው ቤትም የወ/ሮ አስናቀች ወርዶፋ የኑዛዜ ድርሻ ነው፣ አመልካች ስጦታዎቹ ፈራሽ ናቸው በማለት ቢከራከሩም የሚፈርስበትን ምክንያት አልገለፁም፣ ስጦታው እንዲፈርስ በፍርድ ቤት ጠይቀው ያስፈረሱበትን የፍ/ቤት ውሳኔ አላቀረቡም በማለት ያሰፈሩዋቸው ድምዳሜዎች ንብረቶቹን የማከፋፈል ዓይነት ሥራ ያከናወኑ መሆኑን እንደሚጠቁሙ ለመረዳት ችለናል፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 956 እንደተደነገገው የአጣሪው ሥራ ሟቹ አንድ ኑዛዜ ትቶ እንደሆነ መፈለግና በመጨረሻው ውርሱ የሚደርሳቸው ሰዎች እነማን እንደሆኑ ማረጋገጥ፣ የውርሱን ሃብት ማስተዳደር፣ መክፈያቸው የደረሰውን የውርስ እዳዎች መክፈል እና ሟቹ በኑዛዜ ያደረጋቸውን ስጦታዎች መክፈልና የኑዛዜውን ቃል ለመፈፀም ማንኛቸውም ሌሎች አስፈላጊ ጥንቃቄዎች ማድረግ ነው፡፡ እነዚህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት በሚያከናውንበት ጊዜ ደግሞ በኑዛዜው የውርስ ንብረት መሆናቸው ተጠቅሶ የክፍፍል ስርአትም የተቀመጠላቸውና ወራሾች በሙሉ የተስማሙባቸው ንብረቶችና መክፈያቸው የደረሰው የውርስ እዳዎች ሲኖሩ በወራሾቹ ስምምነት መሰረት ንብረቶቹን ሊያከፋፍልና እዳዎችንም ሊከፍል ይችላል፡፡



በኑዛዜው ላይ በተጠቀሱትና ባልተጠቀሱት ንብረቶች የውርስ ሃብት መሆን ያለመሆን ላይ ወራሾቹ ያልተስማሙና ክርክር ያነሱ ከሆነ ግን የአጣሪው ሥራና ሐላፊነት ወራሾች የተስማሙባቸውን ንብረቶች የውርስ ሃብት መሆናቸው መመዝገብ፡፡ ወራሾች ያልተስማሙባቸው ንብረቶችና እዳዎች ካሉ ደግሞ ማስረጃ በመሰማት ማስረጃው ምን እንደሚያስረዳ ሪፖርቱ ላይ በማስፈር እንዲያጣራ ላዘዘው ፍ/ቤት ማቅረብ እንጂ ንብረት አጣሪው ይህ ንብረት የውርስ ሐብት አይደለም የሚሉ ወራሾች ቢኖሩም ማስረጃ በመስማት የውርስ ሃብት መሆኑን ስለተገነዘብኩኝ ንብረቱ የውርስ ሃብት ነው በማለት ወስኛለሁ ወይም ደግሞ ማስረጃውን እንደተመለከትኩት ንብረቱ የውርስ ሐብት ያለመሆኑን ስላረጋገጥኩኝ የውርስ ሐብት አይደለም በማለት ወስኛለሁ ለማለት የሚያስችለው ሥልጣን የለውም፡፡

በዚህ ጉዳይ የውርስ አጣሪው ያደረጉትን የማጣራት ሥራ ስንመለከተው ወራሾቹ የውርስ ሐብት ናቸው በሚሉዋቸው ሁለቱም ቤቶች ላይ ገና ከጅምሩ አንስቶ ያልተስማሙና ክርክር ያነሱ በመሆኑ አጣሪው ማስረጃ መስማታቸው በአግባቡ ነው፡፡ ሁኖም አጣሪው በወራሾች መካከል የተደረገው ክርክር ምን እንደነበረ፣ የኑዛዜ ወራሾችና የሕግ ወራሾች እነማን እንደሆኑ፣ የግራ ቀኙ ማስረጃ ምን እንደሚመልስ፣ እንዲሁም ወራሾች የተማመኑባቸውና ያልተማመኑባቸው የውርስ ንብረቶችና እዳዎቹ ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ሪፖርት ማዘጋጀት ሲኖርባቸው ከዚህ አልፈው ወራሾችን አከራክረው ማስረጃ ከሰሙ በኋላ ክርክሩንና ማስረጃውን ከሕግ ጋር በማገናዘብ ይህ ንብረት የእገሌ እንጂ የእገሌ አይደለም በማለት መወሰናቸው ከተሰጣቸው የውርስ አጣሪነት ሥልጣን በላይ በመሄድ መደበኛ ፍ/ቤት በሚያከናውነው የዳኝነት ሥራ ውስጥ መግባት መሆኑንና ይህም ተገቢ ያለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ውርስ አጣሪው አዘጋጅተው ያቀረቡት ሪፖርት ውሳኔም ጭምር ያዘለ በመሆኑ ሪፖርቱ በቀረበለት ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መጽደቁ ደግሞ በአጣሪው

የተወሰነው ነገር በፍ/ቤት ተቀባይነት አግኝቶ የፀደቀ ተደርጐ ስለሚወሰድ አመልካች አዲስ ክስ አቅርበው የውርስ ድርሻቸውን ለማግኘት የሚያስችላቸውን መብት የሚያጣብብ ነው የሚሆነው፡፡ በመሆኑም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሪፖርቱን መርምሮ ያለበትን ጉድለት እንዲስተካከል ማድረግ ሲገባው እንዳለ ተቀብሎ ማጽደቁ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስለዚህ የውርስ ንብረት አጣሪው ያቀረቡት ሪፖርት የአጣሪንና የመደበኛ ፍ/ቤትን ሥራ አጠቃሎ የያዘ በመሆኑ ሪፖርቱ በአግባቡ የተዘጋጀ ባለመሆኑና የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሪፖርቱን ያፀደቀበትና የፌ/ከ/ፍ/ቤት ደግሞ የቀረበለትን ይግባኝ የሰረዘበት ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆነው ስለተገኙ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04036 ጥር 5 ቀን 97 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37777 ሕዳር 21 ቀን 98 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የሥር ፍ/ቤት የውርስ ማጣራት ሪፖርቱን ያፀደቀው ከነጉድለቱ ጭምር በመሆኑ መጽደቅ አልነበረበትም ብለናል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት እንደገና አጣሪ ሾሞ የውርስ ማጣራቱን ሥራ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 956 መሰረት እንዲከናወን በማስደረግ ሪፖርቱ በአግባቡ የቀረበ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ በሕጉ መሰረት አስፈላጊውን እንዲፈጽም በማለት ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን እንዲችሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



የሰበር መ/ቁ. 25869

ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

መድኅን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ አየለች አልታዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አስናቀች አየለ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በሰበር የቀረበው የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት እና ህዳር 27 ቀን 1993 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 5436 ሚያዝያ 3 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሰኔ 19 ቀን 1998 ዓ.ም ባቀረበችው አቤቱታ ስለጠየቀች ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች የሕፃን ዮናስ ወንድሙና የያሬድ ወንድሙ ወላጅ እናት እና ሞግዚት መሆኗን ገልፃ የሞግዚት አድራጊዎች ወላጅ አባት አቶ ወንድሙ ገብረየስ መጋቢት 3 ቀን 1981 ዓ.ም በሞት ተለይተዋል፡፡ ሟች አቶ ወንድሙ ከተከሣሽ /ከተጠሪ/ ጋር በባልና ሚስትነት እያሉ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 19 ቀበሌ 56 ቁጥሩ 115 የሆነ መኖሪያ ቤት ሠርተዋል፡፡ ስለዚህ የመኖሪያ ቤቱን ግምትና ቤቱን ለሱቅና ለሆቴል እያከራዩች የምታገኘው ገንዘብ ጭምር የሕፃኖቹ ወላጅ አባት የጋራ ሀብት በመሆኑና የውርስ ሀብት ክፍል እንድታካፍለኝ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ

አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ የውርስ ንብረት ክፍል ነው የተባለውን ሀብት አስመልክቶ የተለያየ ክርክርና ማስረጃ ያቀረበች ሲሆን ወ/ሮ ጥሩወርቅ ወንድሙ የተባለች ሴት በበኩሏ የሟች ወንድሙ ገብረየስ ወራሽ እና ልጅ ነኝ በማለት የወራሽነት ማስረጃዋን በማያያዝ በክርክሩ ጣልቃ ገብታለች፡፡

ፍርድ ቤቱ ቤቱና ሌሎች ንብረቶች ተገምተው እንዲቀርቡለት ትእዛዝ ሰጥቶ የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ መሀዲስ የቤቱ ጠቅላላ ዋጋ ብር 19,823.47 /አስራ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ሃያ ሶስት ብር ከአርባ ሰባት ሣንቲም/ ነው በማለት አስተያየት አቅርቧል፡፡ ከዚህ በኋላ የቤቱ ግማሽ ባለቤትነት የተጠሪ፣ የቤቱ ግማሽ ባለቤትነት ደግሞ የአመልካች ሞግዚት አድራጊዎችና የወ/ሮ ጥሩወርቅ ወንድሙ መሆኑን ከዘረዘረ በኋላ ተጠሪና ወ/ሮ ጥሩወርቅ ወንድሙ፣ ለአመልካች ብር 5,551.21/አምስት ሺ አምስት መቶ ሃምሣ አንድ ብር ከሃያ አንድ ሣንቲም/ በመክፈል ቤቱን በጋራ እንዲያስቀሩ ይህንን ማድረግ ካልቻሉ በሀራጅ እንዲሸጥ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርባ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች ልጆቹን ማሣደጊያ ቤት የለኝም፡፡ ንብረቱ በአይነት መካፈል እየተቻለ ተጠሪ ትጠቅልለው መባሉ ተገቢ አይደለም፣ ንብረቱም መሸጥ ካለበት መሀዲሱ ባቀረበው ግምት ሣይሆን በሀራጅ መሆን ይገባዋል፣ የዳኝነት በጋራ ክፈሉ መባሉ ተገቢ አይደለም፣ በአጠቃላይ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያመለከተች ሲሆን፤ ተጠሪ ደግሞ በበኩሏ ቤቱ አመልካችና ተጠሪ ባሉበት በመሐንዲስ የተገመተ በመሆኑ እና በአይነት ሊከፈል የማይችል በመሆኑ፤ አመልካች ያቀረበችው አቤቱታ ሕጋዊ መሠረት የለውም የሚል መልስ የሰጠች ሲሆን አመልካች የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡



ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ሟች ወንድሙ ገብረየስ እና ተጠሪ በባልና ሚስትነት ሲኖሩ በጋራ የሰሩት ቤትና የጋራ ንብረት መሆኑ አልተካደም፡፡ ሟች ወንድሙ የሞተ በመሆኑ እሱ በቤቱ ላይ ያለው የጋራ ባለቤትነት መብት ለወራሾቹ ዮናስ ወንድሙ፣ ያሬድ ወንድሙና ጥሩወርቅ ወንድሙ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ይተላለፋል፡፡ ስለሆነም የቤቱ የጋራ ባለንብረቶች የሟች ወንድሙ ገብረየስ ወራሾች እና ተጠሪ ናቸው፡፡

የማይንቀሣቀስ ንብረት የጋራ ባለቤት የሆኑ ሰዎች የማይንቀሣቀሰውን ንብረት በአይነት ለመከፋፈል የሚችሉ ከሆነ በአይነት መከፋፈል እንደሚችሉ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1272 የተደነገገ ሲሆን ንብረቱ በአይነት መከፋፈል የማይቻል ሲሆን ደግሞ በሀራጅ ተሸጦ ገንዘቡን እንደሚከፋፈሉ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1273 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ንብረቱ በአይነት ለመከፋፈል የሚችል ከሆነ የሟች ወራሾች እና ተጠሪ ንብረቱን እኩል መከፋፈልና የሟች ወራሾች ድርሻቸውን በስምምነት የሚከፋፈሉበት ዕድል ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ስለሆነም ቤቱ በአይነት ለመከፋፈል የሚቻል ሲሆን አመልካችና ተጠሪ ቤቱን በአይነት እንዲካፈሉ ትእዛዝ መስጠት ሲገባቸው አላግባብ ያለፉት በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ በተገለፀው መንገድ ቤቱ በአይነት ለመከፋፈል የሚችል ካልሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1273 መሠረት ግልጽ ሀራጅ ወጥቶ መሸጥ ይገባዋል፡፡ ተጠሪም ሆነች አመልካች የቤቱን ዋጋ በመክፈል የቅድሚያ ግዥ መብታቸው የሚጠበቀው ቤቱ በግልጽ ጨረታ ያወጣውን ከፍተኛ ዋጋ ገቢ ለማድረግ ዝግጁ ሆነው ሲገኙ እንጅ መሀዲሱ ገምቶ ያቀረበውን ዋጋ ገቢ በማድረግ አይደለም፡፡

ስለሆነም አመልካችና ተጠሪ ቤቱን በግልጽ ሀራጅ በሚያወጣው ዋጋ መሠረት ለማስቀረት የሚስማሙ ከሆነ በስምምነታቸው መሠረት መፈፀም አለበት፡፡ አመልካች እና ተጠሪ የማይስማሙ ከሆነ ግን ቤቱ በግልጽ ሐራጅ ተሽጦ የሟች ወራሽ የሆኑት ሶስት ልጆች ግማሹን ለሶስት እኩል እንዲካፈሉ፣ ተጠሪ ደግሞ የቤቱን ግማሽ ዋጋ እንድትወስድ መደረግ ይገባዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ባቀረበችው ክስ መሠረት በክርክሩ ፊት ሆና እያለ ከተጠሪ ጋር ዳኝነት በጋራ እንድትከፍል የሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የሌለውና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ህዳር 27 ቀን 1993 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 5436 ሚያዚያ 3 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. አመልካችና ተጠሪ የሚቻል ከሆነ ቤቱንና ቦታውን በአይነት እንዲከፋፈሉ ቤቱን በአይነት ለመከፋፈል የማይችሉ ከሆነ በግልጽ ጨረታ በሀራጅ ተሽጦ ግማሹን ተጠሪ እንዲወስዱ፣ ግማሹን የሟች አቶ ወንድሙ ወራሾች ለሶስት እኩል እንዲካፈሉ በማለት ወስነናል፡፡
4. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ወጭ ተጠሪ ብቻዋን መሸፈን አለባት ብለናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሣቸው ይቻቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



የሰ/መ/ቁ. 30158

ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ
ታፈሰ ይርጋ
መድሕን ኪሮስ
ዓሊ መሐመድ
ሱልጣን አባተማም

**አመልካቾች፡-** እነ ወ/ሮ ፀሐይነሽ አደም ሞግዚት ሐይሉ ሲሳይ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** የኮ/ል እሸቱ ተስፋዬ ወራሾች ጠበቃ ወርቅዬ አባይነህ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የአማራ ክልል የደሴ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 83/90 መጋቢት 17 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍታብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 04711 ጥቅምት 30 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍታብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 255/1999 ጥር 22 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ እናቴ ወ/ሮ አበበች ጀግሬና አክስቴ በየነች ጌቶ አሁን በህይወት የሉም፡፡ እናቴና አክስቴ ከሟች እናታቸው ወ/ሮ ጀማነሽ አቡዬ በውርስ የተላለፈላቸውንና በደሴ መዝገበ ማርያም የስንዴ ግብር እየከፈሉ ይዘውት የቆዩትን በደሴ ከተማ ቀበሌ 05 ቁጥሩ 407 የሆነ ቤትና 668 ካሬ ሜትር ቦታ አቶ በዛብህ ጉሽ አላግባብ የያዘና በስሙ ያዛወረ ስለሆነ ከውርስ ንብረቱ የሚደርሰኝን ብር 6000 (ስድስት ሺህ ብር ) እንዲከፍል

ይወሰንልኝ በማለት የወራሽነት ክስ በማቅረቡ ነው፡፡ አመልካቾቹ በክሱ የተገለፀው ቤትና ቦታ የአቶ በዛብህ ጉሽ የግል ንብረት እንደሆነና ይኸም በደሴ ማዘጋጃ ቤት እንደተመዘገበ ገልፀው የተከራሩ ሲሆን ንብረቱ ያልተከፍፈለ የውርስ ንብረት ነው ቢባል እንኳን የከሳሽ(ተጠሪ) ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የደሴ ወረዳ ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካቾች በኩል የቀረበውን ክርክር አልፈው ተጠሪ ያቀረበውን የሰው ማስረጃ መሰረት ንብረቱ የውርስ ንብረት ስለሆነ አመልካቾች ለተጠሪ እንዲያካፍሉ በማለት ውሣኔ ሰጥተዋል፡፡ የክለሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ የህግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለበትም በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች ይኸ ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት በደሴ ከተማ ቀበሌ 05 ቁጥሩ 407 የሆነው መኖሪያ ቤት ጥንት ለመዝገበ ምህረት ማሪያም የስንዴ ግብር ተገብሮበት ነበር በማለት ቤተክርስቲያን በፃፈው ቀላጤ መነሻ ለሰላሣ ሁለት ዓመት በስማቸው ያለውን ንብረት አካፍሉ መባላችን መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ንብረቱ በአመልካች ባለቤትና አውራሾች በዛብሕ ጉሽ ስም ስለሆነ ተጠሪዎች ሊጠየቁ ይችላሉ የሚለው ውሣኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው ንብረቱ በውርስ ከወ/ሮ ጀማነሽ አቦዬ በውርስ የተላለፍ ነው፡፡ የተጠሪ እናትና አክስት ይኖሩ ነበር ተጠሪ አውራሽ እናታቸው 1989 ዓ.ም ሞተው በ1989 ዓ.ም የወራሽነት ጥያቄ ያቀረቡ ስለሆነ የይርጋ የጊዜ ገደብ አልተላለፈም፡፡ ንብረቱ የሟች ወ/ሮ ጀማነሽ አቦዬ ስለሆነና ለተጠሪ እናትና አክስት በውርስ የተላለፈ በመሆኑ ተጠሪ ድርሻ መጠየቃቸው ህጋዊ ነው የሚል መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካቾች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎት የአመልካችንና የተጠሪን የቃል ክርክር



ሰምቷል፡፡ ይህ ችሎት ግራ ቀኙ የአከራካሪውን ቤት ባለቤትነት አስመልክቶ ያቀረቡት ክርክር ከመታየቱ በፊት የተጠሪ ክስ በይርጋ የጊዜ ገደብ ይታገዳል ወይስ አይታገድም? የሚለውን ጭብጥ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ተጠሪ ለደሴ ወረዳ ፍርድ ቤት አስቀርቦ ካሰማቸው እና ፍርድ ቤቱ በውሣኔው ላይ የምስክርነት ቃላቸው ከመዘገበው አንደኛ ምስክር ለመረዳት የሚቻለው የተጠሪ እናት እና አክስት አውራሽ ናቸው የተባሉት ወ/ሮ ጀማነሽ አቡዬ የሞቱት በ1949 ዓ.ም ነው፡፡ ይህ ተጠሪ ባቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ከዚህ በኋላ የተጠሪ እናት ወ/ሮ አበበች ጀግሬና አክስታቸው ወ/ሮ በየነች ጌቶ የእናታቸው የውርስ ንብረት እንዲከፈልና ድርሻቸው በስማቸው እንዲዞር ያቀረቡት ክስ የለም፡፡ ንብረቱንም በስማቸው አላዞሩም፡፡ በተቃራኒው የአንደኛ አመልካች ባለቤትና የሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች አባት አቶ በዛብህ ጉሽ የቤቱን ስመ ንብረት በስማቸው አዛውረውና በደሴ ማዘጋጃ ቤት የማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ አስመዝግበው እንደኖሩ ተረጋጋጧል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠሪው ክስ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000(2) የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚታገድ አይደለም የሚል ብይን የሰጡት ንብረቱ ከዘር የወረደ ርስት ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡ በእርግጥ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000 (2) “ሟች ከሞተበት ወይም ተከሳሹ በመብቱ ለመምራት ከቻለበት ቀን አንስቶ አስራ አምስት ዓመት ካለፈ በኋላ ከዘር የወረደ ርስት ካልሆነ በስተቀር የውርስ ጥያቄ ክስ በማናቸውም አስተያየት ቢሆንም ተቀባይነት አያገኝም” በማለት ይደነግጋል፡፡

ከዚህም ድንጋጌ የምንረዳው ሟች ከሞተ ከአስራ አምስት አመት በኋላ ወይም ተከሳሹ በመብቱ ሊሰራበት ከቻለበት ቀን አንስቶ ለምሣሌ ህፃን ልጅ ወራሽ ሲሆንና ሞግዚትና አስተዳዳሪው መብቱን በአግባቡ ያልጠየቀለት ቢሆን አካለ መጠን ከደረሰበትና በመብቱ ሊሰራበት ከቻለበት ቀን አንስቶ

በአስራ አምስት አመት ውስጥ ክስ ካላቀረበ ጉዳዩ በይርጋ እንደሚታገድ በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ ድንጋጌው ከላይ የተገለፀው የአስራ አምስት ዓመት ጊዜ ሣያልፍ የወራሽነት ጥያቄ ክስ ያላቀረበ ሰው ከአስራ አምስት ዓመት በኂላ ክስ እንዲያቀርብ የሚፈቅደው በአንድ ልዩ ሁኔታ ብቻ ነው፡፡ ይኸውም ንብረቱ ከዘር የወረደ ርስት ሆኖ ሲገኝ በአስራ አምስት አመት የይርጋ ጊዜ የማይገደብ መሆኑን በልዩ ሁኔታ የደነገገ በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ክስ ማቅረብ የሚችሉት ክርክር የተነሣበት ንብረት ከዘር የወረደ ርስት ከሆነ ብቻ በመሆኑ ክርክር የተነሣበት "ከዘር የወረደ ርስት" ምን አይነት ንብረትን ያጠቃልላል? በተለይም ከዘር የወረደ ርስት የሚባለው ቤትን ያጠቃልላል ወይ? የሚለውን ትርጉም መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም "ርስት" የሚለውን ቃል ስንመለከት "ቤተዘመድ የሆነ እያረሰ የሚጠቀምበት ለተወላጅ በውርስ የሚተላለፍ መሬት" ማለት እንደሆነ ከአማርኛ ቋንቋ መዝገበ ቃላት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000 (2) "ከዘር የወረደ ርስት" የሚለው አገላለጽ፣ ለተወላጅ በውርስ የተላለፈ መሬትን ብቻ የሚመለከት እንጂ ቤትንና ሌሎች የማይንቀሣቀሱ ንብረቶችን የሚመለከት አይደለም፡፡ መሬት የመንግስትና የህዝብ በመሆኑና አሁን ባለው ህገመንግስታዊ ሥርዓት የመሬት ባለቤት የኢትዮጵያ ብሔር በሔረሰቦችና ህዝቦች እና መንግስት እንደሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40 በግልጽ የተደነገገ በመሆኑ "ከዘር የወረደ ርስት ካልሆነ በስተቀር" የሚለው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000 (2) ድንጋጌ በአሁኑ ሰዓት የተሻረና ተፈፃሚነት የሌለው ነው፡፡

ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ ርስት የሌለ በመሆኑ ሟች ከሞተበት ወይም ተከሳሹ በመብቱ ሊሰራበት ከቻለበት ጊዜ ጀምሮ ከአስራ አምስት ዓመት በኂላ የሚቀርብና በይርጋ የማይገደብ የወራሽነት ጥያቄ የለም፡፡ ስለሆነም የተጠሪ እናትና አክስት አውራሻቸው ወ/ሮ ጀማነሽ አቦዬ ከሞቱበት 1949 ዓ.ም ጀምሮ የወራሽነት ክስ ያላቀረቡ በመሆናቸው ይርጋው መቆጠር ያለበት



ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠር የተጠሪ አውራሽ ወ/ሮ አበበች ጀግሬም ሆኑ ተጠሪ አውራሻቸው ከሞቱ ከሰላሣ ዘጠኝ አመት በኂላ ተጠሪ የወራሽነት ጥያቄ ያቀረቡ በመሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000 (2) በተደነገገው የይርጋ የጊዜ ገደብ ክሳቸው ቀሪ ይሆናል፡፡ የተጠሪ እናት እቤቱ ውስጥ መኖራቸው የውረሱን ንብረት የተካፈሉና በስማቸው ያደረጉት መሆኑን አያረጋጋጥም፡፡ ስለሆነም የደሴ ወረዳ ፍርድ ቤትና የደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ንብረቱ ከዘር የወረደ እርስት ስለሆነ በይርጋ አይታገድም በማለት የሰጡት ትርጓሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ እንደዚሁም ተጠሪው አውራሹ የሆነችው ወላጅ እናቱ የአናቷን የወ/ሮ ጀማነሽ አቦዬን ውርስ ሳትጠይቅ ያሳለፈችው ረጅም ጊዜ በተጠሪው ላይ የሚቆጠርበት መሆኑን ሣያገናዝብ ተጠሪው የይርጋ የጊዜ ገደቡ ሣያልፍ ነው ክስ የቀረበው በማለት የሚያቀርበው ክርክር የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ የተጠሪ የወራሽነት ጥያቄ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000(2) መሰረት በይርጋ የሚታገድ በመሆኑ አመልካችና ተጠሪ የቤቱን ባለቤትነት አስመልክቶ ያነሱትን ክርክር መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ከላይ በተገለፀው መንገድ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000(2) በተሣሣተ መንገድ በመተርጐም የወረዳውና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ የህግና የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለበትም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በማጽደቅ የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍትሐብሄር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 255/1999 ጥር 22 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

2. የደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍትሐብሄር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 04711 ጥቅምት 30 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የደሴ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 83/90 መጋቢት 17 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረበው ክስ በይርጋ የታገደ በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
5. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



የሰ/መ/ቁ. 30991

ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ብርሃኑ አመነው

አቶ መድሕን ኪሮስ

አቶ ዓሊ መሐመድ

አቶ ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** እማሆይ ወይንሸት አድማሱ

**ተጠሪ፡-** እነ ወ/ሮ ክብነሽ ስዩም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን አመጣጡም የአሁኑ ተጠሪዎች ታህሳስ 30 ቀን 99 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ሟች አቶ ስዩም አየለ በወረዳ 3 ቀበሌ 53 ቁጥሩ 143 የሆነውን ቤት እኩል እንድንካፈለው ለኛና ለተከሳሾች ተናዝዘውልናል፡፡ ስለቤቱ አጠቃቀም ውርሱን በማጣራትና በመለየት ቤቱን እስከምንከፋፈል በኪራይም ይሁን በኮንትራት የሚገኘውን ገቢ እየተከፋፈልን እንድቆይ ተስማምተናል፡፡ ሆኖም ተከሳሾች ቤቱን አከራይተው ያገኙትን ገቢ ሊያካፈሉን ፈቃደኞች ባለመሆናቸው በኪራይ ያገኙትን ገንዘብ እንዲያካፍሉን፡፡ ቤቱም ተሽጦ እንድንከፋፈል ይወሰንልን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

የአሁን አመልካቾች (የሥር ተከሳሾች) ደግሞ ለቀረበባቸው ክስ በሰጡት መልስ ያደረግነው ስምምነት ኑዛዜውን የሚተካና ወሳኝነት ያለው አይደለም ክርክር ያስነሳው ቤትም የምንኖርበት እንጅ የሚከራይ አይደለም፡፡ ለተወሰነ ጊዜ ተከራይቶ በነበረበት ጊዜ የተገኘው ገቢም ብር 7560 ነው፡፡ ከዚሁ ገንዘብ የቤት ባለቤትነት ደብተር ለማስወጣት ከፍለንበታል፡፡ ቀሪውን ገንዘብ ተሳስበን ለመክፈል ዝግጁነን፡፡ የቤቱን መከፋፈል ግን የሚደረገው

በኑዛዜው መሰረት ከ1ኛ ተከሳሽ የህይወት ፍፃሜ በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም ከሣሾች ያቀረቡት ክስ ኑዛዜውን መሰረት ያላደረገ መሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረና ማስረጃ ከተማ በኋላ ተከሳሾች ቤቱን በማከራየት ካገኙት ገቢ ውስጥ የከሳሾች ድርሻ የሆነውን ብር 1628.50 ለከሳሾች እንዲከፍሉ፡፡ ቤቱም በሐራጅ ተሽጦ ለወራሾች እንዲከፋፈል በማለት ወስነናል፡፡

ከፍተኛው ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ መሰረት በማድረግ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የሥር ፍ/ቤቱን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካቾች የሰበር አቤቱታው ያቀረቡት በሥር ፍ/ቤቶቹ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ቅሬታቸውም ሟች የተናዘዙት ክርክር ያስነሳውን ቤት 1ኛ ተጠሪ ከሌሎቻችን ወራሾች ጋር በመሆን እንዲገለገሉበት፡፡ ለሌሎቻችን ወራሾች ሊከፋፈል የሚችለው እሳቸው ከዚህ ዓለም በሞት በሚለዩበት ጊዜ መሆኑን ነው፡፡ 1ኛ አመልካች በህይወት እያለ ቤቱን መሸጥና መከፋፈል አይቻልም፡፡ እንደዚሁም ወራሾች በሙሉ ተሰብስበን 1ኛ አመልካችም ጭምር ቤቱ ሳይከፋፈል ከሚያስገኘው ጥቅም እኩል እየተጠቀምን መቆየት እንዳለብን የተስማማንና የተዋዋልን በመሆኑ ተጠሪዎች ቤቱን ለመካፈል ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትና የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ቤቱ በሐራጅ ተሽጦ ገንዘቡን ወራሾች እንዲከፋፈሉት በማለት የሰጡት ውሳኔ የአውራሻችን ኑዛዜና ከዚያም በኋላ ወራሾች ያደረግነውን ውል ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ውሳኔው ሊሻርልን ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር ችሎቱም አቤቱታውን ከመረመረ በኋላ ክርክር የተነሳበት ቤት በአጠቃላይ በሐራጅ እንዲሸጥ በማለት የተሰጠው ውሳኔ የሟችን የኑዛዜ ቃል የተከተለ መሆን አለመሆኑን መመርመር አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘው አቤቱታው ያስቀርባል ሲል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡



ተጠሪዎችም ሐምሌ 2 ቀን 99 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ 1ኛ አመልካች በቤቱ ላይ የጋራ መብት የላቸውም፡፡ ከኑዛዜው በኋላ ጥር 8 ቀን 1987 ዓ.ም በተፃፈው የወራሾች የጋራ የስምምነት ውል 1ኛ አመልካች ቤቱ የማይመለከታቸው መሆኑ ተወስኗል፡፡ ቤቱ የወራሾች የጋራ ንብረት በመሆኑ ተሽጦ እንድንከፋፈለው እንዲወሰንልን ክስ ማቅረባችን አግባብ ነው፡፡ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች በኑዛዜ ያገኘነውን ቤት ክርክር ካስነሳው ቤት ጋራ በሐራጅ እዲሸጥ ተወሰነብን በማለት ያቀረቡት ክርክር በስር ፍ/ቤት ያላነሱት በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ የስር ፍ/ቤቶች ቤቱ በሐራጅ ተሽጦ ገንዘቡን ወራሾች እንዲከፋፈሉት በማለት የሰጡት ውሳኔም አንዳችም የሕግ ስህተት የለበትም፡፡ በመሆኑም ውሳኔው እንዲፀናልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾች ያቀረቡት የመልስ መልስ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

በበኩላችን ደግሞ 1ኛ አመልካች በህይወት እያሉ ወራሾቹ ክርክር ያስነሳውን ቤት በሐራጅ ተሽጦ ሊከፋፈሉት ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም የወራሾቹ አውራሽ የሆኑት ሟች አቶ ስዩም አየለ ነሐሴ 11 ቀን 1984 ዓ.ም በሰጡት ኑዛዜ ወ/ሮ ወይንሸት አድማሱ ክርክር ባስነሳው ቤት ውስጥ ከሌሎቹ ወራሾች ጋር አብረው እንዲኖሩ የፈቀዱና እሳቸው በህይወት እያሉም ቤቱን ሽጬ ድርሻዬን እወስዳለሁ የሚል ካለ ያገዱት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ተናዛዡ ወራሾችን ወይም በኑዛዜ ስጦታ የተሰጣቸውን ሰዎች ከሚደርሳቸው ሃብት ላይ በተለይ ለአንድ ወይም ለብዙ ሰዎች አንድ አገልግሎት እንዲሰጡ ግድ እንዲሆንባቸው በኑዛዜው ለመወሰን እንደሚቻል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 920 ተደንግጓል፡፡ የአመልካቾችና የተጠሪዎች አውራሽ የሆኑት አቶ ስዩም አየለ በኑዛዜያቸው ያስቀመጡት የ1ኛ አመልካች ቤቱን የመጠቀም መብትም ወራሾች እንዲፈጽሙት የሚያስገድዳቸው ነው፡፡ በኑዛዜው ግዴታ

የተገባላቸው 1ኛ አመልካችም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 922/1/ መሰረት የታዘዘላቸውን እንዲፈጽሙላቸው ወራሾችን ለማስገደድ ይችላሉ፡፡

ወራሾቹ ተሰብስበው በውርስ ስለተሰጣቸው ቤት አጠቃቀም ለመወሰን ጥር 8 ቀን 1987 ዓ.ም የደረሱበት ስምምነትም የአውራሹን ኑዛዜ የሚያስቀይር ይዘት ስለሌለው ተጠሪዎቹ ላቀረቡት ክስ በምክንያትነት ሊጠቀስ የሚገባው አይሆንም፡፡ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች በኑዛዜ አገኘነው ያሉትን ቤት በተመለከተ ደግሞ የአሁን ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ ተለይቶ ክስ ያልቀረበበትና የሥር ፍ/ቤትም ይህን አስመልክቶ የሰጠው ውሳኔ ባለመኖሩ በግራ ቀኙ የተደገው ክርክር አግባብነት የለውም፡፡

በመሆኑም 1ኛ አመልካች በኑዛዜ የተሰጣቸውን በህይወት ዘመናቸው ክርክር ያስነሳውን ቤት የመገልገል መብት ወራሾች ሊያሳጡዋቸው የሚችሉበት ምክንያት ባለመኖሩ ተጠሪዎች የውርስ ንብረት የሆነው ቤት ተሸጦ ገንዘቡን ወራሾች እንድንከፋፈለው በማለት ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ቤቱ ተሸጦ ገንዘቡ ወራሾች እንዲከፋፈሉት የሚለው ውሳኔም የ1ኛ አመልካችን በቤቱ የመገልገል መብትና የወራሾቹን 1ኛ አመልካች በህይወት እያሉ ቤቱን ያለመሸጥ ግዴታ የጣሰና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16509 ሰኔ 3 ቀን 97 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 41583 ሚያዝያ 16 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አቶ ስዩም አየለ 1ኛ አመልካች በቤቱ ውስጥ መኖር እንዳይከለከሉ፡፡ እሳቸው በህይወት እያሉ ቤቱን ሸጬ ልካፈል ማለት አይቻልም በማለት የተናዘዙ በመሆኑ በወረዳ 3 ቀበሌ



53 ክልል የሚገኘው ቁጥሩ 143 የሆነው ቤት እማሆይ ወይንሸት አድማሱ በህይወት እያሉ መሸጥ የለበትም በማለት ወስነናል፡፡ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰበር መ/ቁ/ 32414

ሰኔ 24 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጐስ ወልዱ

አቶ ታፈሰ ይርጋ

አቶ መድሕን ኪሮስ

አቶ ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ባዩሽ ደጀኔ - ከጠበቃ ዳኛቸው ተስፋዬ ጋር ቀረበች

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ሃሳብ ከፋይ ጌራወርቅ ቀረበች፡፡

2. ደረጀ ጌራወርቅ - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ኑዛዜን መሠረት በማድረግ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው ክርክሩ በተጀመረበት በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የመጀመያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁንዋ አመልካች ሟች አቶ ጌራወርቅ ህሩይ (ባለቤትዋ) አድርገውት ያለፉት ኑዛዜ መሠረት ተደርጐ የወራሽነት ማስረጃ ይሰጣት ዘንድ በመጠየቅዋ ፍ/ቤቱም ጥያቄዋን በመቀጠል የኑዛዜ ወራሽነት በማለት ማስረጃውን ሰጥቶአት ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአሁኖቹ ተጠሪዎች ማስረጃው መሰጠት አልነበረበትም በማለት መቃወሚያ በማቅረባቸው ፍ/ቤቱ ጉዳዮን በድጋሚ ያየ ሲሆን በመጨረሻም ሟች አድርገውታል የተባለውን ኑዛዜ ከፊሉን በመሻር የተወሰነውን ክፍሉን ደግሞ በማጽደቅ ወስኖአል፡፡ በዚህ ላይ ከአሁንዋ አመልካች ይግባኝ የቀረበላቸው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶችም



ውሳኔው ጉድለት የለውም ብለዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ነሐሴ 4 ቀን 1999 ዓ.ም በጻፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ጉዳዩን ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እደተመለከተው ክርክሩ ሊነሳ የቻለው ሟች አደረገው የተባለው ኑዛዜ ፈራሽ ነው ይባል የሚል ክስ በመቅረቡ ሳይሆን (የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 973) ኑዛዜውን መሠረት በማድረግ የወራሽነት ማስረጃ (የምስክር ወረቀት) ይሰጠኝ (የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996(1)) በማለት አመልካች ጥያቄ በማቅረብዋ ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሕጉ በግልጽ እንደተመለከተው ኑዛዜ ፈራሽ ነው ይባል በሚል የሚቀርበው ክስ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ከሚቀርበው ጥያቄ (አቤቱታ) የተለየ ነው፡፡ ጥያቄዎቹ የተለያዩ በመሆናቸውም የተለያየ ውጤት ነው ያላቸው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996(1) እንደተደነገገው ወራሽነኝ የሚል ማንኛውም ሰው የወራሽነት ምስክር ወረቀት ይሰጠው ዘንድ ለፍ/ቤት ሊያመለክት ይችላል፡፡ ፍ/ቤቱም ጥያቄውን ከመቀበሉ በፊት ጠያቂው ማስረጃዎቹን ሁሉ እንዲያቀርብ በማድረግ እና አስፈላጊ መስሎ የታየውን ዋስትና እንዲሰጥ በማስገደድ ጭምር ዋስትናውን ካገኘ በኋላ የተጠየቀውን የምስክር ወረቀት ሊሰጥ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996(2) ተመልክቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፍ/ቤቱ የአመልካቹን ጥያቄ መሠረት በማድረግ ሰጥቶት የነበረውን የወራሽነት የምስክር ወረቀት ሊሰርዘው እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 998(1) የተቀመጠው ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ ከዚህ እንግዲህ መገንዘብ እንደሚቻለው የምስክር ወረቀቱ በጠያቂው አቤቱታ መነሻነት የሚሰጥ ቢሆንም የተሰጠው ያለአግባብ ነው

የሚል መቃወሚያ ሊቀርብ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩንና መቃወሚያው ተገቢ ሆኖ ከተገኘም የምስክር ወረቀቱ የሚሰረዝ መሆኑን ነው፡፡

ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበለት ፍ/ቤት ጥያቄውን ተቀብሎ የምስክር ወረቀቱን ሰጥቶ እንደነበር እንመለከታለን፡፡ ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996(1) የተመለከተውን ድንጋጌ ተከትሎ የተፈጸመ በመሆኑ ትክክል ነው፡፡ ሌላው ቀጥለን የምናየው ተጠሪዎች የተሰጠውን የወራሽነት የምስክር ወረቀት በመቃወም መቅረባቸው ሲሆን ፍ/ቤቱም መቃወሚያውን መሠረት በማድረግ ለምስክር ወረቀቱ መሰጠት መሠረት የሆነውን ኑዛዜ ይዘት እና ሕጋዊነትን መርምሮአል፡፡ በመጨረሻም ኑዛዜውን በከፊል በመሻር በከፊል ደግሞ አጽድቄአለሁ ብሎአል፡፡ በበኩላችን ትክክለኛ አካሄድ ሆኖ ያላገኘነውም ይህንን ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ በሕጉ የተቀመጠውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ኑዛዜው ፈራሽ ነው እንዲባል ክስ አልቀረበለትም፡፡ የፍ/ቤቱ የዳኝነት ሥልጣን የተወሰነ በመሆኑ በሥልጣን ክልሉ ስር የሚወድቀውን የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ነው ጥያቄ የቀረበለት፡፡ ይህን ጥያቄ ተቀብሎ ሰጥቶት የነበረውን የምስክር ወረቀት ተጠሪዎች ካቀረቡለት መቃወሚያ አንጻር ሲመዝነው ተገቢ አልነበረም የሚል ድምዳሜ ከደረሰም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 998(1) በተደነገገው መሠረት መሠረዝ ነው የነበረበት፡፡ ከዚህ አልፎ ኑዛዜው ፈራሽ ይባል የሚል ክስ በቀረበ ጊዜ ሊደረግ እንደሚችለው ሁሉ ኑዛዜውን በከፊል ሽሬአለሁ ማለቱ ትክክል አይደለም፡፡ የሕግ መሠረትም የለውም፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ ፍ/ቤቱ ወደ ኑዛዜው ይዘት እና ሕጋዊነት ሁኔታ ገብቶ ውሳኔ መስጠት የሚችልበት ሕጋዊ መንገድ አልነበረውም እንጂ ሕጋዊ መንገድ ነበረው ተብሎ ቢሆን ኖሮ እንኳን የደረሰበት መደምደሚያ የኑዛዜን ፎርም እና ማስረጃ ከሚመለከተው ሕግ አንፃር ሊታይ ፍጹም የተሳሳተ ነው፡፡



ለክርክሩ መነሻ የሆነው ኑዛዜ በግልጽ የተደረገ ኑዛዜ እንደሆነ በፍ/ቤቱ ውሳኔ ተመልክቶአል፡፡ በግልጽ የተደረገ ኑዛዜ ሊያሟላቸው የሚገቡትን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881 ስር የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟላ እንደሆነም ፍ/ቤቱ ማረጋገጡን በውሳኔው ላይ አመልክቶአል፡፡ ይህን ሁሉ ካረጋገጠ በኋላ በከፊል ሽሬዋለሁ ያለው ሟች ንብረቱ ባልሆነው ንብረት ላይ ጭምር ተናዟል በማለት እንደሆነ ከውሳኔው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በሕጉ በግልጽ እንደተመለከተው በግልጽ የተደረገው ኑዛዜ በሕጉ መሠረት አልተደረገም ተብሎ ሊነቀፍ የሚችለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881 የተቀመጡትን መስፈርቶች ያላሟላ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ኑዛዜውን ለመንቀፍ ምክንያት ያደገው ነጥብ የኑዛዜውን ሕጋዊነት በተመለከተ አግባብነት የለውም፡፡ ተናዛዡ የእሱ ባልሆነው ንብረት ጭምር ተናዟል የሚባል ቢሆን የንብረት ክርክር ሲቀርብ እራሱን ችሎ የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ይህን ነጥብ በማድረግ የኑዛዜውን ሕጋዊነት (ፎርም) መንቀፍ ተገቢ አይደለም የምንለውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤቶች የተጠሪዎችን መቃወሚያ መሠረት በማድረግ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በድሬዳዋ ጊዜያዊ አስተዳደር የድሬዳዋ ከተማ የመጀመያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 00113/97 የካቲት 30 ቀን 99 ዓ.ም ተሰጥቶ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ.ቁ 106/99 ግንቦት 8 ቀን 99 ዓ.ም በተሰጠው ትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. ቀደም ሲል ለአመልካች የተሰጠው የወራሽነት የምስክር ወረቀት የሚሰረዝበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡

3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ



የሰ/መ/ቁ. 34076

ሰኔ 10 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ዘነበወርቅ ወልዱ ፀጋ - ወኪል እስክንድር ወልዱ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. እማሆይ ድብቅነሽ ግዛው

2. ወ/ሮ አዳነች ወልዱ ፀጋ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በውርስ ንብረት ክፍፍል ላይ የተነሳውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሳሽ የነበረችው የአሁንዋ አመልካች ስትሆን፣ በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረተችው ይዘውት ከሚገኘው የውርስ ንብረት ላይ ድርሻዋን እንዲያካፍሉአት ነው፡፡ የውርስ ንብረት የተባሉት በአዲስ አበባ እና በደሴ ከተማ የሚገኙ ሁለት ቤቶች እንደሆኑም ተገልፆአል፡፡ ክሱ የቀረበለት የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ወደ ክሱ ስረ ነገር ከመግባቱ በፊት አዲስ አበባ ከተማ ይገኛል በተባለው ቤት ላይ የዳኝነት ስልጣን የለኝም፣ ማስተናገድ የምችለው ደሴ ከተማ ውስጥ የሚገኘውን ቤት በሚመለከት የሚቀርበውን ክስ ነው በማለት መዝገቡን ዘግቶአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤትም የግዛት ክልል ስልጣን የለኝም ተብሎ በሚሰጥ ትእዛዝ ላይ ይግባኝ ሊቀርብ አይችልም፡፡ የሚል ምክንያት በመስጠት ይግባኙን ሳያስተናግድ ቀርቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሕዳር 17 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተወሰነው አመልካች ለደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበችው የውርስ ንብረት ክፍፍልን የሚመለከተው ክስ በግዛት ክልል የዳኝነት ስልጣን ምክንያት አይስተናገድም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህም መሠረት ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ትእዛዝ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር መገዝብ እንደቻልነው አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ የሟች አቶ ወልዱ ፀጋ ልጆች ሲሆኑ፣ 1ኛ ተጠሪ ደግሞ የሟቹ ሚስት ናቸው፡፡ ሟች ይኖሩ የነበሩት በደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን እንደሆነና የሞቱትም በዚሁ ቦታ ስለመሆኑ በክርክሩ ተመልክቶአል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተጠሪዎች ሟች በኖሩበትና በሞቱበት በደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን በደሴ ወረዳ ፍ/ቤት የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ማቅረባቸውን ከቀረበው ክርክር ተመልክተናል፡፡

እንደምናየው ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረተችው የውርስ ሃብት ነው ከተባለው ንብረት ላይ ድርሻዋን ለማግኘት ነው፡፡ በአጠቃላይ ክርክሩ የፍትሐብሔር እንደመሆኑ የሚመራው በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት ነው፡፡ በግዛት ክልል ስለሚወሰን የዳኝነት ሥልጣን በተመለከተ በሥነ ሥርዓት ሕጉ አንደኛ መጽሐፍ በምዕራፍ 3 ስር ካሉት ድንጋጌዎች ውስጥ በቁጥር 23 የተመለከተውም ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢነት ያለው ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በውርስ ምክንያት የሚቀርብ ክስ የሚታይበትን ቦታ የሚወሰን ነው፡፡ ክሱ መቅረብ ያለበት ወይም የሚቀርበው የውርሱ ክፍያ በተጀመረበት ቦታ ለሚገኘው ፍ/ቤት እንደሆነም ያመለክታል፡፡ ሕጉ ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ደግሞ የውርስ ሃብት የሆኑ ንብርቶች በተለያዩ ቦታዎች የመኖራቸውን ጉዳይ



ግምት ውጥስ የሚገባ አይደለም፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ትእዛዝ ከዚህ አንጻር ሲታይም የሕግ መሰረት ያለው አይደለም፡፡ ይልቁንም መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ያለበት ሆኖ ነው ያገኘነው፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአማራ ብሔራዊ ክ/መ/ደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16355 ሰኔ 25 ቀን 99 ዓ.ም ተሰጥቶ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 1070/99 መስከረም 27 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ይግባኝ አይባልበትም የተባለው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሮአል፡፡
2. አመልካች ያቀረበችው የውርስ ክፍፍል ክስ መታየት ያለበት በደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ፍ/ቤት በመሆኑ ፍ/ቤቱ ክሱን በማስተናገድ በበኩሉ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ ይስጥበት ብለናል፡፡ ጉዳዩ ይመለስለት፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

# መ ድ ን



የሰ/መ/ቁ. 22530

ጥቅምት 28 ቀን 2000

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
3. አቶ መስፍን እቁበዮናስ
4. አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ
5. አቶ አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- የቀድሞው የኢትዮጵያ ጭነት ማመላለሻ ኮርፖሬሽን በሕግ የተካው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ነ/ፈጅ ፍቅሩ ሽዋ አማረ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- እነ አጂፕ ኢትዮጵያ አክሲዮን ማህበር (23 ሰዎች) - ጠበቃ አጥናፉ ቦጋለ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

## ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ አንደኛ ተጠሪ የሆነው አጂፕ ኢትዮ.አክሲዮን ማህበር በሥር ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ፣የአሁኑ አመልካች ነዳጅ ለማጓጓዝ ገንዘብ እየተከፈለው የትራንስፖርት አገልግሎት ሲሰጥ በአጓጓዥነት የተሰጡትን የነዳጅ ውጤቶች ልማድንና የማጓጓዝ ውልን በመጣስ፣ ብቃት የሌላቸውን መኪናዎች በማሰማራትና በሾፌሮች ጥንቃቄ ጉድለት በተለያዩ ቦታዎች በደረሱ አደጋዎች የተጫነው ነዳጅ በመፍሰሱ የብር 479,273.70 /አራት መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺ ሁለት መቶ ሰባ ሦስት ብር ከሰባ ሳንቲም/ ኪሣራ የደረሰበት መሆኑን ገልጾ አንደኛ ተጠሪ የነበረው የአሁኑ አመልካች ከወለዱ ጭምር እንዲከፍለው ጠይቋል። የአሁኑ አመልካች በበኩሉ፣በአዋጅ ቁጥር 107/69 እንዲሁም በሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 105/79 እና 49/69 መሠረት አመልካች ከተራ ቁጥር 2--23 የተዘረዘሩት ተጠሪዎች ጭነት

እንዲያገኙ በተራ መዝግቦ ከአስጫኝ ጋር በማገናኘት ከሁለቱም ወገኖች ማለትም ከአስጫኝና ከአጓጓዥ የተፈቀደለትን የአገልግሎት ዋጋ ከመቀበል ውጭ የእነርሱ ወኪል ያለመሆኑን፣እንዲሁም በስማቸው የተዋዋለው ውልና የተረከበውም ነዳጅ ስለሌለ በኃላፊነት ሊጠየቅ የማይገባ መሆኑን፤እያንዳንዱ መኪና ሳንጓዘው ነዳጅ ኃላፊነቱ የእርሱ መሆኑን በማስረዳት ተከራክሯል፡፡ የራሱ በሆኑት 9 ተሽከርካሪዎች ለጫኑትና ደረሰ ለተባለው የነዳጅ ጉድለት ደግሞ በን.ሕ.ቁ. 591 መሠረት ከአቅም በላይ የደረሰ አደጋ ስለሆነ ሊጠየቅ የማይገባው መሆኑን በመግለጽ በሰፊው ተከራክሯል፡፡ ከተራ ቁጥር 2-23 የተዘረዘሩት የጭነት ማጓጓዣ ባለቤቶችም በበኩላቸው ከአሁኑ ተጠሪ ጋር የውል ግንኙነት የሌላቸውና ከአቅም በላይ በደረሰ አደጋ ሊጠየቁ የማይገባቸው መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በጉዳዩ የቀረበውን ሰፊ ክርክር መርምሮ፣ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው አዋጅና የሕግ ክፍል ማስታወቂያ መሠረት በአሆኑ አመልካችና ከተራ ቁጥር 2-23 በተጠቀሱት ባለንብረቶች መካከል የባለኮሚስዮንነት የሕግ ውክልና ግንኙነት ተፈጥሯል፡፡ በን.ሕ.ቁ. 60-62 መሠረት አንደኛ መልስ ሰጭ ከሆነው አስጫኝ ጋር ውል አድርጓል፡፡ ውሉም በቀረቡት የገንዘብ መክፈያ ደረሰኞች ተረጋግጦአል፡፡ በመሆኑም በተቀሩት መልስ ሰጭዎችም ላይ ለደረሰው ጉዳት የአሁኑ አመልካች ኃላፊ ነው፡፡ በራሱ ተሽከርካሪዎች ለጫነውና ደረሰ ለተባለው ጉድለትም ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ስለሌለ ከኃላፊነት ነፃ አይደለም በማለት ወስኖ የደረሰው ጉድለት ለመተመን የቀረቡት ማስረጃዎች ክብደት የሚሰጣቸው ባለመሆናቸው ሂሳቡ በባለሙያ ተሰርቶ እንዲቀርብ አዟል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ እንዳለ አጽንቶታል፡፡

ይህ የሰበር ቅሬታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የካቲት 10 ቀን 1998 በዋለው ችሎት የአሁኑ አመልካች በተጠሪዎች (ከ2-23 በተጠቀሱት) ተጭኖ ሲጓጓዝ ብክነት ለደረሰበት ነዳጅ



ኃላፊ መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር እንዲቀርብ በማድረግ ጉዳዩ በሚሰማበትና ከዚያ በኋላ በተያዙ ተከታታይ ቀጠሮዎች ተጠሪዎች ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ታዞ መዝገቡ ተመርምሯል፡፡

በዚህ ጉዳይ የአሁኑ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 107/69 መሠረት ለተሽከርካሪዎች የስምሪት ፈቃድ ይሰጥና በሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 49/69 እና 105/79 መሠረት የተፈቀደለትን የአገልግሎት ክፍያ ይቀበል የነበረ መሆኑ ታውቋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የራሱ በሆኑ የጭነት ተሽከርካሪዎችም የጭነት ማጓጓዝ ሥራ ይሰራ የነበረ መሆኑም አላከራከረም፡፡ የአሁኖቹ ተጠሪዎችም በአመልካች አማካኝነት በሚያገኙት ስምሪትና ጭነት ባለንብረት በሆኑባቸው የግል ተሽከርካሪዎቻቸው ከሳሽ የነበረውን የአሁኑን አንደኛ ተጠሪ ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች ከቦታ ወደ ቦታ ያጓጉዙ እንደነበረ አልተካደም፡፡ የሥር ፍ/ቤት የንግድ ሕግ ቁጥር 60-62 ያለውን መሠረት በማድረግ በሥር ጣልቃ ገብ በነበሩት በአሁኖቹ ከ2-23 በተመለከቱት ተጠሪዎችና በአሁኑ አመልካች መካከል የባለ ኮሚስዮን የሕግ ውክልና ግንኙነት ተፈጥሯል በማለት የአሁኑ አመልካች ከከሳሽ ጋር በገባው የኮሚስዮን ወኪልነት መሠረት በከሳሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት በሙሉ ኃላፊ ነው ብሏል፡፡

በመሠረቱ በንግድ ሕግ ቁጥር 60 ላይ የተመለከተው የባለኮሚስዮንነት ትርጓሜ ማንም አበል ለማግኘት ባለኮሚስዮን ስላደረጋቸው ሰው በራሳቸው ስም ሸቀጦችን ወይም የሚንቀሳቀሱ ዕቃዎችን ወይም ማናቸውም እነዚህን የመሣሰሉ ዕቃዎችን ለመግዛት ወይም ለመሸጥ ወይም የማጓጓዝ ውል ለመዋዋል በራሳቸው ሥም ግዴታ የሚገቡ ሰዎችን ወይም የንግድ ማህበሮችን እንደሚሸፍን ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የአሁኑ አመልካች በወቅቱ በነበረው ፖሊሲ መሠረት የመንገድ ትራንስፖርት ቅንጅትን ለመጠበቅ ሲባል የግል ተሽከርካሪዎች ጭነት እንዲያገኙ ሥራውን

በማዕከላዊነት እንዲመራና ስለአገልግሎቱ ከአስጫኝ እና ከጫኙ ክፍያ እንዲያገኝ መደረጉ ብቻውን እንደ ሕጉ አነጋገር ባለኮሚስዮን ስላደረጉት ሰዎች በራሱ ሥም የማጓጓዝ ውል ለመዋዋል ግዴታ የገባ ነው መባሉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ በሥር ባልቃ ገብ የነበሩት የአሁኖቹ ከ2–23 የተመለከቱት ተጠሪዎች ከአሁኑ አመልካች ጋር በሕግ የታወቀ የኮሚሽን ኤጀንት ግንኙነት የሌላቸው በመሆኑ ዋጋ ተከፍሏቸው በየግል ተሽከርካሪዎቻቸው ላጓጓዙትና ላደረሱት ብክነት በግል ተጠያቂ የማይሆኑበት ምክንያት አላገኘንም፡፡

በሌላ በኩል የአሁኑ አመልካች የራሱ የሆኑ ዘጠኝ ተሽከርካሪዎችን የማጓጓዝ ሥራ ላይ አሰማርቶ ለደረሰው ብክነት በሥር ፍ/ቤት ኋላፊ መባሉ በተመሣሣይ ሁኔታ ከተራ ቁ. 2–23 የተመለከቱት ተጠሪዎች በን.ሕ.ቁ. 591 መሠረት ከአቅም በላይ በሆነ ሆኔታ የደረሰ አደጋ ስለመኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በየግል ንብረቶቻቸው ለባከነው ነዳጅ በየድርሻቸው ኃላፊ መባላቸው በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**ው ሳ ኔ**

- የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች የአሁኖቹን ተጠሪዎች (ከ2–23 የተመለከቱትን) ወክሎ በኮሚሽን ኤጀንትነት ከከሳሽ (1ኛ ተጠሪ) ጋር በገባው ውል መሠረት በከሳሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት በሙሉ ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፣
- አመልካች በራሱ ተሽከርካሪዎች ላደረሰው ብክነት ኃላፊ ነው መባሉ በአግባቡ ነው፣
- ከተራ ቁጥር 2–23 የተመለከቱት ተጠሪዎች በየስማቸው አንፃር በተመለከቱት የግል ተሽከርካሪዎች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለባቸው በማለት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሚያዚያ 13 ቀን 1996 ዓ.ም በመ/ቁ. 03013 የሰጠውንና የፌ/ከ/ፍ/ቤት ጥቅምት 9 ቀን 1998 በመ/ቁ. 33475 የሰጠውን ትዕዛዝ አሻሽለን ወስነናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



የሰ/መ/ቁ. 24703

ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** 1. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ
2. ወ/ት ሂሩት መለሰ
3. አቶ ታፈሰ ይርጋ
4. አቶ መድሕን ኪሮስ
5. አቶ ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ነ/ፈጅ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ት ቢሮ አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ተጠሪ ለሚጠቀምባቸው 10 ተሽከርካሪዎች በገባው የመድን ውል መሰረት መክፈል የሚገባውን ብር 55,068.56 የአረቦን ክፍያ ለመክፈል ፈቃደኛ ስላልሆነ እንዲከፈል ይወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡

የአመልካች ክስና ማስረጃ ለተጠሪ ደርሶ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት ተጠሪ የፍርድ ቤቱ መጥሪያ በአግባቡ ደርሶት ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ፍ/ቤቱ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የአመልካችን ክስና ማስረጃ መርምሮ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በሕግ አግባብ የተቋቋመ የመድን ውል አለ ለማለት ስለማይቻል አመልካች ያቀረበው ማስረጃ ድጋፍ የለውም በማለት ክሱን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ በግራ ቀኙ መካከል በሕግ አግባብ የተቋቋመ የመድን ውል አለ ወይስ የለም? የሚለው በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች ክስ ያቀረበው ከተጠሪ ጋር ባደረግነው የመድን ውል መሰረት ሊከፈለኝ ይገባኝ የነበረው የአረቦን ክፍያ ያልተከፈለኝ ስለሆነ ይከፈለኝ በማለት እንደመሆኑ መጠን ጉዳዩ መታየት ያለበት የግራ ቀኙን ግንኙነት በተለይ ከሚገዛው የንግድ ሕጉ አኳያ ነው፡፡

ከዚህም አንጻር ጉዳዩ ሲታይ የመድን ውል ሲመሰረት እንደማንኛውም ውል የውል አቀራረብና አቀባበል /offer and acceptance/ ሊኖር የሚገባ ሲሆን የውል አቀራረብ /offer/ የሚከናወነው መድን ገቢው በመድን ሰጭው የሚዘጋጅን መግለጫ /proposal form/ ሲሞላና ይህንኑ መግለጫም ለመድን ሰጭው ሲያስረክብ ነው፡፡ በመድን ገቢው የቀረበው የውል አቀራረብ ጥያቄ በመድን ሰጭው ተቀባይነት አግኝቷል ለማለት የሚቻለው ደግሞ በተዘጋጀው ፖሊሲ ላይ በሚፈርምበት ጊዜ /The issuance of policy/ እንደሆነ፣ ከዚህ በኋላም በሁለቱ ወገኖች መካከል የመድን ውል የተቋቀመ መሆኑንና የትኛውም ወገን ሊያቋርጠው እንደማይችል ከንግድ ሕግ ቁጥር 651፣654 እና 657 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የተጠሪ መ/ቤት ለሚጠቀምባቸው ተሽከርካሪዎች የመድን ውል ለመግባት እንደሚፈልግ በመግለጽ የመ/ቤቱን ማሕተም በማድረግና በኃላፊው አማካኝነት በመፈረም ለመድን ሰጭው ለአመልካች መ/ቤት ደብዳቤ ጽፏል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው በተጠሪ በኩል የውል አቀራረብ /offer/ የተደረገ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በኋላም አመልካች በተዘጋጀው ፖሊሲ ላይ መፈረሙ የተረጋጠ እንደመሆኑ መጠን ከላይ



ከተጠቀሱት የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች አኳያ በመካከላቸው የመድን ውሉ የተደረገ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በእርግጥ በፍ/ብሄር ሕጉ በተለየ የአጻጻፍ ሥርአት መደረግ ከሚገባቸው ውሎች መካከል አንዱ የኢንሹራንስ ውል ሲሆን የዚህ ዓይነት ውሎችም በተዋዋይ ወገኖች መፈረም እንዳለባቸውና በሁለት ምስክር ፊትም መረጋገጥ እንዳለባቸው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ቁ.1725 እና 1727 ላይ የተመለከተ ቢሆንም የግራ ቀኙን ግንኙነት በተለይ የሚገዛው ልዩ ሕግ የሆነው የንግድ ሕጉ ስለሆነና በጠቅላላ ሕግና በልዩ ሕግ መካከል አለመጣጣም በሚኖርበት ጊዜ ልዩ ሕግ የበላይነት እንደሚኖረው /The special prevails over the general/ ከሕግ አተረጓጐም መርህ መገንዘብ የሚቻል እንደመሆኑ በዚሁ መሰረትም መድን ሰጭው በሚያዘጋጀው ፖሊሲ ላይ እራሱ መፈረም እንዳለበት በን/ሕ/ቁ. 657 ላይ ከመመልከቱ በስተቀር መድን ገቢው መፈረም እንደሚገባው ያልተመለከተ በመሆኑ በውል ማቅረቢያ /offer/ ሰነዱ ላይ መድን ገቢው ከፈረመና በፖሊሲው ላይ ደግሞ መድን ሰጭው ከፈረመ በሁለቱ መካከል የመድን ውል ስለመደረጉ በቂ አስረጂ እንደሆነ ከንግድ ሕጉ አኳያ መገንዘብ ስለሚቻል በሁለቱ መካከል የመድን ውል አልተቋቋመም ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 528 ታህሳስ 30 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 31510 የካቲት 6 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል ከንግድ ሕጉ አኳያ በአግባቡ የተቋቋመ የመድን ውል መኖሩ የተረጋገጠ ስለሆነና በክስ

በተጠየቀውም ገንዘብ ላይ ተጠሪ ክርክር ስለሌው ይህንኑ በክስ የተጠየቀውን ብር 55,068.56 /አምሳ አምስት ሺህ ስልሳ ስምንት ብር ከሃምሳ ስድስት ሳንቲም/ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ 9% /ዘጠኝ በመቶ/ ወለድ ጋር ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል ይገባል ተብሎ ተወስኗል፡፡

3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



የሰ/መ/ቁ. 24704

ኀዳር 12 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጎስ ወልዱ

አቶ ተገኔ ጌታነህ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አቶ ብርሃኑ አመነው

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት-ጠበቃ አቶ ኃይሉ ተሰማ-ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ ጤና ቢሮ ዐ/ሕግ አቶ ተመስገን መንግሥቴ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ ለሰበር ችሎት የቀረበው ክርክር የመድን ዋስትና ውል ስለመኖር የሚመለከት ነው፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ክስ በአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመሠረተው የአሁኑ አመልካች ሲሆን የክሱ ይዘትም ባጭሩ የተጠሪ ንብረት የሆኑ ሁለት ተሽከርካሪዎች የመድን ሽፋን እንዲያገኙ ጥር 2 ቀን 1995 በደብዳቤ ቁጥር 2915/73/9 በጠየቀው መሠረት አመልካች ተገቢውን ማጣራት ካደረገ በኋላ የሰሌዳ ቁ. 4-28437 ቶዮታ ኮብራ የሆነው የተጠሪ መኪና እ.ኤ.አ. ከ13/3/93 ጀምሮ ለአንድ ዓመት የሚቆይ የመድን ሽፋን ውል በፖሊሲ ቁጥር NK/1/MTPV/0727/03 ተሰጥቶት፣ ለዚህም አገልግሎት አረቦን ብር 11,510.00 /አሥራ አንድ ሺህ አምስት መቶ አሥር ብር/ ተጠሪ ባለመክፈሉ በፍርድ እንዲወሰንበት ሲል ክስ ያቀረበ ሲሆን ከፍተኛው ፍ/ቤትም የተጠሪን የጽሑፍ እና የቃል ክርክር ካዳመጠ በኋላ ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበውን የመድን ዋስትና ውል

አለመኖር የተመለከተ ክርክር ከቀረበው የግራ ቀኝ ማስረጃ አንፃር ከመረመረ በኋላ የመድን ዋስትና ውሉ ላይ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1727/1/ የተዋዋይ ወገኖች ፊርማ መኖር እንዳለበት እና ይህም በሁለት ምስክሮች መረጋገጥ ያለበት መሆኑን ሕጉ የሚያስገድድ ሆኖ እያለ በአመልካች በኩል የቀረበው ማስረጃ ይህንን እና ሌሎች የሕጉን ድንጋጌዎች ስለማያሟላ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ውል ተቋቁሟል ለማለት እጅግ አዳጋች ነው በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ ይህንን ውሣኔ መቃወም አመልካች ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍረድ ቤት ይግባኙ አያስቀርብም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

ለሰበር ችሎት የቀረበው አቤቱታ ይህንን ውሣኔ የሚቃወም ሲሆን አመልካች ያቀረባቸው የአቤቱታ ነጥቦች፣ የመድን ውል አመሠራረት የሚረጋገጠው በንግድ ሕጉ በተደነገገው እንጂ በፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ አይደለም፣ ይህም ሲባል በጉዳዩ ላይ ልዩ ሕግ እያለ የጠቅላላ ሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት አድርጎ የመድን ውል የለም መባሉ አግባብ አይደለም፡፡ እንዲሁም የምስክሮች ፊርማ መኖር ወሳኝና አንገብጋቢ መሆኑን የንግድ ሕጉ አያመለክትም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች የመድን ውል አመሠራረትን በተመለከተ የወሰዱት አቋም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ እንዲታረም ሲል ጠይቋል፡፡

የሰበር ችሎቱም መዝገቡን ከመረመረ በኋላ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የሠነድ ልውውጥ በሕግ የተደነገገውን የመድን ውል ፎርም አያሟላም በሚል አመልካች ያቀረበው ክስ ውድቅ የተደረገው በሕጉ አግባብ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቦ አከራክሯል፡፡

የተጠሪ መ/ቤት ተወካይ የክልሉ ፍ/ቢሮ በአቤቱታው ላይ ሚያዝያ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው መልስ የመድን ውል በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ካልተፈረመና በምስክሮች ካልተረጋገጠ ሕጋዊ ውጤት እንደሌለው የፍ/ብ/ሕግ አንቀጽ 1675 እና የንግድ ሕግ አንቀጽ 659/1/ ያስገነዝባል፡፡



አመልካች የመድን ውል አለ በማለት ያቀረበው ማስረጃ የተጠሪ መ/ቤት ማኅተምና ፊርማ የሌለው በመሆኑ አመልካች ብቻውን ያዘጋጀው ውል ተጠሪን ስለማያስገድድ የመድን ውል ሳይኖር የመድን ውል ግዴታ የለም በማለት በሥር ፍ/ቤት ያቀረበውን ክርክር አጠናክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲፀና ጠይቋል፡፡

አመልካች ግንቦት 16 ቀን 1999 ዓ.ም. ባቀረበው የመልስ መልስ በተጠሪ የቀረበው የመድን ዋስትና ሽፋን ጥያቄ እና በአመልካች የተሰጠው የመድን ውል ፖሊሲ በጋራ ሊታዩ ይገባል በማለት አቤቱታውን አጠናክሮ ተከራክሯል፡፡

በዚህ ጉዳይ ምላሽ የሚያሻው የሕግ ነጥብ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገው የሠነድ ልውውጥ ስለ ኢንሹራንስ ውል አፃፃፍ ፎርም የተመለከተውን ድንጋጌ አሟልቷልን? የሚለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት የሕጉን ይዘት ከመመርመራችን በፊት በፍሬ ጉዳይ ክርክሩ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ንብረትነታቸው የተጠሪ ለሆኑት ሁለት መኪኖች የመድን ሽፋን እንዲሰጠው በተጠሪ መ/ቤት ማኅተም እና በሚመለከተው ሁለት ፊርማ መጠየቁ አመልካች ለአንደኛው መኪና የመድን ሽፋን ለመስጠት ፈቃደኛ ሆኖ የመድን ውል ፖሊሲ ለተጠሪ መስጠቱ ነው፡፡ አከራካሪው ጉዳይ የእነዚህ ሁኔታዎች መኖር በራሱ የኢንሹራንስ ውል በአመልካች እና በተጠሪ መካከል መመሥረቱን ያረጋግጣልን? የሚለው ነው፡፡

የመድን ውል ስለመኖሩ ለማስረዳት አመልካች ያቀረበውን ማስረጃ ከፍተኛው ፍ/ቤት ሲመረምር መሠረት ያደረገው በፍ/ብ/ሕግ ስለውሎች አጻጻፍ ፎርም የተመለከተውን ድንጋጌ ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት ተጠሪ አጥብቆ የተከራከረው የውሎችን አመሠራረት የሚመለከቱ የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌዎች ከመሆኑ የተነሣ ይመስላል ከፍተኛው ፍ/ቤት ትኩረት የሰጠውና ለውሣኔው መሠረት ያደረገው የፍ/ብ/ሕግ አንቀጽ 1719 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎች

ነው። እነዚህ ድንጋጌዎች በጥቅሉ መሠረት ያደረጉት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1725/ለ/ እና 1727/2/ መሠረት የኢንሹራንስ ውሎች በጽሁፍ መደረግ እንዳለባቸው በጽሁፍ የሚደረጉትም በምስክሮች ፊት መሆን እንዳለበት ይህ ካልተፈፀመ ውሉ እንደማይፀና የሚያስገነዝቡ ናቸው የሚለውን የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት መሆኑን ተገንዝበናል።

የኢንሹራንስ ውል አመሠራረት እና የፍ/ብ/ሕግ አንቀጽ 1725 እና 1727 ድንጋጌዎች አፈጻጸም ወሰን እንዲሁም የንግድ ሕግ ስለ ኢንሹራንስ ውሎች የተመለከተውን ድንጋጌ ቁጥር 657 እና ተከታዮቹ በተመለከተ የሰበር ችሎት ከዚህ ቀደም በመዝገብ ቁጥር 23003 ሚያዝያ 16 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ አሁን ከተያዘው ጉዳይ እና ጭብጥ ጋር ተመሣሣይ ሆኖ ስላገኘነው ከዛው ውሣኔ አንፃር መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

በመሆኑም አሁን በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለተጠሪ የሰጠው የመድን ሽፋን ለአንድ ዓመት በመሆኑ የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 23003 በወሰደው አቋም መሠረት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1725 እና 1727 ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት የለውም ብለናል። /የሰበር መ/ቁ. 23003 ይመለከቷል/

ስለዚህ ተጠሪ የመድን ሽፋን እንዲሰጠው በጠየቀው መሠረት አመልካች ለአንድ ዓመት የሚቆይ የመድን ሽፋን በፖሊሲው ፎርም የሰጠው መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ እና የፖሊሲው ይዘት በንግድ ሕግ ቁጥር 654, 657 እና 658 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ይዘት ያሟላ መሆኑ በሥር ፍ/ቤት ያልተካደ በመሆኑና እነዚህ አንቀጾች በአመልካችና በተጠሪ መካከል ለአንድ ዓመት የቆየ የመድን ሽፋን መኖሩን ለማረጋገጥ በቂ ሆነው ሳለ የሥር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1725 እና 1727ን መሠረት በማድረግ በሁለቱ መካከል የመድን ውል አልተመሰረተም በማለት ተጠሪ የጠየቀውን አረቦን እንዳይከፍል መወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል።



## ው ሣ ኔ

1. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በፓሊሲ ቁጥር NK/1/MTPV/07 27/03 በተሰጠው የመድን ፖሊሲ ውል መሠረት ለአንድ ዓመት የቆየ የመድን ውል ተመስርቷል ብለናል።
2. የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 816 መጋቢት 19 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39792 የካቲት 7 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽረዋል።
3. በአመልካችና በተጠሪ መካከል የመድን ውል መኖር ስለተወሰነ በአረቦን አከፋፈል ላይ ፍ/ቤቱ የመሠለውን ውሣኔ እንዲሰጥ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት ጉዳዩ ለአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲመለስ ብለናል። ይፃፍ።
4. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።
5. መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 28254

ሐምሌ 22 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጎስ ወልዱ

ወ/ት ሒሩት መለሠ

አቶ መድሕን ኪሮስ

አቶ ፀጋዬ አስማማው

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - አትናቦን ነጋሳ ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** መኮንን መስፍን ከጠበቃ በሻዳ ገመቹ ጋር ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የመድን ዋስትና ውልን መነሻ ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው ተከሣሽ የመድን ዋስትና የገባለት የሠ.ቁ. 3-28204 አ.አ. የሆነ መኪናዬ በመገልበጥ ምክንያት ጉዳት ደርሶበታል፡፡ ተከሣሽም በገባው ግዴታ መሠረት ከወደቀበት ቦታ አስነትቶ በማምጣት በሪከቨሪ ክፊሉ ያስገባው ቢሆንም፤ በመጨረሻ ግን ሊያስጠግንልኝ አልቻለም፡፡ ስለዚህ በገባው የውል ግዴታ መሠረት መኪናውን አስጠግኖ እንዲያስረክበኝ ወይም የመኪናውን ሙሉ ዋጋ እንዲከፍለኝ መኪናው የንግድ መኪና በመሆኑ እና ተከሣሽም በተገቢው ጊዜ ለመጠገን ፈቃደኛ ሆኖ ባለመገኘቱ የተቋረጠ ጥቅም ታስቦ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ለክሱ በሰጠው መልስ የመድን ዋስትና ውል መግባቴ ትክክል ነው፡፡ ነገር ግን መኪናው የተገለበጠው በውሉ የተደረገውን ስምምነት በመጣስ ተሳቢ ሲጎትት በነበረበት ጊዜ በመሆኑ ኃላፊነት የለብኝም፡፡ የመድን ዋስትና ውሉ የተቋረጠ ገቢ እንዳይጠየቅ የሚከለክል በመሆኑ የተቋረጠ ጥቅምን በሚመለከት የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም፡፡ በተቋረጠ ጥቅም ስም የተጠየቀው የገንዘብ መጠንም የተጋነነ ነው በማለት ተከራክሮአል፡፡ ክሱን ያስተናገደው ፍ/ቤትም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ተከሳሽ በገባው ውል መሠረት የደረሰውን ጉዳት የመካስ ኃላፊነት አለበት፡፡ ስለዚህ መኪናውን አስጠግኖ ወደነበረበት በመመለስ ለከሣሽ ያስረክብ፣ በገባው የውል ግዴታ መሠረት መኪናውን ለማስጠገን ፈቃደኛ ባለመሆኑ የተቋረጠውን ጥቅም ብር 56,300 ይክፈል በማለት ወስኖአል፡፡ ከዚህ በኋላ መጀመሪያ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን፣ ተጠሪም በበኩሉ በተቋረጠ ጥቅም ስም የተወሰነው ገንዘብ አንሶአል በሚል መስቀለኛ ይግባኝ አቅርቦአል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በሁለቱም በኩል የቀረቡትን ይግባኞች መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም አመልካች የደረሰውን ጉዳት የመካስ ኃላፊነት አለበት፡፡ በመሆኑም መኪናውን አስጠግኖ ለተጠሪ ያስረክብ፡፡ እንደዚሁም ተቋረጠውን ገቢ ብር 275,000 ይክፈል በማለት ወስኖአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ኀዳር 18 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ በመደረጉም ሆነ የተቋረጠ ጥቅም እንዲከፍል የተሰጠውን ውሣኔ የሕግ አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የመድን ዋስትና ውል ስለመኖሩ አላከራከረም፡፡ ዋስትና የተገባለት መኪና በስራ ላይ እንዳለ መገልበጡንና በዚህ የመገልበጥ አደጋ የተነሣም ጉዳት የደረሰበት መሆኑም አከራካሪ

አይደለም። አመልካች ውሉን መሠረት በማድረግ መኪናውን ከወደቀበት ቦታ አስነትቶ በማምጣት ወደ ረከቨሪ ክፍሉ ካስገባው በኋላ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለብኝም በማለት ነው ወደ ክርክር የገባው። ክርክሩን በየደረጃቸው የሰሙት የስር ፍ/ቤቶችም አመልካች ኃላፊነት የለብኝም ለማለት በመከራከሪያነት ያነሳውን ነጥብ እግምት ውስጥ በማግባት ክርክሩን ከመምራታቸውም በላይ፣ በግራ ቀኝ ወገኖች በኩል የተቆጠሩትን ማስረጃዎችንም ሰምተዋል። በመጨረሻም ማስረጃዎቹን በማመዛዘን በተሻለ ሁኔታ ያስረዳው ተጠሪ እንደሆነ በመገንዘባቸው የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርገዋል። አመልካች የደረሰውን ጉዳት የመካስ ኃላፊነት እንዳለበትም አረጋግጠዋል።

እንደምንመለከተው አመልካች ኃለፊነት የለብኝም ለማለት በመከራከሪያነት ያነሳው ነጥብ በግራ ቀኝ ወገኖች ከቀረበው ማስረጃ አንፃር ታይቶ እና ማስረጃውም ተመዝኖ እልባት አግኝቶአል። የሰበር ችሎት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጡትን ውሣኔዎች አግባባነት ሊመረምር የሚችለው በሕግ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት አለ ሲባል ነው። በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ግን አመልካች ያቀረበው አቤቱታ በማስረጃ አመዛዘን ረገድ ስህተት ተፈጽሞአል ከሚል ያለፈ አይደለም። በመሆኑም ከፍ ሲል በሰጠነው ምክንያት የምንመረምረው ሆኖ አላገኘነውም። በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለትም አልቻልንም።

ከዚህ በመቀጠል የመረመርነው ተጠሪ በክሱ ከጠየቀው ገንዘብ በላይ እንዲከፈለው ተወስኖለታል በማለት አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ ነው። ተጠሪ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበው የክስ ማመልከቻ የተቋረጠ ጥቅም በማለት እንዲከፈለው የጠየቀው ገንዘብ ብር 130,400 /አንድ መቶ ሰላሳ ሺህ አራት መቶ ብር/ እንደነበር ከመዝገቡ አረጋግጠናል። የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ይህን መነሻ በማድረግ እና የመኪናው



የዓመት ገቢ ነው ያለውን መጠን እግምት ውስጥ በማግባት አስልቶ የተጠየቀው ብር 130,400 ያነሰ ገንዘብ እንዲከፈል ወስኖአል። ተጠሪም በክሱ የጠየቀውን የገንዘብ መጠን ሳይለውጥ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የወሰነው ገንዘብ አንሶኛል በማለት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦአል። በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ገንዘቡ ያንሳል ወይስ አያንስም የሚል ጭብጥ በመያዝ በእርግጥ ተጠሪ ከመኪናው በዓመት የሚያገኘው ገቢ ወይም ጥቅም ምን ያሕል እንደሆነ ለማጣራት በራሱ በኩል ማጣራቱና ማስረጃም መስማቱ ትክክል ነው። በዚህ ረገድ ፍ/ቤቱ ስህተት ፈጥሮአል ማለት የሚቻለው ተጠሪ ከጠየቀው በላይ ገንዘቡን ወደ ብር 275,000 ከፍ አድርጎ በመወሰኑ ነው። በመሆኑም ይህኛውን የውሣኔው ክፍል ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል።

በመጨረሻም የመድን ዋስትና ውሉ የተቋረጠ ጥቅም እንዳይጠይቅ ይከለክላል የሚለውን የአመልካች ክርክር ተመልክተናል። በእርግጥ በውሉ ላይ ይህን መሰል ስምምነት ስለመደረጉ የተካደ አይደለም። ነገር ግን አመልካች መኪናውን አስነትቶ ካመጣና አስጠግናለሁ በሚል እሳቤ ሪከቨሪ ክፍሉ አስገብቶ ከቆየ በኋላ ለማስጠገን ፈቃደኛ አይደለሁም በማለቱ ተጠሪ ወደ ክስ እንዲያመራ አስገድዶታል። መኪናው በንግድ ስራ ላይ ተሰማርቶ የነበረ በመሆኑ በመቆሙ ምክንያት በተጠሪ ላይ ከፍተኛ ኪሣራ እንደሚደርስ የሚያከራክር አይደለም። አንድ ተዋዋይ ወገን እንደ ውሉ ሳይፈጽም ቢቀርና በዚህ ምክንያትም በሌላኛው ተዋዋይ ወገን ላይ ጉዳት ቢደርስ የመካስ ኃላፊነት እንዳለበት በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1771/2/ የተቀመጠው ድንጋጌ በግልጽ ያመለክታል። በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው አመልካች እንደ ውሉ ለመፈጸም ፈቃደኛ ሆኖ ባለመገኘቱ በተጠሪ ላይ ጉዳት እንዲደርስ ምክንያት ሆኖአል። ከዚህ የተነሣም እንደ ውሉ ይፈጽማል የሚል ግምት ተይዞ የተቀመጠውን የውሉን አንድ አንቀጽ በመጠቀም ኪሣራውን ከመክፈል ነፃ ሊሆን የሚችልበት የሕግ ምክንያት የለም። በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት

ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚባል አይደለም። ስናጠቃልለው አመልካች ኃላፊነትንና የተቋረጠ ጥቅምን በተመለከተ ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም። በሌላ በኩል በተቋረጠ ጥቅም ስም የተጠየቀውን የገንዘብ መጠን በተመለከተ የተሰጠውን የውሣኔውን ክፍል ማሻሻል እንደሚገባ አምነንበታል። ስለዚህም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል።

**ው ሣ ኔ**

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00252 ሚያዝያ 11 ቀን 96 ዓ.ም. እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በቁ. 31541 ጥቅምት 2 ቀን 99 ዓ.ም. የተሰጡት ውሣኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል።
2. አመልካች በተጠሪው መኪና ላይ የደረሰውን ጉዳት የመካስ ኃላፊነት አለበት። በመሆኑም መኪናውን አስጠግኖ ለተጠሪ የማስረከብ እና የተቋረጠውን ጥቅም የመክፈል ኃላፊነት አለበት ብለን ወስነናል።
3. ተጠሪ በተቋረጠ ጥቅም ወይም ገቢ ስም ሊከፈለው የሚገባ ካሣ በክሱ በግልጽ የጠየቀው ብር 130,400 /አንድ መቶ ሠላሣ ሺህ አራት መቶ ብር/ ነው ብለናል። አመልካች ይህንኑ ገንዘብ ለተጠሪ ይክፈል።
4. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጡት ውሣኔዎች አልተነኩም።
5. ተጠሪ በመኪናው አለመጠገን በቀጣይ የደረሰበት ኪሣራ ካለ ክስ አቅርቦ የመጠየቅ መብቱ ይህ ውሣኔ አያስቀርበትም።
6. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር የደረሰውን ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ።
7. መዝገቡ ተዘግቷል። ይመለስ።
8. ከፌ/ከ/ፍ/ቤት የመጣው መዝገብ ቁ. 31541 ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 31334

ሐምሌ 1 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድኅን ኪሮስ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ ኃይሉ ተሰማ

**ተጠሪ፡-** 1/ ወ/ሮ ለተብርሃን በየነ

2/ የአቶ ገብረኪዳን ገዳ ወራሾች እነ ፋሲል ገ/ኪዳን - ጠበቃ ኃ/ማርያም ኢቲቻ - ቀረቡ።

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የሰበር አቤታውም ሊቀርብ የቻለው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቶ ተጠሪዎች ባቀረቡት የተከሳሽ ከሣሽነት ክስ መሠረት አመልካች የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍል ይገባል ተብሎ በመወሰኑ ነው።

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ አመልካች በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ባቀረበው ክስ ከሣሽ ንብረትነቱ የአቶ ደረጀ ጉደታ ለሆነ ተሽከርካሪ በደቡብ አብይ ቅርንጫፍ አጠቃላይ የመድን ዋስትና ሰጥቶ በእንቅስቃሴ ላይ እንዳለ ንብረትነቱ በአቶ ገ/ኪዳን ገዳ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ መኪና በመገጨቱና ከፍተኛ ጉዳት መድረሱ ለደረሰው አጠቃላይ ውድመት ከሣሽ ተገቢውን ካሣ የከፈለ ሲሆን በደረሰው አደጋ ጥፋተኛው የተከሣሽን መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ግለሰብ እንደሆነ በማስረጃ

ተረጋግጧል፣ ይሄው አደጋውን ያደረሰው ተሽከርካሪ በኢትዮጵያ መድን ድርጅት ሰሜን ምዕራብ ዓቢይ ቅርንጫፍ የመድን ዋስትና ስለነበረው በዚሁ መሠረት በ3ኛ ወገን ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት እስከ ብር 100 ሺህ ካሣ ለመክፈል ከሣሽ ኃላፊነት ስለነበረበት ይህንን ገንዘብ በቀጥታ ጠያቂ ለሆነው ለደቡብ ዓቢይ ቅርንጫፍ እንዲከፍል ተደርጓል፡፡ ስለሆነም የተከሣሽ መኪና በሌላ የ3ኛ ወገን መኪና ላይ ባደረሰው ጉዳት በዋስትና ከተገባው የ3ኛ ወገን ኃላፊነት ጣሪያ በላይ የሆነውን ብር 369,342.00 እንዲከፍሉ ይወስንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

ተከሣሽ አቶ ገብረኪዳን ገዳ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ስለተባለ የሟች ሚስትና ወራሾች በክርክሩ እንዲተኩ ተደርጎ በሰጡት መልስ አደጋ አደረሰ የተባለው የሰ/ቁ. 3-38201 መኪና በከሣሹ የመድን ሽፋን የተሰጠው ስለሆነና ጉዳቱም የደረሰው በሁለቱም መኪናዎች ላይ በመሆኑ በዚሁ መሠረት በሁለቱም መኪናዎች ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሣ መክፈል ስለሚገባው እኛን መጠየቅ አይችልም በማለት የተከራከሩ ሲሆን በሌላ በኩልም የተከሣሾች መኪና በግጭቱ መውደሙ በከሣሽ የታመነ ስለሆነ የመኪናውን የዋጋ ግምት ብር 265 ሺህ የቅሪቱን ዋጋ እና የተቋረጠ ገቢን ጨምሮ በድምሩ ብር 488 ሺህ ከሣሽ እንዲከፍል ይወስንልን በማለት የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ዋናውን ክስና የተከሣሽ ከሣሽነት ክሱን መርምሮ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ለተጎጂውም ሆነ ለጉዳት አድራሹ መኪና የመድን ሽፋን የሰጠ እንደመሆኑ መጠን ከንግድ ሕግ ቁጥር 663 እና 664 አኳያ ለሁለቱም ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ስላለበት ለተከሣሾች ካሣ የመክፈል ግዴታ አለበት ካለ በኋላ መጠኑን በተመለከተ ከሣሽ ብር 92 ሺህ ካሣ ለመክፈል መስማማቱን ከቀረበው ማስረጃ መረዳት የተቻለ ስለሆነና የመኪናውም ቅሪት ብር 250 ሺ. እንደሆነ ስለተረጋገጠ ይህንን ክፍያ ለመፈጸም ከሣሽ ፈቃደኛ የነበረ ቢሆንም ያልፈጸመ በመሆኑ በድምሩ ብር



342 ሺህ በመኪናው ላይ ለደረሰ ጉዳት ካሣ መክፈል ያለበት ስለሆነ የሟች ሚስት የሆኑት ወ/ሮ ለተብርሃን በየነ ግማሹን ማግኘት ስለሚገባቸው ብር 171 ሺህ እንዲከፈላቸው እንደዚሁም የተቋረጠ ገቢን በተመለከተ ወ/ሮ ለተብርሃን በየነ መኪናው ተጠግኖ ሥራ ቢጀምር ፈቃደኛ መሆናቸውን በ6/2/96 ዓ.ም. ባቀረቡት ማስታወሻ ለከሣሽ ያረጋገጡ ቢሆንም በዚሁ መሠረት መኪናው ተጠግኖ ያልተሰጣቸው ስለሆነ መኪናውን ለመጠገን ያስፈልጋል ተብሎ የሚገመተው የ3 ወር ጊዜ ተቀንሶ ከ6/7/96 እስከ 18/4/98 ዓ.ም. ላለው የ1 ዓመት ከ8 ወር ከ12 ቀናት የተቋረጠ ጥቅም ከሣሽ መክፈል ይገባዋል ካለ በኋላ መጠኑን በተመለከተም ወ/ሮ ለተብርሃን በየነ መኪናው በቀን ብር 700 ገቢ ያስገኝ እንደነበር በመግለጽ በዚሁ ተሰልቶ ካሣ እንዲከፈላቸው የጠየቁትን በመቀበል በዚሁ ስሌት መሠረት የወ/ሮ ለተብርሃን በየነ ድርሻ ብር 214,200 ስለሚሆን ይህንን የተቋረጠ ገቢና ከላይ የተጠቀሰውን የመኪና ጉዳት ካሣ ጨምሮ በድምሩ ብር 385,200.00 ከሣሽ ለወ/ሮ ለተብርሃን በየነ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩልም ከሣሽ ያቀረበውን ክስ በተመለከተም ከሣሽ ለወ/ሮ ለተብርሃንም ሆነ ለአቶ ገ/ኪዳን ገዳ ወራሾች ምንም ዓይነት ክፍያ ሳይፈጽም ክሱን በአቶ ገ/ኪዳን ገዳ ወራሾችና በወ/ሮ ለተብርሃን በየነ ላይ ማቅረቡ በንግድ ሕግ ቁጥር 683/3/ መሠረት አግባብነት የለውም ብሎ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሥር ከሣሽ የአሁን አመልካች በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ ይግባኙን መርምሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ አመልካች በደንበኛው ላይ ለደረሰ ጉዳት የከፈለውን ገንዘብ ደንበኛውን ተክቶ የጉዳት አድራሹን ቤተሰብ በን/ሕ/ቁ/

683/3/ መጠየቅ አይችልም መባሉ፣ በተጠሪዎች መኪና የዋጋ ግምትና በተጨማሪም የተቋረጠ ገቢ አመልካች እንዲከፍል መወሰኑ ለሰበር ቀርቦ ሊጣራ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሹ የጉዳዩ ጭብጦች፡-

አመልካች ያቀረበው ክስ ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረው በአግባቡ ነው አይደለም?

ለተጠሪ የመኪና ዋጋ ግምትና የተቋረጠ ገቢ እንዲከፈል የተወሰነው በአግባቡ ነው አይደለም? የሚሉ ናቸው፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ ከላይ እንደተመለከተው ንብረትነቱ የአቶ ደረጄ ጉደታ የሆነው ተሽከርካሪ በአቶ ገ/ኪዳን ገዳ ተሽከርካሪ ግጭት ደርሶበት ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጭ በመሆኑ ከነተሳቢው ብር 783,512.50 ካሣ የተከፈለ ስለሆነና ከዚህ ገንዘብ ላይ የመኪናው ቅሪት የተሸጠበት ዋጋና እንደዚሁም የተጠሪዎች መኪና በ3ኛ ወገን ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ለተገባ የኃላፊነት ኢንሹራንስ /liability insurance/ የተከፈለው ሲቀነስ በቀሪነት ብር 396,342.00 ስለሚፈለግ ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍሉ ይወስንልኝ በማለት ነው፡፡ የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ መልኩ የቀረበውን ክስ ሳይቀበለው የቀረው መድን ሰጭው በን/ሕ/ቁ. 683/3/ መሠረት በመድን ገቢው ሚስትና ልጆች ላይ የመዳረግ መብት ስለሌለው ለደንበኛው የከፈለው ገንዘብ ይተካልኝ በማለት ጥያቄ ማቅረብ አይችልም በሚል ነው፡፡

የንግድ ሕግ ቁጥር 683 ስለ ኢንሹራንስ ሰጭው በምትክነት መግባት /Substitution of insurer/ የሚመለከት ሲሆን በዚሁ መሠረትም ኢንሹራንስ ሰጭው በከፈለው ካሳ መጠን ጉዳቱ እንዲደርስ ባደረጉት 3ኛ ወገኖች ላይ ክስ ለማቅረብ ኢንሹራንስ ለገባው ሰው በተከፈለው ገንዘብ



መጠን ባሉት መብቶችና ክሶች ኢንሹራንስ ሰጭው ምትክ ሆኖ እንዲገባ በዚሁ አንቀጽ በንዑስ ቁጥር /1/ ሥር ተመልክቷል፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖም ለክፋት የተደረገ ካልሆነ በስተቀር ኢንሹራንስ ሰጭው በኢንሹራንስ ገቢው ወደ ታች የሚቆጠሩ ተወላጆች ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወኪሎች ሠራተኞች ወይም ከእርሱ ጋር ዘወትር አብረው በሚኖሩት ሰዎች ላይ ኢንሹራንስ ሰጭው የመዳረግ መብት እንደሌለው በዚሁ ድንጋጌ በንዑስ አንቀጽ /3/ ሥር ተመልክቷል፡፡ ይህም የአጠቃላይ መርሁ ልዩ ሁኔታ /Exception to the General Rule/ እንደሆነ የሚያሳይ ሲሆን ከዚህም ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው ኢንሹራንስ ሰጭው የመዳረግ መብት የሚኖረው በሕጉ ላይ የተዘረዘሩት ሰዎች የመድን ሽፋን በተሰጠው የመድን ገቢው ንብረት ላይ በክፋት ጉዳት አድርሰው በሚገኙበት ጊዜ እንደሆነ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካች የመዳረግ መብቱን መሠረት በማድረግ በክስ የጠየቀው በተጠሪዎች መኪና ላይ ለደረሰው ጉዳት የተከፈለው ካሣ እንዲተካለት ሳይሆን በተጠሪዎች መኪና ተገጭቶ ጉዳት የደረሰበትንና ካሣ የተከፈለበትን የአቶ ደረጀ ጉደታን መኪና በተመለከተ ስለሆነ ከላይ በተጠቀሰው የንግድ ሕግ ቁጥር 683/3/ መሠረትም የመዳረግ መብት  የሚኖረው ይሆናል ማለት ነው፡፡  ሆኖም ግን የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ አመልካች የመዳረግ መብት የለውም በማለት ክሱን ሳይቀበል መቅረቱ እንደዚሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ ለድንጋጌው የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ወደ 2ኛው ጭብጥ ስናልፍም የመድን ሽፋን የተገባለት የተጠሪዎች መኪና ቅሪቱ ተገምቶ ብር 250 ሺህ እንደሆነ እንደዚሁም የጉዳት ካሣ ብር 92 ሺህ እንደሆነና በድምሩ ብር 342 ሺህ አመልካች ለተጠሪዎች መክፈል እንደሚገባው በሥር ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ተጠሪዎች ባቀረቡት የተከሳሽ ከሣሽነት ክስ የዚህ ገንዘብ ግማሹ ብር 171

ሺ.ህ ለወ/ሮ ለተብርሃን እንዲከፈል መወሰኑ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩልም ተጠሪዎች እንዲከፈላቸው የጠየቁትን የተቋረጠ ገቢ በተመለከተም አመልካች የሚከራከረው ግራ ቀኞችን ባደረግነው ውል የተቋረጠ ገቢ እንደማይከፈል ተስማምተናል በማለት ሲሆን ነገር ግን አመልካች ጉዳት የደረሰበትን የተጠሪዎች መኪና ጠግኖ ለማስረከብ ስምምነቱን የገለጸ እንደመሆኑ መጠን ከውሉ አኳያ የተቋረጠ ጥቅም ለመክፈል የማይገደደው መኪናውን ለመጠገን አስፈላጊ ለሆነው ጊዜ (ማስጠገኑ ለሚወስደው ጊዜ) ብቻ እንጂ ከዚህ አልፎ መኪናው ሳይጠገን ለቀረበት ጊዜ በሙሉ ሊሆን አይችልም፡፡ በዚሁ መሠረትም መኪናውን ለመጠገን ያስፈልጋል የተባለው የ3 ወር ጊዜ በአእምሮ ግምት ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ በዚህ ጊዜ መኪናውን አመልካች ጠግኖ ለተጠሪዎች ካላስረከበ ደግሞ ተጠግኖ ቢሆን ኖሮ ሊያስገኝ ይችል የነበረውንና ነገር ግን ሳይከፈል የቀረውን የተቋረጠ ገቢ መክፈል ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ መጠኑን በተመለከተም መኪናው በቀን ብር 700 ገቢ ያስገባ እንደነበር ተጠሪዎች ገልጸው በዚሁ ልክ ካሣ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ ሆኖም ግን ጉዳት የደረሰበት መኪና ይህን ያሕል ገቢ ያስገባ እንደነበር በማስረጃ አላረጋገጡም፡፡ ከውልም ሆነ ከውል ውጭ ባለ ግንኙነት የጉዳት ካሣ እንዲከፈለው የሚጠይቅ ወገን የደረሰበትን ኪሣራ /Damages/ በማስረጃ ማረጋገጥ እንደሚገባው ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1790/1/ እና 2141 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይሁንና ጉዳት መድረሱ እስከተረጋገጠ ድረስ የነገሩን አካባቢ ሁኔታ ግምት ውስጥ በመክተት የካሣ መጠኑን ዳኞች በርትዕ መወሰን እንዲችሉ ሕጉ ሥልጣን የሰጣቸው እንደመሆኑ መጠን በተያዘውም ጉዳይ የከፍተኛው ፍ/ቤት አመልካች በክሥ የተጠቀውን የገንዘብ መጠን በበኩሉ አስልቶ እንዲከፈል ውሣኔ መስጠቱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡



<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. አመልካች በዚህ ጉዳይ የመዳረግ መብት ስለሌለው በክስ የጠየቀው ገንዘብ ሊከፈለው አይገባም ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ ለንግድ ሕግ ቁጥር 683/3/ የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት ስለሆነ ይህንኑ ሽረን አመልካች የመዳረግ መብት አለው ብለናል፡፡

   ስለሆነም አመልካች በመዳረግ ከጠየቀው ብር 396,342 /ሶስት መቶ ዘጠና ስድስት ሺ.ህ ሶስት መቶ አርባ ሁለት/ ላይ ግማሹን ብር 198,171 /አንድ መቶ ዘጠና ስምንት ሺ.ህ አንድ መቶ ሰባ አንድ ብር/ ተጠሪ ወ/ሮ ለተብርሃን በየነ ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡
2. አመልካች በድምሩ ብር 385,200.00 /ሦስት መቶ ሠማንያ አምስት ሺ.ህ ሁለት መቶ ብር/ ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ተብሎ የተወሰነው የካሣ መጠን በአግባቡ ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡
3. ግራ ቀኙ አንዱ ከሌላው የሚፈልገው ገንዘብ ሲቻቻል አመልካች ብር 187,029.00 /አንድ መቶ ሰማንያ ሰባት ሺ.ህ ሀያ ዘጠኝ ብር/ ለተጠሪ መክፈል የሚገባው ስለሆነ ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍል ተወስኗል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

# ወ ን ጀ ል



የሰበር መ/ቁ. 21411

ጥቅምት 5 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ ሐጐስ ወልዱ

2. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

3. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

4. አቶ አብዱራሂም አህመድ

5. አቶ ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዐ/ሕግ - ቀርቧል

ተጠሪ፡- ወ/ር ሰይድ እንድሪስ ዩሱፍ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካች ነሐሴ 18 ቀን 1997 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡

የጉዳዩ የሥር አመጣጥ ተጠሪ የወ/መ/ሕ/ቁ. 522/1ሀ/ን በመተላለፍ መጋቢት 26 ቀን 1996 ዓ.ም ከምሽቱ 6፡00 ሰዓት ላይ በፖዌ ልዩ ወረዳ በዳንጉር ቀበሌ መክላከያ ካምኘ አካባቢ ሰውን ለመግደል አስቦና አቅዶ ሟች ማስተዋል አማርቸኩል የተባለችውን በእኔ ላይ ወንድ ደርባለች በሚል ምክንያት ቂም ይዞ በመነሳሳት በያዘው ክላሽንኮቭ ጠመንጃ ጭካኔበተሞላበት ሁኔታ በሶስት ጥይት ደብድቦ ገድሏል የሚል ክስ ቀርቦበት ድርጊቱ በማለስረጃ ከተረጋገጠ በኋላ በተጠቀሰበት አንቀጽ መሠረት ጥፋተኛ ተብሎ በእድሜ ልክ ፅኑ እስራት እንዲቀጣ የመተከል ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፈርዷል፡፡ ተጠሪ በቅጣት ውሣኔው ላይ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍርድ ቤቱም በአብላጫ ድምፅ ቅጣቱን ወደ ሃያ አመት ፅኑ እስራት ዝቅ አድርጐለታል የክልሉ ዓቃቤ ሕግም በዚሁ የቅጣት ውሣኔ ቅር ተሰኝቶ ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የሰበር አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪን በማስቀረብ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ ክርክሩንም አግባብ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርም[ል፡፡ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን መርምሮ ተጠሪ ድርጊቱን መፈፀሙን ያለመካዱን፣ ተጠሪ ድርጊቱን ቢያምንም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ ዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎቹን እንዲያቀርብ ማድረጉን እና ተጠሪም እንዲከላከል መብቱ ቢጠበቅለትም የመከላከያ ማስረጃ እንደሌለው መግለፁን አስፍሮ በቀረበው የዓቃቤ ሕገ ማስረጃ መሠረት የጥፋተኝነት ውሣኔ ካሣለፈ በኋላ ዓቃቤ ሕግ ቅጣቱ በተጠሪው ላይ ከብዶ እንዲወሰንበት በመጠየቅ፣ ተጠሪም በበኩሉ ቀደም ሲል ሌላ ወንጀል አለመፈፀሙን እና ለ6 ዓመት በመከላከያ ሠራዊት አባልነት ማገልገሉን በመግለፅ ግራ ቀኙ የየበኩላቸውን የቅጣት አስተየየት ካቀረቡ በኋላ ፍርድ ቤቱ በአንድ በኩል ተጠሪ በመጥፎ አመል በቂመኝነትና በወራዳነት፣ ፍፁም በሆነ ፈቃደኝነትና ከፍተኛ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ሚችን አያ[[ጠ መግደሉ ጨካኝነቱን እንደሚያመለክት ከግምት ውስጥ በማስገባት በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ ማገልገሉና የቀድሞ ሪከርድ የሌለበት መሆኑን መገንዘቡን ገልፆ ቅጣቱን ከማቅለል ይልቅ የወንጀል አፈፃፀሙ ቅጣቱ እንዲከብድ የሚያመዝን ሆኖ መገኘቱን በመግለፅ ተጠሪ በዕድሜ ክል ፅኑ እሥራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ ተጠሪም በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ ባቀረበው ይግባኝ ወንጀሉን የፈፀመው የትዳር ጓደኛው የሆነችው ሚች በርሱ ላይ ሌላ ወንድ መደረቧ ለወንጀል ያነሣሣው መሆኑን እና በወቅቱም በስካር መንፈስ ራሱን ሊቆጣጠር የማይችልበት ደረጃ ላይ በመድረሱ መሆኑን፣ በተጨማሪም የስካር መንፈሱ እንደበረደለት በድርጊቱ ተፀፅቶ እጁን ለፖሊስ መስጠቱን ገልፆ ጠቀላይ ፍርድ ቤቱም ይግባኙን ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ድርጊቱን በደም ፍላትና በስካር መንፈስ ለመፈፀሙ ያቀረባቸው ምክንያቶች ቅጣቱን ለማቅለል የሚያስችሉ ቢሆኑም ተጠሪ ድርጊቱን በዚህ መሠረት ለመፈፀሙ ማስረጃ ያለማቅረቡን በመግለፅ ክርክሩን



ውድቅ አድርጓል፡፡ ፍርድ ቤቱ ከዚህ በመቀጠል 1. ተጠሪ ጥፋቱን አምኖ ለመንግሥት እጁን መስጠቱ 2. በሌላ ማስረጃ ባይረጋገጥም ሚች ሌላ ወንድ ደርባለች በማለት መጠርጠሩ ስሜቱን ሊነካና መረበሽንም የሚያስከትልበት ሆኖ መታሰቡና 3. ተጠሪ እስካሁን ባሉት ክርክሮች የወንጀል ድርጊቱን አምኖ መፀፀቱን ስለሚያመለክት በወ/መ/ሕ/ቁ. 79/1/መ/ እና /ሠ/ እንዲሁም 184/መ/ መሠረት ከመነሻው እድሜ ልክ በመፍረድ ቅጣቱን ወደ 20 አመት ዝቅ አድርጓል፡፡

በመሆኑም በተጠሪ ላይ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተወሰነው የእድሜ ልክ ፅኑ እሥራት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተሻሽሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቅጣትን ለማቅለል ከተጠቀመባቸው ሦስት ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱ ማለትም ተጠሪ ድርጊቱን ከፈፀመ በኋላ እጁን ለመንግሥት መስጠቱ መፀፀቱን ያመለክታል በማለት እና እስካሁን በተካሔዱት ክርክሮችም ተጠሪ ድርጊቱን አምኖ ቅጣቱ ብቻ ይቀነስልኝ ማለቱም በተመሳሳይ ሁኔታ ፀፀትን ያመለክታል በማለት የጠቀሳቸው ምክንያቶች ተቀባይነት ያላቸው ሆነው አልተገኙም ለማለት አልተቻልም፡፡ ምክንያቱም በ1996 ዓ.ም በወጣው አዲሱ የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 82/1/መ/ ላይ ወንጀለኛው ወንጀሉን ካደረሰ በኋላ በእውነት የተፀፀተ መሆኑን ለማስረዳት ጥፋቱን በመገንዘብ ራሱን ለፍትሕ አካላት ካቀረበ፣ በክስ ማመልከቻው የተገለፀውን የወንጀል ዝርዝር በሙሉ ካመነ ቅጣቱ እንደሚቀልለት ተደንግጓል፡፡ ምንም እንኳን ተጠሪ ድርጊቱን በፈፀመበት ወቅት ተፈፃሚው ሕግ የቀድሞው የ1949 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቢሆንም ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ ውሣኔ በተሰጠበት ሰኔ 13 ቀን 1997 ዓ.ም አዲሱ የወንጀል ሕግ ከግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለ በመሆኑና በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 6 ሥር አዲሱ ሕግ ከፀና በኋላ በሥራ ላይ ከነበረው /ከቀድሞው/ የወንጀል ሕግ ይልቅ አዲሱ ሕግ ቅጣት

የሚያቀል ከሆነ በዚሁ ሕግ መሠረት ቅጣቱ እንደሚቀል የተደነገገ በመሆኑ ተጠሪ ድርጊቱን ከፈፀመ በኋላ እጁን ለመንግሥት መስጠቱና የቀረበበትንም ክስ ገና ከመነሻው ጀምሮ አምኖ መገኘቱ የቅጣት ማቅለያ ተጠቃሚ የሚያደርገው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለዚህ ከላይ የተመለከቱት 3 ምክንያቶች ቅጣቱን ለማቅለል የሚያስችሉ በመሆናቸው የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአብላጫ ድምፅ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

**ው ሣ ኔ**

- የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/ይ/መ/ቁ. 647 ሰኔ 13 ቀን 1997 ዓ.ም በአብላጫ ድምፅ የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
- ውሳኔው መፅናቱን እንዲያውቁት የውሣኔው ግልባጭ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ለተጠሪ በየአድራሻቸው ይድረሳቸው፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



የሰበር መ/ቁ. 22069

ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጐስ ወልዱ

አቶ ተገኔ ጌታነህ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አቶ ብርሃኑ አመነው

**አመልካች**፡- የአማራ ብ/ክ/መንግሥት ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤ ሕግ አቶ ደረጀ ኃይሉ

**ተጠሪ**፡- አስማማው አራጌ - ከጠበቃ ወ/ሮ አዜብ ፋንታሁን ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

መዝገቡ ለሰበር ችሎት የቀረበው ተጠሪው በፈጸመው የወንጀል ድርጊት በሥር ፍ/ቤት ጥፋተኛ የተባለበት የወ/መ/ህ አንቀጽ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት መለወጡ አግባብ አይደለም ሲል አመልካች ህዳር 14 ቀን 1998 ዓ.ም አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የሰበር ችሎትም መዝገቡን ከመረመረ በኋላ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የተጠቀሰውን የሕግ አንቀጽ ለመቀየር ሕጋዊ ምክንያት የነበረው መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ግራ ቀኙን አስቀርቦ አከራክሯል፡፡

ከሥር ፍ/ቤት ውሳኔ መረዳት እንደተቻለው ለከፍተኛው ፍ/ቤት የቀረበው ክስ ተጠሪ ሚችን /ሚስቱ የነበረችውን ገነት ገበዬን/ ጨካኝና ነውረኛ በሆነ አኳኋን በመግደሉ በወ/መ/ህግ አንቀጽ 522/1/ሀ/ አመልካች መስሪያ ቤት ክስ አቅርቦ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ከተጠሪው የወንጀል አፈጻጸም አኳያ በተጠቀሰው የወንጀል ሕግ አንቀጽ የጥፋተኛነት ውሳኔ ሰጥቶ በሃያ /20/ ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ፈርዶበታል፡፡ በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት

ይግባኝ በማቅረቡ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የወንጀሉን አፈጻጸም መነሻ ምክንያትና ሁኔታ በመዘርዘር ከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል በወ/መ/ህ አንቀጽ 523 መሠረት ጥፋተኛ በማለት በዚሁ መሠረት በአሥራ ሦስት /13/ ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ፍርድ ሰጥቷል፡፡ ይህ ፍርድ በመሠረቱ የሕግ ስሕተት አለው ሲል አመልካች ያቀረበው አቤቱታ የተጠሪ የወንጀል አፈጻጸም በወ/መ/ህ አንቀጽ 522/1/ሀ/ ጥፋተኛ የሚያደርገው ሆኖ ሳለ ወደ 523 ለመለወጥ የሕግ መሠረት የለውም የሚል ነው፡፡

ከዚሁ አኳያ የሰበር ችሎቱ መዝገቡን መርምሯል፡፡ በከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ሐተታ እንደተመለከተው ሐምሌ 16 ቀን 1994 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ላይ ተጠሪና ሟች መኖሪያ ቤት ውስጥ ሆነው ተጠሪ የመኖሪያ ቤታቸውን በር ከዘጋ በኋላ ሟችን በበር መቀርቀሪያ ግንባሯን መትቷት በወደቀችበት ቦታ ሁለት እጆቿን በማሰር ብልቷ ውስጥ እጁን በማስገባት ከባድ ጉዳት እንዳደረሰባት እና በዚሁ ምክንያት ሐምሌ 23 ቀን 1994 ዓ.ም ሕይወቷ እንዳለፈ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይህንን የወንጀል ድርጊት አፈጻጸም ከቀረቡት ማስረጃዎች ጋር በማገናዘብ የድርጊቱ አፈጻጸም የተጠሪን ጨካኝነት እና ነውረኛነት ያረጋግጣል በማለት የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ለመለወጥ የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ያስቀመጠው ምክንያት “የተጠሪው ድርጊት ዘግናኝ ቢሆንም ሟችን ለመግደል አስቀድሞ ያሰበና የተዘጋጀ ለመሆኑ አልተረጋገጠም” የሚል ነው፡፡ ይህንን የጠቅላይ ፍ/ቤቱን አቋም ከወ/መ/ህግ አንቀጽ 522 ይዘት አንፃር መመርመር አግባብነት ያለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሠረቱ በወንጀል ሕግ የሀሳብ ክፍል የሚረጋገጠው ከወንጀል ድርጊት አፈጻጸም መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የተጠሪ የወንጀል አፈጻጸም በወ/መ/ሕግ አንቀጽ 522/1/ሀ/ ሥር በተመለከቱት ሁኔታዎች ውስጥ እንዲወድቅ ያደረገው ድንጋጌው “አስቀድሞ ማሰብን” እንደዋነኛ ምክንያት ወይም ብቸኛ ምክንያት የተመለከተ አለመሆኑ ነው፡፡ በዚህ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ ከባድ የግፍ አገዳደል ወንጀል መፈጸሙን ለማረጋገጥ ወይም ለማቋቋም የሚታዩት ሁኔታዎች በአማራጭ የተዘረዘሩ ሁኔታዎች መሆናቸው እንጂ አንዱ ከሌላው ጋር በተደራራቢነት እና በጋራ የሚታዩ ጉዳዮች መሆናቸው አልተመለከተም፡፡ በመሆኑም የተጠሪን የወንጀል ድርጊት አፈጻጸም ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት እንደተቻለው በመጀመሪያ በቀን የመኖሪያ ቤቱን በር በመዝጋት በሟች ጩኸት የአካባቢው ሰው ደርሶ እንዳያስጥለው ማድረጉ፣ ሟች ራሷን እንዳትከላከል በገመድ እጇን ወደ ኋላ ማሰሩ፣ እንዲሁም ሟችን በበር መቀርቀሪያ ግንባሯን መትቶ ከጣላት በኋላ ብልቷ ውስጥ እጁን በመክተት እጅግ ከፍተኛ ለሆነ ጉዳት መዳረጉ ሲታዩ ተጠሪው የድርጊቱ ውጤት ይህንን እንዲያስከትል የፈለገ መሆኑንና አስቀድሞ ማሰቡን የሚያመለክቱ ከመሆናቸውም በላይ በሚስቱ የመዋለጃ አካል ላይ የዚህ አይነት ድርጊት መፈጸሙ ነውረኛ እና ጨካኝ መሆኑን በማያጠራጥር ሁኔታ የሚያመለክት ነው፡፡ ከላይ ለማመልከት እንደተሞከረው የተጠሪ የሀሳብ ሁኔታ ከድርጊቱ በመነሳት የሚገመት መሆኑ እንዳለ ሆኖ የድርጊቱ አፈጻጸም በራሱ እጅግ ጨካኝና ነውረኛ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ከዚህም ባሻገር የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ውሳኔውን ለማሻሻል መሠረት ያደረገው ሁኔታ የተጠሪን “የስንፈተ ወሲብ” ችግር ሕብረተሰቡ ከሚያደርስበት ተፅኖ አንፃር በማየት እንደሆነ በውሳኔው ተመልክቷል፡፡ ይህም ሁኔታ የተጠሪው የተፈጥሮ ችግር ቢኖር እንኳ ጋብቻቸውን ከማፍረስ አልፎ የሟችን ሕይወት ለማጥፋቱ እንደተገቢ ምክንያት ተደርጐ መወሰዱ አግባብነት የለውም፡፡ ባጠቃላይ የከፍተኛው ፍ/ቤት የተጠሪን የወንጀል ድርጊት አፈጻጸም በማስረጃ በማጣራት አግባብነት ባለው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 522 /1/ ሀ ሥር የሰጠውን የጥፋተኛነት ውሳኔ እና ቅጣት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በቂ የሕግ ምክንያት ሳይኖረው መቀየሩ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአማራ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ. 05312 ጥቅምት 6 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የደቡብ ጐንደር ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር ወ/00320 በጥቅምት 15 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔውን እንዲያውቁት ይፃፍ፡፡
4. የዞኑ ማረሚያ ቤቶች በዚህ ፍርድ መሠረት እንዲያስፈጽሙ ይፃፍ፡፡
5. መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



የሰ/መ/ቁ. 22452

ሐምሌ 30 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

ወ/ት ሂሩት መለሰ

አቶ ፀጋዬ አስማማው

አቶ በላቸው አንሺሶ

አቶ አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** የኦሮሚያ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** አሣምነው ገ/መስቀል - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ ሊቀረብ የቻለው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምእራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በከሣሽ የአሁኑ አመልካችና በተከሳሽ የአሁኑ ተጠሪ መካከል የነበረውን በግፍ ሰው የመግደል እና በግፍ ሰው የመግደል ሙከራ የወንጀል ክርክር የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በወ/መ/ቁ. 258/94 ግንቦት 19 ቀን 1995 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተጠሪን በግፍ ሰው የመግደል ወንጀል በቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበበት ድንጋጌ፣ በግፍ ሰው የመግደል ሙከራ ወንጀል ደግሞ በዓቃቤ ሕግ በኩል የተጠቀሰበትን ድንጋጌ ዝቅ በማድረግ ተራ በሆነ የሰው መግደል ሙከራ ወንጀል በሚያስጠይቅ ድንጋጌ ጥፋተኛ ከአደረገው በኋላ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የወሰነውን ውሣኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ይኸው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤት ተጠሪን ጥፋተኛ ያደረገባቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን ዝቅ በማድረግ ቅጣቱን በተመለከተም ተጠሪን የሚያርመው ተመጣጣኝ ቅጣት የ8/ስምንት/ ዓመት ጽኑ እስራት ነው በማለት በመወሰኑ ይኸው ውሣኔ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለባቸው የሕግ አንቀጾችም ሆኑ የቅጣት

አወሣሰኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ያሣያል በማለት የአሁኑ አመልካች ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ ስህተት የለበትም በማለት ውሣኔውን በማጽናቱ ነው፡፡

አመልካች በቁጥር 05/I/A-11/1120 በቀን 20/04/98 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የተጠሪ አድራጉት በስር ፍ/ቤት ጥፋተኛ በተባሉባቸው ድንጋጌዎች የሚሸፈን ሆኖ እያለ ውሣኔ የተሰጠበት የሕግ አንቀጽ መለወጡ አግባብነት ስለሌለው ተስተካክሎ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ በዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጐም ሐምሌ 28 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት መልሱን ሰጥቷል፡፡

ይህ ችሎትም ጉዳዩን ከበታች ፍ/ቤቶች የውሣኔ ግልባጭ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የም ራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪን ጥፋተኛ ያደረገባቸውን የህግ አንቀጾች የለወጠው በአግባቡ /በሕጉ ረገድ/ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ተጠሪ በወ/መ/ህ/ቁ. 522/1/ሀ/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በክሱ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ሟች ባለቤቱን፤ ወ/ሮ ዝናሽ ለማ የተባለችውን ሕፃን ልጅ ወልዳ አራስ ቤት በተኛችበት ስፍራ ማካሮቭ ሽጉጥ ተኩሶባት አናቷ ላይ ሁለት ቦታ መቷት ለህልፈተ ህይወት ዳርጓታል፣ በወ/መ/ሕ/ቁ. 27/1/ እና 522/1/ሀ/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ደግሞ በ1ኛው ክስ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ከሟች ዝናሽ ለማ ጋር እንዳይጣላ ሰዎች ጣልቃ ገብተው ለማለያየት ሲገላግሉ ሲሉ እናንተ ነገ ምስክሮች ትሆኑብኛላችሁ አይደል? በማለት ማካሮቭ ሽጉጡን በመተኮስ የግል ተበዳይ የሆኑትን 1ኛ/ ወ/ሪት እስከዳር ጋሻውን በሁለት ጥይት ከፊቷ ላይ መቷት አንዱ ጥይት ከአንገቷ በስተኋላ ሲወጣ አንዱ ጥይት ደግሞ ከአንገቷ ስር በሰውነቷ ውስጥ የቀረ በመሆኑ፣ 2ኛ/ ወ/ሪት መና መሐመድ በምትባለው ላይም አንድ ጥይት ተኩሶባት በመሸሸዋ ህይወቷ መትረፍ የቻለ መሆኑን በመግለጽ በግፍ ሰው የመግደል ሙከራ ወንጀል ፈጽሟል የሚል ክስ በአመልካች በኩል ቀርቦበት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኋላ የተጠሪን የመከላከያ ማስረጃ የአቃቤ ሕግን ማስረጃዎች አያስተባብልም በሚል ምክንያት ውድቅ አድርጐ ተጠሪን በወ/መ/ሕ/ቁ. 27/1/ሀ/፣ 522/1/ሀ/ እና 523 ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ አድርጓል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ግን በተጠሪ ላይ የተሰጠውን የጥፋተኛነት ውሣኔ ከተቀበለ በኋላ አድራጐቶቹ የሚሸፈኑባቸው ድንጋጌዎች ግን የስር ፍ/ቤት የጠቀሣቸው አለመሆናቸውን በመግለጽ አግባብነት አላቸው ወደአላቸው ድንጋጌዎች ለውጦ ተጠሪን ጥፋተኛ አድርጓል፡፡ ይህ ችሎት ለሕግ አንቀጾቹ መቀየር ዋነኛ ምክንያት አድርጐ የያዘው ተጠሪ በወቅቱ በ1ኛ የዐ/ሕግ ምስክር ተሰድቧል የተባለው የስድብ ዓይነት ሲታይ ለወንጀል ድርጊቶቹ ቅድመ ዝግጅት እና ማነሣሣት፣ የክፋትና የጭካኔ ስሜት በሚያሣይ ሁኔታ ሣይሆን በምስክር ድርጊት የተነሣ በንዴት፣ ስሜት ውስጥ በመግባት እራሱን መቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ሁኖ ነው የሚለውን ነጥብ ነው፡፡

በመሰረቱ የሰው ግድያ ወንጀል በወ/መ/ሕ/ቁ. 522/1/ሀ/ መሰረት አንድን ሰው የሚያስጠይቀው ድርጊቱ ሆነ ተብሎ አስቀድሞ በማሰብና በመዘጋጀት ሲፈፀም ወይም በቁጥር 81 ወይም በቁጥር 83 የተመለከቱት አክባጅ ሁኔታዎች በተገኙበት ሁኔታ የወንጀል አድራጊው በተለይ ጨካኝ ወይም አደገኛ መሆኑን ሲያመለክቱ ስለመሆኑ በተጠቃሹ አንቀጽ ተደንግጓል፡፡ ከዚሁ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለውም ለወንጀሉ ማቋቋሚያ የተጠቀሱት ነጥቦች "… ወይም…" በሚል ቃል ተያይዘው የተዘረዘሩ

መሆናቸውንና ምክንያቶቹም ወንጀሉን ለማቋቋም በአንድነት ተጣምረው መገኘት ሣያስፈልጋቸው በራሣቸው ቁመው የወንጀሉ ማቋቋሚያ ሊሆኑ የሚችሉ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ቅድመ ዝግጅት እና የክፋትና የጭካኔ ስሜት ተጣምረው የመገኘት ሁኔታ የወ/መ/ሕ/ቁ. 522/1/ሀ/ ድንጋጌ ብቸኛ የወንጀሉ መቋቋሚያ ነጥቦች አይደሉም፡፡ ይልቁንም በድንጋጌው ስር የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች ለየራሣቸው መቆም የሚችሉ ናቸው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ባለቤቱን ለመግደል የ1ኛዋ የዓቃቤ ሕግ ምስክር ስድብ እንደምክንያት የማይወሰድ መሆኑን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ያመነበት ጉዳይ ሆኖ የምስክሯ አድራጐት ግን የተጠሪን የክፋትና የጭካኔ ስሜት በሚያሣይ ሁኔታ እራሱን በማዘጋጀትና በማነሣሣት ለመሆኑ አያሣይም በሚል ተደምድሟል፡፡ ይሁን እንጂ ይኸው ድምዳሜ ፍ/ቤቱ የምስክሯ አድራጐት ባለቤትን ለመግደል ምክንያት ሊሆን አይችልም ብሎ ከተነሣበት ነጥብ ጋር የሚጋጭ ነው ከመባሉ በተጨማሪ የወ/መ/ሕ/ቁ. 522/1/ሀ/ ስር የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች ለየራሣቸው ሊቆሙ የሚችሉ መሆናቸውን ያላገናዘበ ነው፡፡ ሟች በወቅቱ ወልዳ የተኛች አራስ ከመሆኗም በተጨማሪ በወቅቱ ያደረገችው ምንም አራጐት የሌለ ሆኖ ተጠሪ ለሕልፈት የዳረጋት ግንባሯ ላይ በሁለት ጥይት በመምታት መሆኑ ሲታይ የተጠሪን የጭካኔ እና የክፋት ስሜት በግልጽ የሚያሣይ ነው፡፡ ድርጊቱ የተፈፀመው በውድቅት ሌሊት የጦር መሣሪያን በመጠቀም በወቅቱ አራስ በመሆኗ ልዩ ድጋፍ በሚያስፈልጋትና እንስት መሆኗ ሲታይም አድራጐቱ በቁጥር 81(1)(ሐ) እና (ሠ) ስር እንደተመለከተው በወ/መ/ሕ/ቁ. 522(1)(ሀ) ስር የሚሸፈን መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ ተጠሪ አድራጐቱን የፈፀመው ማንነቱን ተቀብላ አብራው በመኖር ሁለት ልጅ በወለደችለት ባለቤቱ ላይ መሆኑ ከወ/መ/ሕ/ቁ. 83 አኳያ ሲታይ አክባጅ ምክንያት መኖሩን የሚያሣይና በግፍ ሰው የመግደል



አድራጐትን የሚያቋቁም ነው፡፡ በ1ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር ተነገረ የተባለው ስድብ በማናቸውም መመዘኛ አራስ የሆነችን የትዳር አጋር በክፋትና በጨካኝነት መንፈስ ለሕልፈተ-ሕይወት ለመዳረግ የሚያስችል ምክንያት ነው ሊባል አይችልም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በባለቤቱ ላይ የፈጸመው ግድያ ከቁጥር 81(1)(ሐ እና ሠ) እና ከቁጥር 83 ድንጋጌ አኳያ ሲታይም በግፍ መግደሉ ተረጋግጦ እያለ ለዚህ አድራጐት አግባብ ተብሎ በወ/መ/ሕ/ቁ. 523 ስር ጥፋተኛ መባሉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል በ2ኛው ክስ ለተጠቀሰው አድራጐት አግብብነት አለው የተባለው የወ/መ/ሕ/ቁ. 27/1/ እና 524/ለ/ ሲታይ ከምስክሯ አድራጐትና ከነባራዊው ሁኔታ አኳያ ሲመዘን ባግባቡ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አልተገኘም፡፡

በዚህም መሰረት ተጠሪ በባለቤቱ ላይ ለፈፀመው የግድያ ወንጀል ሊጠየቅ የሚገባው በወ/መ/ሕ/ቁ. 522(1)(ሀ) ሲሆን በ2ኛው ክስ በተጠቀሱት የግል ተበዳዮች ላይ ለፈፀመው አድራጐት ደግሞ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በተለወጠው ድንጋጌ መሠረት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ይህ የሚያስገነዝበው ደግሞ ተጠሪ በዚህ ችሎት ጥፋተኛ የተባለው የበታች ፍ/ቤቶች የጥፋተኛነት ውሣኔ የሰጡባቸው ድንጋጌዎች መሻሻላቸውን ነው፡፡

እንዲህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ ሊቀጣ የሚገባው በዚህ ችሎት ጥፋተኛ በተባለባቸው ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡ በአጥፊ ላይ ቅጣት የሚወሰነው ደግሞ በወ/መ/ሕ/ቁ. 86 ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ችሎቱም እነዚህን ሁኔታዎችን ተመልክቷል፤ አመዛዝኗልም፡፡ ተጠሪ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ፣ ብዙም ባለመማሩ የእውቀት ማነስና የመንፈስ ልልነት ያለበት መሆኑ እና የኋላ ታሪኩ ሲታይም መልካም የነበረ መሆኑ በቅጣት ማቅለያነት ሊያዙለት የሚገቡ መሆኑን ከወ/መ/ሕ/ቁ. 86 እና 79(1)(ሀ) ድንጋጌዎች ተገንዝበናል፡፡ እነዚህን

ምክንያቶች መሰረት ስናደርግ ደግሞ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበት የመጀመሪያው ክስ ድንጋጌ ያስቀጣው የነበረው እድሜ ልኩን ሁኖ በወ/መ/ሕ/ቁ. 184/ለ/ መሰረት መጠኑ መቅለል ያለበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለልም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ ባለቤቱን በመግደሉ ሊጠየቅ የሚገባው ድንጋጌ ተራ የሰው ግድያ ወንጀል በሚያስጠይቅበት ማድረጉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ የተጠሪ አድራጐት በግፍ ሰው መግደል የሚሸፈንና የቅጣቱ መጠንም ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ መሰረትም የሚከተለው ተወስኗል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የምእራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 258/94 ግንቦት 19 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠውን የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 02316 የካቲት 15 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠውን የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ እንዲሁም የዚሁ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 11541 ጥቅምት 07 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195/2/ለ/2/ መሰረት አሻሽለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪ በ1ኛው ክስ ለተጠቀሰው ድርጊት ጥፋተኛ የተባለበትን ድንጋጌ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 113/2/ መሰረት በመለወጥ በወ/መ/ሕ/ቁ. 522/1/ሀ/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፈ ጥፋተኛ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. ተጠሪ በ2ኛው ክስ ለተጠቀሰው ድርጊት በወ/መ/ሕ/ቁ. 27/1/ እና 524/ለ/ ስር ጥፋተኛ መባሉ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡



4. ተጠሪ ለጉዳዩ የታሰረበት ጊዜ የሚታሰብለት ሁኖ ሊቀጣ የሚገባው በ20/ሃያ/ ዓመት ጽኑ እስራት ነው ብለናል፡፡
5. ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለማረሚያ ቤቱ ይፃፍ፡፡
6. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 22514

መጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** 1. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

2. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

3. አቶ ታፈሰ ይርጋ

4. አቶ ዓሊ መሐመድ

5. አቶ ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** 1ኛ/ አቶ ኩራት ተገኘ

2ኛ/ አቶ መርሻ ኩራት

**ተጠሪ፡-** ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የወንጀል ጥፋተኝነትንና ቅጣትን የተመለከተ ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው ተጠሪ /ዓቃቤ ሕግ/ በአማራ ክልል ሰሜን ጎንደር ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካቾች ላይ በመሠረተው ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘት በአጭሩ የአሁን አመልካቾች በቂም በቀል ተነሣስተው ሰው ለመግደል በማሰብ ጌጡ ተስፋው እና ብርሌ ባላምባራስ የተባሉ የግል ተበዳዮችን ራስ ራሳቸውን በድንጋይና በዱላ ከደበደቧቸው በኋላ 1ኛ ተከሣሽ በያዘው አጭር አልቤን መሣሪያ አንድ ጥይት ተኩሶ 2ኛ የግል ተበዳይን የግራ ፊቱን በማቁሰሉ በፈፀሙት በግብረ-አበርነት ሰው የመግደል ሙከራ ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡ ፍ/ቤቱ በዓቃቤ የቀረበውን የሰውና የሕክምና ማስረጃ ሰምቶ ተከሳሾች መከላከል ሳያስፈልጋቸው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 141 መሠረት በነፃ ያሰናበታቸው ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በዓቃቤ ሕግ የቀረበለትን ይግባኝ መርምሮ ተከሣሾች በአቃቤ ሕግ ምስክሮች የተመሰከረባቸው ስለሆነ በተመሰከረባቸው መጠን ሊከላከሉ ይገባል፣



በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የተከሣሳሾችን የመከላከያ ማስረጃ በመስማት የመሰለውን ይወስን በማለት ጉዳዩን ወደ ሥር ፍ/ቤት መልሰው፡፡

ጉዳዩ የተመለሰለት ፍ/ቤትም የመከላከያ ምስክሮቹን አዳምጦ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል በመከላከያ ምስክሮቹ ቃል ስላልተስተባበለ ተከሳሾች /የአሁን አመልካቾች/ በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ ናቸው፣ ስለሆነም እያንዳንዳቸው በ10 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ሲል ወስኑ፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ ቅሬታውን ባለመቀበል ፍርዱን አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤታው የቀረበው ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ ይህ ችሎት የስር ፍ/ቤቶችን ውሣኔዎች አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር አመልካቾች ፈፀሙት በተባለው አስቀድሞ በማሰብ ሰው የመግደል ሙከራ ወንጀል ጥፋተኛ የተባሉት በአግባቡ መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ መወሰን ያለበት ነጥብ ሆኖ ስላገኘው ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ በማድረግ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡

አመልካቾች የተከሰሱትም ሆነ ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡት አስቀድሞ በማሰብ ወይም ምክንያት በማድረግ ሰው የመግደል ሙከራ ወንጀል ፈጽመዋል በሚል ነው፡፡ ምንም እንኳ በዓቃቤ ሕግ በምስክርነት የተቆጠሩት የግል ተበዳዮች ድርጊቱ የተፈፀመው በድንበር ግጭት ምክንያት የአሁኖቹ አመልካቾች ቂም በቀል ይዘው ነው የሚል የምስክርነት ቃል ስለመስጠታቸው በስር ፍ/ቤት የውሣኔ ሐተታ ላይ የተመለከተ ቢሆንም ይህ አባባል ከእነሱ ቃል በስተቀር በሌላ ገለልተኛ ማስረጃ ተደግፎ አለመገኘቱን ተገንዝበናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዓቃቤ ሕግ የቀረበው የሰውና የሕክምና ማስረጃ ያረጋገጠው ነገር በግል ተበዳዮች ላይ “የአጥንት ስብራት የሌለበት ቀላል እብጠትና ደም ያለው ምልክት” መሆኑ ታውቋል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ጉዳይ ተፈፀመ የተባለው ተግባር ተራ የሆነ የሰው መግደል ሙከራ ወንጀል

መሆኑን ይህ ችሎት አምኖበታል፡፡ በመሆኑም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 113/2/ መሠረት አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉበትን የወ/መ/ሕ/ቁ. 27/1/ እና 522/1/ሀ/ በመለወጥ አመልካቾች በወ/መ/ሕ/ቁ. 27/1/ እና 523 መሠረት ጥፋተኞች ናቸው ብለናል፡፡

አመልካቾች የቀድሞ የጥፋተኛነት ሪከርድ የሌለባቸው መሆኑን ከሥር ፍ/ቤት ውሣኔ በመረዳት በወ/መ/ሕ/ቁ. 86 ላይ የተደነገገውን ከግምት አስገብተን አመልካቾች እጃቸው ከተያዘ ጊዜ ጀምሮ በ5 ዓመት /አምስት ዓመት/ ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስነናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

- የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በ8/11/97 በመ/ቁ. 00665 የሰጠው ውሣኔ እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በ30/3/98 በመ/ቁ 07247 የፀናው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
- ውሣኔው መሻሻሉን እንዲያውቁት የውሣኔው ግልባጭ ለፍርድ ቤቶቹ ይተላለፍ፣
- ውሣኔው የተሻሻለ መሆኑን አውቆ በተሻሻለው ውሣኔ መሠረት እንዲያስፈጽም የውሣኔው ግልባጭ እስረኞቹ ለሚገኙበት ማረሚያ ቤት ይተላለፍ፣
- መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፣

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰበር መ.ቁ. 23855

ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ ሐጎስ ወልዱ

ወ/ት ሂሩት መለሠ

አቶ ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የጉምሩክ ዐቃቤ ሕግ ሙሉእመቤት ውብአየሁ

ተጠሪ፡- አቶ ፀጋሁን መንግሥቱ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የሰበር አቤቱታ ከመ.ቁ. 23523፣ 24021፣ 23533፣ 23532፣ 23522፣ 23527፣ 24020፣ 23531፣ 23534፣ 23530፣ 23820፣ 23710፣ 27500፣ 23529፣ እና 23528 ጋር በተመሣሣይ የሕግና የፍሬ ነገር ክርክር ላይ ተመስርቶ የቀረበ ስለሆነ ሁሉም መዛግብት ጎን ለጎን ተመርምረው ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በተለያዩ የወንጀል መዛግብት ተጠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 74 የተመለከተውን በመተላለፍ ምንም ዓይነት የጉምሩክ ሥነ - ሥርዓት ሣይፈፀምበት የመንግሥት ቀረጥ ያልተከፈለበትን መኪና ይዘው የተገኙ ስለሆነ በፈፀሙት ሕገወጥ ዕቃ ይዞ መገኘት ወንጀል ተከሰዋል የሚል ክስ አቅርቦ ፍ/ቤቱም በእያንዳንዱ የወንጀል መዝገብ የከሣሽን ማስረጃ ሰምቶ ተከሣሾች በየበኩላቸው ይዘው ተገኝተዋል የተባሉትን መኪናዎች በሕጉ ላይ እንደተመለከተው እያወቁ ይዘው ስለመገኘታቸው በከሣሽ ማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 141 መሠረት ተከሣሾች መከላከል ሣያስፈልጋቸው በነፃ እንዲሰናበቱ ብይን በመስጠቱና በዚሁ ብይን ላይ የቀረበው ይግባኝ በፌዴራል ከ/ፍ/ቤት ተቀባይነት ሣያገኝ በመቅረቱ

አመልካች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታም ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበት መኪና በግለሰብ እጅ መገኘቱ ሕገወጥ በመሆኑ የተያዙት መኪናዎች ሊወረሱ ወይንም ቀረጥና ታክስ ሊከፈልባቸው እንደሚገባ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 60/89 እንደተሻሻለው መደንገጉ እየታወቀ የበታች ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ ምንም ሣይሉ ማለፋቸው ከፍተኛ የሕግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ አመልካች ያቀረበው ቅሬታ ከሕጉ አኳያ ተጣርቶ ሊወሰን እንደሚገባ በማመኑ በየመዝገቡ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ተጠሪዎችም በየበኩላቸው ያቀረቡት ክርክር ተጠቃሎ ሲታይ አመልካች የመኪናዎቹን መወረስም ሆነ የቀረጥ ክፍያን አስመልክቶ የሚያቀርበው ክርክር በወቅቱ በሥራ ላይ ከነበረው አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 74 ድንጋጌ ውጪ ነው፡፡ በዚህ አዋጅ ተከሣሹ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ባይገኝም ንብረቱ እንደሚወረስ ወይንም ቀረጥና ታክስ እንደሚከፍል አልተደነገገም፡፡ አመልካች አዋጅ ቁጥር 60/89 እንደተሻሻለ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበት መኪና ሊወረስ ወይንም ቀረጥና ታክስ ሊከፈልበት እንደሚገባ የተደነገገ መሆኑን ገልጾ ቢከራከርም የአዋጁ ማሻሻያ ወደኋላ ተመልሶ ሊሰራ ስለማይችል አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች በተጠሪዎች ላይ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክስ ያቀረበባቸው ከላይ እንደተጠቀሰው በአዋጅ ቁጥር 60/89 በአንቀጽ 74 ላይ የተመለከተውን



በመተላለፍ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመባቸውን መኪናዎች ይዘው የተገኙ ስለሆነ በፈፀሙት ወንጀል ተከሰዋል በማለት ነው፡፡

በተጠቀሰው ድንጋጌ መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ተከሣሽ የእቃው መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ በዕቃው ላይ ሊከፈል ከሚገባው ጠቅላላ የቀረጥ ሂሣብ በማያንስ የገንዘብ መቀጮና ከ3-5 ዓመት በሚደርስ እሥራት እንደሚቀጣ በድንጋጌው ላይ ተመልክቷል፡፡

ሆኖም በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆኑት መኪናዎች ተገቢው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት እንዳልተፈፀመባቸውና ቀረጥና ታክስም ያልተከፈለባቸው መሆኑን ከማስረዳት በስተቀር በሕጉ ላይ እንደተመለከተው ተከሣሾች በይዞታቸው ሥር የሚገኙት መኪናዎች የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት እንዳልተፈፀመባቸው እያወቁ ይዘው ስለመገኘታቸው ባለማስረዳቱ ተከሣሾች ከቀረበባቸው የወንጀል ክስ መከላከል ሣያስፈልጋቸው በብይን በነፃ ተሰናብተዋል፡፡

አመልካች ክሱን ያቀረበው ከላይ በተጠቀሰው አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 74 መሠረት እንደመሆኑ መጠን በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመኪናው መወረስም ሆነ የገንዘብ ቅጣትና እሥራት ሊወሰን የሚችለው ተከሣሹ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ብቻ ነው፡፡

በሌላ በኩልም ይሄው አዋጅ ቁጥር 60/89 በአዋጅ ቁጥር 388/95 የተሻሻለ ሲሆን በዚህ በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 385/95 አንቀጽ 80(3) መሠረት በወንጀል የተከሰሰው ግለሰብ ከወንጀሉ ክስ በነፃ የተሰናበተ ቢሆንም እንኳን እቃው ወይም ማጓጓዣው የጉምሩክ ሕግን የሚፃረር ስለመሆኑ የቀረበው መረጃ አጥጋቢ በሆነ ጊዜ ፍ/ቤቱ ንብረቱ እንዲወረስ ትእዛዝ መስጠት እንደሚችል ወይንም ተገቢው ቀረጥና ታክስ እንዲከፈል ወይም ሌላ አግባብነት ያለውን ትእዛዝ በመስጠት እቃው ወይም ማጓጓዣው ለባለቤቱ ወይም ለተያዘበት ሰው እንዲመለስ እንደሚያደርግ ተመልክቷል፡፡

በዚህ ረገድ ተጠሪዎች የሚከራከሩት የአዋጁ ማሻሻያ ወደ ኋላ ተመልሶ ሊሰራ አይችልም በማለት ነው።

በእርግጥ የወንጀል ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ እንደማይሰራ በሕገ መንግሥታችን አንቀጽ 22 እንደዚሁም በወንጀለኛ መቅጫ ሕጋችን በአንቀጽ 5 ላይ ተመልክቷል።

ይሁንና የጉምሩክ ሥነ - ሥርዓት ያልተፈፀመበት ንብረት እንዲወረስ ወይንም ቀረጥና ታክስ እንዲከፈልበት በተሻሻለው አዋጅ ላይ መካተቱ የዚህ ዓይነት ግዴታ መሠረት በቀጥታ ከግብር ሕግ የመነጨ ግዴታ እንጂ ከወንጀል ሕግ የመነጨ ኃላፊነት ባለመሆኑ የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ አይሰራም በሚለው የወንጀል ሕግ መርህ ሥር የሚሸፈን አይሆንም።

ከዚህም በተጨማሪ የተሻሻለው አዋጅ የፀናው ከጳጉሜ 1 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን አመልካች በእያንዳዱ ተጠሪ ላይ የወንጀል ክሱን የመሠረተው አዋጁ ከፀና በኋላ በተወሰኑት ላይ በ1996 ዓ.ም በተወሰኑት ላይ ደግሞ በ1997 ዓ.ም ነው። አመልካች የመሠረተው በዋናነት የወንጀል ክስ እንደመሆኑ መጠን መጥቀስ የሚጠበቅበት ወንጀል ነው የተባለው ተግባር ተፈፀመ በተባለ ጊዜ በሥራ ላይ የነበረውን ድንጋጌ እንደሆነ ይታመናል። በሌላ በኩልም የንብረቱን መወረስም ሆነ የቀረጥና የታክስ ክፍያን አስመልክቶ ተሻሽሎ በወጣው ሕግ ላይ የተመለከተው ከወንጀል ኃላፊነት ተነጥሎ መታየት የሚገባው እንደመሆኑ መጠን ከወንጀሉ ክስ ጋር ተያይዞ የቀረበ ቢሆንም ክሱ በቀረበ ጊዜ አዋጁ በሥራ ላይ እስከዋለ ድረስ በዚሁ በተሻሻለው አዋጅ መሠረት ክርክሩ እልባት እንዲያገኝ ቢደረግ ሕጉ ወደ ኋላ ተመልሶ ሠርቷል የሚያሰኝ አይሆንም። ከዚህም ከተሻሻለው ሕግ አኳያ ክርክሩ ሲታይ በተጠሪዎች እጅ የነበሩት ተሽከርካሪዎች ቀረጥ ያልተከፈለባቸው መሆናቸውን አመልካች በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረባቸው ማስረጃዎች በአጥጋቢ ሁኔታ የሚያረጋግጡ እንደመሆናቸው መጠን



የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም ሆነ ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚሁ በተሻሻለው አዋጅ መሠረት ለጉዳዩ ዕልባት አለመስጠታቸው በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም።

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌደራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 34003፣ 52056፣ 51818፣ 33863፣ 33867፣ 33868፣ 33864፣ 34000፣ 34007፣ 34001፣ 33937፣ 34008፣ 33862፣ 33933፣ 33858፣ 33865 እንደዚሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 31745፣ 31625፣ 31104፣ 31063፣ 31698፣ 31619፣ 31068፣ 31621፣31101፣3777፣31623፣ 31103፣ 31624፣ 31776፣ 42070፣ እና 45618 የሰጧቸው ውሣኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው ስለሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348 (1) መሠረት ተሽረዋል።
2. በተጠሪዎች ይዞታ ሥር የነበሩት ተሽከርካሪዎች አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመባቸው መሆናቸው አመልካች ባቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ ተጠሪዎች ለመንግሥት መከፈል ያለበትን ቀረጥና ታክስ በመክፈል መኪናዎቹን እንዲረከቡ ቀረጥና ታክስ ካልከፈሉም መኪናዎቹ እንዲወረሱ በአዋጅ ቁ. 388/95 አንቀጽ 80 (3)(ሀ) እና (ለ) መሠረት ተወስኗል።
3. በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሣኔ ከላይ በተጠቀሱት መዝገቦች ላይ ተፈፃሚነት ስላለው የውሣኔው ግልባጭ በእያንዳንዱ መዝገብ ላይ እንዲያያዝ ታዟል።
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 24278

ኀዳር 10 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. አቶ ሐጎስ ወልዱ

4. ወ/ት ሒሩት መለሠ

5. አቶ ታፈሠ ይርጋ

**አመልካች፡-** ሰለሞን ሄርጳቦ

**ተጠሪ፡-** የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የሥ/ፀ/ሙ/ኮ/ዐ/ሕግ

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የጀመረው በሃዲያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በመሠረተው ክስ አመልካች በሥራው አጋጣሚ እጁ የገባውን ያልተሠራበት አንድ ጥራዝ የገቢ መሠብሠቢያ ደረሰኝ በመሰወር የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት አ/ቁ. 214/74 አንቀጽ 13/1/ን በመጥቀስ ክስ አቅርቧል፡፡ ዐቃቤ ሕግ ክሱን ያስረዳሉ ያላቸውን ማስረጃዎች አቅርቦ አመልካች ክሱን እንዲከላከል በተሠጠው ብይን መሠረት መከላከያ አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አመልካቹ በተጠቀሰበት አንቀጽ ጥፋተኛ ነው በማለት በ6 ዓመት እስራትና በ200 ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍ/ቤትም በአመልካች የቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ ባለመቀበል የሠረዘው ሲሆን የክልሉ ሠበር ችሎትም ውሣኔው የሕግ ስህተት የለበትም ብሏል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

ይህ ችሎትም አመልካች ፈፀመ የተባለው ድርጊት በአዋጅ ቁ. 214/74 አንቀጽ 13/1/ ድንጋጌ የሚሸፈን ነው ወይ? የሚለውን ለመመርመር ሲል ተጠሪ እንዲቀርብ በማድረግ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር አድምጧል፡፡ መዝገቡንም መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው ዐቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው አመልካች የሶሮ ወረዳ የፋይናንስ ጽ/ቤትን ለመመርመር በሄዱበት ወቅት ንብረት ክፍሉን ሲመረምሩ በሥራቸው አጋጣሚ በእጃቸው የገባውን የገቢ ደረሠኝ ሠውረው የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽመዋል በሚል ነው፡፡

በአዋጅ ቁ. 214/74 አንቀጽ 13/1/ መሠረት የተከሰሰ ሰው ጥፋተኛ ሊሆን የሚችለው እንዲጠብቃቸው በአደራ የተረከባቸውን ወይም በሥራው አጋጣሚና ምክንያት በእጁ የገቡትን ንብረቶች የወሠደው ወይም የሰወረው ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማገኘት በማሠብ ከሆነ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ መሠረት ወንጀል ተፈጽሟል ሊባል የሚችለው በሥራ አጋጣሚ በእጅ የገባው ንብረት በመጥፋቱ ብቻ ሣይሆን ንብረቱ እንዲጠፋ የተደረገው ያለአግባብ ለመበልፀግ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማስገኘት በማሠብ ጭምር ከሆነ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የአጥፊው ሃሣብ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች የገቢ ደረሠኞቹን የሠወረ መሆኑ ቢረጋገጥም ሠነዱን የሠወረው ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት በማሰብ ሆነ ብሎ የፈፀመው ድርጊት መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ ይህ የሃሣብ ክፍል መኖሩ ሣይረጋገጥ ሠነዱ በመጥፋቱ ብቻ አመልካቹ በአዋጅ ቁ. 214/74 አንቀጽ 13/1/ ሥር በተመለከተው መሠረት የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በሚል የተሠጠው የጥፋተኛነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

1. የሃዲያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00261 በ11/12/96 የሠጠው ውሣኔ እና የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 7406 በ02/01/98 የሠጠው ውሣኔ እንዲሁም የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 11605 በ25/05/98 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች በተከሠሠበት የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ አይደለም፡፡
3. አመልካች ሌላ የታሠረበት ጉዳይ ከሌለ እንዲፈታ ለማረሚያ ቤቱ የመፈቻ ትዕዛዝ ይፃፍ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ.28952

መጋቢት 16 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጐስ ወልዱ

ወ/ት ሂሩት መለሰ

አቶ ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** የጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ - ሙሉእመቤት ውባየሁ

**ተጠሪ፡-** አቶ ባንቲ ታኤራ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በተጠሪ ላይ አቅርቦት የነበረውን ክስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 122(2) መሰረት ካነሳ በኋላ በድጋሚ ክስ ሊያቀርብ አይችልም በማለት ድጋሚ የቀረበውን ክስ የሥር ፍ/ቤቶች ሳይቀበሉት በመቅረታቸው ነው፡፡

ይህ ችሎትም የቀበረውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ የቀረበው የወንጀል ክስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 122(2) መሰረት ለጊዜው ተቋርጧል ተብሎ ከታዘዘ በኋላ አቃቤ ሕጉ ክሱን ለመቀጠል አይችልም መባሉ ተጠሪ ባለበት ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው ሆኖ በማግኘቱ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

የክርክሩ ነጥብ ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሥር ፍ/ቤቶች ክሱ ሊቀጥል አይችልም ያሉበት ምክንያት አግባብነት እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የወንጀል ክርክር በሚመራበት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥ/ሥ/ቁ. 122(2) መሠረት አንድ ክስ በከሳሽ (በዓቃቤ ሕግ) ጥያቄ እንዲነሳ ከተደረገ በኋላ ክሱን ለወደፊት ለመቀጠል የሚከለክል እንደማይሆን በዚሁ አንቀጽ

በንኡስ አንቀጽ 5 ላይ ተመልክቷል፡፡ የወንጀል ሕግ መርህም የሚከተለው በወንጀል የተከሰሰ ሰው በተከሰሰበት ጉዳይ ጥፋተኛ ነው ከተባለ ወይንም በነጻ ከተለቀቀ በኂላ በዚያው ጉዳይ ዳግመኛ ክስ የማይቀርብበት መሆኑን በተመለከተ ነው፡፡

ስለሆነም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት መሠረት ከሳሽ (ዓቃቤ ሕግ) ክስ ማንሳት እንደሚችልና ያነሳውንም ክስ መቀጠል እንደሚችል የተመለከተ በመሆኑ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተነሳው ክስ ሊቀጥል አይችልም በማለት የዐ/ህግን ጥያቄ ሳይቀበለው መቅረቱ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 43170 በ27/3/97 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 35780 ሕዳር 11 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆኑ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195(2) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች አስቀድሞ ክስ ማንሳቱ በድጋሚ ክሱን ለመቀጠል የሥነ ሥርአት ሕጉ የሚፈቅድት ስለሆነ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክሱን ተቀብሎ ግራ ቀኙን አከራክሮ እንዲወስን ተመልሶለታል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 29325

የካቲት 18 ቀን 2000ዓ.ም

**ዳኞች፡-** 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ሐጎስ ወልዱ

4. ወ/ት ሒሩት መለሠ

5. አቶ ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** ኤርምያስ ካሣ ተፈራ - ጠበቃ ስንታየሁ ባህሩ ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** ዓቃቤ ሕግ - ሺበሺ ይግዛው ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

አመልካች የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 26583 ታህሣሥ 26 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ቀርቦ የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር ተሰምቶአል፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሣሽ የነበረው አመልካች የተከሰሰው የወ/መ/ሕግ ቁ.27/1/ እና 522/1/ሀ/ ድንጋጌን በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሞአል ተብሎ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም አመልካች ቀርቦ ሲጠየቅ ጥፋተኛ አይደለሁም ስላለ ፍ/ቤቱ በቅድሚያ የዓቃቤ ሕግን ማስረጃ ሰምቷል፡፡ በመቀጠልም አመልካች እንዲከላከል ብይን በመስጠት የአመልካችን የመከለከያ ማስረጃ ሰምቶል፡፡ በመጨረሻም አመልካች በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ስላገኘው በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡ አመልካች ይህን ውሣኔ በመቃወም ነው ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበው፡፡ ፍ/ቤቱ ግን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ የወሰነው አመልካቹ በሌለበት ስለሆነ ይግባኝ ከማለቱ በፊት ፍርዱን ለፈረደው ፍ/ቤት

ማመልከት አለበት የሚል ምክንያት በመስጠት ወደ ይግባኙ ስረ ነገር ሳይገባ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎት አቤቱታውን አስቀርቦ የሰማው አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ለወንጀሉ ክስ የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቶ እና የመከላከያ ማስረጃውንም አሰምቶ ተከራክሮ እያለ የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሣኔ ሲሰጥ በመገኘቱ ብቻ ጉዳዩ በሌለበት እንደታየ ተቆጥሮ ይግባኙ ሳይታይ የመታለፉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህንን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ትዕዛዝ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል በዝርዝር እንደተገለፀው ክርክሩ /ጉዳዩ/ ከመሠረቱ አመልካች በሌለበት የታየ አይደለም፡፡ ይልቁንም አመልካች በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርቦ በሰጠው መልስ ክሱን ክዶ በመከራከሩ በዓቃቤ ሕግ በኩል የተቆጠሩት ማስረጃዎች እና በአመልካች በኩል የተቆጠሩት የመከላከያ ማስረጃዎች አመልካቹ ባለበት ተሰምተዋል፡፡ የክርክሩ መሰማት ሂደት በዚህ መልክ ከተካሄደም ቀጥሎ የሚሆነው በተሰማው ክስ እና ማስረጃ መሠረት የመጨረሻ ውሣኔ መስጠት ነው፡፡ ውሣኔው የሚመሠረተውም በተሰማው ክርክር እና ማስረጃ ላይ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየውም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የጥፋተኛነቱንም ሆነ የቅጣት ውሣኔውን የሰጠው አመልካች ባለበት የሰማውን ክርክር እና ማስረጃ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በእርግጥ ውሣኔው በተሰጠበት ጊዜ አመልካች ፍ/ቤት አልቀረበም፡፡ ከዚህ የተነሣም ውሣኔው የተሰጠው አመልካች በሌለበት እንደሆነ በውሳኔው መግቢያ ላይ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም ለተያዘው አቤቱታ አወሳሰን ሊታይ የሚገባው ነጥብ ክሱና ማስረጃው ለውሣኔ በተቀጠረ ጊዜ የቀረ ተከሣሽ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 161/1/ በተደነገገው መሠረት ጉዳዩ በሌለበት እንደተሰማ ይቆጠራል ወይ? የሚለው ነው፡፡



በበኩላችን እንደምናየው በወንጀል የተከሰሰ ሰው ፍ/ቤት እንዲቀርብ የሚጠራው የተከሰሰበትን ወንጀል እንዲያውቅ እና የሚከላከል ቢሆንም ሕጉ በሰጠው መብት እንዲጠቀም ነው፡፡ ተከሣሹ ይህ የመከላከል መብቱን ላለመጠቀም በተደረገለት ጥሪ መሠረት ሳይቀርብ ቢቀር ሕጉ ባስቀመጠው ድንጋጌ መሠረት ጉዳዩ /ክሱ/ ተከሣሹ በሌለበት ተሰምቶ ይወሰናል፡፡ እዚህ ላይ እንግዲህ ትኩረት የሚያስፈልገው ቁልፍ ነገር የተከሣሹን የመከላከል መብት ሲሆን፣ ይህም የእምነት ክህደት ቃል ከመስጠት ጀምሮ የመከላከያ ማስረጃ እስከ መስማት ድረስ ያለውን ሂደት የሚያጠቃልል ነው፡፡ በመሆኑም ተከሣሹ ቀርቦ የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቶ እና የመከላከያ ማስረጃውን አሰምቶ ከሆነ ክሱ እሱ በሌለበት ነው የታየው ለማለት የሚቻልበት የሕግ ምክንያት አይኖርም፡፡ ዓቃቤ ሕግ ለሰበር አቤቱታው የሰጠው መልስ አመልካች የተሰጠበትን ውሣኔ በመሸሽ የተደበቀ በመሆኑ በጠበቃው አማካይነት የቀረበው አቤቱታ ሊታይለት አይገባም በማለት መከራከሩን ተገንዝበናል፡፡ ይሁንና ይህ ክርክር ምን ውጤት ይኖረዋል? የሚለው ይግባኙን በሚሰማው ፍ/ቤት ከሚታይ በስተቀር በዚህ ሰበር የሚስተናገድ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ሲጠቃለል ጉዳዩ /ክሱ/ የታየው አመልካች በሌለበት ነው በሚል የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት የደረሰበት መደምደሚያ የሕግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለዚህ የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 195 መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት አመልካች የቀረበለትን ይግባኝ እንዲቀበል፤ በመሰለው ሁኔታ ይግባኙን አይቶ የራሱን ትዕዛዝ ወይም ውሣኔ እንዲሰጥ ብለን ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ 31731
የካቲት 18 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ
አብዱልቃድር መሐመድ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** የኦሮሚያ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ - ተሾመ ግርማ ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** ዘሪሁን ታደሰ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ተጠሪ አስገድዶ የመድፈር ወንጀል ፈጽሞአል በሚል ቀረበውን ክስ መሠረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀረው በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ በምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ዓቃቤ ሕግ በተጠሪው ላይ ክስ የመሠረተው ተከሣሽ በወ/መ/ሕግ ቁ. 590 የተመለከተውን በመተላለፍ ወ/ሪት አስማረች መርሳ የተባለችውን አስገድዶ በመድፈር ክብረ ንጽሕናዋን /ድንግልናዋን/ ገስሏል በማለት ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት ተጠሪውን አስቀርቦ የእምነት ክህደት ቃል ከሰማ በኋላ፣ ዓቃቤ ሕግ ያቀረበውን የጽሑፍ እና የሰው ማስረጃ ሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ዓቃቤ ሕግ እንደ ክሱ አላስረዳም የሚል ምክንያት በመስጠት ተጠሪ ተከላከል ሊባል አይገባም በማለት ብይን ሰጥቶአል፡፡ በዚህ ብይን ላይ ይግባኝ የቀረበላቸው የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት እና የሰበር ችሎትም ብይኑ ጉድለት የለበትም ብለዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 6 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪው



በተከሰሰበት ወንጀል መከላከል ሳያስፈልገው በነፃ ይሰናበት የተባለበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ብይን እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ክሱ የወንጀል እንደመሆኑ ተከሣሹ /የአሁን ተጠሪ/ የእምነት ክህደት ቃሉን እንዲሰጥ ከተጠየቀ በኋላ፣ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች /ማስረጃዎች/ ተሰምተዋል፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ዓቃቤ ሕግ ያሰማው ማስረጃ የግል ተበዳይን ጨምሮ አምስት ምስክሮች እና አንድ የጽሁፍ ማስረጃን የሚጠቃልል ነው፡፡ የግል ተበዳይ በሰጠችው የምስክርነት ቃል ዓቃቤ ሕጉ በክሱ በተሰጠቀሰው ቀንና ሰዓት ተጠሪ ቡና ታፈላ ከነበረችበት ክፍል ውሃ አቀብይኝ ብሎ እንደጠራት እና አስዋም ውሃ በጀሪካን ስትወስድለት በቤቱ /በራሱ ቤት/ በር ስር ቆሞ በመጠበቅ ይዞአት ወደ መኝታ ክፍሉ በመውሰድ ፖንትዋን /የውስጥ ሱሪዋን/ በግድ አውልቆ እንደደፈራት፣ አስዋም ለጊዜው እራስዋን ስታ እንደነበር፣ ሰውነትዋ እንደደማ፣ በመቀጠልም ጬኸት እያሰማች 3ኛ እና 4ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮችን፣ መጥራትዋን፣ ተጠሪም ቀስ አድርጎ በማስኬድ ወደ ቤትዋ እንዳስገባት በማረጋገጥ እንደመሰከረች የከፍተኛው ፍ/ቤት በሰጠው ብይን ላይ በግልጽ ተመልክቶአል፡፡ በመቀጠል የተሰማችው 2ኛዋ የዓቃቤ ሕግ ምስክርም ተጠሪ የግል ተበዳይዋን ሲደፍር አለማየትዋን በአንድ በኩል ብትገልጽም፤ በሌላ በኩል ግን በዓቃቤ ሕግ ክስ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት የግል ተበዳይ ቡና ስታፈላላቸው ቆይታ ሁለተኛውን /ከአቦል ቀጥሎ ያለውን/ አፍልታ ለማምጣት ወደኩሽና መውጣትዋን ከ30 /ሰላሣ/ ደቂቃ በኋላ ተጠሪ ድንግልናየን ወሰደብኝ እያለች እየጮኸች መምጣትዋን፣ ልብስዋን ወደ ላይ አድርጋ ስታሳያትም ደም ማየትዋን፣ የግል ተበዳይን ይዛ ወደ ተጠሪው ቤት ስትሄድ ተጠሪ እቤቱ ውስጥ ሆኖ ቆዩ ሰው እየመጣ ነው ሲል መስማትዋትን በማረጋገጥ መስክራለች ተብሎ በብይኑ ተገልጸአል፡፡

ሌሎች 3ኛ እና 4ኛ ተብለው የተመዘገቡት የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች እንደዚሁ ሰጡት የተባለው የምስክርነት ቃል እንዳየነው በዓቃቤ ሕግ ክስ በተጠቀሰው ቀን እና ሰዓት አካባቢ በተጠሪው ቤት ተቀምጠው ሳለ የግል ተበዳይ የተጠሪን ቤት ማንኳኳትዋን፣ እነሱም በሩን ከፍተው ወደ ውጪ ሲወጡ ተጠሪ አስገድዶ ስለደፈረኝ ጠይቁልኝ ማለትዋን፣ እነሱም እንጠይቅልሻለን ብለው መልስ እንደሰጡአት መናገራቸውን /መመስከራቸውን/ የሚያመለክት ነው፡፡ በ5ኛ ምስክርነት የተመዘገበው ፖሊስ ሲሆን፣ የመሰከረውም የግል ተበዳይ ተደፈረች በተባለበት ማግስት ከረፋዱ አምስት ሰዓት ላይ መደፈርዋን በመግለጽ ማመልከትዋን /አቤቱታ መቅረብዋን/ እንደሚያውቅ፣ ተጠሪም የግል ተበዳይ ምን ብላ አመለከተች ተብሎ ያኔ እንደ ጠየቀው፣ ምስክሩ ምን ብላ እንዳመለከተች ሲነግረውም ወደፊትም ክሱ የሚደርስበትን ደረጃ ትነግረኛለህ እንዳለው በመግለጽ መመስከሩ ተመዝግቦአል፡፡

በመጨረሻ ክሱን የሰማው ፍ/ቤት የተመለከተው ማስረጃ ከግምቢ ሆስፒታል የተሰጠውን የሃኪም ማረጋገጫ ነው፡፡ በዚሁ ማስረጃ የተገለጸው በግል ተበዳይ ላይ የክብረ ንጽሕና መድፈር ተግባር መፈጸሙን፣ ብልትዋ ወደላይ አብጦ መገኘቱን፣ እየደማም እንደነበር፣ ሁኔታው የግል ተበዳይ ተገዳ መደፈርዋን ሊያመለክት እንደሚችል ነው፡፡

እንደምንመለከተው በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው ክስ እና ማስረጃ ከላይ በዝርዝር የተገለጸው ሲሆን፣ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም ይህንኑ በግልጽ ከመዘገበ በኋላ፣ ዓቃቤ ሕግ እንደ ክሱ አላስረዳም የሚል ምክንያት በመስጠት ተጠሪን በነፃ ለቅቋል፡፡ በመሆኑም እዚህ ላይ ሊነሳ እና በአግባቡ ሊጤን የሚገባው ነጥብ ዓቃቤ ሕግ ክሱን ለማስረዳት ከዚህ የተለየ ምን አይነት ማስረጃ እንዲያቀርብ ይጠበቅበታል? የሚለው ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተመለከተው ዓቃቤ ሕግ ክሱን የመሠረተው በወ/መ/ሕግ ቁ. 590 የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ የወንጀል ድርጊት ተፈጽሞአል በማለት



ነው፡፡ ይህ ድንጋጌም ስንመለከተው "በንጽሕና ክብር ላይ ስለሚደረግ የኃይል ተግባር" የሚል ርእስ የተሰጠው ሲሆን፣ ይዘቱም በኃይል ወይም በብርቱ ማስፈራራት ወይም በማናቸውም አመጣጥ ለመቃወም ከማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ከጣለው በኋላ ግብረ ስጋን በመሰለ ወይም ለንጽሕና ክብር ተቃራኒ በሆነ በማናቸውም ሥራ ጾታው ልዩ የሆነውን ሰው ለመገናኘት የሚያስገድድ ሰው ሕግን እንደተላለፈ ተቆጥሮ የሚቀጣ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ እንግዲህ ዓቃቤ ሕግ እንደ ክሱ አስረድቶአል ወይስ አላስረዳም? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ያሰማውን ማስረጃ ከሕጉ ይዘት ጋር ማገናዘብ ይገባል፡፡

በበኩላችን እንደምናየው ዓቃቤ ሕግ ያቀረባቸው የሰው እና የጽሑፍ ማስረጃዎች በዝርዝር ይዘታቸውም ሆነ በጊዜ እና ሰዓት አጠቃቀስ ረገድ እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ ናቸው፡፡ ሲጠቃለሉም በጊዜው ተፈጸመ የተባለው ድርጊት በሚገባ መፈጸሙን የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ አንድ ክስን የሚሰማ ፍ/ቤት በክሱ አከራካሪ የሆኑትን ነገሮች እውነት መሆን አለመሆን ወይም ሕያው መሆን አለመሆን ማረጋገጥ የሚችለው በሚቀርብለት ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ስለመሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ በእርግጥም የማስረጃውን ይዘት በመመርመር ክብደቱንና ቅለቱን የመመዘን ስልጣንም የፍ/ቤቱ ነው፡፡ ይሁንና ማስረጃውን በግልጽ ከመዘገቡ እና ይዘቱንም ምን እንደሚመስል እያየ ግን ማስረጃ እንዳልቀረበ አድርጎ ማለፍ ይችል ዘንድ ሕግ አይፈቅድለትም፡፡ የአንድ አከራካሪ ነገር አውነት ወይም ሕያው መሆንና አለመሆን የሚረጋገጠው በማስረጃ ነው የሚለውን መርህም መጣስ አይችልም፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ዓቃቤ ሕግ ያሰማው ማስረጃ በሕጉ የተነገረው ወንጀል ስለመፈፀሙ በግልጽ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ግን ይህን የመሰለውን ማስረጃ እንዳላዩ አድርገው አልፈውታል፡፡ በእኛ ግንዛቤ እና እምነት ይህ አይነቱ አካሄድ ሕግን በግልጽ የጣሰ ብቻ ሳይሆን፣ ፍትሕንም በእጅጉ የሚጎዳ ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ

የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/በምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 806 ሰኔ 22 ቀን 97 ዓ.ም. ተሰጥቶ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት እና የሰበር ችሎት በመ/ቁ. 32806 ግንቦት 16 ቀን 98 ዓ.ም. እና በሰበር መ/ቁ. 43754 ሚያዝያ 15 ቀን 99 ዓ.ም. በሰጡአቸው ትዕዛዞች የፀናው ብይን በወ/መ/ሕግ ሥ/ሥ/ቁ. 195 መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. ተጠሪ ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው ማስረጃ የተከሰሰበት ወንጀል ስለመፈጸሙ የተመሰከረበት ስለሆነ ሊከላከል ይገባል ብለናል፡፡ በመሆኑም ክሱን የሰማው የከፍተኛ ፍ/ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ በዚህ ሰበር ችሎት ውሣኔ መሠረት ክርክሩን ሰምቶ ይወስን ብለን ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 31734

ጥቅምት 15 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

ወ/ት ሒሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አቶ ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** አቶ አስናቀ በቀለ - ወኪል አንቀጸ ጌታቸው

**ተጠሪ፡-** ዓቃቤ ሕግ - ፍቅሬ ከተማ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብ/ክ/መንግሥት በሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተከሰሰበት ወንጀል ዋስትና በመከልከሉና ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተውም በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙ ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች በወኪሉ አማካይነት ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ በልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 13/2/፣ አንቀጽ 14/2/ እና አንቀጽ 17/2/ የተመለከቱትን በመጥቀስ ሶስት የወንጀል ክሶችን በሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን አመልካችም በዚሁ ፍ/ቤት ቀርቦ የዋስትና መብት እንዲፈቀድለት ጠይቆ ዓቃቤ ሕግ አመልካች የብዙ ሀገር ፓስፖርትና ቪዛ በእጁ ስለሚገኝ የዋስትና መብት ቢፈቀድለት ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ ይችላል ተብሎ ስለማይገመት ፍ/ቤቱ የዋስትና ጥያቄውን ሊቀበለው አይገባም የሚል ክርክር በማቅረቡ ፍ/ቤቱም ይህንኑ የዓቃቤ ሕግን ተቃውሞ ተቀብሎ ተከሳሹ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ

ሊቀርብ ይችላል ተብሎ ስለማይገመት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67/ሀ/ መሠረት ያቀረበው የዋስትና ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ብይን ሠጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተከሣሹን ይግባኝ ባለመቀበል የከፍተኛውን ፍ/ቤት ብይን አጽንቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ አመልካች የዋስትና መብት የተከለከለበት ሁኔታ አግባብነት ከሕጉ አኳያ ሊጣራ እንደሚገባ በማመኑ ተጠሪን /ዐቃቤ ሕግን/ በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ አመልካች ዋስትና የመከልከሉ አግባብነትም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በመርህ ደረጃ የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት እንዳላቸው በሕገ መንግሥታችን አንቀጽ 19/6/ ላይ የተመለከተ ሲሆን በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ደግሞ ፍ/ቤቱ ዋስትና ለመከልከል እንደሚችል በዚሁ የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ላይ ተጠቅሷል፡፡ ይህም የአጠቃላይ መርሁ ልዩ ሁኔታ /Exception to the General Rule/ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች የዋስትና መብት የተከለከለው የተከሰሰበት ወንጀል የዋስትና መብት የሚከለክል ነው በሚል ሳይሆን ከላይ እንደተመለከተው በዋስ ቢለቀቅ ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም በሚል ነው፡፡ ተከሣሹ የዋስትና ግዴታውን ሊፈጽም አይችልም ተብሎ ሲገመትም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 167/ሀ/ መሠረት ዋስትና መከልከል ይቻላል፡፡

በሌላ በኩልም በዚህ የሥነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌ መሠረት ዋስትና ለመከልከል ግምት ብቻ በቂ ቢሆንም ነገር ግን ለግምቱ በቂ መንደርደሪያ ምክንያት ሊኖር እንደሚገባ ይታመናል፡፡ አለበለዚያ "ግምት" ከሚለው ቃል አጠቃላይነትና ስፋት አኳያ በሰፊው ከተተረጎመ ሕግ አውጭው የዋስ መብት ሊከለክላቸው ያልፈለገውን ተከሣሾችም የዋስ መብት እንዲከለከሉ መንገድ የሚከፍትና ሕጉም የታቀደለትን ዓላማና ግብ እንዳይመታ በትርጉም እንዲዘጋ ስለሚያደርግ በጠባቡ መተርጎም ይኖርበታል፡፡



አመልካች የዋስትና ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም የሚለውን ግምት የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ለመውሰድ የቻሉት አመልካቹ የበርካታ አገር ፓስፖርትና ቪዛ ያለው ስለመሆኑ የተረጋገጠ ስለሆነ ከተከሰሰበት የወንጀል ክብደት አኳያ ከአገር ሊወጣ ይችላል በሚል ነው፡፡

ይሁንና አመልካች ከአንድ በላይ ፓስፖርት አለው መባሉ በእራሱ አከራካሪ ከመሆኑም በላይ የበርካታ አገሮች መግቢያ ቪዛ አለው ቢባል እንኳን ይህ ሁኔታ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም የሚለውን ግምት ለመውሰድ በቂ መንደርደሪያ ምክንያት ሊሆን የማይችልና ድንጋጌው ከሕጉ ዓላማ ጋር ተጣጥሞ ያልተተረጎመ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በሌላ በኩልም የአመልካች ፓስፖርትና የበርካታ አገሮች መግቢያ ቪዛ ይዞ መገኘት ግምቱን ለመውሰድ በቂ ምክንያት ነው ቢባልም ከአገር የማይወጣበትን ሁኔታ በመፍጠር የዋስትና ግዴታውን አክብሮ እንዲቀርብ የሚያደርግ ትዕዛዝ መስጠት እየተቻለ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ዋስትናውን መከልከሉና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ አለማረሙ በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡

**<u>ት ዕ ዛ ዝ</u>**

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 09054 በ11/10/99 ዓ.ም. እንደዚሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 18698 በ26/10/99 ዓ.ም. አመልካችን ዋስትና በመከልከል የሰጡት ብይንና ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በተከሰሰበት ወንጀል የብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ/ ዋስ እንዲጠራ ወይንም ገንዘቡን አስይዞ በዋስ ሆኖ እንዲከራከር በማለት ወስነናል፡፡

3. የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ለአመልካች ዋስትና በተፈቀደለት መሠረት በእጁ የሚገኘውን ፓስፖርት በፍ/ቤቱ እንዲቀይ በማድረግ በዚሁ ልክ ዋስትና አስጠርቶ ወይንም ገንዘቡን እንዲያሲዝ አድርጎ በዋስ ሆኖ እንዲከራከር እንዲያደርግ ታዟል። ይፃፍ።
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል።

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 34077

መጋቢት 9 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ሐጎስ ወልዱ
4. ወ/ት ሒሩት መለሠ
5. አቶ ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ ሰይድ ይመር - ጠበቃ ማስረሻ በላይ

ተጠሪ፡- የአማራ ክልል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን አልቀረበም።

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ በጊዜው ሥራ ላይ በነበረውና በአዋጅ ቁጥር 214/74 ተሻሽሎ በወጣው የልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በቁጥር 23/1/ /ሀ/ እና /ለ/ ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመጥቀስ 3 /ሦስት/ የወንጀል ክሶችን አቅርቧል።

የተጠሪ ክስ ለአመልካች ደርሶም ባቀረበው የመቃወሚያ ክርክር ተከሣሽ የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጊት ፈጽመ ከተባለ በኋላ አዲስ የወንጀል ሕግ የወጣ እንደመሆኑ መጠን ይህም አዲስ የወንጀል ሕግ ተከሣሽን የሚጠቅም ስለሆነ መከሰስ የሚገባኝ በአዲሱ የወንጀል ሕግ እንጂ በቀድሞው ሊሆን ስለማይችል ክሱ ተሻሽሎ ሊቀርብ ይገባል በማለት ተከራክሯል።

ተጠሪም በበኩሉ ከአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 5/1/ አኳያ ክርክሩ መቀጠል የሚገባው በተሻረው ሕግ መሠረት ስለሆነ ክሱ ሊሻሻል ስለማይገባ መቃወሚያው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል።

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ተከሣሽ ድርጊቱን ፈጸመ በተባለበት ጊዜ የነበረው ሕግ

ተሽሮ አዲስ የወንጀል ሕግ የወጣ ሲሆን በተሻረው ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የሙስና ወንጀል ተብሎ የተቀመጠው ድርጊት ተሽሮ በአዲሱ የወንጀል ሕግ የሙስና ወንጀል ተብሎ ከአንቀጽ 407 ጀምሮ የተደነገገ ከመሆኑም በላይ በአዲሱ የወንጀል ሕግ ላይ የተደነገገው ቅጣት ከተሻረው ሕግ ቅጣት ያነሰና ተከሳሽን የሚጠቅም እንደሆነ በብይኑ ላይ አስፍሮ አዲሱ የወንጀል ሕግ ተከሳሽን የሚጠቅም እስከሆነ ድረስ ወደ ኋላ ተመልሶ ሊሰራ ስለሚችል ከሳሽ በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 407/1/ ላይ የተመለከተውን በመጥቀስ ክሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ ይህ ድንጋጌም የዋስትና መብት ስለማይከለክል ተከሣሽ የብር 5000 /አምስት ሺህ/ ዋስትና ሲያሟላ በዋስ ሆኖ ክርክሩን እንዲቀጥል በማለት ብይን ሠጥቷል፡፡

የሥር ከሣሽ የአሁን ተጠሪ በዚሁ ብይን ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ጠቅላይ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የወንጀል ሕግ ተከሳሹን የሚጠቅም ከሆነ ወደ ኋላ ተመልሶ የሚሰራ መሆኑ አከራካሪ ባይሆንም ነገር ግን ተፈፃሚነት የሚኖረው በጥፋተኛነትና በቅጣት ጊዜ ስለመሆኑ በአዲሱ የወንጀል ሕግ በቁጥር 6 ላይ የተመለከተ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት የክርክሩ ሂደት ሳይጠናቀቅ ክሱ እንዲሻሻል በማዘዝ ዋስትና መፍቀዱ በአግባቡ አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤትን ብይን በመሻር መ/ሰጭው /የአሁን አመልካች/ ጉዳዩን በማረሚያ ቤት ሆኖ ሊቀጥል ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ለወንጀል ሕግ ቁጥር 6 የሰጠው ትርጉም ተጠሪ ባለበት ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች የዋስትና መብት ሊፈቀድለት ይገባል? ወይንስ አይገባም? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ በመያዝ አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡



አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነውን ወንጀል ፈጽሟል የተባለው አዲሱ የወንጀል ሕግ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

ወንጀሉ የተፈጸመው አዲሱ የወንጀል ሕግ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ከሆነ ተከሣሹ መከሰስ የሚገባው በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 5 መሠረት በአዲሱ ሕግ ሳይሆን ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ ሥራ ላይ በነበረው ሕግ መሠረት ነው፡፡

በሌላ በኩልም ተከሣሽ የሚከሰሰው በቀድሞው ሕግ መሠረት ቢሆንም የቀድሞው የልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በአዲሱ የወንጀል ሕግ ተሽሮ የሙስና ወንጀሎችንም በተመለከተ በአዲሱ የወንጀል ሕግ በቁጥር 407 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ሥር ተደንግጎ ይገኛል፡፡

በተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 437/97 መሠረትም በተከሣሹ ላይ ሊወሰን የሚችለው ቅጣት ከ10 ዓመት በታች ከሆነ የዋስትና መብት ሊፈቀድለት እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

አመልካች የወንጀሉን ድርጊት ፈጽሟል በተባለ ጊዜ የነበረው ሕግ የተሻረ ቢሆንም መከሰስ የሚገባው ድርጊቱ በተፈጸመ ጊዜ ሥራ ላይ በነበረውና አመልካችም በሚያውቀው ሕግ መሠረት መሆን እንደሚገባው ከሕግ መርህ /Rule of legality/ አኳያ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመርህ ደረጃ የተሻረ ሕግ ተፈፃሚነት ባይኖረውም ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለ ጊዜ ተከሣሹ የሚያውቀው ይህንኑ የተሻረ ሕግ ስለሆነ ክስ መቅረብም የሚገባው ይሄው የተሻረ ሕግ ተጠቅሶ ነው፡፡ ይህም የአጠቃላይ መርሁ ልዩ ሁኔታ /exception to the general rule/ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በአዲሱ የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 5 ላይም የተንጸባረቀው ይህንኑ መሠረት አድርጎ ነው፡፡

አመልካች መከሰስ የሚገባው በቀድሞው ሕግ መሠረት ከሆነ ጥፋተኛም የሚሆነው በዚሁ የቀድሞ ሕግ መሠረት መሆኑ የማይቀር ነው፡፡

በሌላ በኩልም የወንጀል ሕግ በመርህ ደረጃ ወደ ኋላ ተመልሶ እንደማይሰራ ነገር ግን ተከሣሽን የሚጠቅም እስከሆነ ድረስ ወደ ኋላ ተመልሶ ሊሰራ እንደሚችል በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 6 ላይ እና በሕገመንግስታችን አንቀጽ 22 ላይ ተመልክቷል፡፡

የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወንጀል ሕግ ቁጥር 6 ላይ የተመለከተውና የወንጀል ሕግ ተከሣሹን የሚጠቅም በሆነ ጊዜ ወደ ኋላ ተመልሶ ይሰራል ተብሎ የተደነገገው ተፈፃሚነቱ በቅጣት ጊዜ እንጂ ክርክሩ በተጀመረበት ደረጃ ተፈፃሚነት ስለማይኖረው የዋስትናው ጉዳይ መታየት ያለበት ከተከሰሰበት ድንጋጌ አኳያ በመሆኑ የተከሰሰበትም ድንጋጌ የዋስትና መብት ስለማይፈቅድ አመልካቹ በእሥር ሆኖ ሊከራከር ይገባል ብሏል፡፡

በመርህ ደረጃ የተሻረ ሕግ ተፈፃሚነት የሌለው ሲሆን በተሻረ ሕግ ክስ ማቅረብ ደግሞ የመርሁ ልዩ ሁኔታ ነው፡፡ የተሻረውም ሕግ ተጠቅሶ በተከሳሹ ላይ ክስ የሚቀርበው ወንጀሉ ተሰርቷል በተባለ ጊዜ ሕጉ ሥራ ላይ ስለነበርና ተከሣሹም ያውቀዋል ተብሎ ስለሚገመትና በሚያውቀው ሕግ መሠረት መከራከር እንዳለበት የሕግ መርህ /Rule of legality/ ስለማያስገድድ ነው፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው የተሻረው ሕግ የሚጠቀሰው ተከሳሹ ክርክሩን በአግባቡ ለመምራት እንዲያስችለው እንጂ ከዚህ ያለፈ ውጤት የሌለውና መጨረሻም ላይ ቅጣት የሚወሰነው ሥራ ላይ ባለ ሕግ ላይ ተመስርቶ መሆኑን ነው፡፡

ከዚህም ሌላ የዋስትና ጉዳይ በዋናነት የሚታየው ቅጣትን መሠረት አድርጎ ነው፡፡ አመልካች የተከሰሰው የዋስትና መብት በሚከለክል ድንጋጌ ቢሆንም ድንጋጌው የሚጠቀሰው ክርክሩን በአግባቡ ለመምራት ታስቦ እንደሆነ ሕጉ ይዞት የተነሳውን ዓላማ መገንዘብ ከተቻለ የዋስትናው ጉዳይ መታየት የሚገባው ሊወሰንበት ከሚችለው ቅጣት አኳያ መሆን እንዳለበት ይታመናል፡፡



ክርክሩ እልባት ካገኘ በኋላ አመልካች የሚቀጣው በአዲሱ ሕግ መሠረት እንደሆነ ከወዲሁ በግልጽ መገንዘብ እየተቻለ ክርክሩ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በእሥር ይቆይ ማለት ሕግ አውጭው የዋስትና መብት ሊከለክላቸው ያልፈለገውን ተከሣሾች የዋስትና መብት እንደመከልከል የሚቆጠርና ሕጉም የታለመለትን ዓላማና ግብ እንዳይመታ የሚያደርግ ነው፡፡

ስለሆነም በመልካች ላይ ቅጣት ሊወሰንበት የሚችለው በአዲሱ የወንጀል ሕግ በቁጥር 407/1/ ሥር ስለሚሆንና በተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ - ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 437/97 መሠረት ከ10 ዓመት በታች በሚያስቀጡ የሙስና ወንጀሎች የዋስትና መብት የተፈቀደ ስለሆነ አመልካችም ሊቀጣ የሚችለው ከ10 ዓመት በታች ስለሆነ የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱ እንዲሻሻል ትዕዛዝ መስጠቱ አግባብነት ባይኖረውም የዋስትና መብት መፍቀዱ ግን ተገቢነት ያለው ሆኖ ሳለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የዞኑን ከፍተኛ ፍ/ቤት ብይን በመሻር ለአመልካች የዋስትና መብት ሊፈቀድለት አይገባም በማለት የሰጠው ፍርድ ከላይ ከተመለከተው አኳያ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 285/99 ጥቅምት 4 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 195/2/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 14168 በ9/6/99 ዓ.ም. ለአመልካች የዋስትና መብት በመፍቀድ የሰጠው ብይን በአግባቡ ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡ ስለሆነም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ለአመልካች ዋስትና በፈቀደው መሠረት ዋስትናውን እንዲያሟላ በማድረግ አመልካች በዋስ እንዲከራከር ታዟል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 34280

ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን እቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አቶ ግርማይ ደስታ - ጠበቃ ረዳኢ ባራኪ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ዓቃቤ ሕግ - ሚሊዮን ተዘራ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 19769 ሐምሌ 17 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 33217 ጥቅምት 27 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች በመጠየቁ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሟል በማለት ዓቃቤ ሕግ ክስ አቅርቦበት፣ ፍርድ ቤቱን የግራ ቀኙን ክስና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አመልካች የአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 22ን እና ሌሎች ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው ብሎ፣ አመልካች በአምስት ዓመት እስራት እንዲቀጣ ከወሰነ በኋላ፣ ቅጣቱን በሶስት ዓመት ገድቧል፡፡ ዓቃቤ ሕግ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች በሌለበት ይግባኙን ከሰማ በኋላ፣ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ቅጣቱን መገደቡ ሌሎችን ሊያስተምር የሚችል አይደለም በማለት ከፍተኛው ፍርድ ቤት



የሰጠውን የሶስት ዓመት የገደብ ውሣኔ በመሻር አመልካች አምስት ዓመት እስራቱን እንዲፈጽሙ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው፣ ችሎቱ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ የሚያስለውጥ ምክንያት የለም በማለት አጽንቶታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው፣ ይህ ውሣኔ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ነው፡፡ አመልካች በጠበቃቸው በኩል ባቀረቡት ማመልከቻ በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኛነት ውሣኔ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁን በአግባቡ ሳይገነዘቡና ሣይተረጉሙ በመሆኑ መሠረታዊ ስህተት አለበት በማለት ዝርዝር ማመልከቻ ያቀረቡ ሲሆን፣ በዓቃቤ ሕግም በኩል በሰበር ደረጃ ጥፋተኛነቱን ለማስለወጥ ያቀረቡት አቤቱታ ተገቢ አለመሆኑንና የቅጣት ገደቡ መነሣቱ ተገቢ መሆኑን በመጥቀስ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ስለሆነ በሰበር የሚታረም አይደለም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካች ከቅጣት ውሣኔ አሰጣጥና ቅጣትን ስለመገደብ ከተቀመጡት የወንጀል ሕግ መርሆች አንፃር ሲታይ ቅጣትን ለማስተማሪያነት ሣይሆን በመበቀያነቱ ለመጠቀም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባዋል በማለት የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው የሕግ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው፡-

- በሰበር ደረጃ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት የጥፋተኛነት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም?
- በሥር ፍርድ ቤቶች ቅጣቱን ለመገደብና ቅጣቱን ተፈፃሚ መሆን አለበት በማለት የተለያየ ውሣኔ የሰጡበት የቅጣት ውሣኔን

ስለመገደብ የተደነገጉ ድንጋጌዎች በምን አይነት ሁኔታ መተርጎምና ሥራ ላይ መዋል አለባቸው የሚሉትን ነጥቦች መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች ከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ ቅር በመሰኘት በመጀመሪያ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ የነበረባቸው ሲሆን ይህንን ማድረጋቸውን የፍርድ ቤቱ መዝገብ አያሣይም፡፡ በዚህ መዝገብ አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበውን ይግባኝ ሰምቶ በቅጣት ውሣኔው ላይ የተሰጠውን የሶስት ዓመት ገደብ በመሻሩ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በጥፋተኛነት ውሣኔው ላይ፣ የነበራቸውን ቅሬታ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ይግባኝ ወይም መስቀለኛ ይግባኝ በማቅረብ እስከ ሰበር ድረስ በማምጣት መከራከር ነበረባቸው፡፡ አመልካች ይህንን ሥርዓት ተከትለው፣ በጥፋተኝነት ውሳኔው ላይ ተፈጽሟል የሚሉትን የህግ ስህተት ባላቀረቡበት ሁኔታ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔውን መገደቡ ተገቢ አይደለም ብሎ ዐቃቤ ሕግ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረበው የይግባኝ ቅሬታ መነሻነት የተሰጠውን ውሳኔ መሠረት አድርገው የከፍተኛ ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም በማለት የሰበር መከራከሪያ ነጥብ ማድረጋቸው የህግ ድጋፍ የሌለውና ሥርዓቱን ጠብቆ ያልቀረበ በመሆኑ፣ አልተቀበልነውም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ፣ ፍርድ ቤት በአንድ ሰው ላይ የቅጣት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ የቅጣት ውሳኔውን ለመገደብ እንደሚችልና የቅጣት ውሳኔው ሊገደብላቸው የሚገባው ምን መሰረታዊ ሁኔታዎች ሲሟሉ እንደሆነ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 192 ላይ መሰረታዊ መርሁ ተቀምጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቅጣት የወሰነው ፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔውን ከመገደብ በህግ የሚከለከልበት ሁኔታ እንዳለና ይኸም የህግ ክልከላ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 194 የተደነገገ መሆኑን ለመረዳት እንችላለን፡፡ ከዚህ አንፃር



ስንመዝነው የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን የአምስት ዓመት እስራት ቅጣት በሶስት ዓመት መገደቡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን የማይጥስና በሕጉ የቅጣት ውሣኔ እንዳይገደብ የተደነገገውን ክልከላ ተላልፎ፣ የሰጠው አይደለም፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት የቅጣት ውሣኔውን ሲገድብ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 የተደነገገውን የሕግ ክልከላ አልተላለፈም ካልን በሁለተኛ ደረጃ የሚነሣው ጥያቄ አመልካች ቅጣቱ የተገደበለት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 192 የተቀመጡትን መሠረታዊ ሁኔታዎች የሚያሟላ ሆኖ በመገኘቱ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅጣቱን የገደበው አመልካቹ ከዚህ በፊት በወንጀል ያልተቀጣ በመሆኑና ቅጣቱን ተፈፃሚ ከማድረግ ይልቅ ቅጣቱን መገደቡ የተሻለ ውጤት ይኖረዋል በማለት ነው፡፡ በእርግጥ የሥር ፍርድ ቤቶች በዚህ መንገድ አይተው ባሣለፉት ቅጣትን የመገደብ ውሣኔ የይግባኝ ቅሬታ ሊቀርብበት የሚችልና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ውሳኔውን ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 192 መርህ አንፃር በመመዘን ሊሽረው፣ ሊያሻሽለው ወይም ሊያፀናው የሚችል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ካየነው የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአምስት ዓመቱ እስራት ቅጣት በሶስት ዓመት እንዲገደብ የሰጠውን ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መመርመሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም፡፡ ሆኖም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የቅጣት ውሣኔው በሶስት ዓመት ተገድቦ እንዲቆይ የሰጠውን ትዕዛዝ የሻረው፣ አመልካቹ የቅጣት ገደብ ተጠቃሚ የሚያደርጋቸውንና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 192 የተቀመጠውን መሠረታዊ መርህ የሚያሟላ አይደለም በማለት ሣይሆን በአመልካቹ ላይ የተወሰነው ቅጣት መገደቡ ሌሎች ተመሣሣይ ወንጀል የመሠራት ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች ለማስፈራራትና አመልካችን በመቀጣጫነት በማሣየት ትምህርት ለመስጠት የማያስችል ነው በሚል ምክንያት እንደሆነ በውሣኔው ተልጿል፡፡ አመልካቹ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 192 የተቀመጠውን መርህ የሚያሟላበት

ሁኔታ ጠቅላላውን የወንጀል ሕጉን መሠረታዊ ግብ መነሻ በማድረግ ቅጣቱ መገደብ የለበትም ከሚለው መደምደሚያ ላይ መድረሱ የወንጀል ቅጣት አወሳሰንና አፈፃፀም የወንጀል ሰሪውን ልዩና ግላዊ ሁኔታዎች ያገናዘቡ መሆን አለበባቸው በማለት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 41 የተቀመጠውን መሠረታዊ መርህ የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለሆነም ቅጣትን መገደብን የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ግምት ውስጥ በማስገባትና በሕግ የተደረገውን ክልከላ ሣይተላለፍ፣ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ቅጣቱን በመገደብ የሰጠውን ትዕዛዝ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በመሻር የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ስለሆነም ይህ ውሣኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ አመልካች ያልፈፀመው ቀሪው፣ የእስራት ቅጣት በሶስት ዓመት ሊገደብለት ይገባል በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

1. አመልካች ያልፈፀመው ቀሪው የእስራት ጊዜ በሶስት ዓመት የሙከራ ጊዜ የተገደበለት መሆኑን አውቆ፣ ከእስር እንዲለቀቀው አመልካች እስሩን እየፈፀመበት ላለው ማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣቱን አፈፃፀም አስመልክቶ፣ የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአዳሪ ሲሰራ ቆይቶ ግንቦት 21 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 34521

ሰኔ 3 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

መስፍን እቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

**አመልካች፡-** የአማራ ብ/ክ/መ/ ፍትሕ ቢሮ

**ተጠሪ፡-** ስንታየሁ ተፈራ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ተጠሪ በሰው ላይ የመግደል ሙከራ ወንጀል ፈጽሞአል በሚል የቀረበውን ክስ መሠረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክሱን የሰማው የሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ በቅድሚያ የተጠሪን የእምነት ክህደት ቃል ከተቀበለ በኂላ ተጠሪ ወንጀሉን አልፈጸምኩም በማለቱ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረቡትን ምስክሮች ሰምቶአል፡፡ በመቀጠልም ተጠሪ እንዲከላከል ብይን በመስጠት የመከላከያ ምስክሮችን የሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ተጠሪ ወንጀሉን ላለመፈጸሙ በመከላከያው አስረድቶአል በማለት በነፃ አሰናብቶታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ዓቃቤ ሕጉ ውሣኔውን በመቃወም ለአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ ከዚህ በኂላም ፍ/ቤቱ በከፍተኛው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሣኔ በመሻር ተጠሪ በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ነው ብሎአል፡፡ ለጥፋቱ ይመጥናል ብሎ ባመነው መሠረትም ተጠሪ በስድስት /6/ ወር እስራት እንዲቀጣ ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ታህሣሥ 10 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በወ/መ/ሕግ ቁ. 27/1/ እና 523 የተመለከተለውን ድንጋጌ በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሞአል በሚል ጥፋተኛ የተባለውን ተጠሪ በስድስት /6/ ወር እስራት እንዲቀጣ የተወሰነበትን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው ተጠሪ በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ተብሎአል፡፡ ጥፋተኛ የተባለበት የወ/መ/ሕግ ቁ. 523ም የሚያስቀጣው ከአምስት /5/ ዓመት በማያንስ ከሃያ /20/ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ነው፡፡ በእርግጥ ጥፋተኛ በተባለ ተከሣሽ ላይ ቅጣት ሲወሰን /ሕጉን መሠረት ያደረጉ/ የተለያዩ የማክበጃም ሆነ የማቅለያ ምክንያቶችን እግምት ውስጥ በማግባት በመሆኑ እንደ ሁኔታው ቅጣቱ ሊቀልም ሊከብድም የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው የቅጣቱ መነሻ በሕጉ በግልጽ ተቀምጦአል፡፡ የጠ/ፍ/ቤቱ የወሰነው ቅጣት ግን ከመነሻው ወርዶ /ዝቅ ብሎ/ ስድስት ወር ሆኖአል፡፡ አከራካሪ ሆኖ የቀረበውም ፍ/ቤቱ ይህን ያሕል ዝቅ ብሎ ለመውረድ የሚያስችለው የሕግ ምክንያት ነበረው ወይ? የሚለው ነው፡፡

ፍ/ቤቱ ቅጣቱን ለማቅለል ይችል ዘንድ በዋቢነት የጠቀሰው የወ/መ/ሕግ ቁ. 184/መ/ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ ቁጥር 184 ቅጣትን ለማቅለል የሚቻልባቸውን ሁኔታዎች በዝርዝር የያዘ ሲሆን፣ ይህም ከፍተኛው ቅጣት ማለትም ከሞት ቅጣት ነው የሚጀምረው፡፡ የሞት ፍርድን ከሃያ /20/ ዓመት እስከ እድሜ ልክ ጽኑ እስራት፣ የእድሜ ልክ እስራትን ከአስር /10/ ዓመት እስከ ሃያ /20/ በሆነ ጽኑ እስራት ማቃለል እንደሚቻል በንኡስ አንቀጽ /ሀ/ እና /ለ/ የተመለከተ ሲሆን፣ የእስራቱ ቅጣት መነሻ ከፍ ብሎ በተለይ የታዘዘ ከሆነ ደግሞ ቅጣቱን ዝቅ ማድረግ የሚቻለው ከአንድ /1/ ዓመት ጀምሮ እንደሆነ በንኡስ አንቀጽ /ሐ/ ተመልክቶአል፡፡ በወ/መ/ሕግ ቁ. 107 እንደተደነገገው ጽኑ እስራት የሚቆይበት ጊዜ ከአንድ ዓመት እስከ 25 /ሃያ አምስት/ ዓመት ቢሆንም፤ በሕጉ ልዩ ክፍል የቅጣቱ መነሻ ከአንድ ዓመት በላይ ከፍ ብሎ ከተወሰነ ግን በሕጉ አግባብ ያላቸው የማቅለያ ምክንያቶች ካልተገኙ በቀር እንደመነሻ የሚያዘው ይኸው በልዩ ክፍል የተመለከተው ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይም ቅጣቱ መወሰን ያለበት በዚህ መሠረት ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የጠ/ፍ/ቤቱ እግምት ውስጥ ያስገባቸው የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች እንደተጠበቁ ሆነው በተጠሪ ላይ ሊወሰን የሚችለው ቅጣት ከአንድ /1/ ዓመት በታች ሊወርድ የሚችልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የጠ/ፍ/ቤቱ ውሣኔ በሰጠበት ጊዜ ሥራ ላይ በነበረው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 179/ሐ/ እንደተመለከተውም የጽኑ እስራቱ ቅጣት መነሻ ከፍ ብሎ በሕጉ ልዩ ክፍል ተደንግጎ ሲገኝ በዚህ ቅጣት ምትክ በሕጉ ጠቅላላ ክፍል መነሻ ሆኖ ከተደነገገው ከአንድ ዓመት ጀምሮ የጽኑ እስራት ቅጣት ሊወሰን እንደሚቻል ነው፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 103/98 ኅዳር 4 ቀን 2000 ዓ.ም. የተሰጠው የቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሕግ ስ/ስ/ቁ. 195/2/መ/ መሠረት ተሻሎአል፡፡
2. ተጠሪ በአንድ /1/ ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስነናል፡፡ ይኸው ለሚመለከተው ማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 35611

ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ሻለቃ ታደሰ ካሕሳይ - አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 27428 ጥር 23 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት በማመልከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ አመልካች በሰው አካል ላይ ጉዳት አድርሷል በማለት የወንጀል ክስ አቅርቦበት፣ ፍርድ ቤቱ የአመልካችንና የዓቃቤ ሕግን ማስረጃ ከሰማ በኋላ አመልካች በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቶ፣ በዘጠኝ ወር እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይግባኙን ለመስማት ለጥር 23 ቀን 2000 ዓ.ም. የቀጠረ ሲሆን አመልካች በዕለቱ ሣይቀርብ ቀርቷል፡፡ አመልካች በቀጠሮው ቀን ያልቀረበው የአየር ኃይል መሥሪያ ቤት በግዳጅ ላይ በመሆኑ ምክንያት መሆኑን ገልፆ ትብብር እንዲያደረግለት የጠየቀ መሆኑን የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ካሰፈረ በኋላ፣ ይግባኝ ባይ ስላልቀረቡ ይግባኙ እንዲሰረዝ እና ይግባኝ ባይ በዋስትና ያስያዙት ገንዘብ ገቢ እንዲሆን ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ከአቅም በላይ በሆነ የሥራ ጉዳይ ያልቀረብኩ መሆኔ፣ ፍርድ ቤቱ ማስረጃ ቀርቦለትና ማስረጃውም ደርሶት እያለ፣ በቸልተኝነት ቀጠሮ እንዳሣለፍኩ በመቁጠር ይግባኙን መሰረዙ ተገቢ አይደለም ያለ ሲሆን ዓቃቤ ሕግ በበኩሉ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ጉዳዩን የወሰነው አመልካች ባለመቅረቡ ሣይሆን የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ትክክል ሆኖ ስላገኘው ነው የሚል መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀው ሲሆን፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን የሰረዘው አመልካች በቀጠሮ ቀን ባለመቅረቡ ምክንያት መሆኑን በሰጠው ትዕዛዝ በግልጽ ያሰፈረው በመሆኑ ዓቃቤ ሕግ ይግባኙ የተሰረዘው በአመልች አለመቅረብ ምክንያት ነው በማለት በሰበር ያቀረበው መከራከሪያ ተገቢ አይደለም፡፡ ወደ ዋናው ነገር ስንመለስ ይግባኙ የሚሰማበት ቀን ይግባኝ ባዩ ወይም ጠበቃው ካልቀረቡ ፍርድ ቤቱ ይግባኙን እንደሚሰርዘው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193/1/ የሚደነግገው፣ ይግባኝ ባይ ጉዳዩን በትጋት ካልተከታተለ እና በቸልተኝነት የተወው እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠውን ትዕዛዝ ግልጽ በማድረግ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች በሥራው ባሕሪ ምክንያት ወታደራዊ ግዳጅ ላይ እንደሆነ የኢትዮጵያ አየር ኃይል አሣውቋል፡፡ ይህ ከሆነ ፍርድ ቤቱ በሚቀጥለው ቀጠሮ አመልካች ራሱ ወይም ወኪል ጠበቃው እንዲቀርብ ለመጠባበቅ ቀጠሮ መስጠት እየቻለ ይህንን አሳማኝ ምክንያት ወደ ጎን በመተው ይግባኙን መሠረዙ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193/1/ን መሠረታዊ ግብና ዓላማ የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በቀጠሮው ቀን የቀረው በቂ በሆነ ምክንያት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ቀርቦለት እያለ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 79 ድንጋጌ ውጪ አመልካች በዋስትና

ያስያዘው ገንዘብ፣ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

1. የከፍተኛው ፍርድ ቤት፣ በመዝገብ ቁጥር 27428 ጥር 23 ቀን 2000 ዓ.ም. የአመልካች ይግባኝ እንዲሰረዝና የዋስትናው ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የከፍተኛው ፍ/ቤት የአመልካችንና የመልስ ሰጭን ክርክር መርምሮ የመሰለውን ውሣኔ እንዲሰጥ፣ ጉዳዩን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ ቁጥር 2 መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



# ግ ብ ር

የሰ/መ/ቁ. 18809

ሰኔ 12 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን እቁበዮናስ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ ሚሊዮን ዑመር - ጠበቃ አዳሙ ደነቀው - ቀርበዋል

ተጠሪ፡- የፌደራል የአገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን ነገረ ፈጅ ገ/እዛቤር ሙላቸውና ተፈራ ጥላው ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለውሳኔ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 15697 ህዳር 30 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች ተጠሪው ያለአግባብ ከግብር ህግ በተለይም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ካወጣው ደንብ ቁጥር 75/1993 ውጭ የትራንስፖርት መኪና ለመንገድ ስራ ድርጅት በማከራየቴ ብቻ የሰበሰውን ገንዘብ እንዲመልስ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረበው ክስ፣ ሲሆን ተጠሪው በበኩሉ ግብሩ የተሰበሰበው በደንብ ቁጥር 75/1993 አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 9 መሰረት ስለሆነ፣ገንዘቡ መመልስ የለበትም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአመልካች ገንዘብ እንዲመለስ የወሰነ ሲሆን፣ በዚህ ውሣኔ ተጠሪው ቅር በመሰኘት ይግባኝ አቅርቦ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሮታል፡፡



አመልካች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሳሳተ የሕግ ትርጓሜ ሰጥቷል፡፡ ያከራየነው መኪና እንጅ መሣሪያ ባለመሆኑ ደንብ ቁጥር 75/1993 በእኛ ላይ ተፈፃሚነት የለውም በማለት የተከራከረ ሲሆን ተጠሪው በበኩሉ፣ ግብሩ በአግባቡ ነው የተሰበሰበው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመረነው “ኮምፒውተርን ጨምሮ ከተለያዩ መሣሪያዎች ህንፃዎች እና ሌሎች እቃዎች ኪራይ” አምስት ፐርሰንት ግብር እንደሚከፈል፡፡ ደንብ ቁጥር 75/1993 አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 9 ይደነግጋል፡፡

አመልካች “መሣሪያዎች” የሚለው የትራንስፖርት መኪናን አይጨምርም የሚል ክርክር ያቀረበ ቢሆንም መኪኖቹ ለህዝብ ማመላለሻ እና ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠታቸው ቀሞ በኪራይ ለኮንስትራክሽን ድርጅቱ በመከራየታቸው በደንቡ የተመለከተውን ግብር ከመክፈል ነፃ የሚሆኑበት ሁኔታ የለም፡፡ የህግ አውጭው ሐሳብም የህዝብ ማመላለሻ መኪና ከመደበኛው ስምሪት ወጥቶ ከተከራየ ከኪራዩ ግብር ለማስከፈል እንደሆነ ከደንብ ቁጥር 75/1993 ድንጋጌዎችና ይህንን ደንብ ለማሻሻል ከወጣው ደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 2/ሸ/ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም አመልካች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለበት በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ፍሬ ያለው ሆኖ ስላላገኘው ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ውሣኔውን በማጽናት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ይፃፍ፡፡
3. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሰኔ 12 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



# የ ን ግ ድ
# ተ ቋ ማ ት

የሰበር መ/ቁ. 19258

ሐምሌ 12 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አቶ ታፈሰ ይርጋ

አቶ ብርሃኑ አመነው

አመልካቾች፡- 1. አቶ ተክሌ ዋቅጅራ
2. አቶ ጥላሁን ቦባስ
3. አቶ ሃቢብ መሐመድ

መልስ ሰጭ፡- አቶ ሾንጣ ጉቡ ቀረቡ

ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የተወሰነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበር አንድ አባል አገባለሁ ያለውን መዋጮ መቼና እንዴት ማግባት ያለበት መሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

አመልካቾችና መልስ ሰጭዎች ጠቅላላ ግምቱ ብር 800,000 /ስምንት መቶ ሺህ ብር/ ካፒታል ያለው ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መሥርተዋል፡፡ የእያንዳንዳቸው መዋጮ ብር 200,000.00 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ሲሆን የአሁን መልስ ሰጭ በዓይነትም ሆነ በገንዘብ አገባለሁ ካለው መዋጮ ውስጥ ብር 74,838.80 /ሰባ አራት ሺ ስምንት መቶ ሰላሣ ስምንት ብር/ ሣያስገባ ማህበሩ ሥራውን ሲያንቀሣቅስ ከቆየ በኋላ ሌሎች አባላት ይህንኑ ሊያስገባ የተስማማውን መዋጮ በገንዘብ ገቢ እንዲያደርግ ሲጠይቁት መልስ ሰጭ ይህንኑ መዋጮ ማህበሩ ከሚያስገኘው ትርፍ ገቢ በድርሻዬ ከማገኘው እከፍላለሁ እንጂ እንደ ጥያቄያችሁ ክፍያውን ለመፈፀም ግዴታ አልገባሁም በማለቱ ምክንያት ይህ ክርክር ሊከሰት ችሏል፡፡

ይህንኑ ክርክር ያስነሣውን መዋጮ ገቢ ያደርግ ዘንድ አመልካቾች በጌዲኦ ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት ክስ መሥርተው መልስ ሰጭም ከላይ የተጠቀሰውን መከራከሪያ በማቅረቡ ይኸው ፍ/ቤት ጉዩን ተመልክቶ የአሁን መልስ ሰጭ ቀሪ አክሲዮን ድርሻውን /መዋጮውን/ በዚህ ጊዜ አስገባለሁ ብሎ ግዴታ አልገባም ማስጠንቀቂያ የደረሰው መሆኑም አልተረጋገጠም፣ ስለሆነም የሚከፍልበት ምክንያት የለም በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ የአሁን አመልካቾች ቅር ተሰኝተው የይግባኝ አቤቱታቸውን ለደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በማቅረባቸው ግራ ቀኙ በጉዳዩ ላይ ክርክር አድርገዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም የአሁን መልስ ሰጭ አስገባለሁ ካለው መዋጮ ብር 74,838.80 /ሰባ አራት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሣ ስምንት ብር/ ኣላስገባም (አልከፈለም) ሆኖም ይህንኑ ቀሪ ክፍያ ለመፈፀም ውል አድርጓል፡፡ ይህ ውልም ፈራሽ ነው አልተባለም ስለዚህ መልስ ሰጭ ገንዘቡን ሊከፍል ይገባል በማለት ዳኝነት ሰጥቶ ግራ ቀኙን አሰናብቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ ባለመስማማት እና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል የአሁን መልስ ሰጭ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቦ በሰበር ግራ ቀኙ ተከራክረዋል፡፡ ሰበር ሰሚው ችሎት ጉዳዩን መርምሮ እንደሚከተለው ወስኗል፡፡

በንግድ ሕግ ቁጥር 338/1/ አክሲዮኖች በሚገዙበት ጊዜ እጅግ ቢያንስ ከተፃፈባቸው ዋጋ አንድ ሩብ ሊከፈል እንደሚገባ ወይም በሙሉ እንደሚከፈል ተደንግጓል፡፡ ዋጋቸው በሙሉ እስኪከፈል ድረስም አክስዮኖቹ በማህበሩ ስም የሚቆዩ ናቸው ሆኖም ይህ ያልተከፈለው አክሲዮን ማህበሩ በንግድ መዝገብ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ቢበዛ እስከ አምስት ዓመት ድረስ በየጊዜው መከፈል እንዳለበት በዚሁ ሕግ እና ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 2

ተመልክቷል፡፡ በዚህ ሕጉ ባስቀመጠው ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለው የአክሲዮን ክፍያ ካልተፈፀመ ምን ውጤት እንደሚያስከትል ደግሞ በንግድ ሕግ ቁጥር 342 ሥር ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ድርሻ የአክሲዮን ክፍያውን ገቢ አለማድረጉ ከተረጋገጠ በንግድ ሕግ ቁጥር 338/1/ እና 342 መሠረት

- ያልተከፈለባቸውን አክሲዮኖች ስም በማህበሩ ማቆየት፣
- በሐራጅ ማሸጥ፣
- ኪሣራ ካስከተለ መጠየቅ እንዲሁም ከጉባዔ ድምፅ እንዲታገድ ከሚድረግ

በቀር የአክሲዮን ክፍያ ገንዘብ አልከፈለም በሚል እንዲከፍል ማስገደድ ሕጋዊ መሠረት አይኖረውም፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካቹ መክፈል የሚገባውን ቀሪ ብር 74,838.80 /ሰባ አራት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሣ ስምንት ብር ከሰማንያ ሣንቲም/ የአክሲዮን ክፍያ ይክፈል በማለት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ወስነናል የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን ያመለክታሉ ያላቸውን ነጥቦች አመልካች በመጥቀስ እንዲታረምለት ነው፡፡

መልስ ሰጭም በበኩሉ የሥር የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ግድፈት አልተፈፀመበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

እኛም ጉደዩን ተመልክተናል እንደተመለከትነውም አመልካቾችና መልስ ሰጭ ያቋቋሙት የንግድ ማህበር የተወሰነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበር ስለመሆኑና ክርክር ያስነሣውን የብር 74,838.80 መዋጮ መልስ ሰጭ ለዚሁ የንግድ ማህበር ገቢ ማድረግ በሚገባው ጊዜ ያላገባ ስለመሆኑ በክርክሩ ሂደት የተካዱ ነጥቦች አይደሉም ፡፡ እያንዳንዱ ማህበርተኛ በዓይነትም ሆነ በገንዘብ ማግባት የሚገባውን መዋጮ አጠቃሎ መክፈል ያለበት መሆኑን ከንግድ ሕግ ቁ. 516 እና 517 ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡



ይኸውም ማህበሩ ተቋቁሟል የሚባለው በማህበሩ መመሥረቻ ጽሑፍ ዓይነት በተዘጋጀው ግልጽ በሆነ ጽሁፍ ላይ ማህበርተኞቹ ወይም ወኪሎቻቸው የፈረሙበት እንደሆነ ነው፡፡ በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ ላይ ከሚገለፁት ነገሮች አንዱ የማህበሩ ዋና ገንዘብ በሙሉ መግባቱን የመጠቀሱ ጉዳይ ነው፡፡ እንዲሁም በንግድ ሕግ ቁጥር 121 ሥር የአክሲዮኖች ድርሻ መዝገብ ምን ምን ነገሮችን ማካተት እንዳለበት ከተዘረዘሩት መካከል በንዑስ ቁጥር 1(ለ) “እያንዳንዱ ማህበርተኛ ማግባት ያለበትን የመዋጮዎች ግምት” የሚለው መዋጮው ከተቋቋመም በኋላ ወደ ፊት መግባት እንደሚችል በሚገልጽ አኳኋን የተፃፈ ቢሆንም **"the value of all contributions made by the members"** ከሚለው የእንግሊዝኛ ግልባጭ ጋር አጠቃለን ስናየው መዋጮ አስቀድሞ መግባት ያለበት መሆኑን የሚያመለከት ነው፡፡ እነዚህም ድንጋጌዎች ማህበርተኛው አገባዋለሁ ያለውን መዋጮ ማህበሩ በተቋቋመበት ጊዜ አጠቃሎ መክፈል ያለበት መሆኑን የሚያመለክቱ እንጂ ስለ አክሲዮን ማህበር በዚሁ ሕግ ቁ. 338/1/ እንደተመለከተው ክፍያ ሣይፈፀምበት ሊቆይ የሚችል መዋጮ ሊኖር የሚይችል መሆኑን አያሣዩም ማህበርተኞቹ ማህበሩን ሲያቋቁሙ በዚህ መሠረት መፈፀም ሲገባቸው አላደረጉም ሆኖም ማህበርተኛው መዋጮውን ዘግይቶ እንዲያስገባ በማድረግ ማህበሩን መሥርተው በተገኙ ጊዜ ማህበሩ ህልውና የለውም ማለት አይደለም፡፡ ይህንን አስመልክቶም የቀረበ ክርክር የለም፡፡ ይህ በጊዜው ገቢ ያልሆነው መዋጮ መቼ እና እንዴት መከፈል እንዳለበት በመመስረቻ ጽሑፍ ላይ ባይገለጽም መልስ ሰጭው ያልከፈለውና ገቢ ማድረግ ያለበት መዋጮ መኖሩን አምኖ እንደሚከፍል መተማመኛ የሰጠ ለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የህንን መተማመኛ ከሰጠ በኋላ የአሁን መልስ ሰጭ የሚያቀርበው ክርክር ይህንን ገቢ ያላደረግሁትን መዋጮ ማህበሩ ከሚያኘው ትርፍ በአስገባሁት መዋጮ ልክ ከሚደርሰኝ ገቢ እየተሰላ በየጊዜው ልከፍል ከሚገባ በቀር በአንድ ጊዜ የመክፈል ግዴታ የለብኝም የሚል ነው፡፡ ሆኖም ከላይ

እንደተመለተው የተወሰነ ኃላፊነት ያለው ማህበር መዋጮ መክፈል ያለበት ማህበሩ ሲቋቋም እንጂ ተቋቁሞ ሥራውን ከጀመረ በኂላ ባለመሆኑና መልስ ሰጭም ያላገባውን መዋጮ እከፍላለሁ በማለት እራሱን ግዴታ ውስጥ ያስገባ ለመሆኑ የሚያረጋግጥ መተማመኛ የሰጠ በመሆኑ በሂደት ማህበሩ በሚያስገኘው ገቢ ልክፈል የሚለው መከራከሪያው ሕጋዊ መሠረት ያለው አይደለም፡፡

የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት መዋጮ ሣይከፈል ከተገኘ በባለድርሻው ስም ሣይሆን በማህበሩ ስም ተመዝግቦ ሊቆይ እንደሚችልና መከፈል በሚገባው እጅግ ቢዘገይ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልተከፈለ ምን ውጤት እንደሚያስከትል በንግድ ሕግ ቁጥር 342 ተመልክቷል የሚለውን ምክንያት ይዞ መልስ ሰጭ ያላገባውን መዋጮ እንዲከፍል ማስገደድ አይቻልም በሚለው መደምደሚያው የጠ/ፍ/ቤቱን ውሣኔ ሊሽር የቻለው በንግድ ሕግ ቁጥር 338 እና 342 ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ነው ይሁን እንጂ እነዚህ ድንጋጌዎች የአክሲዮን ማህበርን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ የአክስዮን ማህበርና የተወሰነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበር ሁለቱም የንግድ ማህበሮች ይሁኑ እንጂ በአመሠራረታቸው በአለባቸው የኃላፊነት አድማስ፣ በሚሰማሩበት የሥራ ዘርፍ ገደብ ያለባቸው ስለመሆኑና አለመሆኑ ወዘተ ስራ ልዩነት አላቸው፡፡ ለአክስዮን ማህበር የሚሸጡት አክሲዮኖች መቼ ገቢ እንደሚሆኑና ለተወሰነ ኃላፊነት ያለው ማህበር ደግሞ መዋጮው መቼ መግባት እንዳለበት በተለያዩ አኳኋን በየሚመለከታቸው ክፍሎች ተደንግገዋል መዋጮ መቼ መግባት ያለበት መሆኑን ስለአክሲዮን ማህበር የሚደነግጉትን ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ማድረግ እንደሚቻልም ተጠቅሶ አልተገኘም፡፡ ይህ ሆኖ እያለ የንግድ ሕግ ቁጥር 338 እና 342 አሁን ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት እንዳላቸው ቆጥሮ የክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት ለውሣኔው መሠረት ማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል፡፡



**ው ሣ ኔ**

1. መልስ ሰጭ ለንግድ ማህበሩ ገቢ አደርጋለሁ ሲል መተማመኛ የሰጠበትን ብር 74,838.80 /ሰባ አራት ሺ ስምንት መቶ ስልሣ ስምንት ብር ከ80%/ ገቢ ሊያደርግ ይገባል፤ ይከፈል ብለናል፡፡
2. የጌዲኦ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ. 22/92 በ24/3/95 የሰጠው ውሣኔ እና የደቡ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በይ/መ/ቁ. 5648 በ26/04/97 የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
3. የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 3694 በ29/4/96 የሰጠውን ውሣኔ ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰበር መ/ቁ. 23389

ሐምሌ 10 ቀን 1999 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አቶ አብዱራሂም አህመድ

አቶ ብርሃኑ አመነው

**አመልካች፡-** የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አ/ማኀበር - ጠበቃ ኃይሉ አስምር ቀርቧል፡፡

**ተጠሪዎች፡-** እነ ባህሩ አብርሃም /12 ሰዎች/ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመ/ቁ 08449 ላይ በ27/4/97 በዋለው ችሎት የሰጠውን ብይን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ 37119 ላይ በ27/3/98 ለዋለው ችሎት ብይኑን በማፅናቱ አመልካች የካቲት 15 ቀን 1998 ዓ.ም. ባቀረበው ማመልከቻ በስር ፍ/ቤቶች የተፈፀመው የሕግ ስህተት እንዲታረም በመጠየቁ ነው፡፡

የሰበር ችሎቱም መዝገቡን መርምሮ የማኀበሩ አባላት በአስተዳዳሪዎች ላይ ክስ ሊመሰርቱ የሚችሉበት የሕግ አግባብ ምን እንደሚመስል ለማጣራት ሲል ቅሬታው ለተጠሪዎች ደርሶ ታህሣሥ 19/1999 በዋለው ችሎት ቀርበው በጠበቃቸው አማካይነት የቃል ክርክር አድርጓል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም መዝገቡን መርምሯል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ክስ ሲመሰርቱ ተጠሪዎች የአክስዮን ማኀበር



አስተዳዳሪዎች ሆነው ከደንብ ውጪ በአክስዮን ማኀበሩ ከተሰራው ሕንፃ ውስጥ የግንባር ሱቆችን በተደረገው ግልጽ ያልሆነ ስብሰባ ያሳለፉት ውሣኔና የወሰዱት አስተዳደራዊ ውሣኔ ከደንቡ ውጪ ስለሆነ እንዲታገድና እንዲፈርስ የሚል አቤቱታ አቅርበው ለመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪዎች በሰጡት መልስ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ተጠሪዎችን እንደማይመለከትና እንደማያስከስሳቸው፣ ያስከስሳቸዋል ቢባልም እንኳ በን/ህ/ቁጥር 365/1/ መሠረት በተጠሪዎች ላይ ክስ ለመመሥረት የሚቻለው ማኀበሩ እንጂ አመልካቾች ሊሆኑ እንደማይችሉ በመቃወማቸው ፍ/ቤቱም ክርክራቸውን በመስማት አመልካቾች በንግድ ሕግ አንቀጽ 365 ሥር የተመለከተውን ቅድመ ሁኔታ ሳያሟሉ በተጠሪዎች ላይ ክስ መመሥረት አይችሉም በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

በዚህ ችሎትም የታየው መሠረታዊ ጉዳይ አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ በቀጥታ ክስ መመሥረት ይችላሉ ወይ? የሚለው የሕግ ጥያቄ ነው፡፡ በንግድ ሕግ አንቀጽ 364 እስከ 367 በተደነገገው መሠረት የአክስዮን ማኀበር አስተዳዳሪዎች ሀላፊነት ለአክስዮን ማኀበሩ አበዳሪዎች፣ ለአክሲዮን ማኀበሩ ባለድርሻ አባላት ወይም ለሦስተኛ ወገን ሊሆን እንደሚችል ተመልክቷል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ላይ ተጠሪዎች የአመልካቾችን መብት በሚጎዳ መልኩ የሰሩ ስለሆነ ሃላፊነት አለባቸው፣ የሰሩትም ሥራ ሊፈርስ ይገባል የሚል ክስ የቀረበባቸው መሆኑ በሥር ፍ/ቤት መዝገብ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ሆኖም የበታች ፍ/ቤት ክሱን ውድቅ ለማድረግ መሠረት ያደረገው የሕግ አንቀጽ የንግድ ሕጉ ቁጥር 365 ቅድመ ሁኔታዎች አልተሟሉም የሚል ነው፡፡ ሆኖም በዚህ አንቀጽ ድንጋጌ የተመለከቱት ማኀበሩ አስተዳዳሪዎችን ለመክሰስ ሲፈልግ ሊያሟላቸው የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎችን እንጂ የተወሰኑ የአክሲዮን ማኀበሩ ባለድርሻዎች የሚያቀርቡትን ክስ አያጠቃልልም፡፡

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአስተዳዳሪዎች ላይ ክስ ለመመሥረት የሚችሉ ወገኖች ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች በንግድ ህጉ ለየብቻ የተደነገጉ ስለሆነ እነዚህን ለይቶ በአግባቡ ማየት የግድ ይሆናል፡፡ በዚሁ መሠረት አሁን በተያዘው ጉዳይ ላይ አመልካቾች የሚሉት በተጠሪዎች የተፈፀመው ተግባር መብታቸውን የሚጎዳ በመሆኑ የአስተዳደሪዎችን /በተጠሪዎች/ በቀጥታ መከሰስ የበታች ፍ/ቤት አንቀጽ 365ን መሠረት አድርጎ መከልከሉ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡

እኛም ይህንን ሁኔታ ከላይ እንደተመለከተው የተጠያቂነት መሠረቱ ለየብቻ መታየት እንዳለበት የሕጉን ዓላማና መንፈስ መሠረት አድርገን አጽንተነዋል፡፡ በዚሁ መሠረት አመልካቾች የአክስዮን ባለድርሻ አባላት በመሆናቸው አስተዳዳሪዎች /የአሁን ተጠሪዎች/ የአባልነት መብታቸውን በሚጎዳ መልኩ መሥራታቸውን ማረጋገጥ ከቻሉ ቀጥታ መከሰስ እንደሚችሉ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 367 ይፈቅድላቸዋል፡፡

በመሆኑም አመልካቾች የሚጠበቅባቸው በተጠሪዎች የሥራ አመራርና የውሣኔ እርምጃ ተጎጂ መሆናቸውን በንግድ ሕጉ አንቀጽ 367 መሠረት ማረጋገጥ እንጂ የበታች ፍ/ቤት እንደተመለከተው በንግድ ሕግ አንቀጽ 365 የተመለከተውን ቅድመ ሁኔታ ማሟላት አይጠበቅባቸውም፡፡ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 365 የተወሰኑ የአክስዮን ማኅበሩ አባላት በአስተዳዳሪዎች ላይ የሚያቀርቡትን ክስ የሚመለከት ስላልሆነ የሥር ፍ/ቤት ተገቢ ያልሆነውን የሕግ አንቀጽ መሠረት አድርጎ የአመልካቾችን ክስ መዝጋቱ የሕግ ስህተት ነው ብለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05449 የሰጠው ብይን እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37119 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡



2. ጉዳዩ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 341/1/ መሠረት ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ ተመልሶ የፍሬ ነገር ክርክሩ ውሣኔ እንዲያገኝ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪያቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁጥር 28923

ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ አክስዮን ማሕበር አልቀረቡም

**ተጠሪዎች፡-** 1ኛ/ የባህር ዳር ልዩ ዞን አስተዳደር አልቀረቡም

2ኛ/ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ነገረደጅ አቶ አዳነ መጋቡ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

መዝገቡ የቀረበው አመልካች የአማራ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጥር 4 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የካቲት 5 ቀን 1999 ዓ.ም ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በአማራ ብሔራዊ ክልል የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ ፍሬ ጉዳዩም አንደኛ ተጠሪ የአማራ ብሔራዊ ክልል ባወጣው ደንብ መሠረት የ1988 ዓ.ም የቦታ ኪራይ ብር 497,943.54 /አራት መቶ ዘጠና ሰባት ሺ ዘጠኝ መቶ አርባ ሦስት ብር ከሀምሣ አራት ሣንቲም/ እንዲከፍል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ያልከፈለ በመሆኑ እንዲከፍል ውሣኔ ይስጥልኝ በማለት በአመልካች ላይ ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካችም ይህ ዕዳ የባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የመንግሥት የልማት ድርጅት እንደነበርና ወደ ባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ አክስዮን ማሕበር ከመቀየሩ በፊት የነበረ ስለሆነ፣ ሁለተኛው ባለዕዳ፣ ሦስተኛ ወገን ተከራካሪ፣ /ተከሣሽ/ ሆኖ ጣልቃ እንዲገባ በጠየቀት መሠረት ፍ/ቤቱ 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ ያቀረበውን ክስና አመልካቹና ሁለተኛው ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ሁለተኛው ተጠሪ የቦታውን ዋና ግብር 454,511.99 /አራት መቶ ሀምሣ አራት ሺ አምስት መቶ አሥራ አንድ ብር ከዘጠና ዘጠኝ ሣንቲም/ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

ሁለተኛው ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሁሉንም ተከራካሪ ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ ሁለተኛ ተጠሪ ብር 56,159.44 /ሀምሣ ስድስት ሺ አንድ መቶ ሀምሣ ዘጠኝ ብር ከአርባ አራት ሣንቲም/ ብቻ እንዲከፍል ቀሪውን ዕዳ አመልካች እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በክሱ ተከሳሽ የሆነው የባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ አክስዮን ማሕበር የተመሰረተው 1992 ዓ.ም ነው፡፡ ስለዚህ ፋብሪካው ወደ አክስዮን ማሕበርነት ከመለወጡ በፊት የነበረው ዕዳ እኛን የሚመለከት ባለመሆኑና ሁለተኛው ተጠሪ ይህንን ዕዳ የመክፈል ግዴታ በአዋጅ ቁጥር 182/1992 የተጣለበት ሆኖ እያለ አክስዮን ማሕበሩ ዕዳውን እንዲከፍል የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ ስህተት ያለበትና አክስዮን ማህበሩን ለኪሣራ የሚዳርግ በመሆኑ በሰበር ይታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

ሁለተኛው ተጠሪ በበኩሉ ወደ አክስዮን ማሕበሩ የሚተላለፉና የማይተላለፉ ዕዳዎችን የመወሰን ሥልጣን ያለው የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ መክፈል ያለበት ዕዳ ነው በማለት ያሣወቀን 56,159.44 /ሃምሣ ስድስት ሺ አንድ መቶ ሃምሣ ዘጠኝ ብር ከአርባ አራት ሣንቲም/ በመሆኑ ከዚህ ውጭ ያለውን ዕዳ አመልካች መክፈል ይገባዋል የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ አንደኛ ተጠሪ በበኩሉ ዕዳው መከፈል ያለበት ዕዳ

መሆኑን ሁለተኛ ተጠሪና አመልካች እንዳልካዱ ገልፆ በሁለቱ መካከል በሚደረገው ክርክር የከተማው አስተዳደር ማግኘት የሚባውን ክፍያ ሣያገኝ ጉዳዩ እየተጓተተ በመሆኑ በአጭር ጊዜ ታይቶ ዕዳውን ከነወለዱ እንዲከፍሉ ውሣኔ ይሰጥልን በማለት ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና የአመልካችና ተጠሪዎች በሰበር ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች ያለበት ዕዳና አጠቅላይ አሴቱ እና መንቀሳቀሻ ካፒታሉ ተለይቶ የባህርዳ ጨርቃጨቅ ፋብሪካ አክስዮን ማህበር ተብሎ በአዲስ መልክ በአክስዮን ማህበርነት ከመደራጀቱ በፊት ለአንደኛ ተጠሪ መክፈል የሚገባው የቦታ ግብር ዕዳ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም የሚለው ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ብንመዝነው መንግሥት አመልካች ድርጅት ወደ አክስዮን ማህበር ከመቀየሩ በፊት የነበሩበትን ዕዳዎች በኃላፊነት የሚረከብ አንድ ተቋም ማቋቋም በማስፈለጉ ምክንያት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለ አደራ ቦርድን ሥልጣንና ኃላፊነት እንደገና በመወሰንና ሕግ ያወጣ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 208/1992 መግቢያ ለመረዳት ይቻላል፡፡ የባለአደራ ቦርዱ መሠረታዊ ዓላማም የመንግሥት የልማት ድርጅት ወደግል ይዞታ በሚዛወርበት ወይም ወደ አክስዮን ማህበር በሚለወጥበት ወይም ወደ ቀድሞ ባለቤቱ በሚመለስበት ጊዜ ወደ አዲሱ ባለቤት ወደ አክስዮን ማህበሩ ወይም ወደ ቀድሞ ባለቤቱ የማይተላለፉ ሂሣቦችን መሰብሰብ ዕዳዎችን መረከብና ከዚሁ ጋር የተያያዙ የፍርድ ቤት ጉዳዮችን መከታተል እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 208/1992 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የባለአደራ ቦርዱ ወደ አክስዮን ማህበርነት የተቀየሩ ወደ ግል የተዛወሩ ወይም ለቀድሞ ባለቤታቸው የተመለሱ የመንግሥት የልማት ድርጅት ዕዳዎችን ለመንግሥት እያቀረበ እንዲከፈሉ የማድረግ ሥልጣንና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን አዋጅ ቁጥር 208/1992 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1/ሐ/ ይደነግጋል፡፡ በዚህ መዝገብ የባህርዳር ከተማ አስተዳደር የጠየቀው የመሬት ኪራይ የባህርዳር ጨርቀጨርቅ ፋብሪካ ወደ አክስዮን ማህበርነት ከመቀየሩ ከአራት ዓመት በፊት የነበረና የባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የመንግሥት የልማት ድርጅት በነበረበት 1988 ዓ.ም መክፈል የሚባው ዕዳ ነው፡፡ አሁን ያለው የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ አክስዮን ማህበር 1992 ዓ.ም ህጋዊ ሰውነት ያገኘ ድርጅት በመሆኑ ከጅምሩ በፈረሰውና ወደ አክስዮን ማህበርነት በተቀየረው የባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ስም ያቀረበውን ክስ በኃላፊነት ይዞ መከራከር የሚገባው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ እንደሆነ ከአዋጅ ቁጥር 208/1992 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

ሁለተኛ ተጠሪ ዕዳውን ላለመክፈል የሚያቀርበው ምክንያት የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አላሳወቀኝም የሚል ነው፡፡ ሆኖም የመንግሥት የልማት ድርጅቱ ወደ አክስዮን ማህበርነት ሲቀየር በፕራይቬታይዜበሽን ኤጀንሲ ያልታወቀና ውሣኔ ያልተሰጠበት ዕዳ ሁሉ ወደ አክስዮን ማህበሩ ይተላለፋል የሚል ግልጽ የህግ ድንጋጌ ካለመኖሩም በላይ የዚህ አይነት የህግ አተረጓጎም አክስዮን ማህበሩን ለከፍተኛ ኪሣራ የሚዳርግና የባለአደራ ቦርዱ የተቋቋመበትን መሠረታዊ ዓላማ ጋር የሚቃረን ሆኖ አናገኘዋለን፡፡ በመሆኑም ዕዳው አክስዮን ማህበሩ ከመቋቋሙ በፊት የነበረ እስከሆነ ድረስ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በወቅቱ ያላወቀውና ውሣኔ ያልሰጠበት ዕዳ በአክስዮን ማህበሩ መክፈል ይገባዋል በማለት የሰጠው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ትርጉምና ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 07500 ጥር 4 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ የፍርዱ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡

2. የአማራ ክልል የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 03792 ሐምሌ 27 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል። የፍርዱ ግልባጭ ይተላለፍ።
3. ሁለተኛው ተጠሪ ብር 454,511.99 /አራት መቶ ሀምሣ አራት ሺ አምስት መቶ አሥራ አንድ ብር ከዘጠና ዘጠኝ ሣንቲም/ እና የከፍተኛው ፍርደ ቤት ውሣኔ ከሰጠበት ከሐምሌ 27 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት /9%/ ህጋዊ ወለድ ለአንደኛው ተጠሪ ይክፈል ብለናል።
4. አመልካችና ተጠሪዎች ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ።

ይህ ፍርድ ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ



# አፈጻጸም

የሰበር መ/ቁ. 10489

ሐምሌ 24 ቀን 1999 ዓ.ም

*ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ*

*አሰግድ ጋሻው*

*ተሻገር ገ/ሥላሴ*

*ታፈሰ ይርጋ*

*ብርሃኑ አመነው*

**አመልካች፡-** የስራና ከተማ ልማት ሚ/ር ተተኪ መሠረተ ልማት ሚ/ር ነገረ ፈጅ

አቶ ወ/ማርያም ሥዩም ቀረቡ

**መልስ ሰጭ፡-** የቀድሞ ብሔራዊ መሐንዲሶችና ሥራ ተቋራጮች ኃ/የተ/የግል ማህበር

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በግራ ቀኙ መካከል የነበረውን የአፈፃፀም ጉዳይ በሚመለከት የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 5520 ህዳር 30 ቀን 1995 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌ/ከፍተኛው ፍ/ቤትም በይግባኝ ተመልክቶ ይኸው ትእዛዝ ጉድለት የለበትም በማለት የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይታረምልን በማለት ነው፡፡

ጉዳዩም ባጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር ብር 11,908, 734 /አስራ አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሰላሣ አራት ብር/ ከእነ ወለዱ ለመልስ ሰጭ ለብሔራዊ መሐንዲሶችና ሥራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግል ማህበር እንዲከፍል ህዳር 23 ቀን 1991 ዓ.ም የተሰጠውን ትእዛዝ መነሻ በማድረግ አፈፃፀሙ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲታይ ቆይቷል፡፡



ይኸው ፍ/ቤት ክፍያው እንዴት እንደሚፈፀም ግራ ቀኙ በሌሉበት ጉዳዩን ሲከታተል ከቆዩ በኂላ ህዳር 30 ቀን 1995 ዓ.ም በዋለው ችሎት ባለእዳ እዳውን እንዲከፍል የተለያየ ትዕዛዝ ሲሰጥ ቢቆይም ዕዳው አልተከፈለም ፡፡ የፍርድ ባለእዳ የሆነው የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር በአዋጅ ቁጥር 256/94 ፈርሶ መብትና ግዴታው ወደ መሠረተ ልማት ሚ/ር ተላልፏል፡፡ ተተኪው የመሠረተ ልማት ሚ/ር ባለበት ጉዳዩ በመታየት ላይ እንዳለ በጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት በቁጥር ጠ/80 -ጠ4/01/11 በ3/8/94 በተፃፈው ደብዳቤ መነሻነት የብሔራዊ መሐንዲሶች ሥራ ተቋራጭ ማህበርን የቀድሞ ባለንብረቶች ይረከቡት ዘንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ ጉዳዩ ሲታይ የቆየ ቢሆንም ኮሚቴው ውጤታማ ይሆን ዘንድ የመሠረተ ልማት ሚ/ር ሥራውን መሥራት አልቻለም ፡፡

ስለዚህ አስቀድሞ በተወሰነው መሠረት ፍ/ቤቱ አፈፃፀሙን ከመቀጠል ውጭ አማራጭ አላገኘም የሚለውን ምክንያት ካሰፈረ በኂላ የኢት/ያ ብሔራዊ ባንክ የመሠረተ ልማት ሚ/ር ካለው ሂሣብ ላይ ህዳር 23 ቀን 1999 ዓ.ም በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ቀንሶ ለፍርድ ባለመብት ለአሁን መልስ ሰጭ ይክፈል የሚል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ትእዛዝ ቅር በመሰኘት አመልካች የይግባኝ አቤቱታውን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛ ፍ/ቤትም የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ጉድለት የለበትም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍ/ቤቶች ከላይ በተገለፀው አኳሃን የሰጡት ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል፤ ይታረምልን በማለት ነው የአቤቱታው ይዘትም ተጠቃሎ ሲታይ፡፡

በአዋጅ ቁጥር 256/94 አንቀጽ 26/1/ ድንጋጌ መሠረት የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር መብትና ግዴታ ለመሠረተ ልማት ሚ/ር ይተላለፍለት እንጂ ለዕዳ መክፈያ በጀት አልተመደበለትም፡፡ የአመልካች በጀት ለደምወዝና ለስራ ማስኬጃ ብቻ ሆኖ እያለ በጀት ለዕዳ መክፈያ እንዲውል መደረጉ

አግባብነት የለውም፤ የሥር ፍ/ቤት ተቀብሎትና አምኖበት ለእዳው አከፋፈል በኮሚቴ አማካኝነት የንብረት ማስተላለፍ ተግባር እንዲደረግ ታዞ በዚህም መሠረት ሥራው ቀጥሎ ከ80% በላይ ኮሚቴው ሥራውን ማከናወኑ እየታወቀ የሥር ፍ/ቤት የአንድን ወገን አቤቱታ ብቻ አዳምጦ እራሱ የሰጠውን ትእዛዝ እንደይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሆኖ በመሻር ዕዳው በመደበኛ በጀት እንዲከፈል ትእዛዝ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ያመለክታል የሚል ነው፡፡

መልስ ሰጭም ይህንኑ ቅሬታ አስመልክቶ ዝርዝር መልስ ሰጥቶበታል የመልሱም ፍሬ ቃል የሥር ፍ/ቤት ስለአፈፃፀሙ የሰጠው ዳኝነት የሥነ ሥርዓት ሕጉ በሚያዘው መሠረት መሆኑንና ዕዳውንም በመጨረሻ መንግሥት የሚሸከመው መሆኑን አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ናቸው የሚላቸውን በመጥቀስ አስፈላጊም ከሆነ ከመንግሥት ካዝና ወጪ ሆኖ ሊከፈል እንደሚገባ አብራርቷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚው ችሎትም በበጀት የሚተዳደር የመንግሥት መሥሪያ ቤት የፍርድ ባለእዳ ሆኖ ሲገኝ ውሣኔውን ለማስፈፀም ለሌላ ጉዳይ በበጀት የተያዘውን እና የሠራተኛ ደመወዝን የሚጨምረውን ገንዘብ ከባንክ ወጭ ሆኖ እንዲከፈል ማዘዝ ይችላል ወይስ አይችልም የሚለውን መነሻ በማድረግ ነው ያከራከረው፡፡ ክርክሩ በሰበር ከመቅረቡ በፊትም ሆነ በኋላ ጉዳይ በሃ̉ራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ቀርቦ ግራ ቀኙ ሲደራደሩ እንደነበር ለመረዳት ተችሏል፡፡ ድርድሩ የተደረገውም በሠራተኛ ቅነሣ ጥያቄ ዕዳውን እረከባለሁ በማለት ቦርድ ኃላፊነት ሊወስድ የሚገባው የመሆኑን አግባብነት፣ በተገባው ቃል መሠረት የቦታ ርክክብ ሊፈፀም ያለመቻሉን፡

እንዲሁም ተረከቡ ያሉን መሣሪያዎች የተገመቱት ከ5 ዓመት በፊት በመሆኑ በዚያው ዋጋ ተረከቡ መባሉን ፤



የወደቁ መሣሪያዎች ተለይተው ከግምቱ ተቀናሽ መሆን የሚገባቸው መሆኑን፣

ክሱ ተሰልቶ በሚታውቀው ግምት እና እኛ በምንፈልገው ገንዘብ መካከል ያለውን ልዩነት ጊዜ ተሰጥቶን ልንከፍል የምንችልበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል በሚሉት ነጥቦች ዙሪያ ሲሆን ድርድሩ ውጤት ሣያገኝ መቅረቱን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ከዚህ በፊት የተጀመረው ድርድር እልባት ያገኝ ዘንድ በፍትህ ሚ/ር ሰብሣቢነት የሚመራ ኮሚቴ የተቋቋመ መሆኑንና ይህም ኮሚቴ ሥራውን በመስከረም ወር 1999 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሚያዚያ ወር 1999 ዓ.ም ድረስ ከመልስ ሰጭዎች ጋር ሲደራደር ከቆየ በኋላ ደርሰንበታል ባለው ስምምነት መነሻ ስለጉዳዩ በመንግሥት በኩል ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ የውሣኔ ሀሣብ ያቀረበ መሆኑን ግንቦት 30 ቀን 1999 ዓ.ም ከቀረበው ሪፖርት መረዳት ተችሏል፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው በአመልካችና በመልስ ሰጭ መካከል የተነሣውን የአፈፃፀም ጉዳይ የሥር የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት እንደጀመረው ከጠቅላይ ሚ/ሩ በተፃፈው ደብዳቤ መሠረት ዕልባት የሚያገኝ ከሆነ በሚል ይህ ሰበር ችሎትም የእራሱን ጥረት አድርጓል ይሁን እንጅ በተለያዩ ምክንያቶች ውጤት ሣያገኝ ቀርቷል ግራ ቀኝ ተከራካሪ ወገኖች እንደየጉዳዩ እየታየ በፍ/ቤቱ አነሳሽነት በሚቀርብላቸው ጥያቄ መሠረት ጉዳያቸውን በስምምነት መጨረስ ካልቻሉ ሕግን ባገናዘበ ሁኔታ ዳኝነት ሊያገኙ ይገባል ስለሆነም ይህ ችሎት ቀደም ሲል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባል በማለት በምክንያትነት ከያዘው ነጥብ አንፃር ጉዳዩን መርምሯል፡፡

እንደመረመርነውም የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መግባባት አፈፃፀሙ ፍፃሜ እንዲያገኝ ጥረት ቢያደርግም የፍርድ ባለእዳን የተካው የመሠረተ ልማት ሚ/ር የሚጠበቅበትን አልሰጠም በሚል እንደ

መጨረሻ አማራጭ የኢት/ብሔራዊ ባንክ ከመሠረተ ልማት የባንክ ሂሣብ ገንዘቡን ወጭ አድርጎ እንዲከፍል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይህ ከባንክ ወጭ ሆኖ ለዕዳ መክፈያ ይዋል የተባለው ገንዘብ የመ/ቤቱ መደበኛ በጀት መሆኑንም መልስ ሰጭ ክዶ አልተከራከረም ፡፡ መደበኛ በጀት ለሠራተኛ ደመወዝ ፤ለመ/ቤቱ የዕለት ተዕለት ተግባር ማከናወኛ ሲባል የሚመደብ ገንዘብ እንደመሆኑ ለተጠየቀው ዕዳ ክፍያ ይዋል ቢባል የመ/ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴ መግታት ይሆናል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 404 ድንጋጌ ሥር በዕዳ ምክንያት በአፈፃፀም ሊያዙ አይችሉም ተብለው የተዘረዘሩትን የንብረት ዓይነቶችና መጠን አዳምረን ስናይ እነዚህ ለባለእዳው ፍፁም አስፈላጊ የሆኑና ለዕለት ጉርሱ የሚውሉ በመሆናቸው ህልውናውን ለመጠበቅ ታስቦ የተሰጠ የሕግ ጥበቃ መሆኑን እንረዳለን፡፡ አንድ የመንግሥት መ/ቤትም ለህዝብ አገልግሎት እንዲሰጥ ታስቦ ከተዋቀረ ለመደበኛ ሥራው ሲባል የተመደበውን በጀት ለሌላ ተግባር ማለትም ለእዳ ክፍያ እንዲውል ከተደረገ በግለሰብ አቋም እንዳየነው ሁሉ የመ/ቤቱን ሕልውና የሚፈታተንና የህዝብንም ጥቅም የሚጎዳ በመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 404ን በማመሳሰል ሥራ ላይ የማይውልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡

ስለሆነም ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ ሆኖ በተያዘው ነጥብ መሠረት የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አፈፃፀሙ በመሠረተ ልማት ሚ/ር መደበኛ በጀት ላይ ተፈፃሚ እንዲሆን፤ ከመደበኛ በጀት ወጭ ሆኖ እንዲከፈል ሲል የሰጠው ትእዛዝ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል ከዚህ ውጭ የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት ለአፈፃፀሙ ተስማሚ እና ተገቢ ነው የሚለውን መንገድ ተከትሎ ፍርዱን ያስፈጽም ብለናል፡፡



<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 5520 ህዳር 30 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ቀሪ ሆኖ ሌላ ተስማሚ እና ተገቢ ነው የሚለውን መንገድ ተከትሎ ፍርዱን ያስፈጽም ብለናል፡፡
2. በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 5520 በኅዳር 30 ቀን 1995 ዓ.ም የተሰጠው ትእዛዝ እና የከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/ቁ. 16478 ታህሣሥ 30 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ ተሽሯል

ግልባጩ ይድረሣቸው ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 18576

26/09/2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

አሰግድ ጋሻው

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ደስታ መኮንን - ጠበቃ መሰለ ገ/ጊዮርጊስ

**ተጠሪ፡-** ወ/ት መሰሉ ጌታሁን - ቀረቡ።

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል።

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪና ሌሎች 2 ሰዎች ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት የፍርድ አፈፃፀም አቤቱታ የፍርድ ባለዕዳ /የአሁን አመልካች/ የአውራሻችንን ንብረት እንድታካፍለን ክስ አቅርበን ፍ/ቤቱ የውርስ አጣሪ ሾሞልን ውርሱ ተጣርቶ ሪፖርቱ ለፍ/ቤቱ የቀረበ ቢሆንም በሪፖርቱ መሠረት ንብረቱን በስምምነት ለመካፈል ያልቻልን ስለሆነ መኖሪያ ቤቱንና የንግድ ቤቶቹን በፍ/ቤቱ በኩል እንድንካፈል ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል።

የፍርድ ባለዕዳ /አመልካች/ ቀርበውም በሰጡት መልስ የውርስ አጣሪ ሪፖርት ማለት የፍ/ቤቱ ውሣኔ አይደለም። የፍ/ቤቱ ውሣኔ ካልሆነ ደግሞ አፈጻጸም ሊጠየቅበት ስለማይችል አቤቱታው ከሥነ ሥርዓት ውጭ ስለቀረበ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ ቀደም ሲል የውርስ አጣሪ እንዲቋቋም በታዘዘው መሠረት አጣሪው ሥራውን በሕጉ መሠረት ሠርቶ አጠናቋል። ከዚህ በኋላ የሚቀረው ነገር የውርስ አጣሪው በሰራው መሠረት ሀብቱን ማከፋፈል ነው። የንብረት ክፍፍሉን በተመለከተ



በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1060 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት በወራሾች ስምምነት ወይም ይህ ካልተቻለ አንደኛው ወገን በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት በፍ/ቤት ሊፈጸም ስለሚችል የፍርድ ባለዕዳ ክርክር ተቀባይነት የለውም ብሎ የውርስ ንብረቱ በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በኩል በሐራጅ ተሸጦ ግራ ቀኙ ድርሻቸውን በሪፖርቱ መሠረት እንዲከፋፈሉ በማለት ውሣኔ ሠጥቷል።

የፍርድ ባለዕዳ የሆኑት በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ውርስ አጣሪ ተቋቁሞ የውርስ ንብረት ከተጣራ በኋላ አጣሪው በሚያቀርበው ሪፖርት መሠረት ንብረቱን መከፋፈል ካልተቻለ ክስ አቅርቦ ከማስወሰን በስተቀር የአጣሪው ሪፖርት ፍርድ ወይም ውሣኔ ባለመሆኑ በቀጥታ ለአፈፃፀም የሚቀርብ አይደለም ስለሆነም በዚህ መልኩ የቀረበውን ሪፖርት የሥር ፍ/ቤት ተቀብሎ እንዲፈጸም በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ አይደለም በማለት ሽሯል።

የአሁን ተጠሪም በዚሁ የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበዋል። ጠቅላይ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው የውርስ ክርክር በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ውርስ አጣሪ ተቋቁሞ የአጣሪው ሪፖርት ለፍ/ቤት ቀርቦ ፍ/ቤቱም ሪፖርቱን ተቀብሎ መዝገቡን የዘጋ ሲሆን መ/ሰጭ የአሁን አመልካች የሪፖርቱን ትክክለኛነት የማይቀበሉ ቢሆን መከራከር የነበረባቸው ፍ/ቤቱ ሪፖርቱን ተቀብሎ መዝገቡን ከመዝጋቱ በፊት ነበር። በጊዜውና በአግባቡ ሪፖርቱ ላይ ተቃውሞ ካልቀረበ ደግሞ ሪፖርቱን ግራ ቀኙ እንደተቀበሉት ስለሚጠቆጠርና ክፍፍልም የማይደረግበት ምክንያት የለም ብሎ የከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል።

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ለማስለወጥ ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የውርስ አጣሪው ሪፖርት በመ/ቁ. 428

በመመዝገቡ ብቻ ለአፈፃፀም መነሻ ሊሆን ይችላል ተብሎ መወሰኑ ለሰበር ቀርቦ ሊጣራ የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ በውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ተመስርቶ የፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻ ማቅረብ ይቻላልን? የሚለው በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በቅድሚያም የውርስ አጣሪን ሥልጣን መመልከት ለጉዳዩ አወሳሰን ጠቃሚ በመሆኑ በዚሁ መሠረት ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የሕጉን ድንጋጌዎች ተመልክተናል፡፡

የውርስ አጣሪ ሥልጣን መብት አለኝ ባይዎችን ወይንም ወራሾችን መወሰን፣ የሟች ኑዛዜ ካለ መፈለግና በዚህ ኑዛዜ መሠረት ተጠቃሚዎችን መወሰን፣ ውርሱን ማስተዳደር የውርሱን ተካፋይ ገንዘብ መሰብሰብና ዕዳዎችን መክፈል፣ የሟችን ንብረት ማጣራትና ማፈላለግ የኑዛዜ ስጦታዎችን መክፈል እንደሆነ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 944፣ 946 እና 956 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

የውርስ አጣሪው የማጣራቱን ተግባር ካከናወነ በኂላ ሪፖርቱን ለወራሾችና ለፍ/ቤት ማቅረብ እንደሚጠበቅበትም በፍ/ህ ቁጥር 960 ላይ ተመልክቷል፡፡ የውርስ ማጣራቱ ተግባር ከተጠናቀቀ በኂላም በአጣሪው ሪፖርት መሠረት ወራሾች የወራሽነት የምስክር ወረቀት /certificate of Succession/ ከፍ/ቤት ማግኘት እንደሚችሉም በቁጥር 996 ላይ ተደንግጓል፡፡

በሕጉ ላይ የተመለከተው የውርስ አጣሪው ሥልጣን ከላይ የተዘረዘረው ሲሆን የማጣራቱ ውጤትም እያንዳንዱ ወራሽ ከውርሱ የሚደርሰው ድርሻ ተለይቶ የወራሽነት የምስክር ወረቀት ማግኘት ነው፡፡



እያንዳንዱ ወራሽ የወራሽነት የምስክር ወረቀት ካገኘና በክፍፍሉ ረገድ በወራሾች መካከል አለመግባባት ቢፈጠር የወራሽነት የምስክር ወረቀት ክስ ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም /Vested interest/ ከሚሰጥ በስተቀር በእራሱ ፍርድ ስላልሆነ በቀጥታ አፈፃፀም ሊጠየቅበት የሚችል አይሆንም፡፡ ምክንያቱም የውርስ ማጣራቱም ሆነ የማጣሪቱ ተግባር ተፈጽሞ የወራሽነት የምስክር ወረቀት ማግኘት ዓለማው የእያንዳንዱን ወራሽ ድርሻውን በመለየት መብቱን ማረጋገጥ ስለሆነ በዚህ መልኩ መብት ከተረጋገጠ በኂላ በዚሁ መሠረት ወራሾች ድርሻቸውን በስምምነት መከፋፈል ካልቻሉ በድርሻቸው መጠን ዳኝነት ከፍለው ይኸው መብታቸው በፍርድ እንዲረጋገጥ ዳኝነት መጠየቅ ስለሚገባቸው ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ መልኩ ዳኝነት ሳይጠየቅ በውርስ አጣሪው ሪፖርት መሠረት እንዲፈጸም የአፈፃፀም አቤቱታ ማቅረብ ፍርድ ያላረፈበትን ነገር ለማስፈጸም እንደመጠየቅ የሚቆጠርና የሕጉን ዓላማ የሳተ ነው፡፡

ስለሆነም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ ተመስርቶ የቀረበውን የአፈፃፀም አቤቱታ ተቀብሎ ማስተናገዱ ከሕጉ አኳያ አግባብ አይደለም ተብሎ በፌዴራል ከ/ፍ/ቤት መሻሩ ተገቢነት የነበረው ሆኖ ሳለ ይሄው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ተሽሮ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲጸና መደረጉ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 14546 በሐምሌ 2 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ እንደዚሁም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 29686 ጥቅምት 8 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33021 በጥር 3 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ በአግባቡ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንተነዋል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 19283

መጋቢት 9 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
አብዱልቃድር መሐመድ
ተገኔ ጌታነህ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- 1. ወ/ሮ መድኃኒት ኃይሉ - ቀረቡ፡፡
2. አቶ ጌታቸው ተሰማ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ - ነገረ ፈጅ ወይንሸት ቸርነት

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው በአመልካቾች በኩል በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ተጠሪ ሊከፍል አይገባም በማለት በሥር ፍ/ቤቶች በመወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካቾች ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ አመልካቾች በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ከተከሳሽ ጋር በተደረገ የብድር ውል በአዳማ ከተማ ቀበሌ 11 ክልል በካርታ ቁጥር 7006/82 የተመዘገበውን ሆቴል መያዣ ሠጥተን ብር 295,620.00 /ሁለት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሀያ ብር/ ተበድረናል፡፡ ከተከሣሽ የተበደርነውን ገንዘብ ሥራ በማጣታችን ምክንያት መክፈል ባለመቻላችን ተከሣሹ በዋስትና የያዘውን ንብረት አስገምቶ በብር 1,607,607.00 /አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሰባት ብር/ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት ለመሸጥ ጨረታ አውጥቶ የሚገዛ ስለጠፋ ድጋሚ ጨረታ አውጥቶ ያለአግባብ ከአዋጅ

ቁጥር 97/90 ውጪ መነሻ ግምቱን በጣም ዝቅ አድርገ በብር 300,000 /ሶስት መቶ ሺህ/ ወስዶታል፡፡

ስለሆነም ተከሣሹ ልዩነቱን ብር 1,307,607.00 /አንድ ሚሊየን ሶስት መቶ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሰባት ብር/ ንብረቱን ከወሰደበት ቀን አንስቶ ከሚታሰብ 9% /ዘጠኝ በመቶ/ ወለድ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሳሾች ክስና ማስረጃ ለተከሳሽ ደርሶ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ጨረታ ወጥቶ ገዢ ስላልቀረበ ድጋሚ ጨረታ ወጥቶ ከአንድ ሌላ ተጫራች ጋር ተወዳድረን ሚያዝያ 19/1991 ዓ.ም. ተከሣሽ ጨረታውን አሸንፎ በብር 300,000 /ሶስት መቶ ሺህ/ ሆቴሉን ገዝቷል፡፡ ተከሣሽ ሆቴሉን የገዛው በሕጋዊ መንገድ ስለሆነ ክሱ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትን የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን ከቀረበው ማስረጃና ከሕጉ ጋር አገናዝቦ መርምሮ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 430/1/ ሥር እንደተመለከተው የፍርድ ባለመብት የሆነ ወገን በሚሸጥ ንብረት በጨረታ መሳተፍ የሚችለው ፍ/ቤትን አስፈቅዶ ሲሆን በዚሁ መሠረት ተከሣሽ ፍ/ቤትን አስፈቅዶ በጨረታው መሳተፍ ሲገባው ሳያስፈቅድ በጨረታው የተሳተፈ ስለሆነ ተግባሩ ሕገወጥ ነው ካለ በኋላ ተከሣሽ የከሳሾችን ሆቴል በመጀመሪያ ጨረታ ብር 1,607,607.00 መገመቱንና ይህንኑ ሆቴልም በብር 300,000.00 መግዛቱን ያመነ በመሆኑ በልዩነት በከሳሾች የደረሰውን ጉዳት ብር 1,307,607.00 /አንድ ሚሊየን ሶስት መቶ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሰባት ብር/ ተከሣሽ ሊከፍል ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተከሣሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራቀኙን አከራክሮ በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 እና 4 እንደዚሁም በአዋጅ ቁጥር 216/92 አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት ጨረታ ወጥቶ ገዢ ባለመገኘቱ ባንኩ ንብረቱን



ከያዘ ወይም ከወሰደ በመጀመሪያው ጨረታ ላይ በተሰጠው ግምት ያስቀረዋል የሚል ሲሆን ይግባኝ ባይ ባንክ ግን ክርክር የተነሳበትን ሆቴል እራሱ የያዘው ወይም ያስቀረው ሳይሆን በድጋሚ ጨረታ የሸጠው ስለሆነ በባለዕዳው ላይ ጉዳት አድርሷል ለማለት ስለማይቻል የሥር ፍ/ቤት ጉዳት ደርሷል በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ስላልሆነ ይግባኝ ባይ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍል አይገባም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን አመልካቾችም የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ይግባኙ ተቀባይነት የለውም በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሠርዟል፡፡

ይህም ችሎት የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካቾች በክስ የጠየቁትን ገንዘብ ተጠሪ ሊከፍል አይገባም ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ አግባብነት አለውን? የሚለው በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ አቤቱታው ከሕጉ ጋር ተገናዝቦ ተመርምሯል፡፡

አመልካቾች ለክርክሩ መነሻ ምክንያት የሆነውንና በአዳማ ከተማ የሚገኘውን የሆቴል ንግድ ድርጅት ለተጠሪ መያዣ በመስጠት ብር 296,620.00 /ሁለት መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ሃያ ብር/ መበደራቸውን፣ ብድሩ ባለመከፈሉ ምክንያት በሀራጅ መነሻ ግምት ብር 1,607,670.00 /አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሰባ ብር/ የመጀመሪያ ጨረታ ወጥቶ ገዢ በመጥፋቱ በድጋሜ 2ኛ ጨረታ ወጥቶ ተጠሪና ሌላ አንድ ተጫራች ቀርበው ተጠሪ በብር 300,000.00 /ሶስት መቶ ሺህ/ የጨረታው አሸናፊ ስለመሆኑ እነዚህ ፍሬ ነገሮች ግራ ቀኙን አላከራከሩም፡፡

በባንክ መያዣ የተያዙ ንብረቶችን አስመልክቶ በወጣው አዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 መሠረት መያዣ ተቀባይ ዕዳው በውሉ ላይ በተመለተው

ጊዜ ሳይከፈለው ቢቀር ከሰላሣ ቀናት ያላነሰ ማስጠንቀቂያ ለመያዣ ሰጭው /ለባለዕዳው/ በመስጠት በመያዣ የያዘውን ንብረት መሸጥ እንደሚችል የተመለከተ ሲሆን በመጀመሪያ ጨረታ ንብረቱ ሳይሸጥ ቢቀር አዋጅ ቁጥር 97/90 ለማሻሻል በወጣው በአዋጅ ቁጥር 216/92 አንቀጽ 2/1/ መሠረት ድጋሚ ጨረታ ወጥቶ ገዢ ካልቀረበ ለመጀመሪያው ጨረታ መነሻ በተሰጠው የዋጋ ግምት መሠረት አበዳሪው ባንክ ንብረቱን ለመውሰድና የባለቤትነት መብቱም በስሙ እንዲዛወርለት ማድረግ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

በሌላ በኩልም ባንክ በመያዣ የያዘውን ንብረት በሐራጅ የመሸጥ ሥልጣን በሥራ ላይ በሚያውልበት ጊዜ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 394-449 ያሉትን ድንጋጌዎች እንደየአግባብነታቸው ተፈፃሚነት እንደሚኖራቸው በተቀጠሰው አዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6 ላይ የተመለከተ ሲሆን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 430/1/ ላይም የፍርድ ባለመብት የሆነ ወገን በሐራጅ እንዲሸጥ የተወሰነውን ሀብት ለመግዛት ፍ/ቤትን ማስፈቀድ እንደሚጠበቅበት ተመልክቷል፡፡ ይሁንና የሐራጅ ሽያጭ በሚከናወንበት ጊዜ ከላይ የተጠቀሱትን የሥነ - ሥርዓት ድነጋጌዎች ባንክ በሥራ ላይ የሚያውላቸው ከጉዳዩ ጋር አግባብነት በሚኖራቸው ጊዜ እንደሆነ በአዋጁ ላይ ከመመልከቱም በላይ በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት ባንኩ የመያዣ ንብረቱን ሲሸጥ ባለዕዳውን በመወከል የሚያደርገው ሽያጭ ሆኖ እንደሚቆጠር በአንቀጽ 5 ላይ የተመለከተ ስለሆነ ባዕዳውን ሻጭ እራሱን ደግሞ ገዢ ማድረግ ስለማይችል ተጠሪ ሽያጩ በአግባቡ ተከናውኗል በማለት ያቀረበው ክርክር የሕግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም ተጠሪ በመያዣ የያዘውን የሆቴል የንግድ ድርጅት ለመሸጥ የመጀመያውን ጨረታ አውጥቶ ገዢ ሳይቀርብ በመቅረቱ ድጋሚ ጨረታ ሲያወጣም ገዢ ካልቀረበ ሕጉ በጣለበት ግዴታ መሠረት በመጀመሪያው የጨረታ መነሻ ዋጋ ንብረቱን መረከብ ሲገባው እራሱ



በጨረታው መሳተፍም ሆነ አሸናፊ ሆኖ መገኘቱ ከሕጉ ያፈነገጠ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ተጠሪ ንብረቱን የተረከበበት አግባብ ከአዋጁ መንፈስ ውጭ ቢሆንም 2ኛ ጨረታ ወጥቶ ገዢ በመጥፋቱ ምክንያት ለመጀመሪያው ጨረታ መነሻ በተሰጠው የዋጋ ግምት መሠረት ንብረቱን እንደተረከበው ሊቆጠር የሚችል ስለሆነ ንብረቱን በተረከበበት የዋጋ ግምትና ለመጀመሪያው ጨረታ መነሻ በተሰጠው የዋጋ ግምት መካከል ያለውን የዋጋ ልዩነት መክፈል የሚገባው በመሆኑ በዚሁ መሠረት እንዲከፈል የአዳማ ልዩ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ አግባብነት ያለው ሆኖ ሳለ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ተጠሪ ሽያጩን ያከናወነው በግባቡ ስለሆነ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍል አይገባም በማለት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03516 በጥር 26 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 18631 መጋቢት 7 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ለአመልካቾች ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ስለሆነ ጸንቷል፤ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 22481

መጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን እቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አቶ ክፍሌ ወልዴ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ፔትራም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር - አልቀረበም፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን፣ ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ የተከፈተው አመልካች በፍርድ የተወሰነብኝን የተጠሪውን እዳ እንዲያስፈጽም፣ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተሰጠው የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ፣ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን ሳያከብር፣ የፈፀመውን የሀራጅ ሽያጭ የከፍተኛው ፍ/ቤት በማጽደቅ፣ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወደ ይግባኙ የሚያስገባ በቂ ምክንያት የለም በማለት አላግባብ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ በማጽናቱ፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የተፈፀመው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላልታረመ በሰበር ይታይልኝ በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ክርክሩን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፍርድ ባለመብቱን /የተጠሪውን/ ዕዳ ለማስከፈል ይቻል ዘንድ በቡራዩ ልዩ ቀበሌ በቤት ቁጥር 1008 ተመዝግቦ የሚገኘው፣ የአመልካቹ የመናፈሻ ድርጅት በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በኩል በሀራጅ ተሸጦ ለፍርድ ባለመብቱ እንዲከፈል የሰጠውን ትዕዛዝ የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን በአግባቡ ተግባራዊ ሳያደረግ፣ ሽያጩን ፈጽሟል እና ይሰርዝ



የሚል ነው፡፡ አመልካቹ የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ ንብረቴን ከዋጋው በታች በሆነ ግምት፣ የሀራጅ ጨረታ ማከናወኑ፣

- የድርጅቱ ሽያጭ የተከናወነው፣ በግልጽ ጨረታ ሣይሆን፣ ሀራጅ ባይ፣ ብቸኛ ተወዳዳሪ ሆኖ ጨረታውን አሸንፏል ከተባለው ሰው ጋር ባደረገው ድርድር እንጂ በሀራጅ ደንብና ሥርዓት መሠረት ባለመሆኑ፣
- በወቅቱ በሀራጅ ጨረታው ለመወዳደር ስድስት የሚሆኑ ሰዎች ቀርበው የነበሩ ቢሆንም አላግባብ በተንኮል በጨረታው እንዳይሣተፉ በመደረጉ
- ብቸኛ ተጫራች ሆኖ በመቅረብ ንብረቱን ገዝቷል የተባለው ግለሰብ የፍርድ ባለመብት የሆነው የንግድ ድርጅት መሥራች እና ባለአክስዮን የሆኑት የአንደኛው ወንድም በመሆናቸው፣ በአጠቃላይ ሀራጁ የሕግ ስርዓትን ባላሟላ ሁኔታ፣ በተንኮልና በጥድፊያ የተፈፀመ በመሆኑ የሀራጅ ሽያጩ ፈርሶ ሌላ ጨረታ እንዲካሄድ ትዕዛዝ ይሰጥልኝ በማለት፣ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ያመለከቱ ሲሆን ተጠሪው በበኩላቸው የንብረቱን ግምት በተመለከተ ቀደም ብለው ያቀረቡት ተቃውሞ ስለሌለ አሁን ሊከራከሩበት አይችሉም፤
- በጨረታው የተሣተፈው አንድ ተጫራች ብቻ ቢሆንም፤ ከመነሻው ብር 5000 /አምስት ሺህ/ ጨምረው የገቡ በመሆኑ በዚህ በኩል የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም፡፡
- ጨረታውን ያሸነፉት ግለሰብ የፍርድ ባለመብት የሆነው የንግድ ድርጅት የአክሲዮን ባለድርሻ ከሆኑት የአንደኛው ወንድም ናቸው የሚለው አቤቱታም ዕውነትነት የሌለውና ቢሆንም ቢሆኑም እንኳን ጨረታውን ለማፍረስ በቂ ምክንያት ስለማይሆን የፍርድ ባለዕዳው ማመልከቻ ውድቅ ሆኖ የሀራጅ ሽያጩ እንዲፀድቅልን በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ በኩል የቀረበውን ክርክር ከሰማ በኋላ በጉዳዩ ላይ የፍርድ አፈፃፀም መምሪያን ሪፖርትና መግለጫ ከሰማ በኋላ ከመጀመሪያ በሀራጅ ሂደቱ ከሥነ ሥርዓት ውጭ የሆነ ተግባር ተፈጽሟል አልተፈፀመም ተፈጽሞስ ከሆነ ተፈፀመ የተባለው ግድፈት ጨረታውን ለማፍረስ የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ወይስ አይደለም የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ፣

- በጨረታው አንድ ተጫራች ብቻ ቀርቦ፣ ንብረቱ ለእሱ እንዲሸጥ መደረጉ፣ ምንም ዓይነት የሕግ ስህተት የሌለበት አሠራር በመሆኑ፤
- በጨረታው አሸናፊ ሆኖ የፍርድ ባለዕዳውን ንብረት የገዛው፣ የፔትራም ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኀበር የአክሲዮን ባለድርሻና ባለቤት ከሆኑት የአንደኛው ወንድም ነው የተባለው በፍርድ ባለዕዳው የተካደና ማስረጃ ያልቀረበበት በመሆኑና፣ ወንድም ሆነው ቢገኙ እንኳን፣ ሽያጩን ለማፍርስ በቂ ምክንያት ስለማይሆን፤
- ሽያጩ የተከናወነው በድርድር ነው የሚለው፣ ምንም እንኳን ግንቦት 3 ቀን 1997 ዓ.ም. በሀራጅ ባዩ ተዘጋጅቶ የቀረበው ሪፖርት ንብረቱ በድርድር የተሸጠ በሚመስል አገላለጽ ተጽፎ፣ የቀረበ ቢሆንም አገላለፁ፣ በወቅቱ የቀረበው ብቸኛ ተጫራች በመጀመሪያ ንብረቱን በመነሻ ዋጋው ለመግዛት እንደሚፈልግ ለሀራጅ ባዩ ከገለፀ በኋላ ሀራጅ ባዩ ከመነሻ ዋጋው ላይ የተወሰነ ዋጋ ጨምሮ እንዲገዛ ሲነግረው ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ በመጨመር ግዢውን እንደፈፀመ ለመግለጽ ታስቦ የተፃፈ መሆኑን ስለሚያሣይና ይኸም በፍትሐብሔር ስነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 422 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ንብረቱ በግል ውል ወይም በድርድር የተሸጠ መሆኑን ስለማያመለክት እና በአጠቃላይ የሀራጅ ሽያጩ ሊፈርስ የሚችለው፤ ጨረታው እንዲፈርስ በጠየቀው ወገን መብት ለይ ጉዳት ማድረሱ ሲረጋገጥ በመሆኑና ሀራጅ የተባለውን ንብረት



ግምት ብር 438,946 /አራት መቶ ሰላሣ ስምንት ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ ስድስት ሆኖ እያለ ከግምቱ በላይ በብር 443,946 /አራት መቶ አርባ ሶስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ ስድስት ብር/ የተሸጠ በመሆኑና የፍርድ ባለዕዳው የንብረቱ ግምት ከሶስት ሚሊዮን በላይ ነው በማለት ያቀረበው ተቃውሞ፣ ንብረቱ ሀራጅ ከመባሉ በፊት ያልቀረበና ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ የፍርድ ባለዕዳው የሀራጅ ሽያጩ እንዲፈርስ ያቀረቡት ማመልከቻ ተቀባይነት የለውም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ ተፈጽሟል የሚላቸውን ስህተቶችና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ አለበት የሚሉትን የሕግ ስህተት በመግለጽ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ የሚነቀፍበት ምክንያት እና ወደ ይግባኙ የሚያስገባ ምክንያት አለመኖሩን በመግለጽ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

አመልካች ይህንን በመቃወም ለሰበር ባቀረቡት አቤቱታ፡-

- በዕለቱ ሀራጅ የተባለውን ድርጅት ለመግዛት ስድስት ሰዎች መጥተው የነበረ መሆኑንና ባልታወቀ ምክንያት ሌሎች ሰዎች ከሄዱ በኋላ አንድ ተጫራች ብቻ ነው የቀረበው ተብሎ መሸጡን አስመልክቶ ያነሳሁትን ተቃውሞ በተጠሪው በኩል ሣይካድ፣ ፍርድ ቤቱ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 428 ንዑስ አንቀጽ 5 አላግባብ በመጥቀስና በመተርጎም የጨረታው አሸናፊ የሆነው ሰው ብቻውን መጫረቱ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ
- ድርጅቱን የገዛው ግለሰብ፤ በግልጽ ጨረታና በሀራጅ ደንብ፣ መሠረት ሣይሆን ከሀራጅ ባዩ ጋራ በዋጋ በመደራደር፣ የገዛው መሆኑን የሀራጀ ባዩ ሪፖርት እና ማብራከሪያ እያስረዳ ከፍተኛው

ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ሥነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 422 ንዑስ አንቀጽ 3 አላግባብ በመጥቀስና በመተርጎም ሽያጭ ያከናወነው የግልጽ ጨረታና የሀራጅ ደንብን ተከትሎ ነው በማለት የስጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ ስህተት ያለበት በመሆኑ

- ንብረቱን የገዛው ሰው የፍርድ ባለመብት የሆነው የንግድ ድርጅት ባለአክስዮን ድርሻና ባለቤት የሆኑት የአንደኛው ወንድም ነው የሚለውን መቃወሚያ በማስረጃ አልተረጋገጠም፣ ቢረጋገጥም እንኳን፣ ጨረታውን ለማፍረስ በቂ ምክንያት አይደለም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ የተሣሣተ በመሆኑና በአጠቃላይ የጨረታው ሂደት የፍርድ ባለመብቱን መብት በሚጎዳ መንገድ ያልተከናወነ በመሆኑ፣ የሀራጅ ሽያጩ ይፀናል በማለት የሰጠው ትዕዛዝና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ወደ ጉዳይ የሚያስገባ በቂ ምክንያት የለም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሰበር ሰሚው ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ የተፈፀመው ስህተት እንዲታረም ትዕዛዝ ይሰጥልኝ በማለት በጽሁፍ አመልክተዋል፡፡

ሰበር ሰሚው ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማጣራት ካስቀረበ በኋላ፣ በጭብጡ ዙሪያ አመልካችና ተጠሪው የካቲት 29 ቀን 1998 ዓ.ም. ያደረጉትን የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡ በተደረገው የቃል ክርክር አመልካቾች በአብዛኛው በሰበር አቤቱታቸው የገለፁትን ነጥቦች በማብራራት ሀራጅ የተባለው ንብረት በዝቅተኛ ግምት ሀራጅ ጨረታ መቅረቡ፣ ንብረቱን የገዛው ሰው በሀራጅ ደንብና ሥርዓት መሠረት ሣይሆን በድርድር ንብረቱን መግዛቱ፣ በዕለቱ ስድስት ሰዎች ንብረቱን ለመግዛት የቀረቡ መሆኑና በማያውቁት ምክንያት ከግቢው ወጥተው ሲሄዱ እንዳገኟቸው በማብራራት የከፍተኛው ፍርድ ቤት እነዚህን መሠረታዊ ስህተቶች ለመሠራታቸው በቂ ማስረጃ እያለ የሀራጅ ሽያጩ



ይፀናል በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የተጠሪው ጠበቃ በበኩላቸው ፔትራም ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ድርጅት አመልካች የፍርድ ባለዕዳ መሆናቸውን በ1993 ዓ.ም. በፍርድ ያስወስነ ቢሆንም ለሰባት ዓመት ያህል የፍርድ ባለዕዳው በተለያየ ፍርድ ቤቶች ተንኮል ያለበት ክርክር ውስጥ በመግባትና ንብረቱን በማሣገድ ፍርዱን ማስፈፀም እንዳልቻሉ የሀራጅ ሽያጩ በተከናወነበት ቀን እኔ በቦታው ያልነበርኩ ሲሆን፣ ከደንበኞቼ ለመረዳት እንደቻልኩት፣ በወቅቱ ስድስት ሰዎች በጨረታው ለማሣተፍ መጥተው የነበረ መሆኑንና ሰዎቹም መታወቂያቸውን አስይዘው እንደነበር ነገር ግን አመልካቹ ይህ ቤት ሌላ ዕዳ አለበት ብትገዙት ሌላ ጣጣ ትገባላችሁ ብለው ስላስፈራሯቸው ከገዢው በስተቀር ሌሎቹ ጥለው የሄዱ መሆኑንና የጨረታው አሸናፊ በመነሻ ዋጋው ንብረቱን ለመግዛት እየቻለ ሀራጅ ባዩ ዋጋ ጨምር ሲለው ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ የጨመረ መሆኑንና ይህም የአመልካችን መብት የሚያስጠብቅ እንጂ የሚጎዳ ባለመሆኑ፣ በአጠቃላይ የሀራጅ ሽያጩን የሚያፈርስ በቂ ምክንያት የለም በማለት ፍርድ አስፈፃሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ እንዲደርግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የቀረበው የመከላከያ ሀሳብ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የፍርድ ባለዕዳው /አመልካቹ/ ንብረት ሀራጅ በሚባልበት ወቅት ስድስት ሰዎች በቦታው ተገኝተው የነበረ መሆኑንና በመጨረሻ አንደኛው ብቻ ቀርቶ ንብረቱን የገዛ መሆኑን ሁለቱም ተከራካሪዎች አልተካካዱም፡፡ አመልካቹ የመጡት ገዢዎች ምክንያቱን በማላውቀው ሁኔታ ከግቢ ሲወጡ አገኘኋቸው ያለ ሲሆን በተጠሪዎቹ በኩል የመጡት ገዢዎች የሄዱት አመልካቹ ይህ

ቤት ሌላ ዕዳ አለበት ብትገዙት ጣጣ ውስጥ ትገባላችሁ በማለቱና ሁከት በመፍጠሩ ነው በማለት ይከራከራሉ። ቀርበው የነበሩት ስድስት ሰዎች ውስጥ በጨረታ አሸናፊ የሆነውና ብቸኛ ተጫራች ነው የተባለው ሰው ሲቀር ቀሪዎቹ ጨረታውን በአግባቡ ለመከታተል የማያመች ሁኔታ በመፈጠሩ ወይም በመኖሩ ምክንያት ጥለው እንደሄዱ ግራ ቀኙ ተማምነዋል። እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አንድን ንብረት በግለጽ ጨረታ ለመግዛት የተሰበሰቡ ሰዎች በተከራካሪዎቹ ወይም ከተጫራቾቹ አንደኛው በፈጠረው ሁከት ወይም በሌላ ሶስተኛ ሰው ተግባር ምክንያት ጨረታውን በመተው ሲበተኑ አንደኛው ሰው ቢቀርና ሀራጅ ባዩ ለቀረው ሰው ንብረቱን ቢሸጥ ጨረታው በአግባቡ ተፈጽሟል ማለት ይቻላል ወይ? የሚለው ነው።

አንድ ንብረት ሀራጅ በሚባልበት ጊዜ በጨረታው ለሚሳተፍ ጨረታውን ለሚያስፈጽሙና ሌሎች ሰዎች የሀራጅ ሂደቱን በተረጋጋ ሁኔታ የሚከታተሉበት፣ ሰላማዊ ሁኔታ መኖሩ የግድ አስፈላጊ ነው። በያዝነው ጉዳይ ጥፋቱ በማንኛው ተከራካሪ በኩል እንደተፈፀመ ለማየት ባይቻልም በሀራጅ ጨረታውን ለመሣተፍ ከመጡት ስድስት ሰዎች ውስጥ ከአንደኛው በስተቀር ሌሎቹ በወቅቱ ለመወዳደር የሚያስችላቸው ምቹና የተረጋጋ ሁኔታ ባለመኖሩ ጨረታውን ትተው ለመሄድ እንደተገደዱ በመዝገቡ ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ያሣያል።

ስለሆነም አንድን ንብረት በሀራጅ ለመግዛት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆነ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ከመጡና በጨረታውም ለመሣተፍ እንደመጡ ከገለጹ በኋላ ከተከራካሪዎቹ በአንደኛው ወይም በሌላ ሶስተኛ ወገን ወይም በአጋጣሚ በተፈጠረ አደጋና ክስተት ተደናግጠው ሌሎቹ ጥለው ሲሄዱ አንደኛው ብቻ ቢቀር ፍርድ አስፈፃሚው ንብረቱን ለመጫረት የቀረበው አንድ ተጫራች ብቻ እንደሆነ በመቁጠር ጨረታውን ማከናወኑ የፍርድ አስፈፃሚው በአሻሻጡ ሥርዓት ላይ



ግዙፍ የሆነ ስህተት እንዳልፈፀመ ተደርጎ መታየት የለበትም። ምክንያቱም የሀራጅ ሽያጭ በሂደቱ ለመካፈል የሚፈልጉ ሁሉም ተሣታፊዎች ለደህንነታቸው የሚያሠጋቸውና የሚያስፈራቸው ሁኔታ ሣይኖር በተረጋጋ ሁኔታ በሀራጁ ተሳትፈውና ተወዳድረው ከፍተኛ ዋጋ ያቀረበው አሸናፊ የሚሆንበት የሽያጭ ሥርዓት በመሆኑ ነው። ስለዚህ ሀራጅ በሚባልበት ጊዜ በተፈጠረው ሁከት ሣይደናገጥ ወደ ኋላ የቀረው ተጫራች እንደ ብቸኛ ተጫራች በመውሰድ በፍርድ አስፈፃሚው በኩል ሽያጩ መከናወኑ በንብረቱ አሻሻጥ ላይ የሚታየው የመጀመሪያው ግዙፍ ጉድለት በመሆኑና ይህም በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 455 መሠረት ሽያጩን ለማፍረስ የሚያስችሉት መሠረታዊ ምክንያቶች መሆኑ "… በአሻሻጡ ሥርዓት ላይ ግዙፍ የሆነ ጉድለት ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ተግባር ከተፈፀመና …" ይህም በአመልካች ላይ መሠረታዊ ጉዳት የሚያስከትል ከሆነ ሀራጁን ለማፍረስ የሚያስችል በቂ ምክንያት እንደሆነ ሕጉ ካስቀመጣቸው ድንጋጌዎች ለመረዳት እየተቻለ፣

በያዝነው ጉዳይ ንብረቱን ለመግዛት ስድስት ሰዎች ቀርበው በጨረታው ለመወዳደር እንደሚፈልጉ ገልፀውና መታወቂያቸውን ካስያዙ በኋላ በዕለቱ በተፈጠረው ምቹ ያልሆነ ሁኔታና ሁከት ሌሎቹ ሲሄዱ ወደ ኋላ የቀረውን ተጫራች እንደ ብቸኛ ተጫራች በመቁጠር የፍርድ አስፈፃሚው ሽያጭ ማከናወኑ ምንም ዓይነት ስህተት እንደሌለበት በመቁጠር ከፍተኛው ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 428 ንዑስ አንቀጽ 1 በመጥቀስ የሰጠው ትዕዛዝ የክርክሩን መሠረታዊ ጭብጥ የሳተና ከላይ የተነሱትን መሠረታዊ ነጥቦች ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል። በሁለተኛ ደረጃ አመልካቹ ንብረቱ የተሸጠው በሀራጅ ሽያጭ መሠረት አይደለም በማለት የተከራከረ በመሆኑና ከፍተኛው ፍርድ ቤትም ሆነ ተጠሪው በድርድር በሚመስል ሁኔታ ዋጋው የተወሰነ መሆኑን የሚያመላክት አገላለጽ የተጠቀሙ

በመሆኑ ንብረቱ የተሸጠው በሀራጅ ሽያጭ ሥርዓት መሠረት ነው ወይስ በድርድር የሚለው ነጥብ መታየት ይኖርበታል፡፡

አንድ ንብረት በሀራጅ ሲሸጥ፣ የዋጋው ከዜሮ ሲነሣ ወይም ንብረቱ የሚሸጥበት ዝቅተኛ ዋጋ ተገምቶ ሊካሄድ እንደሚችል ይታወቃል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ንብረቱ የሚሸጥበት ዝቅተኛ ዋጋ ተገምቶ ቀርቧል፡፡ ንብረቱን በጨረታ አሸናፊ ሆኗል የተባለው ሰው መጀመሪያ የሰጠው ዋጋ ንብረቱን በግምቱ ማለትም በብር 438,946 /አራት መቶ ሰላሣ ስምንት ሺ ዘጠኝ መቶ አርባ ስድስት ብር/ ለመግዛት ነበር፡፡ ይህ ገዢ ያቀረቡት የመግዣ ዋጋ ፣ ሌሎች ተጫራቾች ቢኖሩ የተሻለ ዋጋ በማቅረብ ለማፍረስና በመጨረሻም ከፍተኛ ዋጋ ያቀረበው የጨረታው አሸናፊ ሆኖ ግቡን የሚፈጽምበት ሥርዓት ትክክለኛው የሀራጅ የሽያጭ ሥርዓት እንደሆነ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1688 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ንብረቱን የገዛው ሰው ብቸኛ ተጫራች ነው፡፡ ይህ ሰው ንብረቱን በመነሻ ዋጋ ለመግዛት ዋጋ ሲያቀርብ ሀራጅ ባዩ በዚህ ዋጋ ከተስማማ ሽያጩ መፈፀሙን ማሣወቅ በተጫራቹ የቀረበው ዋጋ በቂ አይደለም ብሎ ካሰበ ደግሞ ሂደቱን በማቆም ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት ማድረግ ሲገባው የቀረበውን ብቸኛ ተጫራች የተባለውን ሰው ንብረቱን ለመግዛት ከቀረበው ዋጋ በላይ ሀራጅ ባዩ ይህንን ያሕል ጨምረህ ውሰድ በማለት ሽያጭ መፈፀሙ ከገዢው ጋር ንብረቱ የተሸጠበትን ዋጋ በድርድር የወሰነው መሆኑን የሚያሣይ ሆኖ እያለ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይህንን እንደ ትክክለኛ የሀራጅ ሽያጭ መቀበሉ ተገቢ ባለመሆኑና ክርክር የተነሳበት ንብረት የሀራጅ ሽያጭ ሥርዓትን ተከትሎ ሣይሆን ያለ ፍርድ ቤቱ ልዩ ፈቃድ ሀራጅ ባዩ ከገዢው ጋር ባደረገው የዋጋ ድርድር የተሸጠ መሆኑን ስለሚያሣይ ይህም የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 422 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን የሚጥስ



መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት አፈፃፀም በመሆኑ በአጠቃላይ የሀራጅ ሽያጩ በሚፈፀምበት ጊዜ ከላይ የተገለጹት ሁለት መሠረታዊ ግዙፍ ጉድለቶች በመሆናቸውና እነዚህም ጉድለቶች በመልካቹ ላይ ከፍ ያለ ጉዳት የሚያደርሱ መሆናቸው የከፍተኛው ፍርድ ቤት በፍርድ አስፈፃሚው የተሠራ መሠረታዊና በአመልካች ላይ ጉዳት የሚያስከትል ጉድለት የለም በማለት የሰጠው ትዕዛዝና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ወደ ይግባኙ የሚያስገባ በቂ ምክንያት የለም በማለት ይግባኙ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት እንዲሰረዝ የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. ከዚህ በፊት የተደረገው የሀራጅ ሽያጭ መሠረታዊ ግድፈት ያለበት በመሆኑ በዚህ ፍርድ ቤት የተሰረዘ መሆኑን አውቆ ድርጅቱ እንደገና በሀራጅ እንዲሸጥ በማድረግ አፈፃፀሙን እንዲያስቀጥል ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የውሣኔው ግልባጭ ከመሸኛ ጋር ይላክ፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፣ መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁጥር 22930

ሚያዝያ 30 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መሰሠ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ታድሬ አባተ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዓለም ገ/የሱስ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ መዝገብ በአፈፃፀም ላይ የተነሣን ክርክር የተመለከተ ሲሆን የአፈፃፀም ክሱ የተመሠረተው በአ/ብ/ክ/መ የሠሜን ጎንደር ከፍተኛ ፍ/ቤት በአሁን ተጠሪ ነበር፡፡ የአሁን ተጠሪ ክሣቸውን ያቀረቡት አሁን በክርክሩ ውስጥ በሌሉት በአሁን አመልካች የቀድሞ ባለቤት በነበሩት በመሪጌታ መዘምር ዕፁብ ላይ ነው፡፡ የአፈፃፀም ክሱም ይዘት ተከሣሹ መሪጌታ መዘምር ዕፁብ በተጠሪዋ ላይ ላደረሱት የአካል ጉዳት የሞራል ካሣ 1000 ብር የተወሰነልኝ በመሆኑ ተከሣሹ ይህን ውሣኔ በፍርድ ተገደው ይፈጽሙ የሚል ነው፡፡ የሠሜን ጎንደር ዞን ከ/ፍ/ቤትም የአፈፃፀም ተከሣሽ ንብረት ነው በተባለው ቤት ላይ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ትዕዛዝ የሠጠ ሲሆን በዚህ ወቅት አመልካች ተቃዋሚ ሆነው በመቅረብ ይህንን ቤት ከባለቤቴ ከመሪጌታ መዘምር ዕፁብ ጋር በፍቺ ተለያይተን በንብረት ክፍፍሉ ወቅት የእኔ ድርሻ የሆነ በመሆኑ ለአፈፃፀም ሊውል አይገባም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የሠሜን ጎንደር ዞን ከ/ፍ/ቤትም ታህሳስ 12/98 ዓ.ም. በሠጠው ትዕዛዝ "ጣልቃ ገብና የአፈፃፀም ተከሣሽ በመጋቢት 18/95 ዓ.ም ጋብቻቸውን አፍርሰዋል፣ ይሁን እንጂ ውሣኔው የተወሰነው በሠኔ 25/96 ዓ.ም ነው፡፡



በዚህ መሠረት እዳው እንደ ጋራ እዳ ስለሚገመት አፈፃፀሙ ጣልቃ ገብ ንብረቴ ነው በምትለው ቤት ይቀጥል" ብሏል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ የቀረበበት የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሠበር አቤቱታውም የቀረበው የሠሜን ጎንደር ዞ/ከ/ፍ/ቤት አፈፃፀሙ በቤቱ ላይ ይቀጥል ሲል የሠጠው ትዕዛዝም ሆነ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይህን ትዕዛዝ ማጽናቱ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነው በሚል ነው፡፡ አመልካች ጥር 29/98 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሠበር አቤቱታ ይዘት ሲጠቃለል፣ ከውሣኔ በፊትም ይሁን በኋላ ስንለያይ በፍ/ቤት የፍቺ ውል ቀርቦ ንብረታችንን ተካፍለን ካደርን በኋላ ይህ በግሉ የተወሰነበት እዳ በግሉ ተካፍሉ ባደረው ንብረት ላይ ውሣኔ መስጠት እየተቻለ በግል በእኔ ንብረት ላይ ትዕዛዝ መስጠቱ አላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ የሠበር ችሎትም የአመልካችን አቤቱታ ተመልክቶ፣ ብር 1000 እንዲከፍል የተፈረደበት ባልየው ሌላ የግል ንብረት ወይም በክፍፍል ያገኘው ንብረት አለ እየተባለ ሚስት በክፍፍል በደረሣት ወይም በግል ንብረቷ ላይ ዕዳው መፈፀም አለበት በሚል የተወሠነው በህጉ አግባብ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት መዝገቡን ለሠበር ሊቀርብ ይገባል ሲል በየካቲት 24/98 ዓ.ም ትዕዛዝ ሠጥቷል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ መልሣቸውን በጽሁፍ ይዘው ያልቀረቡ ከመሆኑ ባሻገር የግራ ቀኙን ክርክር ለመስማት በተቀጠረበት ቀን ባለመቅረባቸው ክርክር ለማቅረብ እንዳልፈለጉ በመቁጠር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በዚህ መዝገብ በቀረበው ጉዳይ አመልካች ከባለቤታቸው ጋር ፍቺ የፈፀሙት በመጋቢት ወር 1995 ዓ.ም ለመሆኑ በሠበር ማመልከቻቸው እና ለችሎቱም በቃል ከማስረዳታቸው ባሻገር የሠሜን ጎንደር ዞን ከ/ፍ/ቤትም አረጋግጦ የመዘገበው ስለመሆኑ ከመዝገቡ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአመልካቿ ባለቤት በሠው ላይ የአካል ጉዳት በማድረሣቸው የሞራል ካሣ ብር 1000 እንዲከፍሉ የተወሰነባቸው ሠኔ 25/1996 ዓ.ም ለመሆኑ መዝገቡ ያመለክታል፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪዋ በሥር ፍ/ቤቶች ክደው

መከራከራቸውን የሚያመለክት ነገር የለም፣ በዚህ ችሎትም ቀርበው አልተከራከሩም። ይህ በሆነበት ሁኔታ ፍቺ ተፈጽሞ የንብረት ክፍፍል ከተፈፀመ በኋላ አንደኛው ተጋቢ ላመጣው እዳ ሌላኛው ተጠያቂ የሚሆንበት የህግ አግባብ የለም። ይህ በእንዲህ እያለ የሞራል ካሣ የተወሰነው በጋብቻ ውስጥ አይደለም እንጂ በጋብቻ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ ነው ቢባል እንኳ ጋብቻው በፍቺ ከፈረሠ በኋላ ለሚጠየቅ እዳ፣ እዳው የሚመለከተው አንደኛውን ተጋቢ በሆነ ጊዜ የእዳው ክፍያ ሊጠየቅ የሚችለው ባለእዳ ከሆነው ተጋቢ ብቻ እንደሚሆን የአማራ ክልል የቤተሰብ ህግ አ/ቁ/79/95 በአንቀጽ 104/2/ ላይ በግልጽ ተደንግጓል። በተያዘው ጉዳይ ደግሞ የተጠየቀው እዳ የአመልካቹ እና የባለቤታቸው የጋራ እዳ ወይም ደግሞ ለጋራ ጥቅማቸው ሲባል የመጣ እዳ ሣይሆን ከአመልካቿ ባለቤት የግል ተግባር የመነጨ እዳ ስለሆኑ መገንዘብ አያዳግትም። ስለሆነም ይህ እዳ አፈፃፀም የተጠየቀበት ከፍቺ በኋላ እስከሆነ ድረስ የአመልካቿ ድርሻ ለዚህ እዳ ማስፈፀሚያ የሚሆንበት ምክንያት አልተገኘም።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 07974 በ8/5/98 የሠጠው ትዕዛዝ ተሽሯል። ይፃፍ።
2. የሠሜን ጎንደር ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 01772 በ12/4/98 የሠጠው ትዕዛዝ ተሽሯል። ይፃፍ።
3. የአመልካቿ ንብረት በቀድሞ ባለቤቷ ላይ ለተፈረደው የሞራል ካሣ ብር 1000 ክፍያ ማስፈፀሚያ ሊውል አይገባም ብለን ወስነናል።
4. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ። መዝገቡ ተዘግቷል። ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 23733

ህዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች መንበረፀሐይ ታደሠ
ፍስሐ ወርቅነህ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- 1. ሃፍቶም ገ/አብዝጊ ቀረቡ
2. ተኪኢን ገ/አብዝጊ

ተጠሪዎች፡- 1. ሙሉ ካሣ
2. ባይራይ አረጋይ
3. አዜብ አረጋይ - } ቀረቡ
4. አታክልቲ አረጋይ

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ መዝገብ የቀረበው የአፈፃፀም ክርክር ነው፡፡ አመልካቾች በወረዳ ፍ/ቤት ክርክር የተነሣበትን ቤት በውሣኔ መሠረት ለመከፋፈል የአፈፃፀም ክስ አቀረቡ፡፡ ፍ/ቤቱም በባለሙያ በተገመተው መሠረት አመልካቾች ድርሻቸውን እንዲቀበሉ ሲጠየቁ ፈቃደኞች አልሆኑም በማለት አፈፃፀም መዝገቡን ዘግቴትል፡፡ የከፍተኛ ፍ/ቤቱም ይህ የአፈፃፀም ትዕዛዝ በግባቡ የተሠጠ ነው ሲል የይግባኝ ቅሬታውን ሰርዞታል፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትና ሠበር ችሎቱ የአመልካቾችን ቅሬታ ባለመቀበል መዝገቦቹን ዘግተዋል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ቅሬታውም ግምቱ አንሷል ፣ በግምቱ መሠረት እዳ ከፍለን ቤቱን

እንድናስቀር ጠይቀን ተቀባይነት አላገኘንም ይህ ካልሆነ ደግሞ በጨረታ ተሸጦ እኩል እንካፈላለን እንጂ መበላለጥ የለብንም የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የአፈፃፀም ትዕዛዝ የተሠጠው በውሣኔው መሠረት መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሠበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ የሠበር አቤቱታው ለተጠሪዎች ደርሶ ግራ ቀኙ የቃል ክርክር አሠምተዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው ይህ ጉዳይ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ነው፡፡ የፍርድ አፈፃፀምም በፍርድ የተገኘ መብት ውጤት እንዲሠጥ እና የፍርድ ባለመብቱ የተወሠነለትን ነገር እንዲያገኝ የሚከናወን ስርአት ነው፡፡ በመሆኑም በፍርድ አፈፃፀም ጊዜ ፍ/ቤቶች ሊያስፈፅሙ የሚገባው በተሠጠው ፍርድ መሠረት ነው፡፡ በእርግጥ ፍርዱን በሚያስፈጽምበት ጊዜ ፍርዱ ውጤት እንዲያገኝ አመቺ የሆነ የአፈፃፀም ስርአት ሊከተሉ ይገባል፡፡ ከዚህ ውጪ ግን በአፈፃፀም ወቅት የተሰጠው ፍርድ በተለየ መልኩ ውሣኔው እንዲፈጸም ሊያደርጉ የሚያስችላቸው የህግ መሠረት የላቸውም፡፡

በተያዘው ጉዳይ ላይም አመልካች የሥር ፍ/ቤቶች የሠጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ ውሣኔውን መሠረት ያላደረገ መሆኑን ተከራክረዋል፡፡ እኛ እንደተመለከትነው በዋናው ውሣኔ አሁን ክርክር የተነሳበት ቤት ወራሾች እንዲከፋፈሉት ተወስኗል፡፡ ከወረዳ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ለማየት እንደሚቻለው ቤቱን መካፈል የሚችል ከሆነ እንዲካፈሉ፣ የማይካፈል ከሆነ ግን በባለሙያ ተገምቶ ይውሠዱ የሚል ነው፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካቾች ወይም ተጠሪዎች ግምቱን ከፍለው ቤቱን እንዲያስቀሩ የተሠጠ ውሣኔ የለም፡፡ በመሆኑም ግራ ቀኙ ከተስማሙ ቤቱን እንዲካፈሉ መካፈል የማይችሉ ከሆነ ግን አንደኛው ወገን ግምቱን ከፍሎ እንዲያስቀር መብቱ የተጠበቀለት ባለመሆኑ ያለው አማራጭ ቤቱ



ተገምቶ በሃራጅ ተሸጦ የሽያጩን ገንዘብ በድርሻቸው መጠን መከፋፈል ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ተጠሪዎች ግምቱን ከፍለው ቤቱን እንዲያስቀሩ መብታቸው ተጠብቆ የተሠጠ ውሣኔ ሣይኖር ለአመልካቾች ግምት ተከፍሏቸው ቤቱን ተጠሪዎች እንዲያስቀሩ የሠጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ ስህተት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የትግራይ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ችሎት በመ/ቁ 12350 በ08/06/98 የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ የህግ ስህተት የለውም በማለት የሠጠው ውሣኔ እና የሥር ፍ/ቤቶች የሠጡት የአፈፃፀም ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ክርክር የተነሣበትን ቤት ግራ ቀኙ ከተስማሙና ከተቻለ በድርሻቸው መጠን እንዲከፋፈሉ፣ በዚህ የማይስማሙ ወይም መካፈል የማይቻል ከሆነ ቤቱ ተገምቶ በሃራጅ ተሽጦ ከሽያጩ ገንዘብ ላይ ግራ ቀኙ በድርሻቸው መጠን እንዲከፋፈሉ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ በመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 23989

ታህሣሥ 17 ቀን 2000

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ ደስታ ሠርዳ

**ተጠሪ፡-** የመተከል ዞን ፍትህ መምሪያ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ክርክር የተጀመረው በስር የአፈፃፀም ተከሣሽ በነበረው አቶ አምሣሉ ኤቢሣ ላይ ያስፈረደበትን ገንዘብ ለማስመለስ የመተከል ዞን ፍትህ መምሪያ የአፈ/መ/ቁ. 01378 አስከፍቶ የዚሁ የፍ/ባለእዳ የሆኑትን ሁለት የመኖሪያ ቤቶችና አንድ መጋዘን በመሐንዲስ አስገምቶ ለመተከል ዞን ከ/ፍ/ቤት በማቅረቡ፣ የአሁኑ አመልካች ከመኖሪያ ቤቶቹ መካከል በኤበች በር የሚገኘውን ግምቱ 6,340 ብር የሆነውን ቤት ቀድሞ ለእኔ በሽያጭ ስለተላለፈልኝ አፈፃፀሙ በቤቱ ላይ ሊቀጥል አይገባም ሲሉ በመቃወም በመቅረባቸው ነው፡፡ ከማመልከቻውም ጋር ቤቱን ከአፈ/ተከሣሹ ላይ ለመግዛታቸው ያስረዱልኛል ያሏቸውን ለቤቱ ሽያጭ ለወንበራ ወረዳ ማዘጋጃ ቤት በ17/2/97 በካርኒ ንምራ ቁጥር 84777 የተከፈለ ብር 140 እና የመተከል ዞን ፍትህ መምሪያ ቀርቦ የፀደቀ የቤት ሽያጭ ውል አያይዘዋል፡፡ የዞኑ ከ/ፍ/ቤትም የአፈ/ከሣሹ ንብረት ይጣራ ብሎ ከማመልከቱ አስቀድሞ ቤቱ የተሸጠ በመሆኑ፣ለአፈፃፀም የተያዘው በኤበች በር አካባቢ የሚገኘው መኖሪያ ቤት የተቃዋሚው ሕጋዊ ንብረት በመሆኑ ሙሉ ለሙሉ ይለቀቅለት ሲል ወስኗል፡፡



የአሁኑ ተጠሪም በፍ/ቤቱ ውሣኔ ቅር በመሰኘቱ ቅሬታውን ለቤ/ጉ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ተዘዋዋሪ ችሎት በይግባኝ አቅርቧል፡፡ የይግባኙም ፍሬ ሀሣብ በአጭሩ፣ በተጠቀሰው ንምራ ቁጥር የተደረገው ክፍያ የንግድ ትርፍ ግብርና የቴምብር ቀረጥ የተፈፀመበት እንጂ የስም ማዛወር የተደረገበት አይደለም፣ ውሉ በዞኑ ፍትህ መምሪያ ቢፀድቅም መዕደቁ የስም ማዛወር ተግባር አይደለም፣ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1185 እና 2878 መሠረት የቋሚ ንብረት ሽያጭ ውል ፀድቆ ስም ዝውውር አልተፈፀመም የሚል ነው በዚሁ የይግባኝ መዝገብ ውስጥ የስር አፈፃፀም ተከሣሽ 1ኛ መ/ሰጭ የነበረ ሲሆን በመልሱም የሽያጭ ውሉን በተዋዋይነት መፈረሙንና ውሉም በፍ/መምሪያው ፀድቆ መመዝገቡን ገልፆ የስም ዝውውሩን በተመለከተ በተለያዩ ምክንያቶች በቶሎ አለመፈፀሙን አስረድቷል፡፡ በይግባኝ መዝገቡ 2ኛ መ/ሰጭ የነበረው የአሁን አመልካች በበኩሉ ቤቱን በሕጋዊ መንገድ ለመግዛቱ በበቂ ማስረጃ ያስረዳሁ በመሆኑ ይግባኙ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል መልስ ሰጥቷል፡፡

የክልሉም ወ/ፍ/ቤት ለውሣኔው መንደርደሪያ ይሆነው ዘንድ፡ ∀የሽያጭ ውል ሰነድ መቅረቡ፣ይህም ውል በፍ/መምሪያው የፀደቀ መሆኑ እና የሽያጭ ታክስ የተከፈለበት የሠነድ ማስረጃዎች መቅረባቸው ቤቱ ለ2ኛ መ/ሰጪ ተሸጧል ወይም ተዘዋውሯል ማለት እንችላለን ወይ?∀ የሚል ጭብጥ ይዞ መዝገቡን መርምሯል፡፡ በውሣኔውም አንድ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሀበትነት በውል ወይም በኑዛዜ ለማስተላለፍ ምዝገባ ወሣኝ መሆኑን፣ ንብረቱ የሚተላለፈው በሽያጭ ከሆነም ሽያጩ ተከናውኖ በሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ርስት መመዝገቢያ ደብተር ተመዝግቦ ስሙ ተዘዋውሮ የምስክር ወረቀት ሊሰጠው እንደሚገባ፣ ይህም ሲሆን ሦስተኛ ወገን መብታቸውን በመንካቱ ንብረቱ አላግባብ የሚተላለፍ ከሆነ ተቃውሞ በማንሣት መከራከር እንደሚችሉ የፍ/ብ/ቁ. 1195(1)፣ 1185 እና 2878 ጠቅሶ አትቷል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ጉዳይ የሽያጭ ውሉ በሕግ

የመመዝገብና የማዛወር ስልጣን በተሰጠው አካል ስመርስቱ ወደ 2ኛ መ/ሰጪ ባለመዛወሩ፣ ይህ ውል በሦስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም በማለት የዞኑ ከ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር አፈፃፀሙ በቤቱ ላይ ሊቀጥል ይገባል ሲል ወስኗል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው የክልሉ ወ/ፍ/ቤት በ30/5/98 ዓ.ም በመ/ቁ/ 00891 የሰጠውን ውሣኔ ለማስለወጥ የቀረበ ነው። አመልካች ለዚህ ችሎት አቤት ያሉት ቤቱን በመተከል ዞን ለፍትህ መምሪያ በፀደቀ ሕጋዊ የሽያጭ ውል መግዛቱ በማንኛውም ወገን ያልተስተባበለ ሆኖ ሣለ፣ስመርስቱ በአመልካች ስም ባለመዛወሩ በቻ በቤቱ ላይ መብት የለህም ተብዬ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው በማለት ነው። ተጠሪም ለመልሣቸው የአንድ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለቤት መሆን የሚቻለው በመግዛት ብቻ ሣይሆን በፍ/ብ/ሕጉና በሌሎች የማዘጋጃ ቤት ደንቦች መሠረት በርስት መዝገብ ተመዝገቦ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት በመያዝ ሊሆን ይገባል፤ ስለዚህም አመልካች በቤቱ ላይ መብት ስለሌላቸው አቤቱታቸው ውድቅ ሊደረግ ይገባል ሲሉ መልስ ሰጥተዋል።አመልካችም በጽሁፍ የመልስ መልሣቸውን አቅርበው ቅሬታቸውን አጠናክረዋል። ይህም ችሎት መዝገቡን በጥሞና መርምሯል። እንደተመረመረውም በዚህ ጉዳይ መፍትሔ የሚሻው አብይ ጭብጥ ክርክር የተነሣበትን ቤት አመልካች የገዙት መሆኑና ውሉም ተመዝግቦና በቤቱ ማህደር ተያይዞ እያለ፣ የባለቤትነት ስሙ በአመልካች ባለመዛወሩ ብቻ በሦስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም በሚል አፈፃፀሙ ቤቱ ላይ እንዲቀጥል መደረጉ አግባብ ነው ወይ?∀ የሚለው ነው።

የቤ/ጉ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ለውሣኔው መሠረት ያደረገው የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2878 የማይንቀሣቀሱ ንብረቶች ሽያጭ ውል ውሎችን ለማፅደቅ ስልጣን በተሰጠው አካል ከፀደቀ በኂላ ንብረቱ በሚገኝበት ስፍራ በሚገኝ ማዘጋጃ ቤት ወይም የመሬት አስተዳደር መስሪያ ቤት ርስት መዝገብ ተመዝግቦ



ሲገኝ ሦስተኛ ወገኖች በንብረቱ ላይ ለሚጠይቁት መብት መቃወሚያ ሊሆን እንደሚችል ደንግጓል። በዚህ በተያዘው ጉዳይ፣ በአቶ ደስታ ሠርዳ እና በአቶ አምሣሉ ኤቢሣ መካከል በጥቅምት 17 ቀን 1997 ዓ.ም የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል በኀዳር 1 ቀን 1997 ዓ.ም በመተከል ዞን ፍ/መምሪያ የፀደቀ ሲሆን የፍትህ መምሪያው የውሉን መጽደቅ አረጋግጦ ለወንበራ ወረዳ መዘጋጃ ቤት የስም ዝውውሩን እንዲፈጽምላቸው በኀዳር 1 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ መጠየቁን በዚሁም መሠረት የወረዳው ማዘጋጃ ቤት የቤት ሽያጭ ውሉን ከቤቱ ማኀደር ጋር ማያያዙ ታውቋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ሻጩ በመታሠሩ እና በማዘጋጃ ቤቱ የአሠራር ችግር ምክንያት ስመ ንብረቱ በአመልካች ስም ሊዘዋወር አልቻለም። በመሠረቱ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2878 የሽያጭ ውሉ በ3ኛ ወገን ላይ ውጤት እንዲኖረው በተዋዋዮቹ ላይ ውላቸውን በመዝገቡ እንዲፃፍ ከማድረግ የዘለለ ግዴታ አይጥልባቸውም። ተዋዋዮች በሕግ በተጣለባቸው ግዴታ መሠረት ውሉን በሕግ አግባብ ሥልጣን በተሰጠው አካል ዘንድ ፈጽመው እንዲመዘገብ ካደረጉ በኂላ ቀሪ የሚሆነውን የስም ማዛወር ተግባር ሊፈጽም የሚችለው የአስተዳደር መ/ቤቱ እንጂ ተዋዋዮች ራሣቸው ሊሆኑ አይችሉም። በመሆኑም የስም ማዛወሩን ተግባር መ/ቤቱ አልፈፀመም በሚል ተዋዋች ውሉን ለ3ኛ ወገን መቃወሚያ ሊያደርጉት አይችሉም መባሉ ተገቢ አይደለም፣ ሕጉም አይደግፈውም።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የቤ/ጉም/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በጥር 30 ቀን 1998 ዓ.ም በመ/ቁ. 00791 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል።

2/ በቤ/ጉ/ብ/ክ/መ/የመተከል ዞን ከ/ፍ/ቤት በጥቅምት 15 ቀን 1998 ዓ.ም በመ/ቁ/ 01378 የሰጠውን ውሣኔ አጽንተነዋል።

3/ አፈፃፀሙ አመልካች በገዛው ቤት ላይ ሊቀጥል አይገባም ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 25031

ታህሳስ 1 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ወ/ሮ አልታየወርቅ ኃ/ማርያም - ጠበቃ አርአያ

ተጠሪ፡- አቶ ዓለማየሁ ገለቱ - ጠበቃ ጌታቸው እንግዳ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍርድ ባለመብት የአሁን ተጠሪና በፍርድ ባለዕዳው መካከል አፈፃፀም ቀጥሎ የአሁን አአመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 መሠረት አፈጻጸሙን በመቃወም ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለተውም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ውድቅ በማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የክርክሩ ሂትም ባጭሩ ሲታይ የአሁን አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 መሠረት ባቀረቡት አቤቱታ አፈጻጸም እየቀጠለበት ያለው በወረዳ 25 ቀበሌ 01 ክልል የሚገኘውና በሟች አቶ አበራ ገብረስላሴ ስም የተመዘገበውን የቤ/ቁ. 650 የሆነውን ቤት ሰኔ 21 ቀን 1995 ዓ.ም. በተዓፈ ውል ከሟች ወራሾች ሕጋዊ ወኪል ከሆኑት ከፍርድ ባለእዳ ከወ/ሮ አልማዝ ከበደ ላይ በብር 140 ሺህ በመግዛት ቤቱን ተጨማሪ ገንዘብ በማውጣት ያሻሻልኩት ሲሆን የፍርድ ባመብት ከቤቱ ሽያጭ ገንዘብ ላይ ድርሻቸውን መጠየቅ ሲችሉ አመልካች



የገዙት ቤት በሐራጅ እንዲሸጥ ያቀረቡት ጥያቄ አግባብነት ስለሌለው የሐራጅ ሽያጩ ቀሪ እንዲሆን ይታዘዝልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትም የፍርድ ባለመብትን ክርክር ከተቀበለ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካችና የፍርድ ባለዕዳ ባደረጉት የቤት ሽያጭ ውል የፍርድ ባለመብት እስካልተስማሙ ድረስ ከሽያጩ ገንዘብ ላይ ድርሻውን እንዲቀበሉ የማይገደዱ ከመሆኑም በላይ አመልካች በሐራጅ እንዲሸጥ በተባለው ቤት ላይ ቀዳሚ መብት የሌላቸው በመሆኑ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት አፈጻጸሙ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሠጥቷል፡፡

ይግባኝ የቀረበለትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ትዕዛዝ አጽንቶታል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ለሰበር ያስቀርባል ብሎ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች ገና ከመነሻው አቤቱታቸውን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.418 መሠረት ማቅረባቸው አግባብነት ነበረውን? የሚለው ሆኖ ስለተገኘ ከዚሁ አኳያ ተመርምሯል፡፡

በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ክርክር ሲያደርጉ ለክርክሩ መነሻ ምክንያት የሆነውና በወረዳ 25 ቀበሌ 01 ክልል የሚገኘው ቁጥር 650 የሆነው ቤት የፍርድ ባለመብት በነበሩት በአሁን ተጠሪና የፍርድ ባለዕዳ በነበሩት በወ/ሮ አልማዝ ከበደ መካከል ዋናው ክርክር ሲደረግ በዚሁ ቤት ላይ ፍርድ ያረፈበት መሆኑን ግራ ቀኙ ተጠይቀው አረጋግጠዋል፡፡ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ ፍርድ አርፎበታል ከተባለ ደግሞ ይሄው ፍርድ ሊሰረዝልኝ ይገባል የሚለው ወገን አቤቱታ ማቅረብ ያለበት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት እንጂ በ418 መሠረት ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም ሁለቱ የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች የተለያየ ዓላማና ውጤት ያላቸው ስለሆነ ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 መሠረት አቤቱታ አቅራቢ በዋናው ፍርድ ላይ ምንም ዓይነት ክርክር የሌላውና አፈጻጸም እንዲቀጥል ትዕዛዝ በተሰጠበት ንብረት ላይ መብት አለኝ የሚል ወገን መሆን አለበት፡፡ በተያዘውም ጉዳይ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ የፍርድ ውሣኔ እስከተሰጠ ድረስ ከላይ በተጠቀሰው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት አመልካች ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት መቃወሚያ ማቅረብ ሲገባቸው ፍርድ ባረፈበት ንብረት ላይ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 መሠረት አቤቱታ ማቅረባቸው ከሥነ ሥርዓት ውጭ የቀረበ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ከሥነ-ሥርዓት ውጪ የቀረበውን አቤቱታ ከመነሻው መቀበል ያልነበረበት ቢሆንም ግራ ቀኙን አከራክሮ የሰጠው ትዕዛዝ ግን አቤቱታውን ባለመቀበል ስለሆነ ከውጤት አኳያ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 11745 የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 46067 ግንቦት 9 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ከውጤት አኳያ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 መሠረት አቤቱታ ለማቅረብ አይችሉም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰበር መ/ቁ. 26553

ሐምሌ 03 ቀን 1999 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ
አሰግድ ጋሻው
ሂሩት መለሠ
ተሻገር ገ/ሥላሴ
ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** የባህርዳር ልዩ ዞን ገንዘብ መምሪያ አልቀረበም

**መልስ ሰጭዎች፡-** 1. የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ ነገረፈጅ
አቶ ደመቀ ተሾመ ቀረበ
2. ሙክታር መሐመድ አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአ.ብ.ክ.መ.ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 02096 ግንቦት 30 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው፡፡

የነገሩም መነሻ አመልካች የፍርድ ባለመብት ሆኖ በግብር እዳ ምክንያት ያስወሰነውን ገንዘብ ለማስከፈል የሁለተኛ የፍርድ ባለእዳ ንብረት የሆነው በባህርዳር ከተማ ወረዳ 02 ቀበሌ 13 በካርታ ቁጥር 9333 ተመዝግቦ የሚገኘው የመኖሪያ ቤት እንዲሸጥ አፈፃፀሙን ለያዘው ለምዕ/ጎጃም መስ/ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት ጠይቋል፡፡

ይህም ፍ/ቤት ይህ በአፈፃፀም የተመራው ንብረት በእርግጥም የሁለተኛው የፍርድ ባለመብት መሆኑ ከተረጋገጠ በሐራጅ ይሸጥ ዘንድ ተገምቶ እንዲቀርብለት የባህርዳር ከተማን ማዘጋጃ ቤት አዟል፡፡ ማዘጋጃ ቤቱም ይኸው ይገመት የተባለው ንብረት በ1ኛ መልስ ሰጭ እና በኢት/ያ

ንግድ ባንክ የብድር ገንዘብ ምክንያት በዋስትና የተያዘ መሆኑን ገልፆ የግምቱን ሥራ ሠርቶ ውጤቱን አስተላልፏል፡፡

በግምቱም መነሻ ጨረታ ተደርጎ ገዢው እንደታወቀ ከሽያጩ ገንዘብ የፍርድ ባለመብቱ የጠየቀው ይከፈል፤ ተራፊው ለፍርድ ባለእዳው ይመለስለት ሲል የከፍተኛው ፍ/ቤት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይህ ትእዛዝ ከተሰጠ በኋላ የአሁን 2ኛ መልስ ሰጭ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ. 418 መሠረት ጨረታው እንዲፈርስ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታውም ፍሬ ቃል በሐራጅ ይሸጥ የተባለው ንብረት በእዳ ምክንያት በመያዣነት የተያዘ መሆኑ በማዘጋጃ ቤት መረጋገጡ ሲታወቅ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 423/2//ለ/ መሠረት በወጣው የሐራጅ ማስታወቂያ ላይ በመያዣ መያዙ መገለጽ ሲኖርበት ይኸው በሥርዓት ስላልተሟላ፤

እንዲሁም ይሸጥ የተባለው ንብረት የማይንቀሣቀስ ሀብት እንደመሆኑ መጠን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ. 426 መሠረት የጨረታ ማስታወቂያም ወጥቶ ለአንድ ወር ያህል መቆየት ሲገባው ይህ የቆይታ ጊዜ አልተጠበቀም ስለሆነም በአሻሻጥ ሥርዓቱ ላይ ጉድለት የተፈፀመበት ስለሆነ የሐራጅ ሽያጩ በዚሁ ሕግ በቁጥር 445 - 447 በተመለከተው መሠረት ሊሰረዝ፤ ሊፈርስ ይገባል የሚል ነው፡፡

አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤትም ጣልቃ ገብ የክርክሩ ተካፋይ ሆኖ መያዣ የተሰጠበትን የዕዳ መጠን ባልገለፀበት ሁኔታ በቁጥር 423(2)(ለ)መሠረት የመያዣ ልኩን ማወቅ ስለማይቻል በጨረታ ማስታወቂያው ላይ በመያዣ የተያዘ ንብረት መሆኑ አልተገለፀም የሚለው መከራከሪያ ነጥብ ተቀባይነት የለውም፡፡

የጨረታ ማስታወቂያው ማሟላት የሚገባውን አላሟላም ከመባሉ በቀር የሽያጩ ሥርዓት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ተከናውኗል፡፡ የማጭበርበር ተግባር ተፈጽሞበታል አልተባለም ስለሆነም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 445 መሠረት የተደረገውን የጨረታ ሽያጭ ማፍረስ አይቻልም እንዲሁም



የጨረታው ሽያጭ ከፀደቀ እና ባለመብቱ በዕዳ የሚፈልገውን ገንዘብ ከወሰደ እና ተራፊው ደግሞ ለባለእዳው ከተመለሰ በኋላ ሽያጩ ይፍረስ ማለቱ የሐራጅ ገዥውን መብት የሚጎዳ በመሆኑ ጨረታው እንዲሰረዝ የቀረበውን ጥያቄ አልተቀበልነውም በማለት ወስኗል፡፡

የይግባኝ አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤትም በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የሥር ፍ/ቤት አስቀድሞ በመያዣ በተያዘ ንብረት ላይ ለሌላ እዳ ማስፈፀሚያ እንዲውል ጥያቄ ሲቀርብለት በሐራጅ ማስታወቂያው ላይ በመያዣ መያዙን ሣይገልጽና ጨረታውም በጋዜጣ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ማስታወቂያው ለአንድ ወር መቆየቱን ሣያረጋግጥ ጨረታው መካሄዱን በተቃውሞ አማካኝነት እንደተረዳ ጨረታው እንዲፈርስ ማድረግ ሲገባው ይህን ሣያደርግ ሽያጩ እንዲከናወን አድርጎ ገንዘቡ ለ1ኛ መልስ ሰጭ ለአሁን አመልካች እና ለአሁኑ ሁለተኛ መልስ ሰጭ እንዲከፈል ማድረጉ ሕጉን ያልተከተለ በመሆኑ ጨረታውን አፍርሰን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 447(5) መሠረት ገንዘቡ ለገዥ ያለ ወለድ እንዲመለስ በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮ ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ይታረምልን በማለት ነው፡፡ በአቤቱታው የተጠየቀውም ዳኝነት፣

- 1ኛ/ መልስ ሰጭ በአፈፃፀም ይሸጥ የተባለው ንብረት በሌላ ዕዳ ምክንያት ለማሸጥ የሚገመት ለመሆኑ አስቀድሞ ያውቅ ነበር፡፡ በዚህም መሠረት ቀርቦ የመያዣ ልኩን ሣይገልፅ በሐራጅ ማስታወቂያው ላይ ንብረቱ በመያዣ የተያዘ መሆኑ አልተገለፀም በማለት ዘግይቶ ሊከራከርበት ስለማይቻል፡-
- የሐራጅ ማስታወቂያውን የሚቆይበትን ጊዜ አስመልክቶ የሚሸጠው ንብረት ባለበት የፍርድ ባለእዳው አንስቶ

ከሚከራከርበት በቀር 1ኛ መልስ ሰጭ ሊከራከርበት አይችልም፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁ. 423(2) (ለ) እና 426 ን መሠረት አድርጎ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ይታረምልን የሚል ነው፡፡

አመልካችና 1ኛ መልስ ሰጭ በዚህ ሰበር ችሎት ባደረጉት የቃል ክርክር በሥር ፍ/ቤት ያደረጉትን ክርክር በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የአሁን መልስ ሰጭ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 415 መሠረት በአፈፃፀም ክሱ ጣልቃ ለመግባትና ጣልቃ ገብቶም የጨረታውን ሽያጭ በማስረከብ ያቀረባቸው የመከራከሪያ ነጥቦች ሁለት ናቸው አንደኛው የአሁን አመልካች ለዕዳ ማስፈፀሚያነት እንዲውል የመራው ንብረት በ1ኛ መልስ ሰጭ የብድር ገንዘብ ምክንያት በመያዣነት የተያዘ መሆኑን እያወቀ እንዲሸጥ ማድረጉ ተገቢ አይደለም የሚል ሲሆን ሌላውና ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ የአሻሻጥ ሂደቱ የሥነ ሥርዓት ድንጋጌውን የተከተለ አይደለም የሚል ነው፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በሚመለከት ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059(1) የተመለከተን እንደሆነ ፣

1ኛ/ መልስ ሰጭ ተበዳሪ ለሆነው ለሁለተኛው መልስ ሰጭ በሰጠው የብድር ገንዘብ ምክንያት በሐራጅ ይሸጥ የተባለውን ንብረት በመያዣ የያዘው ስለመሆኑ የተካደ አይደለም፡፡ ክርክር የተነሣውም መያዣ ሰጭው ይህንኑ በመያዣ የተያዘውን ንብረት ለሌላ ሦስተኛ ወገን በማስተላለፉ ሣይሆን ሌላ ገንዘብ ጠያቂ ለዕዳ ማስፈፀሚያነት ተሸጦ እንዲከፈለው በማስያዙ ክሱን እንዲህም ያለ ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ የማይንቀሣቀስ ንብረት መያዣ መጠቀምን በሚመለከተው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059(1) መሠረት ለአመልካች በቅድሚያ የመያዣ መብት የተሰጠው በመሆኑ ሌላ ገንዘብ ጠያቂ ከሆነው ከአሁኑ አመልካች ቀድሞ በብድሩ ምክንያት የሚጠይቀውን ገንዘብ



እንዲከፈለው የመጠየቅ መብት የሚሰጠው ካልሆነ በቀር አስቀድሜ በመያዣ ይዤዋለሁ በመያዣ የያዝኩት መሆኑን አመልካች እያወቀ እንዲሸጥ መጠየቅ አልበረበትም ሲል የጠየቀው ዳኝነት ሕጋዊ መሠረት ያለው አይደለም ለምን ቢባል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3084 እንደተመለከተው ምንም እንኳ አንድ ንብረት በዕዳ ምክንያት በመያዣነት ሲያዝም ባለዕዳው የህንኑ ንብረት ለመሸጥ ለመለወጥ የሚችል በመሆኑ መያዣ የያዘው ገንዘብ ጠያቂ ያለው መብት ቢኖር ከላይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059(1) መሠረት ገንዘብ በቅድሚያ የማግኘት መብት ብቻ ነው ፡፡ ከዚህም የምንረዳው በመያዣ የተያዘ ንብረት ሊሸጥ የሚችል መሆኑን ነው፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በአንድ በኩል በአሻሻጥ ሥርዓቱ ላይ ጉድለት የተፈፀመበት ነው የሚለውን በውሣኔው መሠረት ካደረገ በኋላ በስተመጨረሻ ጨረታው ፈራሽ ነው የሽያጩ ገንዘብ ለገዢው ያለወለድ ይመለስለት በማለት መወሰኑ በውስጠ ታዋቂነት ይህንኑ ንብረት 1ኛ መልስ ሰጭ አስቀድሞ በመያዣነት ቢያዝም መሆኑ የተረጋገጠ ስለሆነ ሊሸጥ አይገባውም የሚለውን መልዕክት የያዘ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም የተደረገው የሐራጅ ሽያጭ ተሰርዟል በሚለው ጉዳዩን ቋጭቶ መቆሙ ከላይ በተመለከተው ምክንያት የሕግ ስህተት ፈጽሟል፡፡

በአሁን አመልካች ጠያቂነት ይኸው ይሸጥ የተባለው ንብረት ለዕዳ ማስከፈያ እንዲውል ማሸጥ ይቻል ዘንድ ተገምቶ እንዲቀርብ ሲታዘዝ በሌላ የብድር ገንዘብ ምክንያት በመያዣነት የተያዘ መሆኑን ገልፆ እንዲገምት የታዘዘው ማዘጋጃ ቤት አፈፃፀሙን ለያዘው ፍርድ ቤት አስታውቋል፡፡ እንደ ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 423(2)(ለ) መፈፀም ይቻል ዘንድ ፍርድ ቤቱ በእራሱ አነሣሽነት የመያዣውን ልክ ምን ያህል እንደሆነ ማዘጋጃ ቤቱን በትእዛዝ ጠይቆ መረዳት ሲቻል 1ኛ መልስ ሰጭ የክርክሩ ተካፋይ ሆኖ የመያዣ ልኩን ባላሣወቀበት ሁኔታ በጨረታ ማስታወቂያው ላይ ይህ አልተገለፀም

መባሉ ተገቢነት የለውም ሲል የሰጠው ምክንያት ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

እንዲሁም የማይንቀሣቀስ ንብረት በሐራጅ እንዲሸጥ በማስታወቂያ በተገለፀ ጊዜ ማስታወቂያው ለ30 ቀናት ሣይቆይ በሐራጅ ሊሸጥ እንደማይችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 426 አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ ተደንግጎ እያለ ይህ ጊዜ ሣይጠብቅ ለ16 ቀናት ብቻ ቆይቶ እንዲሸጥ መደረጉ ሥነ ሥርዓታዊ ጉድለት የተፈፀመበት መሆኑን ስለሚያመለክት በእነዚህ ሁለት ምክንያቶች የሽያጩ ሥርዓት ተገቢ ባልሆነ መንገድ መፈፀሙን ስለተረዳን ሽያጩ እንዲፈርስ መደረጉ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ይሁን እንጂ የመጀመሪያው የሐራጅ ሽያጭ አሻሻጥ ሥርዓት ጉድለት ተገኝቶበት እንዲፈርስ ከተደረገ ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለውን በሚመለከት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 447(5) መሠረት ገዥ ነው ተብሎ ለነበረው ወገን የንብረቱ ዋጋ ከእነ ወለዱ ወይም እንደነገሩ አካባቢ ሁኔታ ያለወለድ ገንዘብ የተቀበለው ሰው እንዲመልስ ይደረጋል የሚለው ከመገለፁ በቀር ሌላ የተቀመጠ ውጤት የለም ፡፡ ሆኖም የሽያጩ ሥርዓት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ወይም በማጭበርበር ምክንያት እንዲፈርስ ከተደረገ የፍርድ ባለመብቱ የጠየቀውን ገንዘብ እንዲያገኝ ባለእዳውም ግዴታውን እንዲወጣ ለማድረግ ሲባል ተገቢ በሆነ መንገድ እና ከማጭበርበር ተግባር ነፃ በሆነ ሁኔታ በድጋሚ ሐራጅ ንብረቱ ሊሸጥ እንደሚችል የሚያከራክር ስላልሆነ ንብረቱ በድጋሚ ሐራጅ ሊሸጥ ይገባል ብለናል፡፡

ንብረቱ በድጋሚ ሐራጅ በሚሸጥበት ጊዜ በሽያጩ ገንዘብ ላይ የቀዳሚ መብት ያለው ማን ነው? የሚለውን በሚመለከት በአመልካችና በ1ኛ መልስ ሰጭ መካከል የሚነሣውን ክርክር አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ለአብነትም ያህል በአዋጅ ቁጥር 286/94 በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059 መሠረት ታይቶ ተገቢው ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል፡፡



**ው ሣ ኔ**

1. በምዕ/ጎጃ መስ/ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት አማካኝነት የተደረገው የሐራጅ ሽያጭ ፈርሷል፡፡ ድጋሚ ጨረታ ይካሄድ በጨረታው ሽያጭ የሚገኘውን ገንዘብ የቀዳሚ መብት ላለው ወገን ክፍያው ይፈፀም፡፡
2. የሥር ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡትን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ሽረናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰበር መ.ቁ. 27574

ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ወ/ሮ አለሚቱ ተረፈ

ተጠሪ፡- የትግል ፍሬ ልብስ ስፌት ማህበር

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በአፈፃፀም የተያዘን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች የፍርድ ባለመብት፤ ተጠሪ ደግሞ የፍርድ ባለእዳ ነበሩ፡፡ አመልካች ለአፈፃፀም ያቀረበችው ውሣኔ በሰኔ 26 ቀን 1996 ዓ.ም በሽምግልና ጉባዔ ተሰጠ የተባለው ነው፡፡ የፍርድ ባለአዳው ለአፈፃፀም ክሱ በሰጠው መልስ ለአፈፃፀም የቀረበው ውሣኔ በአስታራቂ ሽማግሌዎች የተሰጠ የድርድር ሃሣብ እንጂ በፍ/ቤት የሚፈፀም ውሣኔ አይደለም በማለት የተከራከረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ይህን ክርክር በመቀበል ለአፈፃፀም የቀረበው ውሣኔ ስልጣን ባልተሰጣቸው አስታራቂ ሽማግሌዎች የተሰጠ ነው፡፡ በግልግል ዳኞች እንደተሰጠ ተቆጥሮ የሚፈፀም አይደለም በማለት የአፈፃፀም ክሱን ዘግቶአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ስህተት የለበትም በማለት ይግባኙን ውድቅ አድርጎአል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ህዳር 17 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪውን አስቀርበን ክርክሩን



አሰምተናል፡፡ በሰበር ችሎቱ እንዲመረመር የተፈለገው ነጥብ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ለአፈፃፀም ያቀረበችው ውሣኔ በፍ/ቤት ሊፈፀም አይችልም ማለታቸው አግባብ ነው ወይ? የሚለው ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ፣ ከቀረበው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተመለከተው አመልካች ለአፈፃፀም ያቀረበችው ውሣኔ በ26.10.96 ዓ.ም የተሰጠው ነው፡፡ ይህ ውሣኔ ሦስት አባላት ባሉት የሽምግልና ጉባዔ የተሰጠ ነው፡፡ የሽምግልና ጉባዔው ሊቋቋም የቻለው ጉዳዩ ስለህበረት ስራ ማህበራት በወጣው አዋጅ ቁ. 147/91 መሠረት መታየት ያለበት በሽምግልና ነው ተብሎ በፍ/ቤት ቀደም ሲል በመበየኑ ምክንያት እንደሆነም ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ በዚህ መሠረት የሽምግልና ጉባዔው ከተቋቋመ በኋላም አመልካች በከሣሽነት፤ተጠሪ ደግሞ በተከሣሽነት ቀርበው ተከራክረዋል፡፡ በመጨረሻም ጉባዔው ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ የሽምግልና ጉባዔው በሰጠው ውሣኔ ላይ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ በዚህ ይግባኝ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ ፍ/ቤቱም የሽምግልና ጉባዔውን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ አመልካች የአፈፃፀም ክሱን ያቀረበችው ከዚህ በኋላ ነው፡፡

እንደምንመለከተው በፍ/ቤት ቀደም ሲል በተሰጠው ብይን መሠረት ሦስት አባላት ያሉት የሽምግልና ጉባዔ ከመቋቋሙም በላይ፤ አመልካች እና ተጠሪም የጉባዔውን ስልጣን በመቀበል ቀርበው ተከራክረዋል፡፡ በመሆኑም ውሣኔውን የሰጠው የሽምግልና ጉባዔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 215(1) እንደተመለከተው በፍ/ቤት ሊፈፀም የሚችል ውሣኔ ሊሰጥ የሚችል አካል ነው ማለት ነው፡፡ በግልግል ወይም በቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች የተሰጠ ውሣኔ የሚፈፀመው በመደበኛ ፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ በሚፈፀምበት አይነትና ሁኔታ እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 319(2) በግልጽ ተመልክቶአል፡፡ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ግን ይህን በግልጽ የተመለከተውን ሕግ የተከተለ

አይደለም፡፡ ስለዚህም ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በዚህ ጉዳይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 3058 ግንቦት 5 ቀን 1997 ዓ.ም እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39254 ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ ውሣኔው ለሰበር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



የሰ/መ/ቁ. 28019

ታህሣሥ 1 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** አቶ ብርሃኔ ገ/እግዚአብሔር - ጠበቃ መሰለ ገ/ጊዮርጊስ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ገርጊስ ናይዝጊ - ጠበቃ ወንድሙ ግዛው

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የጋራ ንብረት ክፍፍልም በተመለከተ ፍ/ቤቱ ውሣኔ ሲሰጥ አሁን ለዚህ ክርክር ምክንያት የሆነው በወረዳ 19 ቀበሌ 55 ክልል የሚገኘው ቁጥር 108 የሆነውን ቤት የገበያ ዋጋ ግምት ግማሽ የአሁን ተጠሪ ለአሁን አመልካች ሰጥተው ቤቱን እንዲያስቀሩ ተጠሪ በዚህ መልኩ የቤቱን የገበያ ዋጋ ግማሽ ለአመልካች ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆኑ ግራ ቀኙ ተስማምተው ቤቱን በገበያ ዋጋ ሸጠው የቤቱን ሽያጭ ዋጋ ገንዘብ ለሁለት እንዲካፈሉ በዚህ መልኩም ቤቱም ለመሸጥ ካልቻሉም በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በኩል በሐራጅ ተሸጦ ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉ የሚል ውሣኔ ሰጥቶ በዚሁ ውሣኔ መሠረት አፈፃፀሙ ቀጥሎ ፍ/ቤቱ የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ቤቱን በመሐንዲስ አማካይኝነት ገምቶ ውጤቱን እንዲልክ ትዕዛዝ ሠጥቶ የቤቱ ግምት ብር 83,596.61 እንደሆነ በመግለጽ ክፍለ ከተማው ለፍ/ቤቱ መልስ በመስጠቱ የዚህን ግምት ግማሹን ተጠሪ ለአመልካች ሰጥተው ቤቱን እንዲያስቀሩ በማለት የአፈፃፀም ትዕዛዝ ሠጥቶ በዚሁ ትዕዛዝ አመልካች ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ

ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ይግባኙ ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ አፈፃፀሙ የቀጠለው በፍርዱ መሠረት ስለመሆኑ ለሰበር ቀርቦ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ የሚሻውም የጉዳዩ ጭብጥ አፈፃፀሙ የቀጠለው በፍርዱ መሠረት ነው ወይንስ አይደለም የሚለው ሲሆን በዚሁ ነጥብ ላይ በመመስረት አቤቱታው ተመርምሯል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የጋራ ንብረት ክፍፍልን አስመልክቶ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10320 መጋቢት 21 ቀን 1996 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ መሠረትም ለዚህ ክርክር ምክንያት የሆነው በወረዳ 19 ቀበሌ 55 ክልል የሚገኘው ቁጥር 108 የሆነው የጋራ ቤት ከላይ እንደተመለከተው የገበያ ዋጋ ግምቱን ተጠሪ ለአመልካች በመስጠቱ ቤቱን እንዲያስቀሩ ፈቃደኛ ካልሆኑም በሁለቱ የጋራ ስምምነት በገበያ ዋጋ ተሸጦ የሽያጩን ገንዘብ እኩል እንዲካፈሉ ይህም ካልተቻለ በፍርድ አፈፃፀም መመሪያ እኩል በሐራጅ ተሸጦ ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉ በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ሆኖም ግን አፈፃፀሙ ሲቀጥል በዚሁ ውሣኔ መሠረት መፈጸም ሲገባው የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት የሆነው ቤት በክፍለ ከተማው መሐንዲስ በኩል እንዲገመት መደረጉ ከውሣኔ ያፈነገጠ ከመሆኑም በላይ በውጤት ደረጃም ቢሆን የመሐንዲስ ግምትና የገበያ ዋጋ ልዩነት እንዳለው የሚታመን ስለሆነ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ በመ/ቁ. 10320 መጋቢት 21 ቀን 1996 ዓ.ም. ፍ/ቤቱ ከሰጠው ውሣኔ ጋር የተጣጣመ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩ በይግባኝ



ሲቀርብለት ይህንኑ ስህተት ማረም ሲገባው ይግባኙን ሳይቀበል በመቅረቱ በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 14724 በ23/9/98 ዓ.ም. የሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 47756 በ19/3/99 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 10320 መጋቢት 21 ቀን 1996 ዓ.ም. በተሰጠው ውሣኔ መሠረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት በገበያ ዋጋ አስገምቶ የግምቱን ግማሽ የአሁን ተጠሪ ወ/ሮ ገርጊስ ናይዝጊ ለአሁን አመልካች ለአቶ ብርሃኔ ገ/እግዚአብሔር በመስጠት ቤቱን እንዲያስቀሩ በዚህ መልኩ ተጠሪ ካልተስማሙ ቤቱን በጋራ በገበያ ዋጋ ሸጠው ገንዘቡን እንዲከፋፈሉ ይህም ካልተቻለ ቤቱ በፍርድ አፈፃፀም መመሪያ በኩል በሐራጅ ተሸጦ ገንዘቡን እኩል እንዲከፋፈሉ እንዲያደርግ ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 28154

ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ነ/ፈጅ አለሙ ኢብሳ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነ/ፈጅ የምስራች ደሳለኝ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የፍርድ አፈጻጸምን የሚመለከት ሲሆን በፍርድ ባለመብት የአሁን ተጠሪና በፍርድ ባለእዳዎች እና አቶ ካሊድ የሱፍ /2 ሰዎች/ መካከል የነበረው የፍርድ አፈጻጸም ክርክር በሥር ፍ/ቤት ቀጥሎ በከፍተኛ 5 ቀበሌ 12 ክልል በ1ኛ የፍርድ ባለእዳ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ቁጥር 1267 የሆነው መጋዘን ተሽጦ ሕዳር 3 ቀን 1969 ዓ.ም በተሰጠው ውሳኔ መሰረት ለፍርድ ባለመብት እንዲከፈል በማለት በቅድሚያ መጋቢት 30 ቀን 1979 ዓ.ም ከዚያም በ15/2/97 ዓ.ም የአፈጻጸም ትእዛዝ መስጠቱን ከመዝገቡ የተረዳን ሲሆን 2ኛው የአፈጻጸም ትእዛዝ ከተሰጠ በኋላ በፍርድ አፈጻጸም እንዲሸጥ ትእዛዝ የተሰጠበት መጋዘን ላይ መብት ያለኝ ስለሆነ አፈጻጸሙ በዚህ መጋዘን ላይ ሊቀጥል አይገባም በማለት የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 መሰረት መቃወሚያ አቅርቦ አፈጻጸሙን በጊዜው ይዞት የነበረው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መቃወሚያው ለፍርድ ባለመብት እንዲደርስ በማድረግ አከራክሮ መቃወሚያው በአግባቡ አልቀረበም የሚልበትን ምክንያት በዝርዝር አስፍሮ ተቀባይነት የለውም ብሎ አስቀድሞ በተሰጠው የአፈጻጸም ትእዛዝ መሰረት ይሄው መጋዘን ተሽጦ በውሳኔው



ከፍርድ ባለእዳዎች የሚፈለገው ገንዘብ ለፍርድ ባለመብት እንዲከፈል በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚሁ ትእዛዝ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ጉድለት የሌለው ነው በማለት ይግባኙን ባለመቀበል ይህንኑ የሥር ፍ/ቤትን ትእዛዝ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ይህም ችሎት በቅድሚያ የተመለከተው የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 መሰረት አፈጻጸሙን በመቃወም ለፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረበው አቤቱታ ለፍርድ ባለመብት ብቻ እንዲደርስ ተደርጐ የፍርድ ባለእዳዎች በዚህ ላይ ክርክራቸውን ሳያቀርቡ ትእዛዝ መስጠቱን አግባብነት በተመለከተ ነው፡፡

በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ 3ኛ ወገኖች መብት ያቋቋምን ስለሆነ በዚህ ንብረት ላይ አፈጻጸም ሊቀጥል አይገባም በማለት 3ኛ ወገኖች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 418/1/ መሰረት መቃወሚያ ሲያቀርቡ ተከራካሪ ወገኖች ይህንኑ መብት የሚቃወሙ ከሆነ ፍ/ቤቱ የተከራካሪ ወገኖችን ክርክር ከሰማ በኋላ ውሳኔ እንደሚሰጥ ከተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 ከፍ ብሎ ከተመለከተውና ከቁጥር 419 ድንጋጌ በግልጽ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በፍርድ አፈጻጸም እንዲሸጥ የተባለው መጋዘን የ1ኛ የፍርድ ባለእዳ ንብረት ነው እንደተባለ በትእዛዙ ላይ የተመለከተ ሲሆን በዚህ ንብረት ላይ ተቃዋሚው የአሁን አመልካች አፈጻጸሙን በመቃወም አቤቱታ ሲያቀርብ ከላይ ከተጠቀሰው የሥነ ሥርአት ሕጉ ድንጋጌ አኳያ አቤቱታው ለፍርድ ባለመብቱና ለባለእዳዎች ደርሶ የሁሉንም ወገኖች ክርክር በመስማት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 419 መሰረት ፍ/ቤቱ ውሳኔ መስጠት ሲገባው አቤቱታው ለፍርድ ባለመብት ብቻ እንዲደርስ በማድረግ ለዚህ

አቤቱታ ምክንያት የሆነውን ትእዛዝ መስጠቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ጉድለት ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 41092 በሰኔ 22 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ የፌዴራል ከ/ፍ/ቤትም በመ/ቁ. 41120 በታህሣሥ 10 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 መሰረት ያቀረበው አቤቱታ ለፍርድ ባለእዳዎችም እንዲደርስ ተደርጐ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢ መስሎ የታየውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ለፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ተመልሷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ትእዛዝ የቀረበው መዝገብ በመጣበት አኳኋን ይመለስ፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



የሰ/መ/ቁ. 28362

ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች** ፡- አቶ መሐመድ ኑር ጅብሪል ቀርቧል፡፡

**ተጠሪ** ፡- እነ ወ/ሪት ውበት ላሊሶ /3/ ሰዎች ቀርባለች፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ በፍርድ አፈፃፀም ላይ የቀረበ አቤቱታ ሲሆን በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ በአዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ በፍርድ ባለመብት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እንደዚሁም በፍርድ ባለዕዳ 3ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው የአፈፃፀም ክርክር ቀጥሎ በአዋሳ ከተማ በከፍተኛ 1 ቀበሌ 02 ክልል የሚገኝ ቤት በሐራጅ እንዲሸጥ የአፈፃፀም ትዕዛዝ ተሰጥቶ እንዳለ የአሁን አመልካች በፍርድ አፈፃፀም በሐራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ የተሰጠበትን ቤት የፍርድ ባለዕዳ /3ኛ ተጠሪ/ በስማቸው ተመዝግቦ እንደሚገኝ የሚያረጋግጥ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት አቅርበውልኝ ቤቱን ከእሳቸው ላይ የገዛሁ ከመሆኑም በላይ ባለቤትነቱ በስሜ ተዛውሮ የሚገኝ ስለሆነ ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥ የተሰጠው ውሣኔ ያለአግባብ በመሆኑን ፍ/ቤቱ ይህንኑ ትዕዛዝ ያንሳልኝ በማለት መቃወሚያ አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በፍርድ አፈፃፀም በሐራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ የተሰጠበት ቤት አቤቱታ አቅራቢው ያልተከፋፈለ የውርስ ሀብት መሆኑን እየተገነዘበ ከፍርድ ባለዕዳ ላይ ስለመግዛቱ መገንዘብ የተቻለ ስለሆነ አቤቱታው ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ አፈፃፀሙ ሊቀጥል ይገባል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚሁ ብይን ቅሬታ አድሮባቸው

አቤቱታቸውን እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ድረስ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎትም የቀረበው አቤቱታ ይህንኑ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎት አቤቱታው ለሰበር ይቅረብ ብሎ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን በጽሑፍና በቃል አከራክሯል፡፡

የዚህን ችሎት ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ አፈፃፀም ሊቀጥል አይገባም በማለት አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ በሥር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት አለማግኘቱ በአግባቡ ነው ወይንስ አይደለም የሚለው ነው፡፡ ከዚሁ ጭብጥ አኳያም ጉዳዩን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም 3ኛ ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት በስማቸው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ከሚመለከተው መንግስታዊ ተቋም ካገኙ በኋላ ሐምሌ 1 ቀን 1995 ዓ.ም በተፃፈ ውል ለአመልካች በሽያጭ ያስተላለፉ ስለመሆኑ የሽያጭ ውሉ ከተደረገ በኋላም አመልካች እንደውሉ ይፈፀምልን በማለት በ3ኛ ተጠሪ ላይ ክስ መስርተው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ በመ.ቁ. 340/96 በ2/4/96 ዓ.ም 3ኛ ተጠሪ በሽያጭ ውሉ መሠረት ቤቱን ለአመልካች እንዲያስረክቡ በማለት ውሣኔ መስጠቱንና በዚሁ ውሣኔ መሠረትም አፈፃፀሙ ቀጥሎ እንዳለ 1ኛ ተጠሪ አፈፃፀሙን በመቃወም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 418 መሠረት አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱም አከራክሮ 1ኛ ተጠሪ አቤቱታቸው በማስረጃ ያልተደገፈ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም ብሎ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል በማለት ትዕዛዝ መስጠቱን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

አመልካች በ3ኛ ተጠሪ ላይ ክስ መስርተው ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት 3ኛ ተጠሪ ለአመልካች ሊያስረክቡ ይገባል ተብሎ ውሣኔ ከተሰጠ ይሄው ቤት በፍርድ አፈፃፀም በኩል በሐራጅ ተሽጦ ተጠሪዎች ገንዘቡን ሊከፋፈሉ ይገባል ተብሎ የተሰጠውን ውሣኔ ተከትሎ አፈፃፀም ሲቀጥል አመልካች በዚሁ ቤት ላይ



በፍ/ቤት ውሣኔ የፍርድ ባለመብት የሆኑ በመሆኑ አፈፃፀሙ በዚህ ቤት ላይ ሊቀጥል አይገባም በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ግራ ቀኙ በቤቱ ላይ ካቋቋሙት መብት አኳያ ታይቶ የአፈፃፀም ትዕዛዝ መስጠት ሲገባው አመልካች በዚህ ቤት ላይ መብት የላቸውም በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ አፈፃፀሙ ይቀጥል ተብሎ በአዋሳ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት የተሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝና እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስም ይህንኑ ትዕዛዝ በማጽናት የተሰጠው ትዕዛዝ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የአዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 147/98 ታህሣሥ 13 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንደዚሁም የአዋሳ ከተማ ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 01015 በ18/5/98 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 13987 ታህሣሥ 25 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው የፍርድ አፈፃፀም አመልካችና ተጠሪዎች በየበኩላቸው ያቀረቡትን ክርክር መርምሮ እንዲወስን ለአዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

**<u>የ ል ዩ ነ ት ሐ ሳ ብ</u>**

የአዋሳ ወረዳ ፍ/ቤት የፍርዱ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል በማለት በሰጠው ትዕዛዝ የይግባኝ ቅሬታ ለሲዳማ ዞን ከ/ፍ/ቤት ቀርቦ በይግባኝ ክርክሩ የአሁኑ አመልካች ተካፋይ ሳይሆኑ ተጠሪዎችን ብቻ በይግባኝ

አከራክሮ 3ኛ ተጠሪ በሽያጭ ለአመልካች ያስተላለፉት ቤት ሙሉ በሙሉ የግላቸው ሳይሆን የ1ኛ እና የ2ኛ ተጠሪዎችም ድርሻ ያለበት ስለሆነ በሽያጭ ውሉ መሠረት በገዢው ስም ሊዛወር የሚችለው በድርሻቸው ልክ እንጂ የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎችን ድርሻ ጨምሮ ስለማይሆን የወረዳው ፍ/ቤት የቤቱ ባለሃብትነት ሙሉ በሙሉ ወደ ገዢው ይዛወር በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ አይደለም በማለት አሻሽሎ በ3ኛ ተጠሪ ድርሻ ብቻ ስም ይዛወር ሲል ውሣኔ የሰጠ በመሆኑ ይህ የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት እንዳለበት መገንዘብ ቢቻልም በይግባኝ እስካልተለወጠ ተፈፃሚነት ያለው ስለሚሆን አመልካች በአዋሳ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 147/98 አፈፃፀሙ በዚህ ቤት ላይ ሊቀጥል አይገባም በማለት ያቀረቡት መቃወሚያ ከከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ አኳያ ታይቶ አፈፃፀሙ ሊቀጥል ይገባል በማለት በተራ ቁ. 2 ላይ ስሜ የተጠቀሰው ዳኛ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ



የሰበር መ/ቁ. 29344

ግንቦት 5 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ተገኔ ጌታነህ

ሂሩት መለሠ

መድህን ኪሮስ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ዝማም ህሉፍ ወኪል ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ መረሣ ገ/ዮሐንስ ጠበቃው ቀርቧል፣፣

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በመቀሌ ዞን ማ/ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁኗ አመልካች የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 46/96 በመስከረም 4 ቀን 1992 ዓ.ም በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የቦታ ሽያጭ ውል ፈርሶ ወደነበሩበት እንዲመለሱ በሰጠው ውሣኔ መሠረት እንዲፈፀምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ተጠሪ ቤት እና ቦታውን ለአመልካች እንዲያስረክቧቸው ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የተመለከቱት የመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ ትዕዛዝ ስህተት የለውም በማለት የቀረበላቸውን የይግባኝ ቅሬታ ውድቅ አድርገውታል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በግራ ቀኙ የተደረገው የቦታ ሽያጭ ውል ሻጭ ባለቤት ሳይሆኑ የተፈፀመ ስለሆነ ውሉ ፈራሽ ሆኖ ተዋዋዮቹ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ተወስኗል፡፡ ይህም ማለት ገዢ ገንዘባቸው እንዲመለስላቸው ቦታው ደግሞ ቦታውን ለማስተዳደር ስልጣን ላለው ማዘጋጃ ቤት እንጂ

ለተጠሪ አይደለም በማለት ተጠሪ ለአመልካች ቦታውን እንዲያስረክቡ የተሰጠውን ትዕዛዝ ነው፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም የተሰጠው የአፈፃፀም ውሣኔ ዋናውን ውሣኔ የተከተለ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡

ከመዝገቡ እንደተረዳነው ከአመልካች ክርክር የሰበር ችሎቱ የሰጠው የአፈፃፀም ውሣኔ በዋናው ጉዳይ ላይ የተሰጠውን ፍርድ የሚለውጥ ነው፣ 3ኛ ወገኖች ክርክር ባላቀረቡበት ጉዳይ መብት እንዲያገኙ የሚደረግበት ህጋዊ መሠረት የለም የሚሉ ይገኙበታል፡፡

ይህ ችሎትም ጭብጥ የያዘው በአፈፃፀም የተሰጠው ውሣኔ ዋናውን ፍርድ መሠረት አድርጐ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ስለሆነ ዋናው ውሣኔ ምን ይላል የሚለውን ማየት ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም አንድ ውሣኔ የሚያስፈጽም ፍ/ቤት በውሣኔው መሠረት ከማስፈፀም ውጪ በአፈፃፀም ጊዜ ዋናውን ፍርድ ሊለውጥ የሚችልበትን የህግ መሠረት የለውም ለአፈፃፀም ምክንያት ከሆነው ውሣኔ ላይ እንደተገነዘብነውም አመልካች ለከብት እርባታ ተብሎ በጊዜያዊነት የተሰጣቸው የመሬት ሽያጭ ውል እንዲፈርስላቸው ያቀረቡት ክስ እስከ ትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ድረስ ከታየ በኋላ አመልካች በቦታው ላይ የባለቤትነት መብት ሳይኖራቸው ያደረጉት የሽያጭ ውል ህግን የሚፃረር በመሆኑ ውሉ እንዳልነበር ተቆጥሮ እንዲፈርስና ተዋዋይ ወገኖች የሽያጭ ውል ከማድረጋቸው በፊት ወደነበሩበት ሁኔታዎች እንዲመለሱ ተወስኗል፡፡ ከዚህ ውሣኔ እንግዲህ መገንዘብ የሚቻለው የውሣኔው ውጤት ሻጭ የሸጠው መሬት እንዲመለስለት ገዢ ደግሞ ለሻጩ የከፈለው ገንዘብ እንዲመለስለት የሚያደርግ መሆኑን ነው፡፡ የሰበር ችሎቱ በዋናው ጉዳይ ላይ ከፍ ሲል የተመለከተውን ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ደግሞ በመቀጠል የመቀሌ ከተማ ቦታን የማስተዳደር ስልጣን የመቀሌ ማዘጋጃ ቤት እሲሆን እያከራከረ ያለው ቦታ



ወደፊት እንዴት ይሁን የሚለውን ሊወስንና እርምጃ ሊወስድ የሚችለው እራሱ ስለሆነ ተከታትሎ አንድ ነገር የማድረግ መብቱ ተጠብቆለታል ብሏል፡፡ በዚህም ጉዳይ አከራካሪ የሆነው ግራ ቀኙ ውሉ ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ ከተወሰነ በኋላ የመቀሌ ማዘጋጃ ቤትን በተመለከተ ፍ/ቤቱ ያለው ነገር ነው፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ዋናው ፍርድ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ሲወሠን ገዢ የከፈሉት ገንዘብ እንዲመለስላቸው እና ቦታው ግን ማዘጋጃ ቤቱ እንዲረከበው ከመወሰኑ በቀር አመልካችን የፍርድ ባለመብት የሚያደርግ ውሣኔ አልተሰጠም በማለት ለደረሰበት መደምደሚያ መሠረት ያደረገው ከውሣኔው በኋላ ማዘጋጃ ቤቱ ወደፊት ቦታውን በተመለከተ ተገቢ ነው ያለውን እርምጃ እንዲወስድ የተሰጠውን ማሳሰቢያ ነው እኛ እንደተረዳነው ግን ሰበር ችሎቱ ማዘጋጃ ቤቱ ቦታውን አስመልክቶ እርምጃ እንዲወስድ ማሳሰቢያ ከመስጠቱ በቀር ቦታው በክርክሩ ተካፋይ ላልነበረው አካል እንዲመለስ የተሰጠው ውሣኔ አለመኖሩን ነው፡፡

ስለሆነም የትግራይ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው የአፈፃፀም ውሣኔ ከዋናው ውሣኔ ያፈነገጠ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በሌላ በኩል ግን ይህ ችሎት ግራ ቀኙን በቃል በአነጋገረበት ወቅት ቦታው ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በተጠሪዎች እጅ መሆኑንና ማዘጋጃ ቤቱም ቦታውን ለተጠሪዎች ሰጥቶ ቦታውን የሚመለከቱ ሰነዶች ለመውሰድ በዝግጅት ላይ እንዳሉ በዚህ ችሎት የዕግድ ትዕዛዝ ምክንያት መቆሙን ተገንዝበናል፡፡ ከዚህም የቦታው ባለቤት የሆነው ማዘጋጃ ቤት ቦታውን ለተጠሪዎች አሳልፎ መስጠቱን ተረድተናል፡፡ የፍ/ባለዕዳው በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ፍርድን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለመፈፀም የማይችል መሆኑን ፍ/ቤቱ ከተረዳው ደግሞ ፍርድ እንዲፈፀም ትዕዛዝ እንደማይሰጥ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 392/2/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን

በዋናው ውሣኔ ውሉ ፈርሶ ቦታው ለአመልካች እንዲመለስ የተወሰነ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ማዘጋጃ ቤቱ ቦታውን ለተጠሪዎች የሰጠ በመሆኑ ፍርዱ ሊፈፀም የሚችል አይደለም፡፡

በዚህም ምክንያት የትግራይ ክልል ሰበር ችሎት የሰጠውን ምክንያት በመቀየር ውሣኔውን አጽንተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 10962 በታህሳስ 5 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

ተ ጨ ማ ሪ ት ዕ ዛ ዝ

ይህ ችሎት ነሐሴ 14/1999 የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዘ/ዘ



የሰ/መ/ቁ. 29371

ታህሣሥ 1 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍስሐ ወርቅነህ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

**አመልካቾች፡-** 1. ሶፊያ መሐመድ ቀረበች፡፡
2. ከድጃ መሐመድ ቀረበች፡፡

**ተጠሪዎች፡-** 1. ኢብራሂም መሐመድ
2. ፋጡማ መሐመድ } ጠበቃ ዘላለም ባይህ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ መሠረቱ የውርስ ንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም በአፈፃፀም ደረጃ ላይ ያለ ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ለአፈፃፃሙ መሠረት የሆነው ውሣኔ የተሰጠው ተጠሪዎች ወንድማቸው በሆነው አብዱልቃድር መሐመድ ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡ ተጠሪዎች በአማራ ብ/ክ/መ/የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ተከሣሽ ይዞት የሚገኘው ከአባታቸው የተገኘውን የውርስ ሃብት እንዲያካፍላቸው የጠየቁ ሲሆን፣ ተከሣሹም ክሱን አምኖ በመቀበሉ ንብረቱ ተከራካሪዎቹን ጨምሮ ለሰባት /7/ የሚች ልጆች እኩል ይካፈል በማለት ፍ/ቤቱ ወስኖአል፡፡ በመቀጠልም ውሣኔን በስሩ የሚገኘው ባቲ ወረዳ ፍ/ቤት እንዲያስፈጽም ትዕዛዝ ሰጥቶአል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤትም ተጠሪዎችንና አብዱልቃድር መሐመድን /የሥር ተከሣሽን/ ብቻ በማከራከር በባቲ ከተማ የሚገኙ አራት ቤቶች እና አንድ መኪና ለተጠሪዎች እንዲሰጡ በማለት ትዕዛዝ በመስጠቱ አመልካቾች ይህን ትዕዛዝ በመቃወም

እና እንደዋናው ውሣኔ አባባል ይፈጸም ዘንድ እንዲታዘዝላቸው በመጠየቅ ለወረዳው ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱ ግን ቀደም ሲል የሰጠውን ትዕዛዝ አልለወጠም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መዝገቡ በጣም የቆየ በመሆኑና ለአፈጻጸምም ስላስቸገረ ለከፍተኛው ፍ/ቤት መቅረብ አለበት በማለት ትዕዛዝ ስለሰጠ የከፍተኛው ፍ/ቤት ይህን መነሻ በማድረግ ጉዳዩን አይቶአል፡፡ በመጨረሻም የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ በማሻሻል ንብረቱ በዋናው ውሣኔ መሠረት ሰባቱም ወራሾች እኩል ይካፈሉት በማለት ትዕዛዝ ሰጥቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪዎች ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው ክርክሩ በድጋሚ የታየ ሲሆን፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ /ትዕዛዝ/ በመሻር ቀደም ሲል በባቲ ወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠውን የንብረት ክፍፍል ትዕዛዝ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም በዚሁ ላይ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አመልካቾች መጋቢት 5 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፉት ማመልከቻ ያቀረቡትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በዋናው ፍርድ ከተሰጠው ውሣኔ በተለይ ሁኔታ የተከናወነውን አፈፃፀም ተፈጽሞ ያለቀ ነው በሚል ብቻ አመልካቾች ዋናውን ፍርድ መሠረት አድርገው ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ እንዲሆን የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አከራካሪ ሆኖ የቀረበው እና በዚህ ሰበር ችሎት ውሣኔ ሊያገኝ የሚገባው ነጥብ አፈፃፀሙ ተከናወነ የተባለው በዋናው ፍርድ በተሰጠው ውሣኔ መሠረት ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነው፡፡ በአማራ ብ/ክ/መ/የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ግልጽ ነው፡፡ በውርስ ተገኘ የተባለው ንብረት የሟች ወራሾች የሆኑት ሰባት ሰዎች እኩል ይካፈሉት የሚል ነው፡፡ ከሰባቱ ወራሾች መካከልም የአሁኖቹ



አመልካቾች ይገኛሉ፡፡ የባቲ ወረዳ ፍ/ቤት በከፍተኛው ፍ/ቤት የታዘዘውም /የተወከለው/ በዚህ መልክ በተሰጠው ውሣኔ መሠረት ንብረቶቹን ለወራሾች እንዲያከፋፍል ነው፡፡ እንዳየነው ግን ንብረቶቹን ለሁሉም ወራሾች እንዲከፋፈሉ አላደረገም፡፡ የተገኙት ንብረቶች እንዳሉ በቀጥታ ለተጠሪዎች ብቻ እንዲሰጡ ነው ያደረገው፡፡ ይህ አካሄድ በግልጽ የሚያሳየው አመልካቾች እና ሌሎቹ ወራሾች በውሣኔ ጭምር ያገኙትን የወራሽነት መብት እንዲያጡ መደረጋቸውን ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም አመልካቾች ትዕዛዝ እንዲታረምና እነሱም ድርሻውን እንዲያገኙ እንዲታዘዝላቸው ፍ/ቤቱን የጠየቁ ቢሆንም፣ ፍ/ቤቱ ተጨማሪ እርምጃ አልወሰደም፡፡ በእርግጥ ጉዳዩ ዋናውን ውሣኔ በሰጠው ከፍተኛ ፍ/ቤት እልባት ማግኘት አለበት በማለት የወረዳው ፍ/ቤት ለከፍተኛው ፍ/ቤት መልሶታል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት በወረዳው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ ሊያርም የቻለውም ይህን መሠረት በማድረግ ነው /የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 374/1/ ይመለከቷል/፡፡ የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በከፍተኛው ፍ/ቤት የተሰጠውን ትዕዛዝ የሻረው ደግሞ አፈፃፀሙ ከመጠናቀቁም በላይ፤ የትዕዛዙም አሰጣጥ ስነ-ስርዓትን የተከተለ አይደለም በማለት ነው፡፡

በበኩላችን እንደምናየው ክርክሩ እልባት ሊያገኝ የሚገባው በዚህ መልክ ሳይሆን፣ ቀደም ሲል እንዳመለከትነው በዋናው ውሣኔ መሠረት ተፈጽሞአል ወይስ አልተፈጸመም የሚለውን ጭብጥ ይዞ ጉዳዩን በመመርመር ነው፡፡ በዋናው ውሣኔ መሠረት የተከናወነ አፈፃፀም እንደሌለ የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤትም እንደተገነዘበ በውሣኔው ላይ አመልክቶአል፡፡ በእርግጥ እኛም እንደተገነዘብነው የከፍተኛው ፍ/ቤት በወረዳው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን የአፈፃፀም ትዕዛዝ ለማረም የተከተለው አካሄድ ትክክል አልነበረም፡፡ የጠ/ፍ/ቤቱ ይህን አካሄድ ትክክል አይደለም በማለት የሰጠው ትችትም ስህተት ነው የምንለው አይደለም፡፡ ትክክል ሆኖ ያላገኘነው ሁለቱም ፍ/ቤቶች ዋናው ውሣኔ ሊፈጸም የሚችልበትን መንገድ አለማመቻቸታቸው

ነው፡፡ ደጋግመን እንደገለጽነው ዋናውን ውሣኔ መሠረት ተደርጎ የተከናወነ አፈፃፀም የለም፡፡ እውነታው ይህ ከሆነ ደግሞ ውሣኔ እንዲፈጸም የሚቀርበው ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል እስካልተባለ ድረስ እንዴ ትዕዛዝ ተሰጥቶአልና ከዋናው ውሣኔ ውጪም ቢሆን አይነካም ብሎ ማለፍ የሚቻል /የሚገባም/ አይደለም፡፡ ይህ ዓይነቱ አካሄድ ሁለት መሠረታዊ ግድፈቶች አሉት፡፡ የመጀመሪያው እንደ ውሣኔው እንዲፈጸም የቀረበውን ጥያቄ የሕግ ምክንያት ሳይኖር ተቀባይነት እንዳ ኖረው ማድረግ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በውርስ ሃብቱ ላይ እኩል መብት ያላቸውን ወገኖች /አመልካቾችና ሌሎች ወራሾች/ ከሕግ አግባብ ውጪ ተካፋይ እንዳይሆኑ ማድረግ ነው፡፡ ስናጠቃልለው አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ የአፈፃፀም ክርክር የተነሳበትን ዋናውን ውሣኔ መሠረት ያላደረገ እና ውሣኔው የሚፈጸምበትን ሁኔታ ያላሣየ በመሆኑ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 622/98 ጥር 14 ቀን 99 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሸሮአል፡፡
2. አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት ዋናውን ውሣኔ /የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው/ መሠረት በማድረግ የውርሱን ሃብት አውራሾች እንዲያከፋፍል ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 29653

መጋቢት 9 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ
ዓብዱልቃድር መሐመድ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሠ ይርጋ

**አመልካች፡-** 1. አቶ ነጋ ደምስ
2. አቶ ኃይሉ ደምስ } ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** 50 አለቃ አዲሱ ደምስ - ቀረቡ፡፡

## <u>ፍ ር ድ</u>

ለሠበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ነው፡፡ የአሁኖቹ አመልካቾች ከሥር አፈፃፀም ባለዕዳ ጋር ተከራክረው ካስወሰኑ በኋላ በውሣኔው መሠረት እንዲፈፀምላቸው የአፈፃፀም ክስ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም በውሣኔው መሠረት ለማስፈፀም የውርስ ንብረት የሆነውን ቤት በሀራጅ አሸጦ ከሽያጩ የተገኘውን ገንዘብ ለማከፋፈል በሒደት ላይ እንዳለ የአሁኑ ተጠሪ እሣቸውም የቀኝ አዝማች ደምስ አስፋው የልጅ ልጅ መሆናቸውንና እናታቸውን ወ/ሮ ይርገዱ ደምስን ተክተው ሊወርሱ እንደሚገባ ገልፀው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት ጣልቃ ገብተው ለመከራከር ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካቾች የአፈፃፀም ባለዕዳ የሆኑትን ወ/ሮ እስከዳር ደምስን ከሰው ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ በውርሱ ቤት እስከ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ሲከራከሩ ጣልቃ ገብተው ያልተከራከሩና በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት ለመቃወም መብት የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ ጥያቄያቸውን ውድቅ አድርጓል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ተጠሪ የአያታቸው ፊትአውራሪ ደምስ አስፋው የልጅ ልጅ በመሆናቸው እናታቸውን ተክተው ሊወርሱ ስለሚገባ ከተሸጠው ከፊታውራሪ ደምስ አስፋው ቤት ድርሻ ገንዘቡን ሊያገኙ ይገባል በማለት የመጀመሪያውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

ይህ ችሎትም የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ለሰበር ችሎት ቀርቦ የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑን ስላመነ መ/ሰጪዎቹን አስቀርቧል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

እኛም መዝገቡን መርምረን እንደተረዳነው ክርክሩ የአፈፃፀም ክርክር ነው፡፡ አመልካቾች የሥር የአፈፃፀም ባለዕዳዋን የአባታቸውን የፊታውራሪ ደምስ አስፋውን ቤት አስመልክተው ከሠው አስፈርደዋል፡፡

ይህ የውርስ ቤት የአመልካቾች እናት እና አባት በመሆኑ አመልካቾቹ የሁለቱንም ወላጆችቻቸው ድርሻ የፍ/ባለዕዳዋ ደግሞ የአባታቸውን ድርሻ ብቻ እንዲያገኙ በተሰጠው ውሣኔ መሠረት ለማከፋፈል ጉዳዩ በአፈፃፀም ደረጃ ደርሶ ቤቱ በሀራጅ ተሸጦ ገንዘቡ ተይዟል፡፡ እንግዲህ በዚህ ደረጃ ነው ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት መቃወሚያ ያቀረቡት፡፡ በመሠረቱ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት መቃወሚያ ሊቀርብ የሚችለው አንድን ውሣኔ ለማስፈፀም ንብረት ሲያዝ በንብረቱ ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ሰው ይህ ንብረት እንዳይያዝ ወይም እንዳይከበር ነው፡፡ ይህ የስነ ስርዓቱ ድንጋጌም የሚመለከተው ለፍርዱ ምክንያት የሆነን ንብረት ሣይሆን ገንዘብ እንዲከፈል የተሰጠን ውሣኔ ለማስፈፀም የተያዘን ንብረት ነው፡፡ ንብረቱ ፍርድ ያረፈበት ከሆነ ግን መብቴ ተነክቷል የሚለው ወገን አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት ውሣኔው ከመፈፀሙ በፊት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ፍርዱን ለፈረደው ፍ/ቤት ነው በመሆኑም



በዋናው ክርክር ገብቶ ተከራክሮ ውሣኔ ያላገኘ ተከራካሪ ወገን በአፈፃፀም ጊዜ ውሣኔ እንዲፈፀምለት ጥያቄ የሚያቀርብበት የሕግ መሠረት የለም፡፡

በተያዘው ጉዳይም ቢሆን አመልካቾች የፍ/ባለዕዳዋን ከሰው አስወስነው ውሣኔውን በማስፈፀም ላይ ይገኛሉ ተጠሪ ውሣኔው መብታቸውን የሚነካ ከሆነ ውሣኔውን በመቃወም ቀርበው እንዲሻሻል ወይም እንዲለወጥ ማድረግ ነበረባቸው በመሆኑም በውሣኔው ያላገኙትን መብት በአፈፃፀም እንዲከበርላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት ቀዳሚነት መብት የሌላቸው መሆኑን እያረጋገጠ የውርስ ንብረት እንዲካፈሉ ሲል የሰጠው ውሣኔ የሕግ መሠረት የለውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10050 መጋቢት 11 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04241 በሐምሌ 13 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁጥር 33760

መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን እቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

መድህን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- 1. ሐጂ ታጁ ለገሠ ቀረበ፡፡

2. መሬም መሐመድ

ተጠሪ፡- የጎንደር ከተማ የመሀል አራዳ ቀበሌ አስተዳደር ነገረ ፈጅ

ፈረደ ሀይለማርያም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

መዝገቡ የቀረበው የአማራ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 11731 መስከረም 6 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት አመልካቾች ኅዳር 2 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ በአፈፃፀም የባልና የሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል በሚደረግበት ሁኔታ ላይ ያተኮረ ነው፡፡

ከዚህ ክርክር አንደኛ አመልካች የሆኑት ሀጂ ታጁ ለገሠ በሁለተኛ መልስ ሰጭ እና ወ/ሮ ሀዋ መሐመድ ጋር በጋብቻ ሲኖሩ የጋራ ንብረት አፍርተዋል፡፡ አንደኛው አመልካች ከወ/ሮ ሀዋ መሐመድ ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍች ሲፈርስ የጋራ ንብረታቸውን እንዲካፈሉ ከተሰማሙ ባልና ሚስት ከቀበሌ በተከራዩት ቤት ላይ ያላቸው የንግድ ድርጅት ተካፍለው ኑሯቸውን እንዲመሩ ወስኗል፡፡ ይህንንና ሌሎች የጋራ ንብረቶችን ለማካፈል



ለወ/ሮ ሀዋ መሐመድ የአፈፃፀም ክሳሽነት የአፈፃፀም መዝገብ ተከፍቶ አፈፃፀሙ በሂደት ላይ እያለ ተጠሪው ቤቱ የቀበሌ 02 በመሆኑ ባልና ሚስቱ ንብረታቸው ያልሆነውን ሊካፈሉ አይገባም በማለት ለጎንደር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት መቃወሚያ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ የንግድ ድርጅቱ የባልና የሚስት የጋራ ንብረት ነው፡፡ ቤቱን አስመልክቶ የተከራይ መብት ነው ያላቸው ስለዚህ ተቃውሞው ተገቢ አይደለም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ ይህንን አውቀውም ተጠሪው ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሣኔ አጽንቷል፡፡

ተጠሪው ይህንን በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቤቱ የቀበሌ ስለሆነ የንግድ ድርጅቱን ሸቀጥና ዕቃ ባልና ሚስቱ እንዲካፈሉ በማለት የወረዳውና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔዎች ሽሮአቸዋል፡፡ አመልካች ይህንን ውሣኔ በመቃወም ባለቤቱ የነበረችው ወ/ሮ ሀዋ መሐመድ በእኔ ስም ከማዘጋጃ ቤት በተከራየሁት ቤት ላይ የነበራትን ድርጅት ከሌላው ንብረት ጋር ተካክሶ የተካፈለች ሲሆን በእሷ ስም ከቀበሌ በተከራየነው ቤት ያለን የንግድ ድርጅት እኔ ልትካፈል አይገባም መባሉ ተገቢ አለመሆኑና ቀበሌውም በዚህ ጉዳይ ተከራካሪ የሚሆንበት ሁኔታ ስለሌለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ይሻርልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የተጠሪ ተወካይ በበኩሉ ቤቱ የቀበሌ ቤት ሆኖ እያለ እንደባልና እንደ ሚስት የጋራ ንብረት ተቆጥሮ ይካፈሉ ቤቱን ለኢንቨስትመንት ስለሚፈለግ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥና በመዝገቡ የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የአንደኛው አመልካች ሚስት በነበሩት በወ/ሮ ሀዋ መሐመድ ስም የነበረው የንግድ ድርጅት የሚካሄድበት ቤት የቀበሌ ንብረት አንደሆነና የኪራይ ውል

ከቀበሌ 02 የተያያዘ መሆኑ ክርክር አልተነሣበትም፡፡ የወረዳ ፍርድ ቤትም ሆነ የከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች እና ወ/ሮ ሐዋ መሐመድ የቀበሌ የሆነውን ቤት ለሁለት ተካፍለው የባለቤትነት መብት ያግኙ የሚል ትዕዛዝ አልሰጡም፡፡

በሌላ በኩል የወረዳና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የጋራ የሆነውና የተጠሪው የሆነውን ቤት በኪራይ ይዘው እየሰሩበት ያለው የንግድ ድርጅት እንዲካፈሉ መወሰኑ ተጠሪውን መብትና ጥቅም የሚነካ አይደለም፡፡ ተጠሪው ፍርድ ቤቶቹ በሰጡት ውሣኔ መሰረት የንግድ ድርጅቱ ሲከፈል የቤቱን መሰረታዊ ይዘትና ዋጋ ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ያደርሣል የሚል ክርክር አላቀረበም፡፡ ድርጅቱ መከፈል የማይቻል ሲሆን አመልካቾችና ወ/ሮ ሃዋ መሐመድ የንግድ ድርጅቱን እንዳለ በመሸጥ ዋጋውን እንዲካፈሉ ለማድረግ የሚያበቃ ምክንያት ከመሆኑ ውጭ ተጠሪውን ከወረዳ ጀምሮ እስከ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረስ ክርክር እንዲያቀርብ ምክንያት ሊሆን የሚችል መሰረታዊ ጉዳይ አይደለም፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የንግድ ድርጅቱ የሚከናወንበት ቤት የቀበሌ ስለሆነ ባልና ሚስቱ ንብረቱንና እቃውን ነው የመካፈል መብት ያላቸው በማለት የሰጠውን ውሣኔ አንድ የንግድ ድርጅት በንግድ መደብርነት በውስጡ አካትቶ የሚይዛቸው ነገሮች በውስጡ ከተቀመጡት ሸቀጦችና እቃዎች የማይወሰን እንደሆነ በተለይ በንግድ ህጉ አንቀጽ 127 ንኡስ አንቀጽ 2 በንግድ መደብር የንግድ ቤቱ ስም የሚነገድበት የተለየየ የንግድ ማስታወቂያ የንግድ ስራ የሚያከናውንባቸው ቤቶች የመከራየት መብት የሚያጠቃልል መሆኑን ሣያገናዝብ የተሰጠና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የንግድ ድርጅት ማካፈል ማለት የንግድ ድርጅቱን ካፒታል እና በውስጡ ያሉ እቃዎች ከመካፈል ውጭ የንግድ ድርጅቱ በሚከናወንበት ቤት ላይ ያላቸውን



የኪራይ መብት አይጨምርም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 11731 መስከረም 6 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ግልባጩ ይተላለፍ፡፡
2. የአማራ ክልል የጐንደር ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 04996 ግንቦት 10 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የስሜን ጐንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 15566 ጥር 22 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡት ወጭ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ነ/ዓ